እግዚአብሔርን መምሰል

የእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ምስጢር



ያሬድ ጥላሁን

ያሬድ ጥላሁን

እግዚአብሔርን መምሰል

«የእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ምስጢር»

እግዚአብሔርን መምሰል
የእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ምሥጢር

ያሬድ ጥላሁን © 2000 ዓ.ም

Godliness
The secret of true spiritual life
Copyright © 2007 by Yared Tilahun

የመጀመሪያው ዕትም 2000 ዓ.ም.

ያለ ደራሲው ፈቃድ ይህን መጽሐፍ ወይም ማንኛውንም የመጽሐፉን ክፍል ለማባዛት፣ ለመገልበጥ፣ ለመቅረጽ፣ ወይም በሌላ መጽሐፍ በስፋት ለመጥቀስ አይቻልም። ሆኖም ግን ለጥናት፣ ለማስተማሪያነትና ለመሳሰሉት ዓላማዎች ማንኛውም ግለሰብ፣ ቡድን ወይም ድርጅት ከዚህ መጽሐፍ ለመጥቀስ ቢፈልግ የመጽሐፉን ስም፣ የደራሲውን ስምና መጽሐፉ የተጻፈበትን ዓ.ም. የመጥቀስ ግዴታ አለበት።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት በ1954 ዓ.ም. በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ከታተመው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ወይም በ1993 ዓ.ም. በኢንተርናሽናል መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ከታተመው አዲሱ መደበኛ ትርጉም ነው።

የሽፋን ዲዛይን፡ በበረከት ታደሰ

አሳታሚ

Golden Oil Ministries
P.O.Box 18007
Addis Ababa, ETHIOPIA
www.goldenoil.org

በሮሮቦት ማተሚያ ድርጅት ታተመ
አዲስ አበባ

አበርክቶት

የዚ'ች መጽሐፍ መታሰቢያነት "የጥሪ ጉዳይ ሆኖ ከሥፍራ ወደ ሥፍራ ስጓዝ ናፍቆታቸው ሲበረብረኝ ፣ እነርሱም እኔን በመናፈቅ ዝለው እንደ እርጉዝ ቀን ለሚቆጥሩት፣ ስመለስም ገና ብዙም ሳንጠጋገብ መልሼ በአገልግሎትና በሥራ ስናውዝ በፍቅርና በርህራሄ ዐይን እያዩኝ ድካሜን ለሚያስረሱኝ

ለውድ ባለቤቴ ለምኞቴ ክፍሌ፣

ለልጆቻችን ለቅዱስ እና ለፍቅር ያሬድ"

የተበረከተ ይሁን።

ቡራኬ

‹በአንድ እጅ አይጨበጨብም፤ በአንድ ዐይን አይለቀስም› እዲሉ አንድ ሰው ለብቻው ለውጤት ይበቃል ብሎ ማሰብ ዘበት ነው፡፡ ያውም በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ፡፡

‹እግዚአብሔርን መምሰልም› በእኔ እጅ ትጻፍ እንጂ የበርካታ ሰዎች አስተዋጽኦ አለባት፡፡ ሁሉንም በስም ለመዘርዘር ቦታ ባይበቃም አንባቢ ይባርክልኝ ዘንድ የጥቂቶቹን ስም ላንሳ፡፡

በ1979 ዓ.ም ጅቡቲ ከተማ ውስጥ ከአፉ የወንጌልን ቃል የሰማሁት በእጁ በቀይ ባሕር ውስጥ የተጠመቅሁት ሆላንዳዊው ጃን ፕሪንሰ እግዚአብሔርን በመምሰል የተቃኘው ሕይወቱ ለዚ‘ች መጽሐፍ መሠረት ቁሏል ለማለት እደፍራለሁ፡፡

በ1980 ዓ.ም በጌታ ምሪት ወደ ኢትዮጵያ ከተመለስኩ በኃላ ለአገልግሎት በምዘጋጅባቸው የመጀመሪያ ዓመታት እግዚአብሔር በእጁ ያስገባቸው ለክርስትና ሕይወቴና አገልግሎቴ የአስተሀሮ መሠረት የጣሉት (አሁን በጌታ ዘንድ የሚገኘው) የቻይናዊው የዋች ማን ኒ መጻሐፍት ለዚ‘ች መጽሐፍ እውን መሆን ያበረከቱት አስተዋጽኦ ግዙፍ ነው፡፡

የማስተምራቸውን ትምሕርቶች በመጽሐፍ እንድጽፋቸው የመከሩኝ ብዙ ቢሆኑም የኤል ኤው ግሩም በኃይሉ ግን ለየት ያለ ነበር፡፡ ግሩም ጌታ ይባርክህ፡፡

በእጄ የሞነጫጨርኩትን በኮምፒውተው ተይባ በሰረዝኩ በደለዝኩ ቁጥር ለማረም ሳትታክት የደከመችው እህቴ ሩት ወንድምአገኘሁ የሰባ ቡራኬ ይገባታል፡፡

ረቂቁን አንብበው ያረሙልኝ በብዙም ደስታ አስተያየታቸውን የሰጡኝ ጌቱ ግዛው፤ ማሙሻ ፋንታና እንደ ሥነ-ጽሁፍ መምህሬ የማየው ንጉሴ ቡልቻን ጌታ ይባርካችሁ እላለሁ፡፡

የመጀመሪያውን ረቂቅ ከማረም አንስቶ የመጨረሻውን ቅርጽ እስከማስያዝ ድረስ ሳይታክት የደከመውን ወዳጀን ተወልደ መኮንንን እንዴት አረሳዋለሁ?

ይ‘ች መጽሐፍ አንባቢያን እጅ እንድትደርስ በጎንዘባቸው የደገፉኝን የጎልደን ኦይል አገልግሎት ተባባሪዎች እና በቢሮ ውስጥ ቀን ተሌት የሚደክመውን ሶፎንያስ መለሰ ጌታ አብዝቶ ይባርካችሁ እላለሁ፡፡

በመጨረሻ፤ ግን በታላቅ አክብሮት የማመሰግነው ለዚህ ሁሉ ስኬት የጀርባ አጥንት የሆነችውን የምወዳትን ባለቤቴ ምኞቴ ክፍሌን ነው፡፡ እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርክሽ፡፡

ማውጫ

መግቢያ 1

1 እግዚአብሔርን የመምሰል ምሥጢር 4

የማይታይ አምላክ 4
በፍጥረቱ መታወቅ የሚወድ አምላክ 6
እግዚአብሔር ራሱን የገለጠባቸው መንገዶች 7
ክርስቶስ የእግዚአብሔር ፍፁም መገለጥ 10
የክርስቶስ አካል 11
የአካል ክፍሎች 13
እግዚአብሔርን መምሰል ምንድነው? 14

2 እግዚአብሔርን የመምሰል ዓላማና ምክንያት 18

ዓላማ 18
ምክንያት 25

3 እግዚአብሔርን የመምሰል ትምህርት 32

የትምህርት ሰንሠለት 32
የትምህርቶቻችን ገጽታ 34
የሐዋርያው ተልዕኮ 36
የትምህርቶች መለኪያ ዘንግ 37
ሕይወት የሚገኝበት ትምህርት 41
ጤናማ ትምህርት 51
የፀጋ ትምህርት 56

4 እግዚአብሔርን የመምሰል መንገድ 69

የመንገዱ ሰዎች 69
መንገዱን ማወቅ 71
የዘላለም ሕይወት 75
የዘላለም ሕይወት ምንድን ነው? 76
የሕይወት ሕግ 88
ባሕሪና ክብር 91

5 ችላ የተባለ ጠላት 104

የሥጋ ሕይወት ምንነት 106
የተዛባ ትኩረት 110
የሥጋ ሕይወት እንቅፋትነት 115
የሥጋ ሕይወት እንዴት ሊወገድ ይችላል? 118

6 የምሳሌ ያለህ 129

አብርሃም ፡- የእምነት ምሳሌ 131
የጳውሎስ የምሳሌነት አስተምህሮና ልምምድ 135
የአባቶች ያለህ 143

7 እግዚአብሔርን የመምሰል ልምምድ 146

የማይደረስበት የሚመስል ቅርብ 150
የእውነት ዓምድና መሠረት 154
ማንን እንመስላለን? 158

8 የክርስቶስ ባሕሪያት 166

ፍቅር 167
ይቅርታ 171
ትህትና እና የዋኅነት 180
ቸርነት ልግሥና 186
ትዕግሥት 190
ንጽህና 195
እግዚአብሔርን መፍራት 201

ማጠቃለያ 208

ማስታወሻ 209

መግቢያ

የዛሬ ስድስት ዓመት የጎልደን አይል የአገልጋዮች ማሰልጠኛ ማዕከልን በአዲስ አበባ ለመክፈት የተለያዩ ጥናቶችን ስናደርግና የጌታን ፊት ስንፈልግ «እግዚአብሔርን መምሰል» የሚለው ትምህርት ከሚሰጡት ኮርሶች አንዱ ብቻ ሣይሆን የማዕከሉ አብይ ትኩረት እንዲሆን ተስማምተን ነበር።

ከዚያም ማዕከሉ ተከፍቶ ሥልጠና ከተጀመረ በኃላ በተለያየ ጊዜያት ከማዕከሉ ተመርቀው የወጡ አገልጋዮች በዚህ ርዕስ ሕይወታቸው እንደተነካ ይመስክሩልን ብሎም በመጽሐፍ መልክ ተዘጋጅቶ ለማየት የነበረቸውን ናፍቆት አበክረው ይነግሩን ነበር።

እንግዲህ ይህ የተማሪዎች ጉትጎታ ነው «እግዚአብሔርን መምሰል» በጽሑፍ እንድትወጣ መነሻ የሆነው።

እኔም እንደብዙዎቹ የአገሬ አገልጋዮች ከመፃፍ ይልቅ መናገር ይቀናኛል። ሕዝባችን ከማንበብ ይልቅ መስማት እንደሚቀናው ሁሉ። ሆኖም ንግግር ውሱን፣ ተፅዕኖውም በቦታ የተገደበ መሆኑን በመገንዘብ ይልቁንም የብዕር ትሩፋት በስፋት የሚተም፣ ዘወትር በእጅ አድሮ የሚናገር ብሎም ለትውልድ የሚተላለፍ መሆኑን በመረዳት በልቤ ያለውን በጽሑፍ ለማስፈር ሞክሬአለሁ።

«እግዚአብሔርን መምሰል» የሚለው ርዕስ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጠንካራ ርዕሶች መካከል አንዱ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። ለዚህም እንደምክንያት ከሚጠቀሱት አንዱ የቋንቋ ጉዳይ ነው።

ምንም እንኳን የርዕሱ ጽንሰ ሃሳብ በብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ውስጥ በስፋት የሰረፀ ቢሆንም በዋነኝነት የተወሰው በአዲስ ኪዳን ውስጥ ነው። የአዲስ ኪዳን ጸሐፍት ይህን መንፈሳዊ ሃሳብ ለመገለጽ አዲስ ኪዳንን ከጻፉበት የግሪክ ቋንቋ «ዮሰቢያ» የሚለውን የግሪክ ቃል ተጠቅመዋል።

ይህ ቃል ምሉጥነትንና ለእግዚአብሄር መገዛትን ያመለክታል እንጂ ቃል በቃል «እግዚአብሔርን መምሰል» አይልም።

ይህን ቃል ሁሉም የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች "Godliness" በማለት ተርጉመውታል። የቀደመው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በዋነኝነት «እግዚአብሔርን መምሰል» በማለት ቢተረጉመውም በዚህ ብቻ ሳይወሰን በአንዳንድ ስፍራዎች «አምልኮ» «እግዚአብሔርን መፍራት» በማለት ጠርቶታል። አዲሱ መደበኛ ትርጉም ግን ሁሉንም «እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት» በማለት ለውጦታል።

ከቃሉ ስያሜ ባሻገር በመላው መጽሐፍ ቅዱስ ይልቁንም በአዲስ ኪዳን ገጾች በስፋት የሚንፀባረቀውን መልዕክት ስንመለከት ግን «እግዚአብሔርን መምሰል» በክርስቶስ ኢየሱስ የተካፈልነውን ዘላለማዊ ሕይወት በምድር ኑሮአችን ውስጥ በተግባር መግለጥ ላይ የሚያተኩር ትምህርት ሆኖ እናገኘዋለን።

በእርግጥ መልዕክቱ በመንፈስ ሕፃናት ለሆኑ አዳዲሶች የሚሰጥ ወተት ሳይሆን መልካምና ክፉን ለመለየት የለመደ ልቦና ላላቸው የሚቀርብ ጠንካራ ምግብ ይመስላል።

ይህንንም የሚያረጋጋጥልን የቃሉ ስርጭት ነው። ቃሉ በአዲስ ኪዳን ውስጥ 15 ጊዜ የተጻፈ ሲሆን ከአስራ አምስቱ ውስጥ አስራ ሁለቱ ሐዋርያው ጳውሎስ «ከእኔ ጋር አብረው

ሠራተኞች» ለሚላቸው ለጢሞቴዎስና ለቲቶ በዓፋቸው ሦስት መልእክቶች ውስጥ መገኘቱ ነው።

ይህች መጽሐፍ ለምን አሁን ወጣች? የምታበረክተውስ አስተዋጽኦ የሚኖራትስ ፋይዳ ምንድነው? የሚል የወቅታዊነት ጥያቄ ከተነሳ ጥያቄውን መመለስ የሚገባው አንባቢ ቢሆንም በዘመናችን ክርስቲያናዊ ባሕሪ ላይ ያለውን ብርቱ ተግዳሮት ከመመከት አኳያ ድርሻ እንደሚኖራት ያለኝን እምነት ላልገልጽ አላልፍም።

በመጨረሻም ንባብዎን ጀምረው እስከሚጨርሱ ባለው ሂደት የእግዚአብሔር መንፈስ የቃሉን አብርሆት እንዲሰጥዎት እና እግዚአብሔርን በመምሰል ጉዞዎ የሚረባዎትን ነገር እንዲሰንቁ በፀሎት የታጀበ ምኞቴን እገልፃለሁ። መልከም ንባብ።

ያሬድ ጥላሁን

ነሐሴ 1999 ዓ.ም

አዲስ አበባ

1

እግዚአብሔርን የመምሰል ምሥጢር

የማይታይ አምላክ

እግዚአብሔር ምን ይመስላል? ማንም በቀላሉ ሊመልሰው የማይችል ከባድ ጥያቄ ነው። ምክንያቱም እርሱ የማይታይ አምላክ ነው።[1] ዘላለማዊ ኃይሉና መለኮትነቱም የማይታይ ባሕሪ አጎናፅፎታል። ስለዚህ ማንም እግዚአብሔር ይህን ይመስላል ብሎ ሊናገር አይደፍርም።

በቁጥቋጦ ላይ በሚነደው እሣት የተገለጠለት፣ በእጁ ከእርሱም በፊት ሆነ ከእርሱ በኋላ ያልተከናወኑ ተዓምራትን የፈፀመበት፣ «አፍ ለአፍ በግልጥ አናግረዋለሁ»[2] ብሎ የመሰከረለት ሙሴ እንኳ «ክብርህን አሳየኝ» ብሎ በጠየቀ ጊዜ የተሰጠው መልስ «ሰው አይቶኝ አይድንምና ፊቴን ማየት አይቻልህም።»[3] የሚል ነበር።

ከሦስት ቀናት በኋላ እግዚአብሔር በዚህ ተራራ ላይ ይገለጣል የሚል አዋጅ የሰሙት የእስራኤል ልጆች ከግብጽ ምድር ያወጣቸው የአባቶቻቸው አምላክ ምን እንደሚመስል ለማየት ጓጉተው ቢጠብቁም በተባለው ዕለት ማየት የቻሉት ከባድ ደመና፣ እሣትና ከእቶን የወጣ የሚመስል ጢስ ብቻ ነበር። የሰሙትም ነጎድጓድ፣ መብረቅ እና እጅግ የበረታ የቀንደ መለከት ድምጽ ነበር።[4] ይህን ሁሉ ማየትና መስማት ቢችሉም እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል ኩልል ያለ ስዕል እንዳልነበራቸው ከትእይንቱ ባሻገር የተሰጣችው ጠንካራ ማስጠንቀቂያ ያመለክታል።

> *«እግዚአብሔር በኮሬብ በእሣት ውስጥ ሆኖ በተናገራችሁ ጊዜ መልክ ስቶ አላያችሁምና እጅግ ተጠንቀቁ ....።» ዘዳ. 4:15*

ሰለሞንም የእግዚአብሔር ስም ይጠራበት ዘንድ በኢየሩሣሌም የሠራውን መቅደስ ባስመረቀ ዕለት ንግግሩን የከፈተው «እግዚአብሔር በጨለማ ውስጥ እኖራለሁ ብሎአል፣ እኔ ግን ለዘላለም ትኖርበት ዘንድ ሠራሁልህ።» በማለት ነበር። በመቀጠልም

> *«ሰውኑ እግዚአብሔር ከሰው ጋር በምድር ላይ ይኖራልን? እነሆ ሰማይ ከሰማያትም በላይ ያለ ሰማይ ይይዝህ ዘንድ አይችልም ይልቁንስ እኔ የሠራሁት ቤተ እንዴት ያንስ ይሆን?» 2ዜና. 6:18*

በማለት እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል ለማወቅ እና ለመግለጽ አስቸጋሪ እንደሆነ መስክሯል።

ሐዋርያው ዮሐንስም፡ -

> *«መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድስ አንኳን የለም ...።» ዮሐ. 1:18*

በማለት የዘመናትን እውነታ በአጭር ቃል ጠቅልሎ አስቀምጧል።

ታዲያ እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል የማይታወቅ ከሆነ እንዴት ሊመሰል ይችላል? «የማያውቁት አገር አይናፍቅም» እንዲሉ የማያውቁትን መምሰል የማይታሰብ ነገር ነውና።

ስለዚህ እግዚአብሔርን ለመምሰል በቅድሚያ እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል ማወቅ ግድ ይላል።

እግዚአብሔር ይህን ይመስላል እንዳይባል የማይታይ ባሕሪና ታውቆ የማያልቅ ማንነት እንዳለው ሰው አይቶት በሕይወት ሊኖር እንደማይችል ከላይ ተዘርዝሯል። ታዲያ ምን ይሻላል? እነዚህን ሆድና ጀርባ የመሰሉ የአንድ እውነት ሁለት ገጾች እንዴት ማስታረቅ ይችላል? እግዚአብሔርን ለመምሰል እርሱ ምን እንደሚመስል ማወቅ ግድ ከሆነ እርሱ ደግሞ የማይታይ

ባሕሪና ታውቆ የማይጨረስ ማንነት ከተጎናፀፈ መፍትሔው ምንድነው?

በፍጥረቱ መታወቅ የሚወድ አምላክ

እግዚአብሔር የማይታይ መለኮት ይሁን እንጂ በፍጥረቱ መታየት ይፈልጋል። ታውቆ የማያልቅ ይሁን እንጂ በእጆቹ ሥራዎች መታወቅ በብርቱ ይሻል። ምክንያቱም ፍጥረት ሊያመልከው፣ ሊያደንቀውና የሚገባውን ክብር ሊሰጠው የሚችለው ሲያውቀው ነው።

ሰይጣን ስለራሱ የሚለውና በሰዎች ልቦና ውስጥ የሚስለው ገጽታ ከእውነተኛ ማንነቱ ጋር ፈጽሞ ስለማይሄድ በእውነት መታወቅን ይሸሻል። ስለዚህ የሚገዛቸውን አይነ-ልቦና ያሳውራል፣ ባለማወቅ ጨለማ ውስጥ ያኖራቸዋል። ሥልጣኑም ጨለማ ሠራሽ አለማወቅ ያጎናፀፈው ሥልጣን ነው።[5] ሰዎች በልባቸው ብርሃን በርቶ ማንነቱን ከተረዱ ረግጠውት እንደሚሄዱ አንጂ በአክብሮትና በፍርሃት እንደማይገዙለት አጥርቶ ስለሚያውቅ ራሱን ባለመታወቅ ጨለማ ውስጥ ከመሰወር ውጪ ሌላ አማራጭ የለውም። እግዚአብሔር ግን መታወቅ ያለበት፣ መታወቅ የሚገባው፣ እርሱም መታወቅ የሚፈልግ፣ ደግሞም በታወቀ ልክ የሚከብር አምላክ ነው።

የብሉይም ሆነ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት የተሞሉት እግዚአብሔርን ለማወቅ በተደረጉ ጥሪዎች ነው። ይህ ደግሞ እግዚአብሔርን የማወቅ፣ ምን እንደሚመስልም የመረዳት ተስፋን በመፈንጠቅ የማይታረቁ የሚመስሉትን የአንድ እውነት ሁለት ገጽታዎች ያስታርቅልናል።

እግዚአብሔር ራሱን የገለጠባቸው መንገዶች

እግዚአብሔር የማይታይ ባሕሪና ታውቆ የማያልቅ መለኮታዊ ማንነት ቢኖረውም በፍጥረቱ ይልቁንም በሰው ልጆች መታወቅ መፈለጉ በዘመናት ውስጥ በሰራቸው ሥራዎች በቃሉ ውስጥ ተዘክሯል።

ከእነዚህም ውስጥ ጎልተው የሚታዩትን ሁለቱን እንመልከት። እነዚህ ሁለት የእግዚአብሔርን ማንነት የመግለጥ ክንውኖች ወደ ሁለት የተለያዩ የሰው ዘር ክፍሎች ያነጣጠሩ ነበሩ። አንደኛው ወደ አሕዛብ ሁለተኛው ደግሞ ወደ እስራኤላዊያን።

1. በፍጥረት በኩል የተላለፈ መገለጥ

ሐዋርያው ጳውሎስ አይሁዳውያንን ጨምሮ የአለም ሕዝቦች ሁሉ ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች ያሉ ተከሳሾች መሆናቸውን በገለጠበት ክፍል «እግዚአብሔር ለእኛ ራሱን አልገለጠልንምና። ሊፈርድብን አይችልም!» ለሚሉት ነገር ግን የማይጠፋውን የእግዚአብሄርን ክብር በሚጠፋ ሰውና በወፎች አራት እግር ባላቸውም በሚንቀሳቀሱትም መልክ መስለው ለለወጡት[6] አሕዛብ መልስ ሲሰጥ እንዲህ ብሎ ነበር።

> *«. . . ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚቻለው ለእነርሱ ግልጽ ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር ለእነርሱ ግልጽ አድርጎታል። ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የማይታየው የእግዚአብሔር ባሕሪ ይኸውም ዘላለማዊ ኃይሉና መለኮትነቱ ከፍጥረቱ በግልጽ ይታያል ስለዚህ ሰዎች ማመካኛ የላቸውም።» ሮሜ 1:19፣20 (አ.መ.ት)*

የእግዚአብሔር የአፈጣጠር ሥርዓት በተወሰነ መጠን ቢሆንም እንኳ እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል የመግለጽ ሚና ተጫውቷል።

ይህም የፍጥረት ሚና ሲተነተን

- የሰማይ ግዑዝ ፍጥረታት

  «ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል ...::» መዝ.(19)1

- የወቅቶች መፈራረቅ፣ የእዝዕርት እና የመብል ሥርዓት

  «... ይሁን እንጂ ዝናብን ከሰማይ እንዲሁም ፍሬያማ ወቅቶችን በመስጠቱ ደግሞም ልባችሁን በመብልና በደስታ በማርካቱ መልካምን በማደረግ ራሱን ያለ ምስክር አልተወም::» ሐዋ. 14:17-18 (አ.መ.ት)

- የዘመን ልክ፣ የመኖሪያ ሥፍራና ዳርቻ (ድንበር)

  «... የሰውን ዘር ሁሉ ከአንድ ወገን ፈጥሮ በምድር ሁሉ ላይ እንዲኖሩ አደረገ:: የዘመናቸውን ልክና የመኖሪያ ስፍራቸውንም ዳርቻ ወሰነላቸው:: ይኸውም ሰዎች እግዚአብሔርን ፈልገው ተመራምረው ምናልባት ያገኙት እንደሆነ ብሎ ነው:: ይህም ቢሆን እርሱ ከእያንዳንዳችን የራቀ ሆኖ አይደለም:: የምንኖረውና የምንንቀሳቀሰው ያለነውም በእርሱ ነውና:: ከራሳቸው ባለቅኔዎችም አንዳንዶቹ እንዲሉት «እኛም ደግሞ ልጆቹ ነን» እንግዲህ የእግዚአብሔር ልጆች ከሆንን አምላክ በሰው ሙያና ጥበብ የተቀረፀውን ወርቅ ወይም ብር ወይም ድንጋይ ይመስላል ብለን ማሰብ አይገባንም:: ሐዋ. 17:26-29 (አ.መ.ት)

2. በነብያት በኩል የተላለፈ መገለጥ

በተራ ቁጥር አንድ የተገለፀው በሰው ብልሃት የተሰሩ ጣአታትን አማልክት ብለው ለሚያመልኩ አሕዛብ እግዚአብሔር እነዚያን የሰው እጅ ሥራዎች እንደማይመስልና የፍጥረት ሁሉ መገኛ ታላቅ አምላክ መሆኑን ለማሳየት ግዑዙን ፍጥረት ተጠቅሞ ለአሕዛብ ራሱን የገለጠበት መንገድ ነበር::

አሁን ደግሞ ከምድር ሕዝቦች መካከል ለሰየውና ሕዝቤ ብሎ ለጠራው ለእስራኤል ራሱን የገለጠበትን መንገድ እንመለከታለን::

ይህን ሐሳብ የዕብራዊያን መልእክት ፀሐፊ በመግቢያው ላይ በአንድ ቁጥር ጠቅልሎ አስቀምጦታል::

«ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ ...::» ዕብ. 1:1

ይህ ክፍል እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ መስራች አባቶች አንስቶ በየዘመናቱ ለተነሱት ትውልድ እንዴት ራሱን

ለመግለጽ እንደተናገረ በዝርዝር ያስረዳል::

- ከጥንት ጀምሮ:- ይህ አባባል ከክርስቶስ ልደት በፊት ሁለት ሺህ ዓመታትን የሚሸፍን ነው:: ስለዚህ ረጅም ዘመንን ያመለክታል::

- በነቢያት:- ይህ አባባል እግዚአብሔር ራሱን ለሕዝቡ ለመግለጥ የተጠቀማባቸው ሰዎች ቁጥር በርካታ መሆኑን ያመለክታል::

- በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና: - ይህ አባባል ደግሞ እግዚአብሔርን ለመግለጽ የተደረገው ጥረት በአንድ መንገድ ብቻ የተላለፈ ሳይሆን የተለያዩ ዘዴዎች፣ ምሳሌዎች፣ ማስረጃዎች፣ ወዘተ... ሥራ ላይ የዋሉበት መሆኑን ይገልፃል::»

ሆኖም ይህ ለአሕዛብም ሆነ ለእሥራኤል ሕዝብ ራሱን ለመገለጽ ያደረገው ጥረት እግዚአብሔርን ሙሉ በሙሉ ሊገልፀውና እንደሚፈልገው ሊያሳውቀው አልቻለም::

የጠፈርና የሕዋ አካላት ድምጽ አልባ ንግግር፣ የወቅቶች መፈራረቅ፣ የእዝርዕትና የመብል እርካታ ምስክርነት፣ የሕዝብ አሰፋፈር፣ የድንበር መካለልና የአገር አስተዳደር መልዕክት እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል ለሰው ልጆች ለመግለጽ የነበረው አቅም ከፍፁምነት እጅግ የራቀ ነበር::

እንኪን የፍጥረታት ድምፅ አልባ መልእክት በእግዚአብሔር መንፈስ ተነድተው የተናገሩት የጥንት ነቢያት ድምጽ እንኳ እግዚአብሔርን ፍንትው አድርጎ በመግለጽ በፍጥረቱ የመታወቅን ናፍቆት በሰው ልጆች የመመሰልን ጥማት ሊያረካ አልቻለም:: ለዚህም ነው ሌላ አዲስና ሕያው መንገድ የተመረቀው::

ክርስቶስ የእግዚአብሔር ፍፁም መገለጥ

ፍጥረታትና ነቢያት፣ እንደ ጥላና እንደ ምሳሌ ሲገልጡት የሞከሩት እግዚአብሔር በመጨረሻው ዘመን ጅማሬ ላይ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በአካል ተገልጿል። ይህ የዘመናት ታላቅ ሚስጥር መገለጥ የጀመረው ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ ሲወለድና ሰው ሆኖ ሲመጣ ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ከመወለዱ አንስቶ እስከ እርገቱ ያለው እያንዳንዱ አንቅስቃሴ የማይታየውን አምላክ ፍንትው አድርጎ ገልያታል። ይህም መገለጥ ግዑዙንም ሆነ መንፈሳዊውን ዓለም ሰውንም ሆነ መላዕክትን ምንም ሳያስቀር ሁሉን የጠቀለለ ነው።

ለዚህ ነው ሐዋርያው፦

> *«. . . በሥጋ የተገለጠ*
> *በመንፈስ የፀደቀ*
> *በመላዕክት የታየ*
> *በአሕዛብ የተሰበከ*
> *በአለም የታመነ በክብር ያረገ።» 1ጢሞ. 3:16*

በማለት በግጥም ቃና ' እግዚአብሔርን የመምሰል ሚስጥር መገለጡን የተረከው።

በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል የተገለጠው በራዕይ በሕልም ወይም ልዩ በሆነ ሚስጥራዊ መንገድ ሳይሆን ሊታይና ሊዳሰስ በሚችል ግልፅ ሁኔታ ነበር።

ላመኑትም እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል ማወቅ ብቻ ሣይሆን እርሱን መምሰል የሚችሉበትን በር ወለል አድርጎ ከፍቷል።

የኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ መምጣት «እግዚአብሔር ምን ይመስላል?» ለሚለው ጥያቄ የመደምደሚያ መልስ ሰጥቷል። ይህ ጥያቄ የሰው ብቻም አይመስልም መላእክትም በመገለጡ ዝርዝር ተካተዋልና « . . . በመላዕክት የታየ . . . » በሚል። ባጠቃላይ ለፍጥረት ሁሉ እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል በናዝሬቱ ኢየሱስ መገለጡን ይህ ክፍል ያረጋግጥልናል።

ወንጌላዊው ዮሐንስ፦

> *«መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው ሰንድስ ሰንኪን የለም በአቅፉ ያለው ሰንድ ልጁ አርሱ ተረከው።» ዮሐ. 1:18*

በማለት እንደገፈው በኢየሱስ ሕይወት እግዚአብሔር በቃል፣ በሥራ፣ በኑሮ ተተርኳል።

የክርስቶስ አካል

ይህ እግዚአብሔርን የመግለጥ ሚስጥር ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ በመምጣቱ ተጀምሮአል። ሆኖም በምድር አገልግሎቱ ብቻ አላከተመም። የጌታ ኢየሱስ የምድር አገልግሎት በአንድ አገር (በእስራኤል) የተገደበና በአብዛኛው በአይሁድ ሕዝብ ዘንድ የተወሰነ በመሆኑ የተቀረው ዓለም የእግዚአብሔርን መልክ የሚያይበት ባሕሪውን የሚረዳበት ሌላ መንገድ አልነበረውም። ስለዚህ ይህ የማይታየውን እግዚአብሔርን የመግለጥ የኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ መቀጠል ነበረበት።

ቀጣይነቱም ከፀሐይ መውጫ እስከ መጥለቂያዋ ያሉ የሰው ልጆች የእግዚአብሔርን መልክ እንዲያዩ ሲሆን በዚህም ሳይወሰን የእግዚአብሔር ልዩ ልዩ ጥበብ በሰማያዊ ሥፍራ ላሉ አለቆችና ስልጣናት ጭምር እንዲገለጥ ነው።

ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም። ጌታ ኢየሱስ በሰላሣ ሦስት ዓመታት የምድር ቆይታው

በመጨረሻም በመስቀል ሞቱ እግዚአብሄር ምን እንደሚመስል ለመግለጥ አካል አስፈልጎታል ይህም አከል በድንግል ማርያም ማህፀን ውስጥ መዘጋጀት ነበረበት።[5]

ይህ የሥጋ አካል ኢየሱስ ከሙታን ከተነሳ በኃላ ወደ ሰማያት አርጎ ሊታይ በማይቻል የክብር ብርሃን ውስጥ ተሰውሩአል።

እግዚአብሔርን በሥጋ አካል የመግለጡ ሂደት ግን አላከተመም። ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሊሞትና ሞትን አሸንፎ ሊነሳ ያስፈለገበት አንዱ ምክንይት ይህን ተግባር በቀጣይነት በምድር ላይ የምትፈጽም ሕያው አካል ለማዘጋጀት ነበር።

ይህችም አካል በወንጌል አምነው በዳኑ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በአካሉ ውስጥ ተጠምቀው ብልቶች በሆኑ ቅዱሳን የተገነባች፣ በሕብረቷ የእግዚአብሔርን ሕይወት በየሥፍራው ሁሉ የምትገለጥ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ናት። በዚች አካል ውስጥ የእግዚአብሄር ለፍጥረት መገለጥ አዲስ ጅማሬ ሳይሆን ክርስቶስ በሥጋ በመምጣቱ የተጀመረው ሥራ ቀጣይ ነው። ያኔም ከምድር በወሰደው አካል የተገለጠው አሁንም በአካሉ በቤተ-ክርስቲያን የሚገለጠው አንዱ እየሱስ ክርሰቶስ ነው።

ጳውሎስም በቤተክርስቲያን በኩል የሚገለጠው ጥበብ በግዑዙ አለም ብቻ የተገደበ ሣይሆን በሰማያዊ ስፍራ ወዳሉ አለቆችና ሥልጣናት ጭምር የዘለቀ መሆኑን በግልጽ ቃላት አስቀምጦልናል።[9]

ሆኖም አንድ ልብ ማለት ያለብን ቁም ነገር አለ። በቀደመው ንዑስ ርዕስ ውስጥ ያየነው ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ በመምጣቱ የሆነው የእግዚአብሔር መገለጥና አሁን በአካሉ በቤተክርስቲያን በኩል የሚካሄደው መገለጥ መሰረታዊ ልዩነት አላቸው።

ይኸውም የቀደመው ፍፁም መገለጥ ሲሆን ሁለተኛው ከፍፁምነት የራቀ ነገር ግን ወደዚያው የሚገሰግስ መሆናቸው ነው።

አዲስ የሰው ዘርና የበኩራት ዓይነት በመሆን በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ የተወለደችው ቤተክርስቲያን በአንድ በኩል ዓለም አቀፋዊ ማንነት ያላት ብትሆንም በሌላ ጎን አጥቢያዊ ገጽታ ስላላት በየትኛውም ሥፍራ ለሚኖሩ የሕብረተሰብ ክፍሎች እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል የማሳየት ተልዕኮ ለመወጣት አመችቷታል።

ይህንንም በአምልኮዋ፣ በንፁህ አካሄዷ፣ እርስ በርስ ባላት ፍቅርና በውጭ ላሉት በምታከናውናቸው በጎ ተግባራት እንድታንፀባርቅ ተሠጥቷታል።

ማንኛውም ሰው የልቡን ሃሳብና ስሜት የአካል ክፍሎቹን ተጠቅሞ ተግባራዊ እንደሚያደርግና በዙሪያው ያሉ ሰዎችም በአካሉ መልክና ቅርጽ አማካኝነት ለይተው እንደሚያውቁት ሁሉ ክርስቶስ ለዓለም ራሱን የሚገልጠው በአካሉ በቤተክርስቲያን በኩል መሆኑ ጥርጥር የሌለው ጉዳይ ነው።

ሆኖም ይህ እውን የሚሆነው ቤተክርስቲያን የዚህ እውነት ዓምድና መሠረት ስትሆን ነው።

የአካል ክፍሎች

እግዚአብሔር ምን ይመሰላል? ለዘመናት መልስ ያልነበረው ጥያቄ ቢሆንም ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ መምጣቱ መልስ አግኝቷል። ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ምን ይመስላል? ለሚለው ቀጣይ ጥያቄ መልስ ይሆን ዘንድ ሥራውን ፈጽሞ ወደሰማይ ከመሄዱ በፊት በምድር ላይ ሕይወቱን የሚገልጥባት ሕያው

አካል (ቤተክርስቲያን) ለመመሥረት የነበረውን ዓላማ ገልፆአል።[10] ይችም አካል በተለያዩ ብልቶች (የአካል ክፍሎች) የተገነባች ሕዋስ ናት። እነዚህም የአካል ክፍሎች በክርስቶስ አምነው የዳኑ ቅዱሳን ናቸው። የክርስቶስ ሙሉ ገጽታ በአንድ የአካል ክፍል (ግለሰብ አማኝ) ብቻ ሊታይ አይችልም ነገር ግን በአንድ አካባቢ በሚኖሩ ቅዱሳን ሕብረት (አጥቢያ ቤተክርስቲያን) ውስጥ በሙላት ሊገለጥ ይችላል። ሆኖም ለዚህ ውጤት ወሳኝ ሚና የሚጫወተው የእያንዳንዱ አማኝ መረዳትና ኑሮ መሆኑ የማይካድ ነው።

ሁላችንም የተጠራነው ክርስቶስ እንዲገለጥልንና እንዲገለጠብን ነው። በቅድሚያ ግን የምንገልጠው ሊገለጥልን ይገባል። በእኛ ውስጥ ያልተሳለውን ጌታ በሌሎች ፊት ልንስለው አንችልምና። ስለዚህ እያንዳንዱ አማኝ (ግለሰብ) የተገለጠለትንና የተገለጠበትን ሕይወት ይዞ ወደ ሕብረቱ ሲመጣ የእያንዳንዱ አማኝ በፍቅር መተሳሰር ሕያው አካል ይፈጥራል (ቤተክርስቲያን)። በዚህም አካል ውስጥ የሕይወት ራስ የሆነው (ክርስቶስ) ይታያል። ክርስቶስም በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት አካሉን ተጠቅሞ በሚሠራው ሥራ በዙሪያ ላለው ዓለም እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል ይገለጣል። ያኔ የእግዚአብሔር መንግስት ይሰፋል። ይህም እግዚአብሔርን የመምሰልን ሚስጥር ወደ ብርሃን ያወጣዋል።

እግዚአብሔርን መምሰል ምንድነው?

ለመሆኑ እግዚአብሔርን መምሰል ምንድነው? እግዚአብሔርን መምሰል ከቃሉ ትርጉም ያለፈ ግዙፍ ሃሳብ ነው። «እግዚአብሔርን የመምሰል ልምምድ» የተሰኘውን መጽሐፍ የፃፉት ጀሪ ብራጅስ ይህንን በተመለከተ እንደዚህ ብለው ነበር።

«እንደ እውነቱ ከሆነ እግዚአብሔርን መምሰል የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳናችን የተጠቀሰው በጥቂት ሥፍራዎች ብቻ ነው። ሆኖም መላው መጽሐፍ ቅዱስ ከዳር እስከ ዳር የሚናገረው እግዚአብሔርን ስለ መምሰል ነው።» [11]

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ለትርጉምም ሆነ ለመረዳት አስቸጋሪ ከሆኑት ቃላት ውስጥ እግዚአብሔርን መምሰል የሚለው ቃል ዋናውን ስፍራ ይይዛል ቢባል ማጋነን አይሆንም። ቃሉን ለመተርጎም አስቸጋሪ ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎች ይህን ሃሳብ ለመግለጽ የሰጡት የተለያየ ስያሜ ነው። ይህ ደግሞ የምንተረጉመው አንድ ቃል ቢሆንም ፍቺ የምንፈልግላቸው ቃላት ግን በርካታ እንዲሆኑ ያደርጋል። ከቃላት ጥናት ያለፈ ሌላው ተግዳሮት ደግሞ በቃል ትርጉም የማይገናኙ ነገር ግን ተዛማጅ መልዕክት ያላቸው በርከታ ሃሳቦች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መስፈራቸው ነው።

«እግዚአብሔርን መምሰል» ሙሉ በሙሉ የአዲስ ኪዳን ቃል ሲሆን የግሪክ መጠሪያውም «ዮሴብያ» የሚል ነው። ቃሉ በአዲስ ኪዳን ውስጥ 15 ጊዜ ተጠቅሷል።

ትርጉሙም ምሉጥ፣ለእግዚአብሔር የተሰጠ፣ትዕዛዛቱንና ፍቃዱን የሚከተል፣ አመለካከቱ በእግዚአብሔር ሕልውና የተቃኘ ሰውን ያመለክታል። የ1962 እትም የቀድሞው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ሥፍራዎች «እግዚአብሔርን መምሰል» እያለ ቢጠራውም በጥቂት ሥፍራዎች የተለያየ ስያሜ ተሰጥቶት እናገኛለን።

ይህ ትርጉም በ1ጢሞ. 2:10 ላይ «እግዚአብሔርን መፍራት» ሲለው በ2ጢሞ. 3:5 እና በቲቶ 1:2 ላይ ደግሞ «አምልኮት» ይለዋል።

ከ«ኒው ኢንተርናሽናል ቨርዥን» የተተረጎመው አዲሱ መደበኛ ትርጉም የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ግን ይህንን ቃል «እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት» በሚል መጠሪያ ተክቶታል።

ይህ ትርጉም «ዮሴቢያ» የሚለውን የግሪክ ቃል በጥሩ ሁኔታ የተረጎመው ቢሆንም እንኳ የቃሉ ሃሳብ ከቃሉ ትርጉም የሰፋ በመሆኑ ትክክለኛ መልዕክቱን ለማግኘት ሌሎች ተመሣሣይ ቃሎችን መመርመር የግድ ይሆናል። «ምሳሌ፣ መልክ ፣ መምሰል» የተሰኙት ቃሎች ምንም እንኳ ዮሴቢያ ከሚለው ቃል ጋር በቀጥታ አንድ ባይሆኑም በተዘዋዋሪ የሃሳብ ተዛማጅነት ስላለቸው የርዕሱን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይዘት አጉልተው ያሳዩናልና ተራ በተራ እንመልከታቸው።

ምሳሌ የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ 34 ጊዜ የተጠቀሰ ሲሆን በዕብራይስጥ «ዴሞት» በግሪክ ደግሞ «ሆምዮማህ» ተብሎ ይጠራል። ትርጉሙም በቅርጽ ወይም በመልክ መመሳሰልንና ምሳሌነትን ያመለክታል። ከዚሁ ጋር ተዛማጅ የሆነው «መልክ» የሚለው ቃል ትርጉም በዕብራይስጥ «ፀለም» በግሪክ ደግሞ «ኤኮን» ተብሎ ሲጠራ ትርጉሙም መምሰልን፣ ውክልናን፣ መመሳሰልን፣ ምሳሌነትን የሚገልጽ ነው።[5]

አንግዲህ እግዚአብሔርን መምሰል የተሰኘውን ቃል መጽሐፍ ቅዱስ አምልኮ፣ እግዚአብሔርን መፍራት፣ እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት በማለት በተለዋጭ የሚጠራው ከሆነ ከአንድ ነጠላ ርዕስነት ባሻገር የክርስትና ሕይወታችን ዋና ጉዳይ እንደሆነ መረዳት አያስቸግርም።

ከላይ እንዳየነው ከትርጉም ውስብስብነት የተነሳ እግዚአብሔርን መምሰል ምን ማለት እንደሆነ አጭርና ግልጽ ትርጓሜ መስጠት አስቸጋሪ ቢመስልም ፍቺውን ከመረዳት አኳያ መጽሐፍ ቅዱስ ከዳር እስከ ዳር ስለ ርዕሰ ጉዳዩ የሚናገረውን

ሃሳብ በመጭመቅ በአንድ ዓረፍተ ነገር ጠቅልሎ ማስቀመጡ አስፈላጊ ብቻ ሣይሆን ግድ ይሆናል። ስለዚህ እግዚአብሔርን መምሰል «የእግዚአብሔርን ሕይወት በሰው ማንነትና ኑሮ ውስጥ መግለጥ» ማለት ነው።

የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ሃሳብ፣ የማይለወጥ የፈቃዱ ምክር፣ ለዘመናት ተሰውሮ የኖረው ሚስጥሩ ምንድነው? ቢባል፦ እግዚአብሔር የገዛ ሕይወቱን በሰው ውስጥ ተገልፆ ለማየት መውደድ ነው። የእግዚአብሔር ሕይወት ከራሱ ከእግዚአብሔር ውጭ በሰው ውስጥ ተገልፆ ሊታይ ከሁሉ በላይ እግዚአብሔርን የሚያሳርፍና የሚያረካ መሰዕብ እንዳለው ከዚህ እውነት መረዳት እንችላለን።

2
እግዚአብሔርን የመምሰል ዓላማና ምክንያት

ዓላማ

በቀደመው ምዕራፍ «እግዚአብሔር ምን ይመስላል?» ከሚለው ጥያቄ በመነሳት እግዚአብሔርን የመምሰል ሚስጥር እንዴት እንደተገለጠ ለመመልከት ሞክረናል።

በዚህም ምዕራፍ ደግሞ «እግዚአብሔርን መምሰል ለምን አስፈለገን?» የሚለውን ጥያቄ በማንሳት በዓላማ ዙሪያ እናጠነጥናለን።

የዓላማ ጥያቄ በራሱ ግዙፍ ነው። የመኖር ዓላማ ሲሆን ደግሞ ግዝፈቱ የበለጠ ይጨምራል።

ክክርስቶስ ልደት በፊት ከኖሩ ጥንታዊ የግሪክ ፈላስፎች አንስቶ እስከ ዘመናችን የሳይንስ ተመራማሪዎች ድረስ የሰው ልጆችን የመኖር ዓላማ ጠይቆ ያልመረመረ ሊቅ የለም ቢባል ማጋነን አይሆንም።

ሆኖም እነዚህ ሁሉ ምርምሮች «ከየት መጣሁ? እኔ ማን ነኝ? የምኖረው ለምንድነው? መጨረሻዬስ የት ነው ?» ለሚሉት ዕድሜ ጠገብ የሰው ልጅ ጥያቄዎች መልስ ሊያፈልቁ አልቻሉም።

ይህ ጽሑፍ ግን አንድም በድፍረት አንድም በትህትና ለሰው ልጆች የመኖር ዓላማ ጥያቄ የማያሻማ መልስ አለ ይላል።

ትህትና ያስፈለገው ይህ መልስ የተገኘው በሥጋ ምርምርና የዕውቀት ልቀት ሳይሆን እግዚአብሔር በምህረቱ ይሁን ባለው

ሰማያዊ ብርሃን አማካይነት የተገኘ በመሆኑ ሲሆን ድፍረት ያስፈለገበት ምክንያት እያሌ ሰው ሰራሽ ግኝቶችና የሥጋ አእምሮ ጭማቂዎች ሰማያዊውን እውነት ለመሰወር ሽር ጉድ ስለሚሉ እውነትን በጽድቅ ድፍረት መግለጥ ስለሚገባ ነው።

እውነቱ ምንድነው? አንድ አማኝ የመመረጡ፣ የመፈጠሩ፣ የመዳኑና በቀጣይነት ለዘላለም የመኖሩ አላማ እግዚአብሔርን ከመምሰል ጋር በጽኑ የተቆራኘ ነው። ይህንንም ተራ በተራ እንመለከታለን፦

1. አለም ሳይፈጠር በፊት

> *«... ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር ይሆን ዘንድ አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወስኖአልና ...።» ሮሜ 8:29*

በዚህ ጽሑፍ ስለ ቅድመ-ውሳኔ፣ ስለምርጫና ስለ ዘላለማዊ መተማመኛ አንስቶ ለመነጋገር ጊዜውም ዝግጅቱም የለኝም። ሳድርገውም ብል ከተነሳሁበት ዓላማ ያወጣኛል። ነገር ግን ከላይ ባነሳሁት ክፍል ላይ ብቻ በመወሰን የሰው ማንነት እግዚአብሔርን ከመምሰል ጋር ያለውን ጥንታዊ ዝምድና ለማሳየት እሞክራለሁ።

እግዚአብሔር አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ የወሰነው አስቀድሞ ነው። ይህ ቅድመ-አውቅና እና ቅድመ ውሳኔ የሚጠቁመን የጊዜ ሰሌዳ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት የነበረውን የዘላለም ዘመን ነው። በዚህ ጥንተ-ዘላለም እግዚአብሔር ሰውን ያሰበው ከአንድ የከበረ እውነት ጋር በተዛመደ ነው። ይህን እውነት ሐዋርያው ጳውሎስ «አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ወስኖአል።» በማለት ገልጾታል።[12]

ከዚህም በመነሳት ሰው በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን ይመስል ዘንድ የታሰበው ዓለም ሳይፈጠር በፊት መሆኑን መገንዘብ አያዳግተንም። ይህም ሰው የተፈጠረበትን ዓላማ በጉልህ ያሳየናል።

2. የመጀመሪያው ሰው ሲፈጠር

«... እግዚአብሔርም አለ፦ ሰውን በመልካችን እንደምሳሌአችን እንፍጠር።»

የአንድ ነገር ዓላማው ሠሪው ሲፈጥረው ካሰበለት ኦርጅናል እቅድ እና እንዲኖር ከተፈለገበት ምክንያት ጋር በጽኑ የተቆራኘ ነው።

በዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ ውስጥ «እግዚአብሔርም አለ» የሚለው ቃል ሰባት ጊዜ ተመዝግቧል። ይህም የእግዚአብሔርን የመፍጠር ሥርዓት ያሳየናል። እግዚአብሔር አንድን ነገር ከመፍጠሩ በፊት በልቡ ያለውን ዓላማ ቃል አውጥቶ ይናገራል ያም የተፈጠረ ነገር በዘመኑ ሁሉ ለዚያ ዓላማ ይኖራል።

ለምሳሌ በሦስተኛው ቀን እግዚአብሔር ፦ -

«ምድር ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን በምድር ላይ እንደ ወገኑ ዘሩ ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን ታብቅል አለ። እንዲሁም ሆነ። ምድርም ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን እንደ ወገኑ ዘሩም ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን እንደ ወገኑ አበቀለች።» ዘፍ. 1:11-12

ዛሬ በዱር፣ በጋራ፣ በሜዳ፣ በሸንተረር፣ የምናያቸው ዛፎች ሁሉ አንድ የሚጋሩት ነገር አላቸው። እንደ ወገናቸው ዘራቸው ያለበትን ፍሬን ያፈራሉ። በኩሪያቸው ላለው ፍጥረት ከሚያበረክቷቸው አያሌ አስተዋጽኦ ባሻገር ፍሬያቸው ለመብል በፍሬያቸውም ውስጥ ያለው ዘር ለቀጣይነት ያገለግላል።

የተፈጠሩበት ዓላማ ነውና ይኖሩለታል፣ ይኖሩበታል። ይህ የአፈጣጠር ስርዓት በስድስት ቀን በተፈጠሩት ሁሉ ላይ በተመሳሳይነት ሲሠራ እናያለን።

አያንዳንዱ ፍጥረት «እንዲህና እንዲያ ... ይሁን» ተብሎ የተፈጠረበት ቃል አለው። የተፈጠረበት ዓላማም የሚገኘው በዚያ በተፈጠረበት ቃል ውስጥ ነው። ሰውም እንደ ሌሎቹ ፍጥረታት ሁሉ የተፈጠረበት ቃል አለው።

«እግዚአብሔርም አለ፦ ሰውን በመልካችን እንደምሳሌያችን እንፍጠር ...» ዘፍ. 26

ይህ ቃል የተፈጠርንበት ብቻ ሣይሆን የተፈጠርንለት ቃል ነው። የመኖር ዓላማችን በዚህ ቃል ውስጥ ተገልጿልና። ከዚህ ቀደም በምድር ላይ ኖረው ያለፉ፣ አሁንም በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱ ገናም ወደፊት በመወለድ ወደዚህች ምድር የሚገቡ የሰው ልጆች ሁሉ የተገኙት በዚህ ቃል ነው። ብርሃን ቀንና ሌሊትን እንዲለይ፣ ጠፈር በውሆች መካከል እንዲለይ፣ ዛፎች ዘሩ በውስጡ ያለበትም ፍሬ እንዲያፈሩ፣ የሰማይ ብርሃናት ለምልክቶች፣ ለዘመናት፣ ለወራትና ለዓመታት መለያ እንዲሆኑ፣ አእዋፋት በአየር እንዲበሩ፣ ዓሦች በባሕር እንዲዋኙ፣ እንስሳትና አራዊት በምድር እንዲንቀሳቀሱ እንደተፈጠሩ ሁሉ ሰው እግዚአብሔርን እንዲመስል ተፈጥሯል።

ቀጥሎው ባሉት ቁጥሮች እግዚአብሔር ሰውን እንዲበዛ ሲባርከው፣ እንዲገዛ ሲሾመው ብናይም መግዛት ሥራው መብዛት ደግሞ በረከቱ እንጂ የመኖሩ ዋነኛ ዓላማው አይደሉም። ሰው በትክክል መግዛትና መብዛት የሚችለው ሰተፈጠረበት ዓላማ ሲኖር ብቻ ነው። ያም አላማ እግዚአብሔርን መምሰል ነው። ይህም በማድረግ እና በመሆን መካከል ያለውን ልዩነት ያሳየናል። ዓላማም በዋነኛነት የመሆን ጉዳይ ነው።

እግዚአብሔር በግለሰቦች ሕይወት ውስጥ የግል ሕይወታቸውን በተመለከተ ዓላማ እንዳለው እሙን ነው። በዚህ ስፍራ የምናየው ዓላማ ግን የሰውን ዘር ሁሉ የሚጠቀልል ሁሉን

አቀፍ ዓላማ እንጂ ፈጽሞ ግላዊ አይደለም። ይህም ዓላማ በተፈጠርንበት ቃል ውስጥ አጭር እና ግልጽ ሆኖ ተቀምጧል።

በእርግጥ ሰው በኃጢአት በመውደቁ፣ በመንፈስ በመሞቱና በክፉ ኃይላት በመታሠሩ ከተፈጠረለት ዓላማ ርቆ በጨለማ ተቅበዝብዙአል። ሆኖም ለወንጌል ጥሪ ምላሽ የሰጡ ከእስራት ተፈተው ለተፈጠሩበት አላማ የሚኖሩበት አዲስ የሕይወት ምዕራፍ ተከፍቱአል።

ታዲያ ለሰው ልጅ ከኃጢአት ነጽቶ፣ በመንፈስ ሕያው ሆኖ እና የልብ አይኑ በርቶ ከተፈጠረለት ዓላማ ጋር ሲገናኝ ብሎም ለተገለጠለት እውነት ሲኖር ከማየት የበለጠ ምን የሚያስደስት ነገር አለ።

አሁንም ልብ እንበል የተፈጠርንለት ዓላማ በተፈጠርንበት ቃል ውስጥ ተገልጧል። የእግዚአብሔር መልክ እና ምሳሌ እንዲኖረን በአጭር ቃል እግዚአብሔርን እንድንመስል ተፈጥረናል።

3. አዲሱ ሰው ሲፈጠር

«... ለእውነትም በሚሆኑ ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ።» ኤፌ. 4:24

በተራ ቁጥር አንድ ላይ ሰው በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን ይመስል ዘንድ የታሰበው ዓለም ሳይፈጠር በፊት መሆኑን ተመልክተናል። ቀጥለንም ሰው የተፈጠረው ከዚሁ ጋር ተዛማጅ በሆነ አሳብ መሆኑን ለማየት ሞክረናል። አሁን ደግሞ ሰው የዳነው እግዚአብሔርን ከመምሰል ሃሳብ ጋር በተያያዘ መሆኑን ልንመለከት ነው። ሆኖም በተራ ቁጥር ሁለት እና ሦስት መሃል የተፈፀመውን የሰውን ውድቀት በጥቂቱም ቢሆን ሳንጠቅስ ማለፍ አግባብ አይሆንም። እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል ለፍጥረት ይገልጥ ዘንድ

በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ የተፈጠረው የመጀመሪያው ሰው በውድቀት ምክንያት ጥሪውንና ተልዕኮውን መወጣት ተስኖት

«ሰው ግን ክቡር ሆኖ ሳለውቅም እንደሚጠፉት እንስሳት መሰለ።» መዝ. 49:12

ተብሎ እንደተጻፈ እንስሳትን መስሏል።[1]

እግዚአብሔር ግን የሰው ውድቀትና ውድቀቱ ያስከተለው መዘዝ ሳያዳግተው በክርስቶስ ሥራ ሰውን ዓለም ሳይፈጠር በፊት ወዳሰበው ሥፍራ ሊያደርሰው አዲስ የምሕረት በር ሊከፍት እናያለን። የእግዚአብሔር ሃሳብ ዘላለማዊ ነውና የሰይጣን ተንኮል ወይም የሰው ድካም ሊገድበው አይችልም።

አዲስ ልደት ስናገኝ በኃጢአት ሙት የነበረው የውስጥ ሰውነታችን እውነተኛ በሆነ ጽድቅ እንዲሁም ቅድስና እግዚአብሔርን እንዲመስል ተፈጥሯል።

ሆኖም እግዚአብሔርን መምሰል በውስጥ ተሰውሮ የሚቀር ሚስጥር ሳይሆን በሁሉ ፊት በብርሃን ሊገለጥ የሚገባው ጉዳይ መሆኑን ከላይ የጠቀስነው ክፍል (ኤፌ. 4:24) « አዲሱን ሰው . . . ልበሱት» በማለት ያረጋግጥልናል።

4. በሚመጡት ዘመናት

«ወዳጆች ሆይ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን ምንም እንደምንሆን ገና ስልተገለጠም። ዳሩ ግን ቢገለጥ እርሱ እንዳለ እናየዋለንና እርሱን እንድንመስል እናውቃለን።» ፩ዮሐ. 3:2

የአማኞች እግዚአብሔር መምሰል በምድር ቆይታ በዚህ የድንኳን ኑሮ ውስጥ የሚያበቃ ሳይሆን ወደሚመጣው ዘመን ወደ ታላቅ ክብር የሚሸጋገር የዘላለም ተስፋ ነው።

እንዲያውም ዓለም ሳይፈጠር በሃሳብና በውሳኔ ደረጃ የነበረው ይህ ጉዳይ ሙሉ ፍፃሜ የሚያገኘው የተባረከው ተስፋችን የታላቁ አምላካችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ክብር

ከሰማይ ሊገለጥ ነው።[13] በኢየሱስ ዳግም ምጽአት የሚመረቀው ይህ አዲስ ዘመን የዘላለም ዘመን እንደመሆኑ መጠን እግዚአብሔርን መምሰላችንም እንዲሁ ለዘላለም የሚቀጥል ነው።

በዚህ ዘመን መንፈስ ቅዱስ ቅዱስ ቃሉን ሲያበራልን ብዙ አስደናቂ እውነቶች ተገልጠውልን በመደነቅ ተውጠን ሊሆን ይችላል። ነገር ግን የበለጠ መገለጥና ታላቅ መደነቅ የሚጠብቀን በሚመጣው ዘመን ነው። ምናልባትም ከሚያስደንቁን ነገሮች አንዱና ዋነኛው የሚሆነው እግዚአብሔርን መምሰላችን ሳይሆን አይቀርም። ምን ዓይነት መልክ እንደምንለብስ የማናውቅ ሰዎች እርሱ ሲገለጥ የዘላለም መልካችንን በእርሱ ላይ ስንመለከት እርሱንም ስንመስል ምንኛ ያስደንቅ?

እንግዲህ «እግዚአብሔርን መምሰል ለምን?» የሚለውን የዓላማ ጥያቄ ለመመለስ ያደረግነው መከራ የተሳካ ይመስላል። በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን መምሰል ዓለም ሳይፈጠር በፊት የታሰብኩበትና የተመረጥኩበት ዓላማ ከሆነ፣ በአዳም ውስጥ ስፈጠር የተፈጠርኩበት ዓለማ ከሆነ፣ በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ከሞት ወደ ሕይወት ስሻገር የዳንኩበት ዓላማ ከሆነና አሁንም የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ከሰማይ መገለጥ የምጠብቅበት ብቸኛ ተስፋዬ ከሆነ እኔ እግዚአብሔርን ከመምሰል ውጭ የምኖርበት ወይም የምኖርለት ሌላ ማንነት የለኝም ሊኖረኝም አይችልም። ለዚህ ነው በክርስቶስ አምኖ የዳነ ሁሉ እግዚአብሔርን መምሰል የሕይወት ዓላማው ሊሆን ይገባል የምንለው፡

ምክንያት

ከሰማይና ከምድር ልደት አንስቶ ሰው በኃጢያት አለከወደቀበት ድረስ ያለውን የመጀመሪያ ክንውን የሚተርኩልን የዘፍጥረት የመጀመሪያ ሦስት ምዕራፎች መጠናቸው ቢያንስም በውስጣቸው የታመቀው እውነት ግን ተተርኮ የሚያልቅ አይመስልም።

በእነዚህ ጥቂት ምዕራፎች ውስጥ የሞሉትን መልዕክቶች አንድ ባንድ የመዘርዘር ሃሳብ ባይኖረኝም እግዚአብሔርን ከመምሰል ምክንያት ጋር በተዛመደ ሁለት ነጥቦችን ላነሳ ወደደድሁ። አንደኛው ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ባለው ግንኙነት ዙሪያ የሚያጠነጥን ሲሆን ሁለተኛው ሰው ከፍጥረት ጋር ያለው ግንኙነት ላይ የሚያተኩር ነው።

1. የእግዚአብሔር አረፍት

እግዚአብሔር በስድስት ቀናት ውስጥ የመፍጠርን ሥራ ካከናወነ በኃላ በሰባተኛው ቀን ከሥራው ሁሉ እንዳረፈ ዘፍጥረት ይነግረናል። ለምን አረፈ? ብሰን ብንጠይቅ ከክፍሉ የምናገኘው መልስ ‹‹ሥራውን ስለጨረሰ›› ከሚል የዘለሰ አይሆንም። ነገር ግን ‹‹አዲስ ኪዳን በብሉይ ኪዳን ውስጥ ተሰውሯል፤ ብሉይ ኪዳንም በአዲስ ኪዳን ውስጥ ተገልጧል›› በሚለው እውነት አዘል ብሂል መሠረት የዚህን ሃሳብ ፍቺ ርቀን በአዲስ ኪዳን መጻህፍት አውድማ በዕብራዊያን መልዕክት ውስጥ እናገኘዋለን።

የዕብራዊያኑ መልዕክት ጸሐፊ በክርስቶስ እየሱስ አምነው ከዳኑ በኃላ ከገዛ ወገኖቻቸው በደረሰባቸው ጽኑ መከራ ተናውጠው ከጀመሩት የእምነት ጉዞ ወደኃላ በማለት ላይ ያሉትን አይሁዳዊያን አማኞች የተሰጠውን ተስፋ ለመውረስ እየተቃረቡ እንደሆነ በመግለፅ ባለማመን ጠንቅ እንዳይወድቁ በዚህም ተስፋውን መውረስ ተስኗቸው በምድረበዳ የቀሩትን የቀደሙትን አባቶች ታሪክ እንዳይደግሙ በብዕሩ ይማፀናቸዋል። በመቀጠልም የሚወርሱት ተስፋ እንደጥንቶቹ አባቶች ማርና ወተተት የምታፈስ ምድር ሳይሆን በኑሯቸውና በአገልግሎታቸው የሚገለጥ እግዚአብሔርን የሚሳርፍ ሕይወት እንደሆነ ይነግራቸዋል።

ከምድር ልደት አንስቶ እግዚአብሔር በምድር ላይ ማረፊያ ይፈልጋል።[14] የሚያርፈውም በሰው ሕይወት ውስጥ እንጂ በግዑዝ ምድር ወይም የሰው እጅ በሰራው ቤት ውስጥ አለመሆኑን በነቢዩ አፍ እንዲህ በማለት ይገልፃል ፦

> *«እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ፦ ሰማይ ዙፋኔ ነው፥ ምድርም የእግሬ መረገጫ ናት፤ የምትሰሩልኝ ቤት ምን ዓይነት ነው? የማርፍበትስ ስፍራ ምንድነው? እነዚህን ሁሉ እጄ ሰርታለችና እነዚህ ሁሉ የእኔ ናቸው፥ ይላል እግዚአብሔር ነገር ግን ወደዚህ ወደ ትሁት መንፈሱም ወደ ተሰበረ በቃሌም ወደሚንቀጠቀጥ ሰው አመለከታለሁ።»* ኢሳ. 66፡1-2

የእግዚአብሔር ዕረፍት አካላዊ ሳይሆን የልብ ዕረፍት ነው። ስለዚህ የዕብራዊያን መልዕክት ፀሐፊ ይህንን ለመግለፅ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ የእግዚአብሔር ዕረፍት ተምሳሌት ሆነው የቀረቡትን ሦስት ጥላዎች ያነሳላቸውና እውነተኛው አካል በመምጣቱ ጥላና ምሳሌ የነበሩት ከመንገድ እንደተወገዱ ይነግራቸዋል ። እነዚህም ጥላዎች ፦

1.1 መቅደስ

«ለመካከላቸውም አድር ዘንድ መቅደስ ይሥሩልኝ» ዘፀ 25:8

በማለት በተራራ ላይ ለሙሴ በተሰጠው ንድፍ መሠረት የተሰራውና ቆይቶም በንጉሥ ዳዊት የታደሰው የማደሪያ ድንኳን፤ ቀጥሎም በሰለሞን የተሰራውና በባቢሎን ሠራዊት ፈርሶ ከሰባ ዓመታት በኃላ በነዘሩባቤል እንደገና የተገነባው መቅደስ የነበረው አንድ ግልፅ ተልዕኮ እግዚአብሔርን በምድር ላይ ማሳረፍ ነበር። ሆኖም ምሳሌ ከመሆን ባሻገር እግዚአብሔርን በእውነት ማሳረፍ ስላልቻለ እግዚአብሔር ሌላ ዘላለማዊ ማረፊያ ማበጀቱን ጸሀፊው እንዲህ በማለት ነግረናል።

« . . . እኛም የምንደፍርበትንና የምንመካበትን ተስፋ እስከ መጨረሻ አጽንተን ብንጠብቅ ቤቱ ነን።» ዕብ.3:6

ይህም እኛ የአዲስ ኪዳን አማኞች ከዳንበት ጊዜ አንስቶ በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን ወደ መምሰል የምናደርገው ጉዞ ፍጻሜው የእግዚአብሔር ዕረፍት መሆኑን ያረጋግጥልናል።

1.2 የከነዓን ምድር

ወደ ከነዓን ምድር መግባት የእስራኤላውያን ዕረፍት እንደሆነ እናስባለን። ነገር ግን የከነዓን ምድር በዋነኝነት የእግዚአብሔር ዕረፍት ነበር። እግዚአብሔር ራሱ ‹ዕረፍቴ›2 በማለት ጠርቶታልና። እውነቱም ይህ ነው የእስራኤል ልጆች ያረፉት

በተዘረጋችና በፀናች እጅ ከግብፅ ባርነት በወጡ ጊዜ ነበር። የተቀረው ጉዞ ያሳረፋቸውን እግዚአብሔር በኑሯቸው ሁሉ ማሳረፍ ወደሚችሉበት ስፍራ ለመድረስ የተደረገ ጉዞ ነበር። ሆኖም ወደዚህ ደረጃ መድረስ ከግብፅ ለወጡት ሁሉ አልተቻላቸውም ባለመታዘዝ ጠንቅ በምድረበዳ ወድቀዋልና። የዕብራዊያን መልዕክት ጸሐፊም የከነዓንን ተምሳሌት በመጥቀስ የአዲስ ኪዳኖቹን እኛን ፦

> ‹‹እንግዲህ ወደ ዕረፍቱ ለመግባት ተስፋ ገና ቀርቶልን ከሆነ ምናልባት ከእናንተ ማንም የማይበቃ መስሎ እንዳይታይ እንፍራ።›› ዕብ. 4:1

በማለት ያስጠነቅቃል። ምንም እንኳ በምድረበዳ የተወለደው አዲስ ትውልድ በኢያሱ መሪነት ወደ ከነዓን ምድር ቢገባና ተስፋውን የወረሰ ቢመስልም እንኳ ያገኘው ምሳሌና ጥላውን እንጂ እውነተኛውን አካል አልነበረም። ይህንንም ፦

> ‹‹ኢያሱ ሰላርፈፋቸው ኖሮ ቢሆንስ ከዚያ በኋላ ስለ ሌላ ቀን ባልታገረ ነበር። እንግዲስ የሰንበት እረፍት ለእግዚአብሔር ሕዝብ ቀርቶላቸዋል።›› ዕብ. 4:8-9

1.3 የሰንበት እረፍት

ጸሐፊው በሦስተኛ ደረጃ የሚያነሳው በምድር ላይ የሚገለጽ የእግዚአብሔር እረፍት ምሳሌ ‹ሰንበት› ነው።

እስከ አሁንም ድረስ የአይሁዳዊያን ሳምንት መጨረሻ ቀን ተደርጎ የሚከበረው ሰንበት (ቅዳሜ) ከመሰረቱ ስንመለከተው የእግዚአብሔር እረፍት እንጂ የሰው ዕረፍት እንዳልሆነ መመልከት አያስቸግርም ቃሉ ፦

> ‹‹ እግዚአብሔርም የሠራውን ሥራ በሰባተኛው ቀን ፈጸመ፤ በሰባተኛውም ቀን ከሠራው ሥራ ሁሉ አረፈ።›› ዘፍ 2:2

ይለናልና።

ሆኖም ይህ የእግዚአብሔር እረፍት ሲቀጥል አንመለከትም ወዲያው ሥራ ውስጥ ሲገባ እናያለንና። ጌታ ኢየሱስ እንኳ ‹‹ሰንበት ለምን ፈወስክ?› ተብሎ በኃይማኖት ሰዎች በተጠየቀ ጊዜ የሰጠው ቀጠተኛ መልስ

> ‹አባቴ እስከዛሬ ይሠራል፤ እኔም ደግሞ እሠራለሁ።› ዮሐ. 5:17

የሚል ነበር።

እግዚአብሔር ከእረፍቱ ወጥቶ እንዴት እንደገና ሥራ ውስጥ ገባ? የሚል ጥያቄ ሊፈጠርብን ይችል ይሆናል። የዚህን ጥያቄ መልስ ለማግኘት ግን አስቀድሞ እንዴት? በምን? አረፈ የሚለውን ጥያቄ መመለስ ይኖርብናል። ምንም እንኳ ዘፍጥረት ይህንን ግልጽ ባያደርግልንም እንደ ዕብራዊያን ካሉ የአዲስ ኪዳን መጻህፍት እንደምንረዳው እግዚአብሔር በሰባተኛ ቀን ያረፈው በስድስተኛው ቀን ሰውን በመልኩና በምሳሌው ከፈጠረ በኃላ ነበር። ይህም የሚያሳየን የእግዚአብሔር ልብ በምድር የሚያርፈው እርሱን የሚመስሉ ሰዎች ሲኖሩ እንደሆነ ያመለክተናል። የእረፍቱ ምክንያት ምን እንደሆነ ካረጋገጥን በኃላ ተመልሶ ወደ ሥራ ውስጥ የገባበትን ምክንያት ለማወቅ ፈጽሞ አያስቸግረንም። ለእግዚአብሔር በምድር ላይ ማረፊያ እንዲሆን የተፈጠረው ሰው በኃጢያት በመውደቁና በመንፈስ በመሞቱ እርሱን የሚመስልና ልቡ የሚያርፍበት ሰው ዳግመኛ እስኪፈጥር ድረስ እግዚአብሔር ከእረፍቱ ወጥቶ ሥራ ውስጥ ገብቷል። ዳግመኛ ወደሥራ የማያስገባው ዘላለማዊውን ሰንበት (እረፍት) ለማምጣት ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ ወደ ምድር መጣ። የመጣውም

በሞቱና በትንሳኤው እግዚአብሔርን የሚመስል አዲስ ሰው ለመፍጠር ነበር።[15]

ለእግዚአብሔር እውነተኛ የሰንበት ምክንያት የሚሆን አዲስ የሰው ዘር ለመፍጠር የመጣውን ኢየሱስን አይሁዳዊያን ቀን እንዲያከብር ይጠብቁበት ነበር።

አንድ ቀን በሰንበት ደቀ-መዛሙርቱ በእርሻ መካከል ሲያልፉ ተርበው ነበርና እሸት ቀጥፈው ሲበሉ የተመለከቱ ፈሪሳውያን ሲከሷቸው ጌታ የሰጣቸው መልስ እንዲህ የሚል ነበር ፦

> *«ምሕረትን እወዳለሁ መሥዋዕትንም አይደለም ያለው ምን እንደሆነ ብታውቁስ ኃጢያት የሌለባቸውን ባልኮነናችሁ ነበር። የሰው ልጅ የሰንበት ጌታ ነውና።» ማቴ. 12:7-8*

አምን ኢየሱስ የእግዚአብሔር እረፍት ብቻ ሳይሆን ለዘላለም የእረፍቱ ምክንያት የሚሆነውን አዲስ የሰው ዘር በሞቱና በትንሣኤው በመፍጥር የሰንበት ጌታ ሆኗል። ለዚህም ነው የዕብራዊያን መልዕክት ጸሐፊ ፦

> *«ሥራው ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ምንም እንኳ ቢፈጸም፦ እንግዲህ ፦ ወደ እረፍቴ አይገቡም ብዬ በቁጣዬ ማልሁ እንዳለ እኛስ ያመንን ወደ እረፍቱ እንገባለን። ስለ ሰባተኛው ቀን በአንድ ሥፍራ፦ እግዚአብሔር በሰባተኛው ቀን ከሥራው ሁሉ አረፈ ብሎአልና፤ በዚህ ሥፍራም ደግሞ፦ ወደ እረፍቴ አይገቡም።» ዕብ.4:3-5*

ስለዚህ ለእኛ ሰንበት እግዚአብሔርን ወደ መምሰል ሕይወት በመጓዝ በትጋት ተጋድለን በብቃት ታዘን የምንወርሰው ተስፋ ነው። የእግዚአብሔርን ልብ በምድር ላይ ለማሳረፍ በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን መምሰል ግድ ነውና።

2. መግዛት

እግዚአብሔር ሰውን በመልኩና በምሳሌው ከፈጠረ በኃላ የሰጠው የሥራ ድርሻ መግዛት ነበር። በሰማይ የሚበሩትን አዕዋፋት፤ በምድር የሚንቀሳቀሱትን እንስሳት፤ በባህር ውስጥ የሚኖሩትን አሶች ባጠቃላይ ምድርንና ሞላዋን እንዲገዛ ትዕዛዝ ሲሰጠው እናያለን። ሆኖም አዳም ምድርን ለመግዛት ሰይፍ መሳል፤ ጦር መስበቅ ወይም ሰራዊት ማስከተት አላስፈለገውም። ሁሉ እንዲገዛለት የሚያደርግ ምሥጢር ነበረዋ! ያም ምሥጢር እግዚአብሔርን መምሰል ነበር። ከውስጡ የሚሰረፀው ባሕሪ፤ በወጭው የሚያንፀባርቀው ክብር ሁሉን ፀጥ ለጥ አድርጎ ለመግዛት በቂ መሳሪያ ነበር። የእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ ገዢ ነውና።

የእግዚአብሔር ምሳሌ ሆኖ የመጣው ጌታ ኢየሱስ በሶስት ዓመት ተኩል አገልግሎቱ በምድር ሲመላለስ ባልተለመደ መልኩ ፍጥረትን ሲገዛ ደግሞም ሲታዘዝለት እንመለከታለን። በቃሉ አሦች ሲሰበሰቡ ፣በቃሉ ማዕበልና ወጨብ ፀጥ ሲል፣በቃሉ በለስ ስትደርቅ ወ.ዘ.ተ. ለምን? አምላክ ስለሆነ ? አይደለም። በአምላክነቱማ ሁሉን ፈጥሯል ነገር ግን እግዚአብሔርን የሚመስል ሰው ሆኖ በምድር ላይ በመመላለሱ ለሰው የተሰጠውን ወድቆም የነበረውን የገዥነት በትር እንስቶ ሲጠቀም እናያለን።

ይህም ለመግዛት እግዚአብሔርን መምሰል ምትክ የሌለው መሣሪያ መሆኑን ያሳየናል።

3
እግዚአብሔርን የመምሰል ትምህርት

እግዚአብሔርን በመምሰል ሂደት ውስጥ የትምህርት ድርሻ ከፍተኛ ነው። ትምህርት አውቀትን የማስተላለፊያ መንገድ እንደመሆኑ መጠን ደረጃ በደረጃ እየተገለጠ ሥራውን ይፈጽማል። የእግዚአብሔር ሥራ በጨለማና በስውር የሚከናወን ሚስጥር ሳይሆን ቢያንስ ለግለሰቡ እንደሚገባ ሆኖ በብርሃን የሚከናወን ተግባር ነው። ይህም ብርሃን ከቅዱስ ቃሉ የምናገኘው አውቀት ነው። ያለዚህ አውቀት እግዚአብሔርን መምሰል ሊታሰብ አይቻልም።

«... የፈጠረውንም ምሳሌ እንዲመለስ አውቀትን ለማግኘት የሚታደሰውን አዲሱን ሰው ለብሳችሁታል ...።» ቆላ. 3:10

በውስጣችን ያለው አዲስ ሰው እግዚአብሔርን በመምሰል በኑሮ ሊገለጥ የሚችለው አውቀትን በማግኘት ሲታደስ ብቻ ነው።

ሆኖም ይህ አውቀት በውሸት አውቀት የተባለ ከንቱ መለፍለፍ ሳይሆን በክርስቶስ የሆነ ጤናማ ትምህርት መሆን ይኖርበታል።

ከዚህም በመቀጠል ትምህርትን በተመለከተ የአዲስ ኪዳንን እውነት ከዘመናችን የቤተ-ክርስቲያን የትምህርት ይዘት ጋር እያመሳከርን እንመለከታለን።

የትምሕርት ሰንሠለት

ትምህርት ከመድረክ የምንሰማው ወይም ሌሎችን የምናስተምረው አውቀት ብቻ ሳይሆን በውስጣችን ተዋህዶ፣ በደማችን ሰርፆ የምንኖረው ሕይወት ነው። ይህን ለመረዳት ሐዋርያው ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በፃፋቸው ሁለት መልእክቶች

ውስጥ ስለ ትምህርት ያነሳውን ሰንሠለት መሰል ቅጥልጥል መመልከት በቂ ነው።

«የእግዚአብሔር ሰምና ትምህርቱ እንዳይሰደብ ... » 1ጢሞ. 6:1

ሐዋርያው «ትምህርቱ» ብሎ በመጥራት የእግዚአብሔር ትምህርት መሆኑን ግልፅ አድርጎልናል። ይህም እግዚአብሔር ትምሕርቶች ሳይሆን አንድ «ትምህርት» እንዳለው ይህም ትምህርት «ክርስቶስ» እንደሆነ ይጠቁመናል። በመቀጠልም ፡ -

«አንተ ግን ትምህርቴን . . . ተከተልህ» 2ጢሞ. 3:10

በማለት አስቀድሞ የጠቀሰው የእግዚአብሔር ትምህርት የራሱ (የጳውሎስ) ትምህርት እንደሆነ ይጽፋል። ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? ካልን ትምህርቱ አስቀድሞ የእግዚአብሔር ትምህርት ነበር። እግዚአብሔር ግን ይህን ትምህርት ለአሕዛብ እንዲደርስ የተርሴሱን ሳውል በአስደናቂ ሁኔታ በመጥራት ለሦስት ዓመታት በአረብ አገርና በደማስቆ በመንፈስ ቅዱስ ካስተማረውና ከገለጠለት በኃላ በውስጡ ተዋህዶ በደም ሥሩ የሚዘዋወር ሕይወትና እስትንፋሱ እንዲሆን አድርጎ ላከው። ለዚህ ነው ጳውሎስ በድፍረት «ትምህርቴ» የሚለው። ይህ ትምህርት ጳውሎስ በመድረክ የሚሰብከው ብቻ ሳይሆን ዕለት ዕለት የሚኖረው ሕይወት ስለነበረ ጢሞቴዎስ ከመማር አልፎ ሊከተለው ችሏል። ጳውሎስ በመቀጠልም፡-

*«ለራስህና ለትምህርትህ ተጠንቀቅ ...።»*1ጢሞ. 4:16

በማለት ይህ ትምህርት የእሱ ብቻ ሳይሆን ጢሞቴዎስ አብሮት ባሳለፈው ዘመን ሁሉ ወደ ውስጡ ሰርፆ በመግባት አስተሳሰቡን እና ኑሮውን ወርሶ የገዛ ሕይወት መሆኑን ያሳየዋል።

በመጨረሻም ሐዋሪያው በሰማዕትነት ሕይወቱ ሊያልፍ በተቃረበበት አስጨናቂ ወቅት የዚህ ትምህርት ቀጣይነት እንዳይቋረጥ በማሰብ ይህ ትምህርት ትምህርታቸው የሆነና

ትምህርታቸውም ይሆን ዘንድ ለሌሎች ማስተላለፍ ለሚችሉ ሰዎች አደራ እንዲሰጥ ጢሞቲዎስን እንዲህ በማለት ሲያዘው እንመለከታለን ፡ -

«ብዙሀ ምሥክር ፊት ከእኔ የሰማኸውን ሌሎችን ለማስተማር ብቃት ላላቸው ለታመኑ ሰዎች ዐደራ ስጥ።» 2ጢሞ. 2፡2

እንግዲህ ለንሠለት ያልነው ቅጥልጥል ትምህርቱ (የእግዚአብሔር)፣ ትምህርቱ (የጳውሎስ)፣ ትምህርትህ (የጢሞቴዎስ)፣ ትምህርታቸው (ሌሎችን ለማስተማር ብቃት ያላቸው የታመኑ ሰዎች) መሆኑን ነው። ይህም ከዘላለም ዘመናት ጀምሮ የነበረ የእግዚአብሔር ትምህርት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

የትምህርቶቻችን ገጽታ

በሚያሳዝን መልኩ እግዚአብሔርን መምሰል የዘመናችን መታወቂያ አይደለም። ይልቅ እግዚአብሔርን የመምሰል ተቃራኒ ባሕሪያት ከምንጊዜውም ይልቅ በቤተክርስቲያን ውስጥ ተንሰራፍተዋል። ይህ ለምን ሆነ?

«ሰው ኑሮውን ይመስላል» እንዲሉ አማኝም ትምህርቱን ይመስላል። ሰው ወደ ሆዱ የሚያስገባው ምግብ ስጋው ላይ ለውጥ እንደሚያመጣ ሁሉ አማኝም ወደ መንፈሱ የሚያስገባው ነገር የመንፈሳዊ ሕይወቱን ገጽታ ይወስነዋል።

የትውልዳችንን መንፈሳዊ እውነታ ለመመልከት በየአብያተክርቲያናቱ እና ፕሮግራም አሰ በተባለበት መድረክ የሚሰጠውን ትምህርት ማዳመጥ በቂ ይሆናል። ሕዝብ የሚሰማው ነገር ውጤት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ «እምነት

ከመስማት ነው» እንደሚል የነገርነውን ይሰማል፣ የሰማውንም ያምናል ያንኑ ይኖራል። ታዲያ ሕዝባችን ምን እየሰማ ነው?

በእርግጥ ሕዝባችን በጎም ሆነ ክፉ አንድ ወጥ የሆነ ነገር ይሰማል ብሎ ማለት አስቸጋሪ ነው። እንደው ሌላው ይቅርና በሳምንት አንዴ በስንክት ወደቤተክርስቲያን የሚሄድ አንድን ሰው ምሳሌ ብንወስድ በዓመት ውስጥ ባሉት ሃምሳ ሁለት ሣምንታት ሃምሳ ሁለት የተለያዩ ነገሮችን ሊሰማ የሚችልበት አጋጣሚ ሰፊ ነው። አንዳንዴ ያለፈው ሳምንት የተናገረውን የእሁኑ ሲያፈርሰው እሁን የተናገረውን ደግሞ የሚመጣው ሲያፈርሰው ማየት የተለመደ ክስተት ነው። ተናጋሪዎቹ ቢለዋወጡም ይህ ሰው ግን ሳይለወጥ ይሰማል። በዓመቱ መጨረሻ ምን ጨበጥክ? ምን ሊመልስ እንደሚችል መገመት አስቸጋሪ ነው። ከዓመታት በፊት አንድ አገልጋይ ባልንጀራዬ «ጉባዔአችን እኮ እንደ አብዶች ማሣ ነው። አብዶች በጋራ የሚያርሱት ማሳ ላይ አንዱ ስንዴ፣ ሌላው ገብስ፣ ሌላው ደግሞ ጤፍ ይዘሩና የመከር ወራት ሲመጣ የምን እርሻ እንደሆነ እንኳን አይታወቅም። የእኛም ጉባዔዎች የተለያዩ ሰዎች የተለያየ ነገር በየሣምንቱ ስለሚዘሩባቸው በፍፃሜው ውጥንቅጥ እንጂ ምርት አይኖርም» ያለኝ ፍፁም አይረሳኝም።

ሕዝብ እግዚአብሔርን መምሰል ይለማመድ ዘንድ እግዚአብሔርን በመምሰል አስተምሮ የተቃኙ አገልጋዮች መኖራቸው ግድ ነው። እንዲህ ሲባል ሁልጊዜ መሰበክ ያለበት «እግዚአብሔርን መምሰል» በሚል ርዕስ ነው ማለታችን አይደለም።

ሰዎች ከጨለማ አሰራት ተፈትተው ከልዩ ልዩ ተፅዕኖ ተላቀው አዲስ ፍጥረት ከሆኑ በኋላ በክርስቶስ እንዲያድጉና ከዘላለም ዘመናት በፊት እግዚአብሔር ወደ ወሰነላቸው ክብር እንዲደርሱ የምናስተምራቸው ትምህርት ሁሉ እግዚአብሔርን የመምሰል ትምህርት ነው። እግዚአብሔርን መምሰል ባመንን ጊዜ ያገኘነውን ሕይወት በምድር ኑሮአችን መግለጥ እንደመሆኑ መጠን ቅድስና ቢሆን ፍቅር፣ መስጠት ቢሆን ይቅርታ ሌሎችም ያልጠቀስናቸው ርዕሶች በሙሉ እግዚአብሔርን በመምሰል ትምህርት ውስጥ ይካተታሉ። ስለዚህ እግዚአብሔርን መምሰል የትምህርቶች መፍለቂያ የሆነ አንድ ወጥ አስተሳሰብ እንጂ እንደ አንድ ርዕስ ብቻ ተደርጎ ሊወሰድ አይገባውም።

አንድ ሰው ሲያስተምርም ሆነ ሲማር ሊጠይቅም ሆነ ሊጠየቅ የሚገባው ያስተማርኩት «እግዚአብሔርን በመምሰል» ርዕስ ላይ ነው ወይ? ላይሆን እግዚአብሔርን ከመምሰል አስተምህሮ ጋር ይጣጣማል ወይ? የሚለው መሆን ይኖርበታል።

የሐዋርያው ተልዕኮ

«የእግዚአብሔር ባሪያና የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ የሆነ ጳውሎስ በእግዚአብሔር ለተመረጡት እምነት እንዲሆንላቸው በዘላለም ሕይወት ተስፋ እንደ አምልኮት ያለውን እውነት እንዲያውቁ የተላከ ...» ቲቶ 1:1

በዚህ ክፍል ውስጥ ጳውሎስ ለምን ሐዋርያ እንደሆነ የተልዕኮውን ዋና ዓላማ በሁለት በመክፈል ግልጽ አድርጎ አስቀምጦልናል።

1. በእግዚአብሔር ለተመረጡት እምነት እንዲሆንላቸው
2. በዘላለም ሕይወት ተስፋ እንደ አምልኮት ያለውን እውነት እንዲያውቁ

ይህንኑ ክፍል አዲሱ መደበኛ ትርጉም እንዲህ ይለዋል፡-

«የእግዚአብሔርን ምርጦች አምነትና ወደ እውነተኛ መንፈሳዊነት የሚመራውን የእውነት ዕውቀት ለማሳደግ የእግዚአብሔር ባሪያን የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ የሆነው ጳውሎስ ...፡፡»

የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ያሳተመው የ1980 እትም የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ፡-

«የእግዚአብሔር አገልጋይና የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ ከሆነው የእግዚአብሔርን ምርጦች በእምነት ለመርዳትና የሃይማኖታችንም እውነት እንዲያውቁ ለማድረግ ከተሾመው ከጳውሎስ፡፡»

የመጀመሪያው «አምልኮ»፣ ሁለተኛው «እውነተኛ መንፈሳዊነት»፣ ሦስተኛው ደግሞ «ኃይማኖት» ብለው የተረጎሙበት ቃል አዲስ ኪዳን በተጻፈበት በግሪክ ቋንቋ «ዮሴቢያ» የሚለውን አንድ ቃል ነው። ይህ ቃል ደግሞ በሌሎች ሥፍራዎች በሙሉ «እግዚአብሔርን መምሰል» ተብሎ ተተርጉሟል። ይህንን ቃል የእንግሊዘኛ መፅሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች በሙሉ እግዚአብሄርን መምሰል (Godliness) ብለው ተርጉመውታል።

ከዚህም በመነሳት ሐዋርያው ጳውሎስ ተልዕኮዬ የሚለው በእግዚአብሔር የተመረጡት በእርሱ ስብከት ወደ እምነት እንዲመጡና ያመኑት ደግሞ እግዚአብሔርን ወደ መምሰል የሚያደርሳቸውን እውነት እንዲያውቁ ለማስተማር መላኩን ነው። ይህም እርሱ ራሱ በ1ጢሞ. 2:7 እና በ2ጢሞ. 1:11 ላይ እንደገለፀው ከጌታ የተሰጠውን ሐዋርያዊ የወንጌል ሰባኪነትን እና የአስተማሪነት ፀጋ ያመለክታል።

የትምህርቶች መለኪያ ዘንግ

መቼም መለኪያ በሌለበት ሁሉ ልክ ነው። ሁሉ ልክ በሆነበት ደግሞ ስህተት በነፃነት ይኖራል።

ይህ ደግሞ ለእግዚአብሔር አይመቸውም። እግዚአብሔር የእውነት አምላክ ነውና ቱንቢ ሲወገድ፣ መሠረት ሲንጋደድ፣ ውሃ ልክ ሲዛባ ዝም አይልም። የግንበኞችን እብደት፣ የአናጢዎችን ቸልታ አይታገስም። በውጤቱ የሚጎዳው ሕዝብ እንደሆነ ያውቃልና ይነሣል ይፈርዳል።

ከክርስቶስ ልደት 700 ዓመታት በፊት በኢየሩሣሌም የነበሩ መሪዎች የእግዚአብሔርን ሕዝብ ያስተዳድሩ የነበረው በተሳሳተ መንገድ ነበር። ይህ አካሄድ በፍፃሜው ፍርድንና መፍረስን እንደሚያመጣ እግዚአብሔር በነቢዩ አማካይነት ደጋግሞ ተናግሯቸው ነበር። መሪዎቹ ግን በማፌዝ፦

> *«ሞት ጋር ቃል ኪዳን አድርገናል ሲኦልም ጋር ተስማምተናል፣ ሐሰትን መሸሸጊያችን አድርገናልና በሐሰትም ተሰውረናልና የሚተረፈረፍ መቅሰፍት ባለፈ ጊዜ አይደርስብንም . . .።»* ኢሳ. 28:14-15

ይሉ ነበር። በዚህን ጊዜ እግዚአብሔር፦

> *«እነሆ በጽዮን ድንጋይን ለመሠረት አስቀምጣለሁ የተፈተነውን የከበረውን መሠረቱ የፀናውን የማዕዘን ድንጋይ የሚያምን አያፍርም . . .።»* ኢሳ. 28:16

በማለት በዘመኑ ለነበረው መዛባት መልስ ሰጠ። ይህ መልስ በጊዜው ለነበሩት ለፌዘኞቹ የጽዮን መሪዎች የተሰጠ ማስጠንቀቂያ ቢሆንም በዋነኝነት ለሰው ልጆች የዘመናት ጥያቄ ዘላለማዊ መልስ ይሆን ዘንድ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የተነገረ ትንቢት ነበር።

ለዚህ ነው ጴጥሮስ በመልእክቱ ሕይወታችንን ልንገነባ የሚገባን ግንበኞች ንቀው ቢጥሉትም እግዚአብሔር ግን መርጦና አክብሮ ባስቀመጠልን ሕያው ድንጋይ ልክ መሆን እንዳለበት የሚነግረን። ይህም ሕይወታችንን ልንገነባበት የሚገባ «ልክ» የጌታ ቃል እና ትምህርት መሆኑን ሲያስረዳ እንዲህ ይላል፦

> *«እንግዲህ ክብሩ ለእናንተ ለምታምኑት ነው ለማያምኑ ግን አናጢዎች የጣሉት ድንጋይ እርሱ የማዕዘን ራስ የእንቅፋትም ድንጋይ የማሰናከያም ዓለት ሆነ የሚያምኑ ስለሆኑ በቃሉ ይሰናከሉበታልና . . .»* 1ጴጥ. 2:7-8

እኛ የምናምን በሙሉ ልብ የተቀበልነው የማያምኑትም የተቃወሙትና የተሰናከሉበት ያው «ቃሉ» ነው። ስለዚህ የማዕዘን ራስ ሆኖ የተቀመጠልን የጌታ ቃልና ትህምርት መሆኑን መረዳት አያዳግትም። ጌታንና ቃሉን መነጣጠል አይቻልምና።

ይህ የክርስቶስ ትምህርት ሁሉን ልንመዝንበት የሚገባ እግዚአብሔርን የመምሰል ትምህርት ነው።

> *«ማንም ልዩ ትምህርት የሚያስተምር ከጌታችንም ከኢየሱስ ክርስቶስ በሆነው ጤናማ ቃልና እግዚአብሔርን ለመምሰል በሚስማማ ትምህርት የማይጠጋ ቢሆን በትዕቢት ተነፍቷል፣ አንዳችም አያውቅም ነገር ግን ምርመራን በቃልም መዋጋትን እንደበሽተኛ ይናፍቃል... ለእምሮአቸው በጠፋባቸው እውነትንም በተቃሙ እግዚአብሔርን መምሰል ማትረፊያ የሚሆን በመሰላቸው ሰዎች ይገኛሉ። ነሮዬ ይበቃኛል ለሚለው ግን እግዚአብሔርን መምሰል እጅግ ማትረፊያ ነው።...እኔ ግን የእግዚአብሔር ሰው ሆይ ከዚህ ሽሽ ጽድቅንና እግዚአብሔርን መምሰል እምነትንም፣ ፍቅርንም፣ መጽናናትንም፣ የዋህነትንም ተከታተል።»* 1ጢሞ6:3-5

ቀደም ሲል እንዳልኩት ልዩ ትምህርቶችን ለመያዝ አንድ እንደመለከያ የምንጠቀምበት ትክክለኛ ትምህርት ሊኖረን የግድ ነው። ሐሰት ብዙ ነው እውነት ግን አንድ ነውና ብዙ ሊሆን አይችልም። በተለያየ ዘመን የሐሰት ትምህርቶች መልካቸውን እየቀያየሩ ይመጣሉና የመጡትን የስህተት ትምህርቶች ሁሉ ለማወቅ በመጣር ከስህተት መትረፍ አይቻልም። ይልቅ የማይለዋወጠውን አንዱን እውነት በማወቅ ስህተት ከእውነት አንዳልሆነ በቀላሉ መረዳት ይቻላል። ይህም መለኪያ ዘንግ እግዚአብሔርን የመምሰል ትምህርት ነው። ለዚህ ነው ሐዋርያው ከውስጥና ከውጭ በተለያዩ የስህተት ትምህርቶች በተወረረችው በኤፌሶን ለሚገኘው ለወጣቱ ጢሞቴዎስ ልዩ ትምህርቶችን አበጥሮ እንዲለይበት እግዚአብሔርን የመምሰልን ትምህርት ብቸኛ መሣሪያ አድርጎ የሰጠው። ማንኛውም

ትምህርት የፈለገውን ያህል መንፈሳዊ ቢመስል፣ በስመጥር ሰዎች ቢሰጥ፣ በድንቅና በተአምር ቢታጀብና ከቅዱሳት መፃሕፍት ተጠቅሶ ቢነገርም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጤናማ ቃል ጋር ካልተስማማና የሰሚዎቹን እግዚአብሔርን የመምሰል (የእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት) ልምምድ ካላነሰበት ሰለ ስህተትነቱ ብዙ መመራመር አያስፈልግም። እንዲህ ዓይነቱን ትምህርት ከቻሉ ማራቅ፣ ካልተቻለም መራቅ አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው።

ዛሬ የክርስቶስን ቤተክርስቲያን እንደጭንቁር (ጋንግሪን የተባለ አካልን በልቶ የሚጨርስ ቁስል) እየበሉ ያሉት ትምህርቶች ስም የወጣላቸው፣ ታውቀውና ተለይተው በውጭ ያሉ የስህተት ትምህርቶች ሳይሆኑ በተሸለሙ መድረክቻችን በነፃነት የሚንሸራሸሩ በአልልታና በጭብጨባ የምናጅባቸው ነገር ግን እግዚአብሔርን መምሰልን የሚፃረሩ ትምህርቶች ናቸው።

መለኪያ በሌለበት ሁሉ ልክ ነውና። ደግሞም ሐሰት ሲደጋገም እውነት መምሰሉ አይቀርምና በመድረኮቻችን ላይ ከመክረማችው የተነሳ ማንም ሊቃወማቸው እለከማይደፍር ድረስ የተንሰራፋ እግዚአብሔርን በመምሰል ሚዘን ሲመዘኑ ግን ቀለው የሚገኙ በርከታ ትምሕርቶች ሞልተዋል።

ትምህርትን የምንመረምረው ከመድረክ ሲተላለፍ ብቻ አይደለም። ምንም እንኳ ይህ አንዱ መንገድ ቢሆንም ዋነኛው መመዘኛ የአስተማሪዎቹ ኑሮና ውስጣዊ ሕይወት ነው። የበግ ለምድ የለበሰን ተኩላ ቀለሙን አይቶ ወይም ፀጉሩን ዳብሶ መለየት አይቻልምና ውስጡን መመርመር ግድ ይላል። ውስጥ የሚታየው ደግሞ በፍሬ ነው። የዛፍን ምንነት የምናውቀው ግንዱን ገምጠን ወይም ቅጠሉን አኝከን ሳይሆን

ፍሬውን በመቅመስ እንደሆነ ሁሉ የአስተማሪዎችን ትምህርት ለመለየት ዝንባሌያቸውን፣ ትኩረታቸውን፣ አሴታቸውን፣ አካሄዳቸውን እና በልባቸው የሚቃጠለውን ማወቅ አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው።

ሕይወት የሚገኝበት ትምህርት

ትምህርት ሁሉ ሕይወት አይገኝበትም። ሕይወት የሚገኝበት ግን አንድ ትምህርት አለ። እርሱም የክርስቶስ ትምህርት ነው። ማንኛውም ትምህርት በክርስትና ስም እየተሰጠ ሕይወት የሚገኝበት ካልሆነ ግን ከሌሎች የሳይንስና የፍልስፍና ትምህርቶች ተለይቶ ሊታይ አይችልም። የቀለም ትምህርት በአግባቡ ከተሰራበት ቢያንስ ለምድር ሕይወት አስተዋፅኦ አለው ከክርስቶስ የተለየ የኃይማኖት ትምህርት ግን ሰሚዎችን ከማፍረስ በስተቀር አንዳች አርባና የለውም።

የክርስትና ጉዞ የሚጀምረው በክርስቶስ ኢየሱስ አምኖ ሕይወት ከማግኘት ነው። ይህም ሕይወት የሚበዛ ሕይወት ነው። የሚበዛውም በትምህርት ነው። ማንኛውም ነገር ሲሞላ ተርፎ እንደሚፈስ ሁሉ ሕይወትም ሲበዛ በኑሮ ይገለጣል። ይህንንም የሕይወት መገለጥ እግዚአብሔርን መምሰል (እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት) ብለን እንጠራዋለን።

ከዚህ በመነሳት እግዚአብሔርን በመምሰል ሂደት ውስጥ ትምህርት ምን ያህል ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው እንመለከታለን። ይህ ደግሞ አስተማሪዎችን ብቻ ሳይሆኑ ተማሪዎችንም የሚመለከት ጉዳይ ነው።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለቤተክርስቲያን የሰጠው ታላቁ ተልእኮ ወንጌልን በመስበክና የአማኞችን ቁጥር በማብዛት ብቻ የተወሰነ አይደለም። ያመኑትን ደቀመዛሙርት የማድረግ ተልእኮም አለበት። «ደቀመዝሙር» የሚለው ቃል በግሪኩ «ማቴቴስ» ማለት ሲሆን መምህሩን መምሰል ግቡ አድርጎ የሚጓዝ ተማሪን ያመለክታል። ይህ ቃል ክርስቶስን በመምሰል ልምምድ ላይ ስለሚያተኩር በደቀ መዝሙር ትምህርትና እግዚአብሔርን በመምሰል ትምህርት መካከል ከፍተኛ ዝምድና መኖሩን ማየት እንችላለን።

ደቀመዛሙርትን ለማፍራት የተሰጠው መሣሪያ ደግሞ ትምህርት ነው። ያም ትምህርት በሰዎች ብልሃት የተፈጠረ ፍልስፍና ሳይሆን የክርስቶስ ትምህርት ነው።

> «. . . ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ አደርጎ ተማራችኋቸው ደቀመዛሙርት አድርጓቸው።» ማቴ.28:19

ብሏልና።

እዚህጋ ምንም እንኳ የጽሑፉ ዋና ዓላማ ባይሆንም በስብከትና በትምህርት መካከል ያለውን ልዩነት በጥቂቱ ለማንሳት እገደዳለሁ።

ስለ ሁለቱ ልዩነት ሲነሳ ተመሳሳይ ጥያቄ የጠየቅሁት አንድ ወጣት ቀልድ በተቀላቀለበት ስሜት «ጮክ ብለውና መድረክ ላይ እየተንጎርደዱ ካቀረቡት ስብከት፣ አንድ ቦታ ቆመው ዝግ ባለ ድምጽ ካቀረቡት ደግሞ ትምህርት ይሆናል» በማለት የመለሰልኝ ፈጽሞ አይረሳኝም። ይህንን አባባል እኛ እንደ ቀልድ ብንወስደው እንኳ ከምር የሚወስዱት ትምህርትንና ስብከትን በዚህ መስፈርት የሚለዩ እንደማይጠፉ መገመት ጥሩ ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ ስብከት ሳላመኑ ሰዎች የሚታወጅ

የምሥራችና ያመኑትንም ለአንድ ተግባር ለማነሳሳት የሚቀርብ መልእክት ሲሆን ትምህርት ግን አምነው ለዳኑት በተከታታይነት የሚሰጥ የሕይወት ግንባታ ነው።

ለመሆኑ ዛሬ በየመድረክቻችን የሚተላለፈው ምንድነው? ብለን ብንጠይቅ አብዛኞቹ በስብከት ስም የሚሰጡ ትምህርቶች ናቸው ለማለት እንደፍራለን። ከዚህ በመነሳት ቀጥሎ ባሉት ክፍሎች «ትምህርት» የምንለው ለአማኞች አስከተሰጠ ድረስ ስብከትንም የሚጠቀልል ይሆናል።

ትምህርቶቻችን ምን ያህል ሕይወት የሚገኝባቸው ናቸው? አስተማሪዎቻችንን እየቀረፀ ያለው ሥርዓት ምንድነው? የዘመናት የቤተክርስቲያን ተግዳሮት በትምህርቶች ይዘት ዙሪያ የሚያጠነጥን በመሆኑ እነዚህን ጥያቄዎች ማንሳቱ አግባብነት አለው።

በየዘመናቱ አስተማሪዎችን የሚጠራና የሚልክ እግዚአብሔር እንደሆነ ብናውቅም አስተማሪዎቹ በዙሪያቸው ባለው ሁኔታ ተፅዕኖ አያድርባቸውም ብሎ ማሰብ ግን አጉል የዋህነት ነው። የዘመናችንን የቤተክርስቲያን ገጽታ በትኩረት ስንመለከት ከነገሮች ጀርባ ያለውን እውነታ ጠልቀን ለመመርመር እንገደዳለን። «ንግድ» የሚለው ቃል በግርድፉ ስንተረጉመው ፍላጎት ባለበት ስፍራ ለተጠቃሚዎች አቅርቦትን ማመቻቸት ይሆናል። ከዚህ በመነሳት ገበያን የሚመራው የነጋዴው ፍላጎት ሳይሆን የሸማቹ ምርጫ እንደሆነ እና የነጋዴው ድርሻ የሸማቹን ፍላጎት በማጥናት አቅርቦቱን አቀላጥፎ ትርፍ ማግኘት እንደሆነ እናውቃለን።

ልክ እንዲሁ የአማኙ ሕብረተሰብ ፍላጎት የአስተማሪዎቻችን የትምህርት ይዘት ላይ ተጽእኖ ማሳደሩ አይቀሬ ነው። ለዚህም በአሜሪካ ሃገር በታላላቅ መድረኮችም ሆነ ከዚያው በሳተላይት ለዓለም የሚሠራጨትን ስብከቶች እንደ አብነት ብንመለከት በዋነኝነት ከዕዳ ነፃ በመውጣት ላይ ያተኮሩ ናቸው። ለምንየ ቢባል የአሜሪከን የኢኮኖሚ ሥርዓት የተመሠረተው በክሬዲት (ብድር) ላይ ነው። እያንዳንዱ አሜሪካዊ በፈለገበት ጊዜ በአቅራቢያው ከሚያገኘው አውቶማቲክ (ሰው አልባ) የገንዘብ መክፈያ ማሽን (ATM) የሚስጥር ቁጥር አስገብቶ ገንዘብ ማውጣት የሚችልበትና ግዥ በሚፈፅምበት ቦታ ሁሉ በእጁ ብር ሳይቆጥር ክፍያ መፈጸም የሚችልበት ካርድ ይሰጠዋል። ይህን ካርድ በመጠቀም ከኪሱ ሳያወጣ የፈለገውን ነገር ወዲያውኑ እንዲገዛ ይገፋፋል። በዚህ ዓይነት እዳ ውስጥ ገባ ማለት ነው። እንዲህ የሚደረገው (እኔ እንደሚመስለኝ) ግለሰቡ ያን ዕዳ ለመክፈል ሥራ ሳይመርጥ ተግቶና ሰዓት ጨምሮ ስለሚሠራ ሳያውቀው ለአገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት አስተዋጽኦ ያደርጋል ተብሎ ስለሚታመን ነው።

ከዚህ የተነሳ የአሜሪካ ሕዝብ በተለይ ዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ያለው ክፍል በመበደር እና ዕዳ በመክፈል ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ ውስጥ ለመዘፈቅ ተገዷል። እንግዲህ «ከዕዳ ነፃ መሆን» የሚል ርዕስ ሲነሣ የዚህን ሕብረተሰብ ቀልብ እንዴት እንደሚስብ መገመት አያስቸግርም።

ይህ ከዕዳ ነፃ ስለመውጣት የሚሰጠው ትምህርት የገንዘብ አጠቃቀም ላይ ያተኮረ የሂሳብ ማኔጅመንት ወይም የኢኮኖሚክስ ትምህርት ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ከዕዳ ነፃ ለመውጣት እንደ መፍትሄ የሚቀርበውም ትምህርቱን

ለሚያቀርቡት ሰባኪዎች ገንዘብ መስጠት ነው። የዚህን እውነታነት ለማረጋገጥ ሲባል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የማይሉትን እንዲሉ አለ አግባብ ይለጠጣሉ። የሰሚዎቹ ችግር በአሜሪካን የሸቀጥ አቅርቦትና የማስታወቂያ ብዛት ተማርኮ ከአቅም በላይ ገንዘብ ማውጣት ነው። ከገቡበት የገንዘብ ዕዳ ለመውጣት መፍትሔ ሆኖ የቀረበላቸውም ለም መሬት በሆኑትና ቢዘራባቸው ብዙ እጥፍ በሚያሳጭዱት አስተማሪዎቻቸው ላይ ገንዘብ መዝራት ነው።

ይህ ደግሞ የግብጽን አስማተኞች ያስታውሰናል። በእግዚአብሔር ትዕዛዝ በሙሴ አማካኝነት መቅሰፍቶች ሲወርዱ የችግሩ ገፈት ቀማሽ የነበረው ሕዝብ መፍትሔ ፍለጋ ወደ አማልክቶቹ ካህናት በመሄድ አቤት ይል ነበር። ጠንቋዮቹ ግን አንድም ጊዜ ውሃ ወደ ደም ሲቀየር ደሙን ወደ ውሃ አልመለሱም፣ ውሃ ወደ ጓጉንቸርነት ሲቀየር ጓጉንቸሩን ወደ ውሃነት አልመለሱም፣ ትቢያ (አፈር) ወደ ቅማልነት ሲለወጥ ቅማሉን ወደ ትቢያነት (አፈርነት) አልመለሱም፣ ይልቅ እነርሱም በአስማታቸው ውሃን ወደ ደም በመቀየር፣ ጓጉንቸሮችን በማውጣት ለሕዝቡ በችግሩ ላይ ችግር ጨመሩለት እንጂ መፍትሄ አላመጡለትም።

ዛሬም በአሜሪካ ገኖ የምናየውና እንደ ጥሩ ውሃ በዓለም እየተሠራጨ ያለው ትምህርት ዕዳ ላናወዘው ሕዝብ ዕዳ ገብተህ ስጥና ከዕዳ ነፃ ትወጣለህ የሚል የብልጽግና ትምህርት ተብዬ ነው።

መስጠት መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ ስለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም። እግዚአብሔር ቸር ነው፣ ለጋስ ነው፣ መስጠትም የሕይወቱ ባሕሪ፣ የባሕሪውም ሕግ ነው።

እግዚአብሔርን ከምንመስልባቸው ነገሮች አንዱም መስጠት መሆኑ እሙን ነው። ነገር ግን የእግዚአብሔር ዓይነቱ መስጠት በፍቅር፣ በእምነት፣ በደስታ፣ በርህራሄ፣ በፀጋ፣ በእውቀት፣ በበጎ ፈቃድ የሆነ እንጂ ገና ለገና ትርፍ አገኛለሁ ብሎ በማሰብ፣ ከአውዳቸው ውጪ ተለጥጠው በሚቀርቡ ጥቅሶች በመታለል እና ሰጥተን ሚሊየነር ሆንን በሚሉ ሰዎች የማስታወቂያ ምስክርነት በመደለል እጅ ተጠምዝዞ ሲሰጥ አይደለም።

ለአገልግሎት ገንዘብ እንደሚያስፈልግም የታወቀ ነው። ሆኖም የላከን እርሱ እንደሚያዘጋጅ በመታመንና ሊገኝም ኑሮዬ ይበቃኛል በማለት በሥርዓት ሊወጣ እንጂ ለቅንጦትና ለመንደላቀቂያ ሊውል አይደለም።

ወደ አገራችንም ስንመጣ የኑሮ ደረጃውና ሥርዓቱ ስለሚለይ ተመሣሣይ ነገር ባይሰበክም ሥራ-አጥነትና ድህነት ያደቀቀውን የሕዝባችንን የኑሮ ሁኔታ በመንተራስ ክስመድ ትነሳለህ፣ ባሰጠጋ ትሆናለህ፣ ከአገር ትወጣለህ የሚሉ ትምህርቶች በስፋት ይናኛሉ። የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት በኢየሱስ ክርስቶስ አምነን በስሙ ሕይወት ማግኘት፣ ያገኘነውንም ሕይወት በኑሮ በመግለጥ እግዚአብሔርን ለመምሰል ራስን ማስለመድ መሆኑ ቀርቶ የሰዎችን የኑሮ ደረጃ ለመቀየር የተፃፈ እስኪመስል ድረስ ስብከቱም መዝሙሩም ይህን ሃሳብ ሲያቀነቅን መስማት የተለመደ ሆኖአል።

ይህን ሃሳብ ያነሳነው ስለመስጠት ለማስተማር ወይም ስለ አሜሪካ እና ስለ አገራችን ክርስትና በጥልቀት ለመግፍ ሳይሆን የምናገለግለው ጎብረተሰብ የኑሮ ሁኔታ እንዴት

ትምህርቶቻችንን ሊቃኝ እና ሊቀርጽ እንደሚችል ለማሳየት ብቻ ነው።

እንደው እግረ መንገዴን በአሜሪካ ሳልቶ ስለሚታየው የመስጠት አስተምህሮና በአገራችን ስላለው ያለ ሥራ በተስፋ ብቻ ከድህነት የመውጣት አባዜ አነሳሁ እንጂ በአሜሪካም ሆነ በእኛው አገር ከዚህ ስብከት ነፃ ወጥተው የጽድቅ ኑሮ የሚኖሩና ጽድቅንም የሚሰብኩ አገልጋዮች መኖራቸውን ዘንግቼው አይደለም። እግዚአብሔር ከግብጽ ሳዳነው ሕዝብ የሚሰጠውን መመሪያ ፍለጋ ሙሴ አርባ ቀን በተራራ ላይ በፀሎት ሲተጋ አሮን የሕዝቡን የልብ ትርታ በማዳመጥ በብዙኃኑ ጥያቄና አቅርቦት የወርቅ ጥጃ በመስራት ይተጋ እንደነበር ዛሬም የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ሃሳብ ለማግኘት በፊቱ የሚቃትቱ እንዳሉ ሁሉ የህዝብን የልብ ትርታ እያዳመጡ ትምህርታቸውን የሚቀርፁም ሞልተዋል። መንገዱ በእግዚአብሔር የተጠላ ትምህርቱም መርዝ የተሞላ መሆኑን ጠንቅቆ እያወቀ በስጦታ ብዛት ዐይኑ ተሸብቦ በአብደት የተነዳው በለዓም ለምንለው ነገር ተጨማሪ ማስረጃ ይሆነናል።

የሕዝብን ፍላጎት በሚሟላት በአቋራጭ የመክበር ፈተና መቼም ቢሆን በቀላሉ ሊታይ አይገባም። ስበቱ ኃያል ነውና። ከስበቱ ነፃ መሆንም በፉከራ ሳይሆን በተግባር ብቻ የሚገለጽ ነው። ሐዋርያው፡ -

> *«ለኛስ ትርፍ ለማግኘት ብለው የእግዚአብሔርን ቃል ቀላቅለው እንደሚሸቃቅጡት እንደ ብዙዎቹ አይደለንም ...።» 2ቆሮ. 2:17*

እንዳሰው ብዙዎች የእግዚአብሔርን ቃል ለትርፍ ለመሸቀጥ ታልፈው ይሰጣሉ። አገልግሎታቸውም የዘመናችን የፖለቲካ መሪዎች እንደሚሉት ገበያ መር፣ ጥቅም ተኮር ይሆናል።

በእግዚአብሔር ፊት ባላቸው የልብ ሁኔታ ሳይሆን በሰው ፊት ባላቸው የውጭ ገጽታ ይመካሉ። ይሄኔ ነው እግዚአብሔርን መምሰል የሕይወት ኃይልነቱ ተክዶ መልኩ ብቻ የሚቀረው። እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔርን መምሰል የትርፍ ምንጭ አድርገው ስለሚያስቡት በውስጥ የሌላቸውን በውጭ ለማስመሰል የማይቆፍሩት ጉድጓድ የማይፈነቅሉት ድንጋይ አይኖርም። እንዲህ ዓይነት መምህራን በእግዚአብሔር ፊት የተጣሉ ቢሆኑም እንኳ ፈላጊዎቻቸው ብዙ ናቸውና ብቻቸውን አይቀሩም። ሁልጊዜ እየተማሩ እውነትን ወደ ማወቅ የማይደርሱ፣ መርሃቸው ከነፈሰው ሁሉ ጋር አብሮ መንፈስ የሆኑ ሰዎች በራቸው ለእንዲህ ዓይነት መምህራን ዘወትር ክፍት ነው።

ይልቅ ሕይወት የሚገኝበት ትምህርት በውስጣቸው የተሞሉ አገልጋዮች ክብርን ስለማይፈልጉ፣ ዝናን አነፍንፈው ስለማይከተሉ፣ እውነትን ስለማይሸቅጡና፣ ለጥቅም ስለማያመቻምቹ ብዙ ፈላጊ ላይኖራቸው ይችላል። ይህ ደግሞ ዛሬ የመጣ አባዜ ሳይሆን ጥንትም የነበረ ሕፀጽ ስለመሆኑ ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ በማለት ይገልፀዋል።

> *«ቃሉን ስበክ ፤ በጊዜውም አለጊዜውም ጽና፤ ፈጽመህ አየታገስህና እያስተማርህ ዝለፍና ገሥጽ፣ ምክርም። ሕይወት የሚገኝበትን ትምህርት የማይታገሱበት ዘመን ይመጣልና ነገር ግን ጆሮቻቸውን የሚያሳክክ ሰለ ሆነ እንደ ገዛ ምኞታቸው ሰራሳቸው አስተማሪዎችን ያከማቻሉ፤ እውነትንም ከመስማት ጆሮቻቸውን ይመልሳሉ፤ ወደ ተረትም ፈቀቅ ይላሉ።» 2ጢሞ. 4:2-4*

እነዚህ ሰዎች ሕይወት የሚገኝበትን ትምህርት የማይታገሱት፣ እውነትን ከመስማት ጆሮአቸውን የሚመልሱት እና ለገዛ ሰራሳቸው አስተማሪዎችን የማያከማቹት ለምን ይሆን? አዲሱ መደበኛ ትርጉም እንዲህ ያስቀምጠዋል።

> *« . . . ይልቅ ለገዛ ምኞቶቻቸው የሚስማማውን፣ የሚያሳክክ ጆሮአቸው ሊሰማ የሚፈልገውን እንዲነግሯቸው በዙሪያቸው ብዙ አስተማሪዎችን ይሰበስባሉ።» 2ጢሞ. 4:3*

ጉንፋን ሊይዘን ሲከጅል ጆሮአችንን ማሳከክ የተለመደ ክስተት ነው። ችግሩ ግን ማሳከኩ ሳይሆን ደርሰን በማከክ ስሜታችንን ማርካት አለመቻላችን ነው። ለዚህ ነው አንዳንዴ ከውጭ አመልካች ጣታችንን ጆሮአችን ውስጥ ከተን በኃይል በመነቅነቅ፣ ከውስጥ ደግሞ ጉሮሮአችንን አርስ በርሱ በማፋጨት ለማከክ የምንጥረው ያም ሆኖ አያረካም። እነዚህም ሰሚያች ጆሮ እንዲያሳክክ የሥጋ ምኞታቸው ያሳከካቸውን ደርሰው ማከክ ስላልቻሉ በትምህርቶቻቸው የሚያኩሳቸውን አስተማሪዎች በመብራት ይፈልጋሉ። ባገኙም ጊዜ በታላቅ ሆታ ይከተላሉ።

ይህንን ሁሉ የምንሰው ሌሎችን ለማብጠልጠል ሳይሆን እኛ ራሳችን ከዚህ መሰሉ ወጥመድ እናመልጥ ዘንድ ሕይወት የሚገኝበትን ትምህርት ሕይወት አልባ ከሆነው የምንሰይበትን መለኪያ ዘንግ አንድንጨብጥ በማሰብ ነው።

ትምህርት ሊሰካ የሚገባው ሰውን በመለወጥ ኃይሉ ነው። መለወጥ ስንልም ሰበኳ መለወጥ የሚሰው በጽኑ ሊሰመርበት ይገባል። ትምህርት ለክፉ የሚሰውጣቸውም አሉና። እንዲያም ሆኖ የሚታየው የትምህርት የመለወጥ ኃይል ነው። አንደ አውሮፖውያን አቆጣጠር መስከረም ዘጠኝ ሁለት ሺህ አንድ በኒወርክ በሚገኘው የዓለም ንግድ ማዕከል መንታ ሕንፃዎች እና በቨርጂኒያው የአሜሪካን የመከላከያ ቢሮ (ፔንታጎን) ሕንፃ ላይ የአጥፍቶ መጥፋት ርምጃ የወሰዱትን ሰዎች ስንመለከት በሁለንተናቸው እንደኛው ሰው ናቸው። እንዲያውም አንዳንዶቹ እንኳን ሰው ዝንብ ሲገደል የሚዘገንናቸው ሩህሩህ እንደነበሩ አብሮአደግ ጓደኞቻቸው በመገረም መስክረዋል። ታዲያ ምን አገኛቸውና የሆኑትን ሆኑ? እንል ይሆናል። መልሱ «ትምህርት» ነው። እነዚያ የዕለቱ

የጥፋት ተዋንያን ወደዚያ እኩይ ተግባር ከመሰማራታቸው ቀደም ሲል በአፍጋኒስታን እና በፓኪስታን ትምህርት በመውሰድ ረዥም ጊዜ እንዳይጠፉ የአሜሪካን የመረጃ ቢሮ ይፋ አድርጓል። ትምህርታቸውም በአብዛኛው የቴክኒክ እና የታክቲክ ሳይሆን ሃይማኖታዊ ትምህርት ነበር። ትምህርቱ ምን ያህል እንደለወጣቸው የምናየው በአፍጋኒስታን ዋሻዎች ውስጥ የተማሩትን በአሜሪካ ታላላቅ ከተሞች ውስጥ በተግባር ለመፈፀም ባለማመንታታቸው ነው። ምንም እንኳን ትምህርታቸው የጥፋት፣ የመራቸውም ወደ ዘላለም ጥፋት ቢሆንም የትምህርትን የመለወጥ ኃይል ምን ያህል እንደሆነ አስገንዝቦን አልፏል።

እንኳን የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት ሰማያዊ ትምህርት ምድራዊው የቀለም ትምህርት እንኳ የሰዎችን ማንነት የመለወጥ አቅሙ ከፍተኛ አይደል? ለምሳሌ ሚስማር እንጨት ላይ መትቶ ማስገባት የማይቻል ወይም የዶሮ ቤት ለመስራት የሚቸገር አንድ 12ኛ ክፍልን የጨረሰ ወጣት ዩኒቨርሲቲ ገብቶ ለ5 ዓመታት ሲቪል ኢንጂነሪንግ ካጠና በኋላ የአገር ፎቅ የሚሠራ መሃንዲስ ሆኖ ሲወጣና ኢንጂነር እከሌ ተብሎ ሲጠራ መስማት ምን ያህል ማንነቱና ደረጃው በትምህርት እንደተቀየረ ያሳየናል። ሐኪሙም፣ ዳኛውም፣ ... እንዲሁ። ታዲያ የዓለም ትምህርት ለዎችን ይህን ያህል ከለወጠ መንፈሳዊው ትምህርት የማይለውጠው ለምንድነው? የትምህርቱ ጊዜ አንሶ ነው እንዳንል አንዳንዶቻችን የእግዚአብሔርን ቃል በመማር ያሳለፍናቸው ጊዜያት ከዚያ ቢበልጡ እንጂ ጨርሶ አያንሱም። በጌታ ቤት ሃያ ዓመታት የቆየን አማኝ እንደ ምሳሌ እንውሰድ። ቢያንስ በሣምንት ሁለት ኘሮግራም ይካፈላል እንበል። ዛሬ ድረስ ቢያንስ ለሦስት

ሺህ አንድ መቶ ሃያ አንድ ሰዓታት የእግዚአብሔርን ቃል ተምሯል። ለአንድ ተማሪ በዩኒቨርሲቲ ውስጥ አንጂነርም ሆነ ሐኪም ወይም የሕግ ተመራቂ ለመሆን የሚፈጀው ከፍተኛ ሰዓት ከ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ሰዓት አይበልጥም። ይህ ቀመር ያለመለወጣችን ከስብሰባ ማነስ ወይም ከጊዜ እጥረት እንዳልሆነ ያረጋግጥልናል።

ጌታ ኢየሱስ በሦስት ዓመት ተኩል የማስተማር ሂደት በነዚያ አሣ አጥማጆችና ቀራጮች ሕይወት ውስጥ ያመጣውን ሊነገር የማይችል ለውጥ ስናስብ ወይም ጳውሎስ በዚያ የመከራና የስደት ወራት በኤፌሶኑ ጢራኖስ ት/ቤት ለሁለት ዓመት ያሰለጠናቸውንና መላዋን ኤዥያን በወንጌል ያጥለቀለቁትን የወንጌል አርበኞች ስናይ እውነተኛ ትምህርት ምን ያህል እንደሚለውጥ መመልከት እንችላለን። ይህ ደግሞ ዛሬ ችግሩ ያለው በእኛው የትምህርት ይዘት እና የትምህርት አሰጣጥ ላይ እንደሆነ ቁልጭ አድርጎ ያሳየናል።

ጤናማ ትምህርት

በሥጋ ሕይወት ለመኖር ምግብ አስፈላጊ ነው። ሆኖም መመገብ ስላለብን ብቻ ያገኘነውን ሁሉ እንመገብም። ለጤናችን ተስማሚ የሆነውን እንመርጣለን። ጤናችን የሚወሰነው ወደ ውስጣችን በምናስገባው ምግብ ነውና።

መንፈሳችንም በሕይወት ለመኖር መንፈስና ሕይወት የሆነውን ቃል መመገብ ያስፈልገዋል። እንዲያም ሆኖ ግን ያገኘነውን ሁሉ መመገብ አይኖርብንም። በአርግጥ ቃል ብርቅ በሚሆንባቸው ወራት ምርጫው ስለማይኖር ከአርያዎች አሰር

ሊጠበብ ይመኝ እንደነበረው የጠፋው ልጅ ምሳሌ ያገኘነውን ሁሉ ለማግበስበስ ይዳዳን ይሆናል። በረሃብ ተገደን ዛሬ ይህንን ብናደርግ ውሎ አድሮ ጤና ማጣት በኑሮአችን እና በግንኙ ነታችን ላይ መንፀባረቁ አይቀርም።

ስለዚህ የዕለት ተዕለት ምግባችን ጤንነት ግድ እንደሚለን ሁሉ የትምህርታችን ጤንነት ሊያሳስበን ይገባል። በጤንነቱ ያልተማመንበትን ምግብ እንድንበላ ማንም ሊያስገድደን እንደማይችል ሁሉ የእግዚአብሔርንም ቃል ማንም በግድ ሊግተን አይችልም። የምንሰማውን መምረጥ መርጠን የሰማነውን ደግሞ ማጣጣም የእኛ ድርሻ ነውና። በእርግጥ አስቀድመን እንዳልነው ጤናማ ያልሆነውን ለማወቅ አስቀድሞ ጤናማውን ማወቅ የግድ ነው።

በድህነት ምክንያት በልጅነቱ የበቆሎ ገንፎ ሲበላ ያደገ ሕፃን ካደገም በኋላ ከበቆሎ ገንፎ ውጪ ሌላ ምግብ እንዳለ ላያስብ ይችላል። ለዚህ ደግሞ በተሰይ ጌታን በተቀበልንባቸው የመጀመሪያ ወራት ያገኘናቸው መንፈሳዊ ምግቦች ወሳኝነት አላቸው።

ዛሬ ሕዝባችን የትምህርት ጤንነት ምን ያህል ግድ ይሰዋል? ቢባል መልሱ አሳፋሪና አስደንጋጭ እንደሚሆን መገመት አያስቸግርም።

በቤት ኪራይ ምክንያት ከቀድመው ቤተክርስቲያኑ በመራራቁ አቅራቢያው ወደሚገኝ አጥቢያ ቤተክርስቲያን መሄድ የጀመረ ባልንጀራዬ በጥቂት ሳምንታት ልምምዱ የታዘበውን እንዲህ ብሎ አጫውቶኝ ነበር። «በሄድኩበት የመጀመሪያ እሁድ ተጋባዡ አገልጋይ በአንድ ርዕስ ላይ ይናገር ነበር ሕዝቡም

በአልልታ በጭብጨባ ድጋፋቸውን ይገልጡለት ነበር። እሜን እና ሃሌሉያ ያስተጋባ ነበር። ኘሮግራሙ አልቆ ተበተነ። በሳምንቱም ሄድኩ በዕለቱ የተጋበዘው ሌላ አገልጋይ የሚናገረውን በጥሞና ስሰማ ባለፈው ሳምንት ከሰበክው ሰው ሃሳብ ጋር መሠረታዊ ልዩነት ያላቸውና እርስ በርስ የሚቃረኑ ነገሮች ይናገር ነበር። ያስገረመኝ ግን የሁለቱ ተናጋሪዎች የሃሳብ መለያየት ሳይሆን የሕዝቡ አልልታና ጭብጨባ ቅንጣትም አለመለወጡ ነበር። አእምሮዬ በጥያቄ እንደተወጠረ ከኘሮግራሙ ስወጣ አንድ የማውቀው ሰው አግኝቼ ጥያቄዬን አጋራሁት እርሱም ያለምንም ግራ መጋባት «በዚህ አትገረም ሕዝቡ ለሁለቱም አጨበጨበ እንጂ ሁለቱም ያሉትን ላይቀበል ይችላል። እያንዳንዱ አማኝ ለራሱ ጌታ ተናግሮኛል የሚለው ሦስተኛ አቋም ሊኖረው እንደሚችል አትጠራጠር» አለኝ። በማለት አጫውቶኛል።

እኔም ራሴ ከሦስት ዓመት በፊት ወደ ሁለት ሺህ አምስት መቶ የሚጠጋ ሰው በሚገኝበት ትልቅ ጉባኤ ውስጥ እንድከፈል ተጋብዤ ያጋጠመኝ ተመሳሳይ ሁኔታ ፈጽሞ የሚረሳ አይደለም። እንዳጋጣሚ አስተናጋጆች ያስቀመጡኝ ፊት ወንበር ከተለያዩ አገልጋዮች አጠገብ ነበር። ሰባኪው ለአንድ ሰዓት ተኩል ያህል ከሰበከ በኃላ ድንገት በከፍተኛ ድምፅ አንድ ነገር ተናገረ «ባለፉት ቀናት እግዚአብሔር ሶስተኛ ውን በር ከፈተልኝ። አሁንም ከዚህ ሳትወጡ ሶስተኛውን በር ይከፍትላችኃል» ጉባኤው ተናወጠ አንዳንድ ሰዎች ወንበር ላይ ቆመው መጮህ ጀመሩ። እኔ ግን ነገሩ ቀደም ሲል ከተባለው ጋር ስላልተያያዘልኝና ሶስተኛው በር ምን እንደሆነ ስላልገባኝ መጨረሻውን ለማወቅ በጉጉት ስጠብቅ ሳለሁ አጠገቤ ተቀምጦ የነበረ በርቀት የማውቀው ፓስተር እጆቹን እያወዛወዘ ከጮኸ

በኃላ ወደ እኔ ዞሮ «ዝም ትላለህ እንዴ!» በማለት በስሜት ወዘወዘኝ። ስብከቱ ቀጠለ እኔ ግን የሶስተኛው በር ጉዳይ ግልጽ ስላልሆነልኝ ያን አገልጋይ ቀስ ብዬ «ሶስተኛው በር ምንድነው?» በማለት ጠየኩት። አገልጋዩም ጥቂት ካሰበ በኃላ «ባክህ እኔም አልገባኝም» በማለት መለሰልኝ። ስለግልጽነቱ ባደንቀውም ትልቅ ሽክምና ኃዘን በልቤ አድሮ ወጣሁ።

የምንሰማውን ቃል ለመመርመር መሣሪያ ያስፈልጋል። መሣሪያችንም ራሱ የእግዚአብሔር ቃል ነው። መጽሐፍ ቅዱስን ምን ያህል እናውቀዋለን? ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ያለን እውቀት የሚለካው በቃላችን ባጠናነው ጥቅስ ብዛት ሳይሆን ባጠቃላይ የመጽሐፍ ቅዱስን ዓላማ በመረዳትና ጥቅስን በከፍሉ (በአወዱ) የክፍሉን አውድ በኪዳኑ፣ ኪዳኑን ደግሞ ባጠቃላይ የመጽሐፍ ቅዱስን ጥቅል ሃሳብ በመመልከት መተርጎም ስንችል ነው። ዛሬ በየጉባዔያችን የሚታየው ገጽታ ግን ከዚህ የተለየ ነው።

በቅርቡ በአንድ የክፍለ ሃገር ኮንፈረንስ ላይ አብሮኝ የተጋበዘ አገልጋይ ያጫወተኝን ሰፈገግታ ያህል እንኳ ሳካፍላችሁ።።

ሰባኪው መድረክ ላይ ቆሞ በማስተማር ላይ ሳለ ለጉባኤው «ብመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስንት ማሪያሞች አሉ?» የሚል ጥያቄ ያቀርብና መልስ ይጠባበቃል። አንዱ ሰው እጁን አወጣና «አምስት» አለው። አስተማሪው በምላሹ ተደስቶ በጌታ ስም ከባረከው በኃላ ተጨማሪ ጥያቄ በማስከተል እነማን እንደሆኑ ዘርዝርልኝ ይለዋል። ሰውየውም በድፍረት በጉባዔው ፊት ከቆመ በኃላ በታሳቅ ድምጽ «አንድ የአዳዲዋ

ማርያም፣ ሁለት ጽዮን ማርያም፣ ሦስት መርጦለዬ ማርያም. . .» ብሎ ሳይጨርስ አስተማሪው እንዳስቆመው ሰምቻለሁ።

ለነገሩማ የማይሆን ነገር ሲነገር አሜን የሚሉ በማስታወቂያ መሃል እልል የሚሉ ሰዎችን መስማት የተለመደ ሆኖ የለ።

እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ የትምህርትን ጤንነት በመመርመር እግዚአብሔርን ወደ መምሰል ማደግን አስቸጋሪ ያደርገዋል። ሆኖም መፍትሔ የሌለው ተስፋ አስቆራጭ ጉዳይ አይደለም። መፍትሔውም ያለው በአስተማሪዎች እጅ ነው ጤናማ ትምህርት ያላቸው አስተማሪዎች ሲበዙ በጤናማ ቃል የሚመገብ አማኞች ይበዛሉ፣ ጤናማ ምግብ ሲበዛ ደግሞ ጤናማ ኑሮ የሚኖር ሕዝብ ይበረክታል። ጤናማ ሕዝብ የጤናማ ሕብረተሰብ መሠረት እና የጤናማ መሪዎች መፍለቂያ ነው። አለዚያ ግን ጤናማ ብልቶች በሌሉበት ጤናማ አካል ይኖራል ብሎ ማሰብ ከንቱ ድካም ይሆናል።

ይህ ጤናማ ትምህርት ምንድነው? ከየትስ ይገኛል? ብለን የምንጠይቅ ከሆነ ጳውሎስ እንዲህ በማለት ይመልስልናል፦

> *«ይህ ጤናማ ትምህርት በሩካ እግዚአብሔር ለእኔ በአደራ ከሰጠኝ የክብር ወንጌል ጋር የሚስማማ ነው።»*
>
> *«ከእኔ የሰማኸውን በክርስቶስ ኢየሱስ ባለ እምነትና ፍቅር የጤናማ ትምህርት ምሳሌ አድርገህ ያዝ።» 2ጢሞ. 1፡13*

እንግዲህ እኛም እንደጢሞቴዎስ ይህንን ጤናማ ትምህርት እንደ ምሣሌ እንያዝ።

የፀጋ ትምህርት

ፀጋ ለማይገባው የሚሰጥ፣ ተቀባዩ የማይመጥነው፣ እድሜ ልኩን ቢለፋ በደሞዝ ወይም በሽልማት ሊያገኘው የማይችል ነፃ ሥጦታ ነው።

እግዚአብሔር የራሱን ሕይወት በፀጋ ሰጥቶናል። ስለዚህ ከእግዚአብሔር ያገኘነው ሁሉ የፀጋ ሥጦታ እንጂ እንደሚገባን የምንቆጥረው መብታችን የሆነ አንዳች ነገር የለም። የተጠራነው በፀጋ ነው፣ የተመረጥነው በፀጋ ነው፣ የምናገለግለው በፀጋ ነው፣ የምንዘምረው በፀጋ ነው፣ አሁንም የምንኖረው ለዘላለምም የምንቀጥለው በፀጋ ነው። በሕይወታችን ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ግንኙነት በፀጋ ያልሆነ አንዳች ነገር የለም።

የእግዚአብሔር ፀጋ ከመገለጡ አስቀድሞ ሕግ የተሰጠበት አንዱ ምክንያት ሰው በስራው ሊፀድቅና የእግዚአብሔርን የጽድቅ መሥፈርት ሊያሟላ እንደማይችል ለማሳየትና በክርስቶስ ኢየሱስ ለሚገለጠው የእግዚአብሔር ጽድቅ ለማዘጋጀት ነበር።

አሁን ግን ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ፀጋ ተገልጧል። ይህም ፀጋ አስተማሪ ነው። አስተማሪ የተባለውም የራሱ ትምህርት ስላለው ነው። ትምህርቱም «የፀጋ ትምህርት» ነው።

ሆኖም የፀጋ ትምህርት ከሰይጣን ተንኮልና ከሰዎች ማታለል የተነሳ ሊወድቅባቸው የሚችል ሁለት ጽንፎች አሉ። ይህ

ክስተት በታሪክ ውስጥ በተደጋጋሚ የታየ ሲሆን «ታሪክ ራሱን ይደግማል» እንዲሉ በእኛም ዘመን እየታየ ነው።

አንደኛው ጽንፍ የራስን ጽድቅ ከመፈለግ ተነሳስቶ ሰዋዊ የጽድቅ መስፈርት በማውጣት ሕግ ተኮር ሆኖ የእግዚአብሔርን ፀጋ መጣል ሲሆን፣ ሁለተኛው ጽንፍ በፀጋ ሥም ለሥጋ ላርነት በመስጠት ፀጋን የኃጢአት የፈቃድ ወረቀት አድርጎ በርኩሰት መጋለብ ነው። አንድ የእግዚአብሄር ሰው እንዳሉት አንዱ ጽንፍ «ገዳማዊነት» ሲሆን ሌላው ደግሞ «ዓለማዊነት» ነው። እነዚህ ሁለቱም የፀጋ ትምህርት ጠንቆች ናቸው። የፀጋ ትምህርት የማዳን ኃይሉና የመለወጥ ጥበቡ በሙላት የሚገለጠው ትክክለኛ ሚዛኑን ይዞ ሲተላለፍ ብቻ ነው።

ፀጋ ነፃ እንጂ ርካሽ አይደለም። ወደ እኛ በነፃ የመጣው አስቀድሞ ውድ ዋጋ ስለተከፈለበት እንጂ በነፃ ስተሰጠኝ አይደለም። ስለዚህ ፀጋ ነፃም ውድም ነው። እኛ ሕይወት ያገኘነው ሕይወት ተከፍሎ ነው። ታዲያ ይህ በፀጋ ያገኘነው ሕይወት በእኛ ይገሰጥ ዘንድ እኛም ዋጋ መክፈል ይጠበቅብናል። ያም ዋጋ መስቀሉን በመሸከም የሥጋ ፈቃዳችንን ለመግደል መወሰን ነው።

ነገር ግን በፀጋ ድኛለሁ እያልን ፀጋውን የሚመጥን ኑሮ ካልኖርን ፀጋውን እያረከስነውና ዋጋ እያሳጣነው እንደሆነ ልንገነዘብ ይገባል። የፀጋ ትምህርት የሥጋን ፈቃድ እየገደልን የእግዚአብሔርን ሕይወት በዕለት ተዕለት ኑሮአችን የምንገልጥበት የኑሮ ሥርዓት ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ ለቲቶ በፃፈው መልእክቱ ፀጋ ምን እንደሆነና እንዴት እንደሚሠራ ሲገለጽ እንዲህ ብሎታል።

«ለሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ፀጋ ተገልጿልና» ቲቶ 2:11-12

ማንኛውንም ዘመናዊ ዕቃ ከገበያ ገዝተው ካርቶኑን ሲከፍቱ በቅድሚያ ፊት ለፊት የሚያገኙት ሊያዩት የናፈቁትን እቃ ሣይሆን እነስተኛ መጽሐፍ ነው። «ማኑዋል» ይባላል። ይህ መጽሐፍ እቃው አይደለም። ስለ እቃው ማንነት፣ ምንነት፣ የሚተርክ የእቃውን ባሕሪ፣ የአጠቃቀምና የአያያዝ ሕጎች የሚተነትን መጽሐፍ ነው። ከበላዩም «ይህን እቃ ለመገጣጠም እርምጃ ከመውሰድም በፊት ይህን መጽሐፍ ያንብቡት» የሚል የእቃው አምራቾች ማስጠንቀቂያ አዘል ምክር ተጽፎበታል።

እግዚአብሔር የራሱን ሕይወት ሰጠን። የሰጠንም በፀጋ ነው። የተሰጠንም እንድንኖርበት ነው። በአግባብ እንድንኖርበት ግን ስለዚህ ሕይወት ማወቅ ያስፈልገናል። እግዚአብሔርም ይህን በማሰብ መጽሐፍ ቅዱስን እንደ ማንዋል ሰጥቶናል። ይህ ሁሉ ሕይወትን በኑሮ እንገልጠው ዘንድ ለማስቻል ነው። ስለዚህ የፀጋ ትምህርት መንፈስ ቅዱስ ቃሉን በመጠቀም የእግዚአብሔርን ሕይወት በኑሮ እንዴት እንደምንገልጽ የሚሠጠን የትምህርት ዓይነት ነው።

የትምህርት ዓይነቶቹም በሦስት የሚከፈሉ ሲሆን፦

1. መካድ
2. መኖር እና
3. መጠበቅ ናቸው።

እነዚህ የትምህርት ዐይነቶች ፊጽመው ሊነጣጠሉ አይችሉም። ካልካድን መኖር ፣ካልኖርን መጠበቅ አንችልምና።

መካድ ባለፈው ጊዜ በተከናወነ አውነት ላይ ተመስርተን የምንፈጽመው ሲሆን መኖር የአሁኑን ጊዜ፣ መጠበቅም የወደፊቱን የሚያመለክት በመሆኑ ትምህርቱ ሁሉንም የሕይወት ደረጃ የሚዳስስ እንዲሆን ያደርገዋል።

ከዳንበት አንስቶ ጌታን በክብር አስከምናይበት ጊዜ ድረስ ያለውን የሕይወት ሂደት የሚያሳዩትን እነዚህን ሶስት ደረጃዎች በሚገባ ለመረዳት አንድ በአንድ ለማየት እንሞክር።

«ለሰዎችን ሁሉ ...»

እነዚህ ሰዎች እነማን እንደሆኑ ጳውሎስ ቀደም ሲል በዝርዝር አስቀምጧል። ቲቶ በነበረበት በቀርጤስ ቤተክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ የተለያየ የኅብረተሰብ ክፍልን የሚወክሉ አማኞች ናቸው። ቤተክርስቲያን በክርስቶስ አምነው የዳኑ እግዚአብሔርንም ለማምለክ የሚሰበሰቡ ሰዎች ማኅበር እንጂ የአንድ የተመሳሳይ ዕድሜ ክፍል ፆታ ያላቸው ሰዎች ስብስብ አይደለችም። ስለዚህ ጳውሎስ አረጋውያን፣ አሮጊቶች፣ ወጣት ሴቶች፣ ወጣት፣ ወንዶችና ባሮች በማለት በዝርዝር ያስቀምጣቸዋል።

የተጠቀሱት ሰዎች በዕድሜ በፆታና በኑሮ ደረጃ የተለያዩ ናቸው። የተሰጣቸውም ትዕዛዝ እንደየሁኔታቸው የተለያየ ነው። ነገር ግን ሲሆኑ የሚገባቸውን ሲሆኑ የሚችሉበት ፀጋ አንድ ነው።

ሽማግሌ፣ ወጣት፣ ወንድ፣ ሴት፣ የተማረ፣ መሃይም፣ ባሪያ ነፃ ሳይል ሁሉን የሚያድን አንድ ፀጋ።

ይህ ፀጋ የተገለጠ እንጂ አዲስ የተፈጠረ አይደለም። አስቀድሞም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ለሰው ልጆች ግን ተሰውሮ ነበር አሁን ግን በክርስቶስ ኢየሱስ ተገልጣል።

«....የሚያድን .... »

ይህ ፀጋ የመጀመሪያው ሥራው ማዳን ነው። የሚያድነውም በራሳቸው መዳን እንደማይችሉ የተረዱት ናቸው። መዳን ማለት ከሚገዛን ኃይልና ስልጣን ማምለጥ፣ ከተጽእኖ መውጣት፣ ከጭቆና መላቀቅ ባጠቃላይ ነፃ መሆን ማለት ነው። በኃጢአት፣ በልዩ ልዩ ምኞትና በሞት ፍርሃት የዲያቢሎስ ባርያ የነበርነውን ፀጋው አዳነን። እኛ ድምፁን ሰምተን ከማመን ብሎም ከመከተል በስተቀር ያደረግነው አንዳች አስተዋጽኦ የለም። የእኛ ሥራ ሳይጨመርበት ፀጋው አዳነን።

«... ያስተምረናል ...»

ሆኖም የፀጋው ሥራ በማዳን ብቻ የተወሰነ አይደለም። ዛሬ በርካታ ክርስቲያኖች በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ የሚያውቁት የሚያደንቁትም ከሰይጣን አገዛዝ መለቀቃቸውን ብቻ ነው። ከዚህ የተነሳ ቀጣዩን የእግዚአብሔርን ዓላማ በመረዳት ከፀጋው ጋር አብረው የሚጓዙ እምብዛም አይደሉም።

የእግዚአብሔር ዓላማ ሰውን ከዲያቢሎስ፣ ከኃጢአትና ከሞት ባርነት አድኖ መተው ሲሆን ኖሮ ደህንነት እንዴት አሳዛኝ እንዴትስ ተስፋ አስቆራጭ በሆነ ነበር። የዚህን አባባል ትክክለኛ ገጽታ ለመመልከት የሚረዳን የዘወትር ምሣሌያችን የእስራኤል ልጆች ናቸው። የእግዚአብሔር አጀንዳ እስራኤልን ከግብጽ ባርነት በማዳን ብቻ የተወሰነ ቢሆን ኖሮ። በታሳቅ ክብር ቀይ ባሕርን የተሻገረው ሕዝብ በምድረበዳ ተቅበዝብዞ የሚጠፋ ምስኪን ሕዝብ በሆነ ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር እስራኤልን ከፈርኦን እጅ ከማስለቀቅ ይልቅ የከበረ ቀጣይ አቅድ ነበረው። ያም ከግብጽ የዳነውን ሕዝብ የተስፋይቱን ምድር ማውረስ ነው።

ልክ እንዲሁ በክርስቶስ ለእኛ የተገለጠው የእግዚአብሔር ፀጋ ከሰይጣን ከኃጢአትና ከአለም ጽኑ አገዛዝ ነፃ በማውጣት አያካትምም ካደነን በኋላ ከዘላለም ዘመናት በፊት የተሰጠንን ተስፋ እርሱም የእግዚአብሔርን ሕይወት ወደምንካፈልበት ክፍታ ያደርሰናል ብሎም ያወርሰናል።

ታዲያ ፀጋው ይህንን የሚያከናውነው በማስተማር ነው። ምንጊዜም በማዳን ሥራ ላይ ትልቁን ሚና የሚጫወተው ኃይል ነው። ተስፋችንን ወደምንወርስበት ሥፍራ ለማድረስ ትልቁን ሚና የማጫወተው ግን ብርሃን ነው። ብርሃን እውቀት ነው እውቀትም የሚገኘው በትምህርት ነው። እናት በምጥ ጊዜ ልጇን በሥቃይና በኃይል ወልዳ ከተወለደ በኋላ ዕለት ዕለት በፍቅር እየመገበች እንደምታሳድገው ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል በሆነው በክርስቶስ የዳንን እኛ የእግዚአብሔር ጥበብ የሆነው ክርስቶስን እየተመገብን እናድጋለን። ከዘላለም ዘመናት በፊት እግዚአብሔር ለክብራችን የወሰነውን ዓይን ያላየውን ጆሮ ያልሰማውን በሰውም ልብ ያልታሰበውን እግዚአብሔር ግን ለሚወዱት ያዘጋጀውን የእግዚአብሔርን ሕይወት በመላት ወደምንካፈልበት ደረጃ እንመጣለን።

ይህንንም የሚፈጽመው ያው ፀጋው ሲሆን በመሣሪያነት የሚጠቀመውም ትምህርትን ነው።

እንግዲህ ወሳኙ ጥያቄ ትምህርቶቻችን ምን ያህል ከዚህ እውነት ጋር ይጣጣማሉ? የሚለው ነው። መንፈስ ቅዱስ የክርስቶስን አካል ወደዚህ ደረጃ ለማድረስ በውስጧ አድሮ እየሠራ ነው። ታዲያ እኛ የምንማረውም ሆነ የምናስተምረው ትምህርት ከመንፈስ ቅዱስ የልብ ትርታ ጋር ምን ያህል አብሮ ይሄዳል?

ከአስተማሪዎቻችን አንደበት ወደ እኛ ጆሮና ልብ የሚንቆረቆረው ትምህርት እፁፅ የሞላበት ይሁን ፀጋ የሞላበት በምን እናውቃለን።(ቲቶ 2:11-13)

እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ በዚሁ ክፍል ውስጥ ጳውሎስ በመቀጠል የሚዘረዝራቸውን ሦስት ዋና ዋና ነጥቦች እንመልከት፡-

<u>መካድ</u>

> *«... ይህም ፀጋ ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊ ምኞትን ክደን ...» የ1962 እ.ኤ.አ. አትም*
>
> *«... ይህም ፀጋ በኃጢአት መኖርንና ዓለማዊ ምኞትን ክደን ...» የ2001 እ.ኤ.አ. አትም*

ከላይ እንደምናየው ሁለቱ የአማርኛ ትርጉሞች በማለት የሚገለፁትን ሁሉም የእንግሊዝኛ ትርጉሞች "Denying Ungodliness" እግዚአብሔርን አለመምሰል ክደን ብለው ታል።

ይህ መጀመሪያ ከተፃፈበት ሃሳብ ጋር የሚስማማ ትርጉም እንደኛውንና የመጀመሪያውን የፀጋ ትምህርት ዓላማ ቁልጭ አድርጎ አስቀምጦታል።

በፀጋ የተሰጠን መንፈስ ከእግዚአብሔር ያልሆነውን፣ ከእርሱ ያልመነጨ፣ እርሱን የሚያከብረውን፣ እርሱን ማዕከል ያላደረገውን ባጠቃላይ እርሱን የማይመስለውንና እርሱን የማይገልጠውን ያስተምረናል።

ምክንያቱም እግዚአብሔርን የማይመስለውን ካልካድን እግዚአብሔርን ወደ መምሰል መጓዝ አንችልማ። እግዚአብሔርን መምሰል የራሱ መንገድ ያለው የሕይወት ስልት እንደሆነ ሁሉ ኃጢአተኝነትም እንዲሁ ራሱን የቻለ ጎዳና ነው። ሁለቱ መንገዶች ጎን ለጎን ሊኬድባቸው የማይቻሉ ተቃራኒ አቅጣጫዎች እንደመሆናቸው መጠን ለአንዱ

ፊታችንን ስንሰጥ ለሌላው ጀርባችንን፣ ለሌላው ጀርባችንን ስንሰጥ ለአንዱ ፊታችንን መስጠታችን የማይቀር ነው። ለዚህ ነው አንዱን ለመከተል ሌላውን መካድ የግድ የሆነው። ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊ ምኞትን ስንክድ እግዚአብሔርን ወደመምሰል እየተንቀሳቀስን እንደሆነ ሁሉ ወደ ኃጢአተኝነትና ዓለማዊ ምኞት ስንንቀሳቀስ እግዚአብሔርን መካዳችን መሆኑ አያጠያይቅም። በአፋችን ባይሆን እንኳ በስራችን እንክደዋለንና።

«መካድ» ጥሬ ቃሉን የተመለከትን እንደሆነ «የሚያውቁትን አላውቅም» የሆኑትን አልሆንኩም ብሎ ድርቅ ማለት ነው። ኃጢአተኝነትንና (Ungodliness) ዓለማዊ ምኞትን መካድ ያስፈለገን ቀድሞ ስለኖርንበት፣ ስለተገዛንለትና ይነስም ይብዛ ያላለፍነው ታሪክ ስላለን ነው። ታዲያ አሁን በቀጥታ ሊገዛን ባይችል እንኳ ሊጋብዘን ሲመጣ «ያ የምታውቀው ሰው እኔ አይደለሁም፣ እኔም አላውቅህም» በማለት መካድ ይጠበቅብናል። ታዲያ ይህ መካድ ከንቱ ሽምጠጣ አይደለም ጽኑ መሠረት ያለው ተግባር ነው።

መካድ ቀጣይ ሂደት እንጂ የአንድ ጊዜ ጉዳይ ወይም ቅጽበታዊ ተግባር አይደለም። ፀጋው ካሳገዘን በስተቀር በሥጋ ሥጋዊነትን መካድ አንችልም። ከፀጋው ተምረን በመንፈስ የሥጋን ሥራ መግደል ግን ይቻላል።

ፀጋው እንዲያስተምረን እኛም ተማሪዎች መሆን መቻል ይኖርብናል። ተማሪ ማለት ደግሞ ይህ ቃል በተፃፈበት ዘመን ደቀመዝሙር በመባል ይጠራ ነበር።

ስለዚህ እግዚአብሔርን የማይመስለውን ሁሉ ለመካድናእግዚአብሔርን ወደ መምሰል ለመጓዝ የፀጋው ተከታይ ተማሪ (ደቀመዝሙር) መሆን ይናርብናል።

መኖር

«... አግዚአብሔርን በመምሰል በአሁኑ ዘመን አንድንኖር ያስተምረናል ...።»

ወንጌል ስለ አየሱስ ክርስቶስ ስቅለት የሚያውጅ የሞት መልዕክት ብቻ ሣይሆን አዲስ ሕይወት የሚጀምርበት የትንሣኤ አቅጣጫም አለው። የመስቀሱን አቅጣጫ መመልከት ለኃጢአት በባርነት ይገዛ የነበረውን አሮጌውን ሰው ለመካድ አስፈላጊ ሲሆን በጽድቅና ራስን በመግዛት እግዚአብሔርን በመምሰል ለመኖር ግን የትንሣኤው አቅጣጫ ወሳኝ ነው። ያልሞተ ሲነሳ ያልተነሳ ሊኖር አይችልምና። ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን በመነሣቱ «ለሕያው ተስፋ ለማይጠፋና እድፈት ለሌለበት ለዘላለማዊ ርስት ዳግመኛ ተወልደናል።»

በዚህ እውነት ላይ ዐንተን ከቆምን ፀጋው እግዚአብሔርን ወደ መምሰል ሊመራን አይቸገርም። የፀጋው ትምህርት እኛን በተመለከተ ራሳችንን በመግዛት ሌሎችን በተመለከተ ጽድቅን በማድረግ እግዚአብሔርን በተመለከተ ደግሞ እርሱን በመምሰል እንድንኖር የሚያስተምረን ነው።

ጌታን የተቀበልኩ አካባቢ አንድ ክባድ ፈተና ገጠመኝ። ይህ ዛሬ ፈተና ሆኖ የከበበኝ ነገር ከመዳኔ በፊት ሰረቻም ጊዜ የኖርኩበት ልምድ ነበር። ጠራርጎ እንደሚወስድ ሳርፍ እያስገመገመ የመጣው የፈተና ማዕበል ልቤን አርዶት ሳለ አንድ ብርሃን በውስጤ በራ «ከአንግዲህ ወዲያ ለኃጢአት እንዳንገዛ የኃጢአት ሥጋ ይሻር ዘንድ አሮጌው ሰጋችን

ከክርስቶስ ጋር እንደተሰቀለ እናውቃለን።» የሚል የቃሉ ብርሃን።

በዚህ ብርሃን ርዳታ ለኃጢአት ይገዛ የነበረው የቀደመው ማንነቴ እንደሞተና ኃጢአት ሊገዛው የማይችል አዲስ ማንነት በውስጤ እንደተተካ ማየት ቻልኩ። ባገኘሁት ድፍረት ተሞልቼ በወስጤ ለሚያስገመግመው የኃጢአት ኃይል ሰው እንደሚያናግር ድምፄን አውጥቼ መናገር ጀመርኩ። «ሰማ ኃጢአት የመጣኸው አድራሻ ተሳስተህ ነው። አምን አንተ የምትሰው ፈቃድህንም ይፈጽም የነበረ ሰው እዚህ ይኖር ነበር። ነገር ግን ከወራት በፊት ሞቶ ተቀብሮ ባሕር ውስጥ ተቀብሯል (የተጠመቅሁት ጅቡቲ ቀይ ባሕር ውስጥ ስለነበር) አሁን እዚህ ማደሪያ ውስጥ የሚኖረው ሌላ አዲስ ሰው ነው።» በማለት ተናገርኩ። ወዲያው የከበበኝ ኃይል እንዳለም ሲቀለኝ፣ እንደ ጢስ ሲበን ይታወቀኝ ነበር። ክህደት ይሏል እንዲህ ነው። የድሮውን ወዳጅ አላወቅህም ብሎ መካድ።

አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔርን በመምሰል መኖር የሚቻለው በሚመጣው ዓለም ብቻ ነው ብለው ያስባሉ። ነገር ግን ይህ ለሚቀጥለው ሕይወት በቀጠሮ የሚተላለፍ ጉዳይ አይደለም። ቃሉ ፀጋው ... «በአሁኑ ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል» ይላል። ጳውሎስ «የአሁኑ ዘመን» የሚለው የእርሱ ዘመን ከእኛው «የአሁኑ ዘመን» ጋር ሲነፃፀር ኃጢአተኝነትና አለማዊ ምኞት ይበልጥ የነገሠበት እግዚአብሔርን በመምሰል ለመኖር እጅግ የሚያዳግት ፈተናና ትግል የሞላበት ዘመን መሆኑ እሙን ነው።

ሆኖም ዘመኑ ምንም ያህል ቢለወጥ ፀጋው ስላልተለወጠ ያኔ አባቶቻችንን ያኖረ ፀጋ እኛንም እግዚአብሔርን በመምሰል ለማኖር የሚያስችል አቅም አለው።

ክርስቶስ በሥጋ የመጣው አስቀድሞ ሕግ ወደተሰጠው የእስራኤል ሕዝብ ነው። ኢየሱስ በመጣበት ዘመን ሕግን መፈፀም ተስኗቸው ጫንቃቸው በትዕዛዛት ሸክም የጎበጠውን ወደ እርሱ ጫና ያወረደውን ሕግ ሸክም ከላያቸው ካነሳ በኃላ ሌላ የሕይወት ሕግ አሸከማቸው። የአሁኑ ከቀደመው ይልቅ የሚከብድ ስለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም። ነገር ግን አንድ ተስፋ ሰጣቸው እርሱም ራሱ በእነርሱ ውስጥ ሆኖ ቀንበሩን እንዲሸከም። ይህ አባባል አንድን እውነት ያረጋግጥልናል «ክክርስቶስ በቀር ክርስትናን መኖር የሚችል ማንም የለም» «ክርስትናን ለመኖር የግድ ክርስቶስን ይጠይቃል።» «በጽድቅ፣ እግዚአብሔርን በመምሰልና ራስን በመግዛት መኖር የሚቻለው ክርስቶስ በእኛ ውስጥ በሕያውነት ሲኖር ብቻ ነው።» አለዚያ ግን እግዚአብሔርን መምሰል የሕይወት ኃይል የሌለው ትርፍ ማግኛ የውጭ መልክ ብቻ ሆኖ ይቀራል።

<u>መጠበቅ</u>

መካድ፣ መኖርና መጠበቅ ተከታታይ ሂደቶች ብቻ ሣይሆኑ እድገትን የማያሳዩ ደረጃዎች ናቸው። አንዱ ከሌላው ይበልጣል። ምንም እንኳን መካድ ቀጣይ ተግባር ቢሆንም በዋነኝነት የአዲስ ሕይወት የመጀመሪያ ምዕራፍ ነው። መኖር ደግሞ በመካድ ላይ የሚመሠረት ሌላ ምዕራፍ በመሆን ልቀቱን ያሳያል። መጠበቅ ግን ከሁለቱም በላቀ ሁኔታ የሚታይ ከፍተኛና የመጨረሻ ደረጃ ነው። ክርስቲያን ተብለው ከሚጠሩ ኃይማኖቶች መካከል አብዛኛዎቹ የወንጌላዊያን አማኞች ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ እንደሚመጣ ያምናሉ። ከዚያም ውስጥ ጥቂቱ ክርስቶስ ዳግም እንደሚመጣ በደፈናው ከማወቅ ባሻገር የመምጣቱን ምልክቶች፣ የአመጣጡን ሁኔታዎች፣ ቅድመ መከራ፣ እኩሌታ

መከራ፣ ድህረ መከራ በማለት ከፋፍለው ይተነትናሉ። ዋናው ቁምነገር ግን የአመጣጡን ስነመለኮታዊ ፍቺ ማወቅና ትንታኔ መስጠት ሳይሆን ኃጢአተኝነትንና አለማዊ ምኞትን ክዶ በጽድቅ እግዚአብሔርን በመምሰልና ራስን በመግዛት እየኖሩ የጌታን መገለጥ መጠባበቅ ነው።

ታዲያ ስንቱ ክርስቲያን ነው የጌታን መገለጥ የሚጠባበቀው? መጠበቅ የሚረጋገጠው አንጋጦ ሰማይን በመመልከት ሳይሆን በኑሮ ነው። የጌታን ቀን መጠበቃችን፣ የአስተሳሰብ ይዞታችን፣ የአመለካከት ስርዓታችን፣ የአኗኗር ዘይቤያችን ላይ የጽድቅ ተጽእኖ ካላመጣ ጌታን እየጠበቅን ነው ለማለት አያስደፍርም።

ጌታን መጠበቅ ማለት ሲከፋን፣ ነገር ሲጨልምብን፣ በዙሪያችን ካለ ሰዎች ጋር በሰላም መኖን ሲሳነን በር ዘግቶ በአንባ የምጽአት መዝሙር መዘመር ማለት አይደለም። በክፍታም ይሁን በዝቅታ፣ በማግኘት ይሁን በማጣት፣ በመከበር ይሁን በመዋረድ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ የማያቋርጥ የሕይወት ባሕሪ ነው።

የሥጋ ሕይወት እግዚአብሔርን የሚናፍቅበትና የማጠብቅበት ባሕሪ የለውም። ስለዚህ በሥጋ ጌታን መጠበቅ አይችልም። የእግዚአብሔር ሕይወት በውስጣችን ሲገለጥ ግን ከሚንፀባረቁት ባሕሪያት አንዱ እግዚአብሔርን ያለገደብ መፈለግ ያለልክ መናፈቅ ነው። ያኔ ጌታን መጠበቅ ጥረታችን ሳይሆን ባሕሪያችን ይሆናል።

እዚህ ጋ መድረስ የሚችሉት በክርስቶስ መስቀል በተሠራው እውነት ላይ ቆመው ዕለት ዕለት መስቀሉን እየተሸከሙ ኃጢአተኛነትንና ዓለማዊ ምኞትን የሚክዱ፣ በትንሣኤው

ኃይል ወደፊት እየገሰገሱ በጽድቅ እግዚአብሔርን በመምሰልና ራስን በመግዛት የሚሄዱ አማኞች ብቻ ናቸው።

እነርሱ እያንዳንዱን ውሣኔና ርምጃ የሚመዝኑት ጌታ ሲገለጥ ከሚያገኙት ዘላለማዊ ክብር አንፃር እንጂ ዛሬ ከሚያመጣላቸው ፋይዳ ወይም ጊዜያዊ ረብ አንፃር አይደለም።

ለእንዲህ ዓይነቱ ደግሞ አክሊል ተዘጋጅቶላቸዋል። ይህንንም አክሊል መልካሙን ገድል ከተጋደሉት፣ ሩጫቸውን ከጨረሱት፣ የኃይማኖትን ጤንነት ከሚጠብቁት ከነጻውሉስ ጋር በዚያን ቀን ይረከባሉ። የክርስትና ሕይወት ጫፍ ላይ ደርሰዋልና በምድር የመፋተንነት ኑሮ ኖረዋልና ዕለት ዕለት በንዮቀት መንፈስ ተመላልሰዋልና ጌታ ሲገለጽ ክብርን ይጎናፀፋሉ።

> *«... ወደፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶኛል ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም።» 2ጢሞ. 4:8*

4
እግዚአብሔርን የመምሰል መንገድ

አንድ የሚያጓጓ ነገር የተነገረው ሰው «ታዲያ ይህን የተባለውን ነገር ማግኘት የምችለው እንዴት ነው?» ብሎ መንገዱን ቢጠይቅ አያስገርምም።

አንባቢም እግዚአብሔርን የመምሰል ሕይወት እንዴት ሊገኝ እንደሚችል መንገድ መጠየቁ አይቀርም። ይህም መጠየቅ እንዲሁ የሚመጣ አይደለም እግዚአብሔር ወደ ፈቃዱ አንድንደርስ ሲሻ አስቀድሞ በውስጣችን ጉጉት ይፈጥራል።

ይህን የሚያደርገው በጉጉት ሊያስቀረን ሳይሆን በውስጣችን የተፈጠረው ያ ጉጉት መድረስ የሚገባን ሥፍራ እስክንደርስ ድረስ በጽናት የመጓዝ ጉልበት እንዲሆነን ነው።

የታሰበው ቦታ ለመድረስ ደግሞ መንገድ ወሳኝ ነው።

እግዚአብሔርን ወደመምሰል መጓዝ ሰሚሹ ሁሉ እነሆ አዲስና ሕያው መንገድ ተመርቆ ተከፍቷል። ያም መንገድ ሕይወት ነው። ያም ሕይወት እየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱ ራሱ ስለራሱ እንደመሰከረ ወደ ሕይወት የሚያደርስ እውነተኛ መንገድ ነው።

ስለዚህ ይህ ምዕራፍ እግዚአብሔርን ለመምሰል ብቸኛ መንገድ ስለሆነው ሕይወት የምናወሳበት ይሆናል።

የመንገዱ ሰዎች

የክርስቶስ ተከታዮች ለመጀመሪያ ጊዜ በአንጾኪያ «ክርስቲያን» ተብለው ከመጠራታቸው በፊት እምነታቸው «መንገድ»

እነርሱም «የመንገዱ ሰዎች» ተብለው ይጠሩ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክርልናል። [16]

ክርስትና መንገድ ከሆነ ወደ አንድ ሥፍራ የሚያደርስ ጎዳና እንጂ አንድ ቦታ ተተክሎ የሚቆም ሃውልት ወይም የሕዝብ ሰፈራ አይደለም። እንድ ደቀ መዝሙር መምህሩን የሚከተልበት ዓላማ መምህሩን መምሰል እንደሆነ ሁሉ [17] እኛ ም ጌታን የምንከተልበት አንድና ብቸኛ ምክንያት በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን መምሰል ነው።

እግዚአብሔርን የመምሰል ጎዳና አባጣ ጎርባጣ ያለው፣ ተራራ ሸለቆ የሞላው፣ መውደቅ፣ መነሳት፣ መቁሰል፣ መላላጥ፣ የበዛበት የሕይወት ጉዞ ነው። ቢሆንም ከሚያስገኘው ዘላለማዊ ክብር አንፃር ሲታይ የሚከፈለው ዋጋ ኢምንት ነው። ይህን ጉዞ የሚጀምሩ አዕላፋት ቢሆኑም ጨርሰው የሚሸለሙት ግን ኢምንት መሆናቸውን መጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ምሳሌዎች ያረጋግጥልናል። ከግብጽ ከወጡት ስድስት መቶ ሺህ አባወራዎች መካከል ወደ ተስፋይቱ ምድር የገቡት ሁለት ሰዎች ብቻ መሆናቸው በራሱ በቂ ማስረጃ ይሆናል። ታዲያ የተቀሩት ለምን በምድረበዳ ወደቁ? ብንል መንፈስ ቅዱስ፦

> *«ዘዚያ ትውልድ ላይ የተቆጣሁት ለዚህ ነበር እንዲህም አልሁ «ልባቸው ሁልጊዜ ይስታል መንገዴንም አላወቁም» ስለዚህ በቁጣዬ እንዲህ ብዬ ማልሁ «ወደ እረፍቴ ከቶ አይገቡም።»* ዕብ. 3:10-11

በማለት ምሳሌዎቻችን የሆኑት የእስራኤላውያን የውድቀት ምክንያት መንገዱን አለማወቅ መሆኑን ይነግረናል።

በመሠረቱ መንገድ መሄጂያ እንጂ መኖሪያ አይደለም። እስራኤላውያን ግን መቃብር ሲያደርጉት እንመለከታለን። ምንም ከግብፅ ቢወጡ ግብፅ ከእነርሱ አልወጣችም ነበርና በምድረበዳ ወድቀው ቀሩ። አልገባቸውም እንጂ የምድረበዳው

ዓላማ እነርሱን ለማሰቃየት ሳይሆን የግብፅን ባህሪ ከልባቸው በማውጣት የእግዚአብሔርን ሥርዓት ለመተካት የተዘጋጀ ነበር።

ታዲያ እኛስ የዛሬዎቹ ምን ያህል መንገዱን አወቀናል? ምን ያህልስ እየሄድንበት ነው? እግዚአብሔርን በመመሰል ሂደት ወስጥ ዋናው ጥያቄ ደርሰሃል? ወይስ አልደረስክም? ሳይሆን መንገዱ ላይ ነህ? ወይስ አይደለህም? የሚለው ነው።

መንገዱን ማወቅ

የትኛውም የመንገድ ጉዞ እንደተጀመረ አይጨረስም። አነሱም በዛ የሚፈጀው ጊዜ፣ የሚጠይቀው ጉልበት አለ። በጉዞው ሂደት ላይ ምንም ያህል ወደኋላ ብንቀር እንኳን በትክክለኛው አቅጣጫ እስከተራመድን ድረስ የመድረስ ተስፋ አይቆረጥም። ችግሩ መንገድ ስንስት ብቻ ነው። በዚህ መንገድ ላይ ሂደው ሩጫቸውን የጨረሱት የእምነት አባቶች ለእኛ ለዛሬዎቹ ተረኞች የጎዳና ስም የመንገድ መብራትንና ጠቋሚ ምልክት እንደሚሆኑልን የዕብራውያን መልእክት ፀሐፊ ይነግረናል።[17]

አንድ በመኪና የሚጓዝ ሰው በምናባችን እንሳል። ሰውየው በማለዳ ከአዲስ አበባ ሲነሳ ዓላማው ደሴ ከተማ ደርሶ ከናፈቃቸው ወዳጆቹ ጋር ምሹቱን ማሳለፍ ነው እንበል። እናም ሰውየው በአዋሳ መንገድ ላይ በሰዓት መቶ ሃያ ኪሎ ሜትር እየነዳ ይነጉዳል። ይህ ሰው በስንት ሰዓት ደሴ የሚገባ ይመስሎታል? አንድ ቦታ ላይ መንገድ መሣቱን ተረድቶ ቀኝ ኋላ አስካልዞረና ትክክለኛውን አቅጣጫ አስካልያዘ ድረስ መቼም ቢሆን ደሴ አይደርስም። ምሽቱን ከጓደኞቹ ጋር የማሳለፍ ፍላጎቱም ሕልም እንጂ እውን ሊሆን አይችልም።

እግዚአብሔርን በመምሰል ወደ ክርስቶስ ሙላት ለመድረስም «አቅጣጫ» ወሳኝ ነው። ስለዚህ በድጋሚ የሚነሳው ጥያቄ «እርስዎስ በመንገዱ ላይ ነዎት ወይ?» የሚል ነው።

ሕይወትዎን በመንፈሱ ብርሃን በቃሉ መስታወት ሲመለከቱት እፍረት ተሰምቶዎታል? እንኳን ክርስቶስን አጠገብዎ ያለውን መልካም የሚሉትን ሰው መምሠል ተስኖዎታል? በየእለቱ ዙሪያዎትን ለሚከቡዎት የፈተና መዓት የሥጋዎትን አስደንጋጭ ዝንባሌ ተመልክተው ፍርሃት ፍርሃት ብሎዎታል? ወይስ የመንገዱን ርቀት፣ የሥጋዎን ዝለት አስበው ልብዎ ርዷል። በፍፁም ተስፋ አይቁርጡ! ጥያቄው መውደቅ መነሳት፣ መድከም መበርታት አይደለም በትክክለኛው አቅጣጫ በእውነተኛው መንገድ ላይ መገኘት ብቻ ነው። በትክክለኛው መንገድ ላይ እስከ ተገዙ ድረስ የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ ይደርሳሉ። እርስዎ ፈቃድዎትን ይስጡ እንጂ ሰጉዞ ኃይልን የሚሰጥዎት የጠራዎት በመንገዱም ፍፃሜ ላይ ሊያከብርዎት የሚጠብቆት ጌታ ነው። እርሱ ራሱ በዚህ መንገድ አልፏልና እያንዳንዱን ስሜትዎን ይረዳል። ድካሞትንም ያግዛል።

ይህን ጉዞ በድል የሚጨርሱት በአቅማቸው የሚመኩ፣ በራሳቸው የቆሙ የሚመስላቸው ኃያላንንና ብርቱዎች ሳይሆኑ ድካማቸውን አውቀው በመንገዱ ላይ ሆነው ጌታን የሚጠባበቁ አማኞች ናቸው። እንዲህ ተብሎ እንደተፃፈ፦

> *«እግዚአብሔር የዘላለም አምላክ የምድር ዳርቻ ፈጣሪ ነው። አይደክምም አይታክትምም ማስተዋሉም አይመረመርም። ለደከማ ኃይልን ይሰጣል፣ ጉልበት ለሌለውም ብርታትን ይጨምራል። ብላቴኖች ይደክማሉ ይታክቱማል፣ ጎበዛዝትም ፈጽሞ ይወድቃሉ፣ እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ ግን ኃይላቸውን ያድሳሉ እንደ ንሥር በክንፍ ይወጣሉ፣ ይሮጣሉ፣ አይታክቱም ይሄዳሉ አይደክሙም።»* ኢሳ. 40:28-31

ስለዚህ በመንገዱ ላይ ይሁኑ እንጂ ስለመድረስም አይጨነቁ እንኳን እርስዎና ያ የወንጌል አርበኛ ጳውሎስ እንኳ ክርስቶስን ስለመምሰል ሲጽፍ፦

> *«ይህን ሁሉ አግኝቻለሁ ወይም ፍፁም ሆኛለሁ ማለት አይደለም። . . . ወንድሞች ሆይ እኔ እንደያዝኩት አድርጌ ራሴን አልቆጥርም ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ ከኋላዬ ያለውን እየረሳሁ ከፊቴ ወዳለው እዘረጋለሁ።»* ፊሊ. 3:12

ይሰን የለ? ከኋላ ያለውን እየረሱ ከፊት ያለውን ለመያዝ መዘርጋት የመንገደኛ ባሕሪ፣ የተጓዥ ተግባር ነው። ስለዚህ የመጨረስን ራእይ ሰንቀው የዛሬን ድርሻ ይሩጡ ቢደክሙም እንኳ ያዝግሙ። ያም ቢሳንዎት በዳዲም ሆነ በእንፋቅቅ ይሳቡ። መንገዱን ሙጥኝ ይበሉ። የመንገዱ ሰው ይሁኑ። መንገዱ ወደ ሕይወት ሙላት የሚያደርሰው ኢየሱስ ክርስቶስ ነውና ያደርሶታል።

አንድ መንገድ ብቻ ባለበት የመሳት እድል አነስተኛ ነው። መንገዶች በበዙበት ግን ጉዞ ከመጀመሩ በፊት ቆም ብሎ ማሰብና ማስተዋል ይጠይቃል። ያለን ዕድሜ ውስን ነውና በአያንዳንዱ መንገድ ላይ ዳር ድረስ እየሄድን አጣርተን መመለስ አይቻልምና በየመንታ መንገዱ መቆም፣ መጠየቅ፣ ማወቅና በትክክለኛው ጎዳና መሄድ ግድ ይላል። ለዚህ ነው ነቢዩ :-

> *«እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በመንገድ ላይ ቁሙ ተመልከቱም የቀደመችውንም መንገድ ጠይቁ መልካሚቱ መንገድ ወዴት እንደሆነች እወቁ በእርስዋም ላይ ሂዱ ለነፍሳችሁም እረፍት ታገኛላችሁ . . . .።»* ኤር. 6:16

ያለው።

ጥንት «መንገዶች ሁሉ ወደሮም ይወስዳሉ» ይባል ነበረና ዛሬም መንገዶች ሁሉ እግዚአብሔርን ወደ መምሰል ያደርሳሉ

ብሰን ካሰብን በእርግጥ ተሳስተናል። ወደዚያ የሚያደርሰው መንገዱ አንድ ብቻ ነው።

እግዚአብሔርን መምሰል ማለት ድካም የሌለበት ከስህተት የፀዳ ውድቀት የማይነካው ሰው መሆን ማለት አይደለም። ምንም እንኳን የከበረ መዝገብ እርሱም የእግዚአብሔር ሕይወት በውስጣችን ቢኖርም ይህ ሕይወት ያደረበት የሸክላ አቃ እርሱም ሥጋችን እስካለ ድረስ መድከም የማይቀር ነው። ከሸክላ አቃ የተቀዳ ውሃ አስር ንፁህ ቢሆን ሸክላ ሸክላ ማለቱ እንደማይቀር ሁሉ በሥጋ አካል እስካለን ድረስ የሥጋ ሕይወታችን ተፈጥሮ መንፀባረቁ አይቀርም። ሆኖም የመንገዱ ሰዎች ከሆንን በሕይወት ይዋጣል እንጂ ፈጽሞ አይውጠንም። ይህንንም እውነት ጳውሎስ ከልምምዱ ሲያካፍለን እንዲህ ብሎ ነበር፡-

> *«ነገር ግን የኃይሉ ታላቅነት ከእግዚአብሔር እንጂ ከእኛ አንዳይሆን ይህ መዝገብ በሸክላ ዕቃ ውስጥ አለን በሁሉ እንገፋለን እንጂ አንጨነቅም፤ እናመነታለን እንጂ ተስፋ አንቆርጥም፤ እንሰደዳለን እንጂ አንጣልም፤ እንወድቃለን እንጂ አንጠፋም። የኢየሱስ ሕይወት ደግሞ በሥጋችን ይገለጥ ዘንድ ሁል ጊዜ የኢየሱስን መሞት በሥጋችን ተሸክመን እንዞራለን።» 2ቆሮ.4፡7-10*

እግዚአብሔርን በመምሰል ጎዳና ትልቁ ቁምነገር በመንገዱ ላይ መገኘት እንጂ የፍፁምነት ጉዳይ እንዳልሆነ ከዳዊት ታሪክ በላይ ምሥክር ሊቀርብ አይችልም። እግዚአብሔር «ልቡ ልቤን ይመስላል» ያለው ዳዊት በሕይወት ዘመኑ ብዙ ድካሞችና በርካታ ውድቀቶች እንደነበሩበት መጽሐፍ ቅዱስ ሳይሸሽግ ይተርክልናል። በእስራኤል ላይ ንጉሥ እንዳይሆን እግዚአብሔር የናቀው ሳኦል እንኳ የዳዊትን ያህል ስህተት የፈፀመ አይመስልም። ነገር ግን የመንገዱ ሰው አልነበረምና ፍፃሜው በውርደት ተደመደመ። ከብሳቴናነቱ ዘመን አንስቶ እግዚአብሔርን በመምሰል ጎዳና የተጓዘው ዳዊት ግን የመውደቅ የመነሳት ታሪክ ቢኖረውም የመንገዱ ሰው ነበርና

በሕይወት ዘመኑ እግዚአብሔርን ስለመምሰሉ ተመስክሮለት በፍፃሜውም እድሜን ባለጠግነትንና ክብርን ጠግቦ አንቀላፋ።

እያልን ያለነው ዋና ቁም ነገር ይህ ነው በብርቱ ሊያሳስበን የሚገባው በመንገድ ላይ ያጠፋነው ጊዜ ወይም የሸፈንነው የርቀት መጠን ሳይሆን ኢየሱስ ክርስቶስ በመረቀው አውራ ጎዳና ላይ እየተጓዝን መሆናችን ነው። የመንገዱ ሰዎች ከሆንን በእርሱ ረድኤት እንደርሳለንና። መንገዱም በክርስቶስ ኢየሱስ የተገለጠው የዘላለም ሕይወት ነው።

የዘላለም ሕይወት

ማንኛውንም እውነት በተግባር ወደ መተርጎም ከመግባታችን በፊት የወደፊት ልምምዳችንን የምንገነባበትን መሠረት መጣል የግድ አስፈላጊ ነው።

እግዚአብሔርን መምሰል በኑሮ የሚገለጥ በተግባር የሚታይ የሕይወት ልምምድ ቢሆንም በውጭ የማይታይ መሠረት አለው። መሠረት የሌለው ቤት ውሉ አድሮ እንደሚፈርስ ሁሉ እግዚአብሔርን የመምሰል ልምምዳችንም በእግዚአብሔር ቃል ጽኑ መሠረት ላይ የቆመ መሆን ይኖርበታል። አለዚያ የአንድ ሰሞን ሞቅታ እንጂ ዘላቂ እውነታ ሊሆን አይችልም።

እግዚአብሔር ዓለም ሳይፈጠር አስቀድሞ በዘላለም ዘመናት ውስጥ አንድ ተስፋ ሰጠ። ተስፋው የተሰጠው ለሰው ልጆች ቢሆንም እንኳን ሰው ገና ባለመፈጠሩ ተስፋው በተወካዩ ተሰጠ። ከሥላሴ አካላት መካከል ሰውን ሊወክል የሚችል ወደፊት ሰው ይሆን ዘንድ የተወሰነለት ወልድ ስለነበር በእርሱ እጅ ተስፋው ተሰጠ። ይህንን በጥንት ዘላለም ውስጥ የተስናወነ

ትዕይንት ሐዋርያው ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ መረዳት እንዲህ በማለት ያስቀምጠዋል፦

> «... ስለዚህም ሕይወት የማይዋሽ እግዚአብሔር ከዘላለም ዘመናት በፊት ተስፋ ሰጠ ...::» ቲቶ 1:2
>
> «... ይህም ፀጋ ከዘላለም ዘመናት በፊት በክርስቶስ ኢየሱስ ተሰጠን . . . አሁን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ታይቷል እርሱ ሞትን ሽሯልና . . . ሕይወትንና አለመጥፋትን ወደ ብርሃን አውጥቷል» 2ጢሞ. 1:10

በእነዚህ ሁለት ክፍሎች በጉልህ እንደምናየው ተስፋው «ሕይወት» ሲሆን የተሰጠውም «በክርስቶስ ኢየሱስ» በኩል ነው:: ይህም ሕይወት በአማርኛ «የዘላለም ሕይወት» ብለን የምንጠራው ነው::

«ሶይኔ» በተሰኘው የግሪክ የገበያ ቋንቋም ሆነ «ክላሲካል» በሚባለው የሥነ-ጽሑፍ ቋንቋ «ሕይወት» የሚለው ቃል ብዙ ስያሜዎች አሉት:: ታዲያ ወደዚህ ውስብስብ ሥራ ውስጥ ከመግባቴ በፊት የግሪክ ቋንቋ መሣይም መሆኔን መናዘዝ ይኖርብኛል:: ምናልባት ከአንባቢዎቼ አንዱ «መሣይም ከሆንክ ታዲያ አርፈህ አትቀመጥም?» ይለኝ ይሆናል:: ሆኖም በዚህ ደረጃ ለመመርመር የገድ የቋንቋው ሊቅ መሆን የሚያስፈልግ አይመስለኝም:: እንደ አንድ ተራ ሰው ሊቃውንቱ የፃፉትን መመልከት በራሱ ዕውቀት ነውና ከተለያዩ የታመኑ መጽሐፍት የተሰባሰቡትን መረጃዎች በጥቂቱ እንቃኝ::

<u>የዘላለም ሕይወት ምንድን ነው?</u>

የዘላለም ሕይወት የሚለው ቃል የሁለት የተለያዩ ቃሎች ቅንብር እንጂ አንድ ወጥ ቃል አይደለም:: እነዚህም ሁለት ቃሎች በተናጠል የየራሳቸው ፍቺ አላቸው:: ዘላለም፣ ዘመንን፣ ሕይወት ደግሞ የመኖር ኃይልን ያመለክታሉ::

ከዚህ በመነሳት ማንም ሰው «የዘላለም ሕይወት» የሚለውን ቃል ሲሰማ ፈጥኖ ወደ አእምሮው የሚመጣው መረዳት ከሞት በኋላ ለዘላለም መኖር፣ መጨረሻ ለሌለው ለማያልቅ ዘመን መኖር እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም::

መንፈስ ቅዱስ የአዲስ ኪዳን መጽሐፍትን እውን ለማድረግ የተጠቀመባቸው የአዲስ ኪዳን ፀሐፍት፦«ሕይወት» የሚለውን ሃሳብ ለመግለጽ አሥራ አንድ የግሪክ ቃላቶችን ተጠቅመዋል:: እነርሱም (ሶኬይ፣ ቢዮስ፣ ቢዮቲካስ፣ ቢዮሰሲ፣ ኦኽሱክስ፣ ዛእ፣ ዘአፖዮአ፣ አጎጌይ፣ ኑይማ እና ዞዊ) ናቸው::[18] እነዚህን በአዲስ ኪዳን ውስጥ ብቻ 183 ጊዜ የተጠቀሱ ስያሜዎችን በሙሉ ታዋቂው የንጉሥ ጀምስ የእንግሊዝኛ ትርጉም (KJV) «ሕይወት» ብሎ የተረጎማቸው ሲሆን ከዚህ የእንግሊዘኛ ትርጉም ጋር ተቀራራቢ የሆነው የቀድሞው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ፦

- ነፍስ፣
- ኑሮ፣
- የሕይወት ዘመን፣
- ትዳር፣
- ምድራዊ ሕይወት፣
- አነዋንዋር፣
- በሕይወት መኖር፣
- ሕያው መሆን፣
- አካሄድ፣
- እስትንፋስ ወይም ትንፋሽ

በማለት ተርጉሟቸዋል::[19]

ሆኖም በዚህ ውስጥ አንድ ልብ ልንለው የሚገባ ቁም ነገር ሕይወትን ለመግለጥ ሥራ ላይ የዋሉት አሥሩም የግሪክ ስያሜዎች ባብዛኛው ከሥጋ ሕይወት፣ ከምድራዊ ኑሮና አኗኗር ጋር የተቆራኙ ሲሆኑ የእግዚአብሔርን ሕይወት ለመግለጥ በስፋት ሥራ ላይ የዋለው አንድ ቃል «ዞዊ» የተሰኘው ብቻ ነው። የተቀሩት አሥሩ ቃላት በአዲስ ኪዳን መፃሕፍት ውስጥ 51 ጊዜ የተጠቀሱ ሲሆን ከጠቅላላው 183 ድግግሞሽ ውስጥ 132ቱን የሸፈነው «ዞዊ» የተሰኘው የግሪክ ቃል ነው። ቃሉ ዘላለማዊ ሕይወትን፣ መንፈሳዊ ሕይወትን፣ የእግዚአብሔር ሕይወትን፣ እውነተኛ ሕይወትን፣ የማያልፍ ሕይወትን፣ የማይሞት፣ የማይጠፋና የማይለወጥ ሕይወትን ባጠቃላይ ሰው ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን የሚያገኘውንና ከሰማይ የተገለጠውን ሕይወት ለማመልከት ሥራ ላይ ውሏል። እንጂ የትኛውም ፀሐፊ አንድም ቦታ ምድራዊ ሕይወትን ለመግለጥ አልተጠቀመበትም። ከዚህ በመነሳት «ዞዊ» ማለት «የእግዚአብሔር ሕይወት» ማለት ነው ወደሚለው ድምዳሜ ለመምጣት እንችላለን።[18]

እየተረዳነው ወዳለነው «የዘላለም ሕይወት» ስያሜ ስንመጣም በግሪኩ «ኤዮኒያስ ዞዊ» የሚል መጠሪያ አንዳለው እንመለከታለን። ይህም ሁለት ቃል ሲነጣጠል «ኤዮኒዮን» የዘላለም ዘመን ወይም የማያልቅ ዘመን ማለት ሲሆን፣ «ዞዊ» ደግሞ ከላይ እንዳየነው የእግዚአብሔርን ሕይወት የሚያመለክት ነው።

እንግዲህ ልንፈታው የምንፈልገው የቋንቋ ቅብብሎሽ የፈጠረው የመረዳት እክል ይህ ነው። በግሪክ ቋንቋ የእግዚአብሔርን ሕይወት ለመግለጥ ራሱን ችሎ የተሰየመ ቃል መኖሩን

ሳናውቅ ሕይወትን በገዛ ቋንቋችን «መኖር» ብለን ማለቂያ ከሌለው ዘመን ጋር በማጣመር «የዘላለም ሕይወትን» ዘላለም መኖር በማለት ልንተረጉመው ተገደናል። «የዘላለም ሕይወት» «ኤዮንያስ ዞዊ» ግን የመኖርን ዕድሜ ዘመን ለመግለጽ የተፃፈ ቃል ሳይሆን ከምድር የተለየ፣ ሰማያዊና መንፈሳዊ የሆነ፣ የማይሞትና የማይጠፋ፣ ያለምንም ድጋፍ በራሱ ኃይል ለዘላለም ክብርና ደምቆ የሚኖር የሕይወት ዓይነትንና ማንነትን ለመግለጽ የዋለ ቃል ነው። ስለዚህ የዘላለም ሕይወት የእግዚአብሔርን ሕይወት ለመግለጽ ሥራ ላይ ከዋሉ በርካታ ስያሜዎች መካከል አንዱ መሆኑን ልናውቅ ይገባል።

በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕይወት በተለዋጭ ከተጠራባቸው ስያሜዎች መካከል

- ሕይወት ዮሐ. 1:4
- የብርሃን ሕይወት ዮሐ. 8:12
- እውነተኛ ሕይወት 1ጢሞ. 6:18
- የማይጠፋ ሕይወት 2ጢሞ. 1:11
- የማይሞት ሕይወት 1ጢሞ. 6:16
- የማያልፍ ሕይወት ዕብ. 7:16
- የእግዚአብሔር ሕይወት ኤፌ. 4:18
- ማለቂያ የሌለው ሕይወት ዮሐ. 3:15
- የዘላለም ሕይወት ዮሐ. 3:16
- የትንሳኤ ሕይወት ዮሐ. 11:25
- መንፈሳዊ ሕይወት ዮሐ. 6:63

የሚሉት ይገኙበታል።

ለዚህ የቃላት ትርጓሜ ትኩረት የሰጠነው ያለ ምክንያት አይደለም። ይህን አንድ ቃል በትክክል መረዳታችን በእምነታችንና በመንፈሳዊ ሕይወት እድገታችን ላይ የሚያመጣው በጎ ተጽዕኖ ቀላል ስላልሆነ ነው።

ይህን ቃል በተመለከተ በ1985 ዓ.ም ከአገር ውጪ ሳገለግል የገጠመኝን እንደ ምሳሌ ላንሳ። ከአገልግሎት በኋላ ወደ አንድ የቤተክርስቲያን መሪ ቤት ተጋብዤ ሄድኩ። በቤቱም አንድ ወጣት ተዋወቅሁ። የጋበዘኝ ሰው ሥራ ፍለጋ በቅርብ ከአገር ቤት የመጣ ዘመዱ እንደሆነና ጌታንም እንደማያውቅ አስቀድሞ አጫውቶኛል። ይህ እንግዳ በወቅቱ የ23 ዓመት ወጣት ነበር። ይህ ወጣት ሲቪል ኢንጅነር ነው። ስድስት የውጭ ቋንቋዎችን ይናገራል። በሦስቱ ያስተምራል። በዚህ ጥቂት አድሜው ያልሞከረው ነገር የለም ማለት ይቻላል። ልቤ በጣም ወደደው። «ይህ ሰው ቢድን እኮ!» አልኩ በውስጤ። ከዚያም ይዤው ወጥቼ ስለ ጌታ ልመሰክርለት ወሰንኩና ተያይዘን የእግር ጉዞ ጀመርን። ረዥም መንገድ በእግራችን ከተጓዝን በኋላ አንድ ቦታ አረፍ አልን። እኔም ስለ ዘላለም ሕይወት ብነግረው ፈቃደኛ እንደሆነ ጠየቅኩት። ፈቃደኝነቱን ከገለጠልኝ በኋላ በተመሰጠ ይሰማኝ ጀመር። እኔም መመስከሬን ቀጠልኩ። ድንገት በመሃል «ጥያቄ መጠየቅ ይቻላል?» በማለት አቋረጠኝ። እኔም «ምንም ችግር የለም የፈለከውን ጥያቄ መጠየቅ ትችላለህ» አልኩት። ወዲያው ቀበል አደረገና «የዘላለም ሕይወት ያልከውን ለመግባት ተስማምቻለሁ ነገር ግን ከደበረኝ መውጣት እችላለሁ?» ብሎኝ አረፈው። በመጀመሪያ ክት ብዬ ሳቅኩና ከተረጋጋሁ በኋላ ይህን ዓይነቱን ጥያቄ እንዴት ሊያነሳ እንደቻለ ጠየቅሁት። «እንዴ ምን ነካህ እሰከ አሁን የኖርኩት 23 ዓመት እንኳን

ረዝሞብኝ ሰልችቶኛል። ታዲያ ለዘላለም እንዴት ነው የሚኖረው? አይደብርም? ኧሃ. . . እንዲህ ዓይነት ከባድ ውሳኔ ውስጥ መውጫ መኖሩን ሳላረጋግጥ መግባት አልፈልግም» አለኝ።

የዘላለም ሕይወት ቀኑ አልመሸ ብሎት እየተዟዟረ ሌሊቱ አልነጋ ብሎት ጣራ እየቆጠረ እንደሚኖርበት የአሁኑ ኑሮው እንዳመሰሰውና የዘመኑ ርዝመት አልገፋ ብሎ እንዳስጨነቀው በመረዳት ምስክርነቴን ቀጠልሁ። ያ ሰው ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ጌታን ተቀብሎ አሁንም በጌታ ቤት አለ።

ይህን ታሪክ ያነሳሁት ያለ ምክንያት አይደለም። «የዘላለም ሕይወት» የሚለው መጠሪያ የሚያስተላልፈውን መልእክት በጥሞና እንድናየው ነው። አንዳንዶቻችን የዘላለም ሕይወት ብለን የምናስበውም ሆነ ለሌሎች የምንሰለው በደንብ ካሰብነው ከሲያል የማይሻል ነገር ነው። ለነገሩማ ሰይጣን፤ መላእክቱና የተከተሉአቸው ሰዎች ሁሉ ለዘላለም ይኖሩ የለ?[19]

ጥያቄው የት እንዴት በምን ዓይነት ሁኔታ ከማን ጋር መኖር የሚለው እንጂ መጨረሻ ለሌለው ዘመን የመኖር ጉዳይ አይደለም።

ከላይ እንዳየነው የአዲስ ኪዳን ፀሐፊዎች የዘላለምን «ሕይወት» ለመግለጽ የተጠቀሙበት ቃል «ዞዊ» የሚል ሲሆን የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ሕይወት ነው።

ይህ ስያሜ በመኖር ዘመን ላይ ብቻ ሳይሆን በሕይወት ማንነትና ዓይነት ላይ ያተኩራል። ስለዚህ የዘላለም ሕይወት ለዘላለም እንደ እግዚአብሔር መኖር እንጂ እንዲሁ ለዘላለም መኖር ማለት አይደለም። የዘላለም ሕይወት ዘመን ሳይሆን በሥጋ የተገለጠ ሕይወት መሆኑን ዮሐንስ በመልእክቱ እንዲህ

ገልፆታል፦

«... እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው።» 1ዮሐ. 20

የዘላለም ሕይወት ዘመን የመቁጠር ጉዳይ ሣይሆን የእግዚአብሔርን ሕይወት በመካፈል ባሕሪይውንና ክብሩን የመከፈልና የመገለጥ ጉዳይ ነው።

ጌታ ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የዘላለምን ሕይወት ፍቺ እንዲህ በማለት ገልጦታል፦ «እውነተኛ አምላክ የሆንኸውን አንተንና የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት።» ዮሐ. 17:3

ባጭር ቃል የዘላለም ሕይወት የራሱ የእግዚአብሔር ሕይወት ነው። ዓለም ሳይፈጠር በፊት ለሰው ልጆች በክርስቶስ በኩል የሰጠው፣ በዘመን መጨረሻ በሞቱና በትንሣኤው በመንፈስ ቅዱስም መሰጠት ሊፈጽም የጀመረው፣ በዳግም ምጽአቱ ወደ በመላት ሊገልጠው የገባው ዘላለማዊ ተስፋ ነው።

እንዲህ እግዚአብሔርን የመምሰል ሚስጥር የታመቀው በዚህ ሕይወት ውስጥ ነው። ይህ ሕይወት ያልተገለጠለት ሰው እግዚአብሔርን መምሰል ምን እንደሆነ ሊያውቅ ብሎም ሊለማመደው አይችልም።

የዘላለም ሕይወት ከሞት በኋላ የምናገኘው ሳይሆን ባመንን ጊዜ በመንፈሳችን የተካፈልነው፣ ዘላለም የምንኖርበት ብቻ ሣይሆን ከእግዚአብሔር ጋር ሕይወትን እየተካፈልን፣ እግዚአብሔርን እየመሰልን የምንኖርበት ሕይወት ነው።

በሰው ልጆች ታሪክ ዓለማችን ለመጀመያ ጊዜ ይህ ሕይወት ተገልጦ ያየችው ክርስቶስ በምድር በተመላለሰባቸው ወራት ነበር። በክርስቶስ የተገለጠው ሕይወት እንጂ ኃይማኖት

አልነበረም። አዲስ ኃይማኖት የሚያስፈልግበትም ምክንያት አልነበረም እግዚአብሔር ራሱ የመሠረተው የእስራኤል ኃይማኖት ነበረ። ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣበት ምክንያት በአይሁድ ኃይማኖት ውስጥ የተሰጠውን የሕይወት ተስፋ ለመፈጸም እንጂ አዲስ ኃይማኖት ለመመሥረት አልነበረም። ይህ ሕይወት በተገለጠ ጊዜ ቀንደኛ ተቃዋሚዎች ሆነው የተነሱት የሕወት ተስፋ ያልገባቸው የኃይማኖት ሰዎች ነበሩ።

መቼም ኢየሱስ እንደ ኃይማኖት የሚጠላው፣ ኃይማኖትም እንደ ኢየሱስ የሚጠላው ያለ አይመስለኝም። ይህንንም ለማረጋገጥ ሩቅ መሄድ አያስፈልግም። ወንጌላትን ስናነብ በሕይወት እና በኃይማኖት መካከል የተደረገውን ግጭትና ፍልሚያ እንመለከታለን። ይህም ግጭት እየጦዘ ሄዶ እስከ መስቀል ደርሶአል። በመስቀል ላይ ከእግዚአብሔር ሕይወት የራቀ የሥጋ ኃይማኖት በእግዚአብሔር ስም እግዚአብሔርን ከመስቀል እንደማይመለስ ተረጋግጦአል።[20]

አሁን ግን እግዚአብሔር በእውነትና በመንፈስ እናመልከው ዘንድ ፈልጎ በሌሎች ዘመናት የሰው ልጆች ያልተለማመዱትን አዲስ ሕይወት ገልጦልናል።

ይህ ለማያዊ ሕይወት በክርስቶስ የምድር ኑሮ በተገለጠ ጊዜ በቅርበት የተከታተሉት በኃይማኖተኞች ሚዛን እዚህ ግቡ የማይባሉት የኢየሱስ ደቀመዛሙርት በእርሱ ያዩትን ሕይወት ከዓመታት በኋላ ለተከታዮቻቸው እንዲህ በማለት ሊገልፁት ምክረዋል።

«ስለ ሕይወት ቃል ከመጀመሪያው የነበረውንና የሰማነውን፣ በዓይኖቻችንም ያየነውን፣ የተመለከትነውንም፣ እጆቻችንም የዳሰሱትን እናወራለን። ሕይወት ተገለጠ አይተንማል እንመሰክርማለን። ስለ ዘንድ የነበረውንም ለእኛም የተገለጠውን የዘላለምን ሕይወት እናወራላችኋለን ...» 1ዮሐ. 1:1-2

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣው ይህን ሕይወት በማሳየት ሊያስደንቀን ሣይሆን እኛም እርሱን መስለን እንኖር ዘንድ ሊያከፍለንና ሊያለማምደን ነው። ለዚህ ነው ተከታዮቹ እርሱ ያደረጋቸውን ነገሮች እንዲያደርጉ ያበረታታ የነበረው።[21]

ይህ ሕይወት በጌታ የምድር ኑሮ በገሃድ የተገለጠ ቢሆንም እንኳ ያወቁትና የተረዱት ግን ጥቂቶች ነበሩ። በመልክ ለሚፈርዱ ኢየሱስ የመጣበት ውጪያዊ ገጽታ የሚያሰናክል ነበርና። የተገለጠላቸው ግን ከተናቀው ፊቱና ከገረጣው ቁርበቱ ባሻገር ጠልቀው ማየት ሆኖላቸው ስለማንነቱ መስክረዋል። ለዚህም እንደ ምሣሌ ልንጠቅሰው የምንችለው የዮና ልጅ ስምዖን ጴጥሮስ ነው።

«ሰዎች እኔ ማን እንደሆንሁ ይላሉ?» በማለት ሲጠይቅ ደቀ መዛሙርት ስለ ኢየሱስ ማንነት የሕዝቡን አስተያየት ሲዘረዝሩ ከቆዩ በኋላ «እናንተስ እኔ ማን እንደሆንኩ ትላላችሁ?» ለሚለው ድንገተኛና አስደንጋጭ ጥያቄ በዝምታ ተውጠው በነበሩበት ሰዓት።

> *«አንተማ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ»*

በማለት ዝምታውን ለሰበረው ጴጥሮስ የጌታ ፈጣን መልስ

> *«የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ ይህንን የሰማዩ አባቴ እንጂ ሥጋና ደም አልገለጠልህምና ብፁህ ነህ. . . . አንተ ጴጥሮስ ነህ በዚህችም ዓለት ላይ ቤተክርስቲያኔን እሠራለሁ የገሃነምም ደጆችም አይችሏትም።»* *ማቴ. 16:13-18*

የሚል ነበር።

ይህ አባባል ኢየሱስን ለማወቅ ሰማያዊ መገለጥ እንደሚያስፈልግ የሚያረጋግጥልን ሲሆን ያ መረዳትም ለእምነት ጽኑ መሠረት መሆኑንም ያሳየናል። ጴጥሮስ ይህ ስለተገለጠለት ነበር በቃሉ ተሰናክለው ብዙዎች ጥለውት

ሲሄዱ ጌታ ደቀመዛሙርቱን ሳይቀር «እናንተስ ልትሄዱ ትወዳላችሁን?» በማለት ሲጠይቅ

> *«ጌታ ሆይ ከአንተ ወደ ማን እንሄዳለን? አንተ የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ። እኛስ አንተ ክርስቶስ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆንህ አምነናል አውቀንማል . . . ።»* *ዮሐ.6:67*

ያለው።

በፍፃሜ ላይ የተገለጠው የስምዖን ጴጥሮስና የአስቆሮቱ ይሁዳ መሠረታዊ ልዩነትም ስለ ኢየሱስ ማንነት በነበራቸው መረዳት ላይ የተመሠረተ እንደነበር ከፍፃሜያቸው ለማየት ይቻላል።

ጌታን በተከተሉበት እድሜ፣ ጌታ ታልፎ በተሰጠበት ጊዜ በገጠማቸው ፈተና በመውደቅ ተመሣሣይ የነበሩት ጴጥሮስና ይሁዳ የውስጣቸው ልዩነት በገሃድ የተገለጠው በመጨረሻው ሰዓት ላይ ነበር። ለጴጥሮስ ኢየሱስ «ሊመጣ ያለው መሲህ፣ የሕይወት ቃል፣ የእግዚአብሔር ልጅ» ሲሆን።[22] ለይሁዳ ግን አንድ «ወንጀል የሌለበት ንፁህ ሰው ነበር» ማቴ.27:4 ። ይህ ስለ ኢየሱስ የነበራቸው የተለያየ ግንዛቤ አንዱን በንስሃ ወደ ሕይወት ሲመልሰው ሌላውን ግን በፀፀት ወደ ዘላለም ጥፋት መርቶታል።

ከዚህ የምንረዳው ሕይወት የሆነው ክርስቶስ ሊታወቅ የሚችለው ከመንፈስ ቅዱስ በሚገኝ መገለጥ መሆኑንና ይህም መረዳት በማንኛውም ማዕበል ውስጥ አጽንቶ የሚያቆም የሕይወት መሠረት መሆኑን ነው። ጌታ ራሱ፡ -

> *«ስለ ብዙ በቀር ወልድን የሚያውቅ ማንም የለም። ከወለድ በቀር ወልድም ሊገለጥለት ከሚፈቅድ በቀር አብን የሚያውቅ የለም።»* *ማቴ. 11:27*

ብሎ የለ?

ይህ ሕይወት ራሱ ራሱን የሚገልጥ ብርሃን በውስጡ መኖሩ አለ። ለዚህ ነው ዮሐንስ፦

«በእርሱም ሕይወት ነበረች ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች»

ካለ በኋላ፡ -

«ብርሃንም በጨለማ ይበራል ጨለማም አላሸነፈውም።»

በማለት ሕይወትን የሚገልጥ ብርሃን በዚሁ ሕይወት ውስጥ መኖሩን የሚናገረው። እግዚአብሔርን ያለ እግዚአብሔር ሕይወት ማወቅ አይቻልምና።

«ለዘላለምም ሕይወት ይህች ናት፥ አንተን የእውነተኛ አምላክ የሆንህውን አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት» ዮሐ. 17:3

እኛ ፈቃደኞች ከሆንንና ይህን ሕይወት ለማወቅ ከተዘረጋን እንዳናውቀው (እንዳይበራልን) ማድረግ የሚችል ምንም ዓይነት የጨለማ ወይም ያለማወቅ ኃይል አንደሌለ ይህ ክፍል ያረጋግጥልናል።

እንግዲህ እግዚአብሔርን መምሰል የሚመሠረተው ይህን ዘላለማዊ ሕይወት በማወቅ ላይ ነው።

የእግዚአብሔርን ሕይወት ስለተካፈልን እግዚአብሔር አንሆንም። ፈጽሞ! ነገር ግን ሰው መሆናችን እንዳለ ሆኖ እግዚአብሔርን እንመስላለን፣ እንደ እግዚአብሔርም እንኖራለን፣ እግዚአብሔርን እንገልጣለን እንጂ።

ስለ መምሰል ስናስብ በአካል ያላየነውን እግዚአብሔርን ይቅርና በዙሪያችን ያሉ በየዕለቱ የምናያቸውን ሞዴሎች እንኳ መምሰል ምን ያህል አድካሚና አሰልቺ እንደሆነ የምናውቀው ጉዳይ ነው። ተዋናይ እንኳን ከማንነቱ ውጭ የሆነውን ገፀ ባሕሪ ተላብሶ ለመጫወት እና ለመድረክ ዕድሜ ያህል እንኳ ለመምሰል ብዙ ይጠበባል። ታዲያ ሁለንተናው እኛን የሚመስለውን ሰው ለመምሰል እንዲህ ካስቸገረ እንዴት

አድርገን ነው እግዚአብሔርን ለመምሰል የምናስበው? እምን በሥጋ ሕይወት ይህ ፈጽሞ የሚታሰብ አይደለም። የእግዚአብሔር ሕይወት ከሥጋ ሕይወታችን ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል ከፍ ያለና የራቀ ነውና።

የሥጋ ሕይወታችን እግዚአብሔርን እንዲመስል ከማስለመድ እንሰላን ፊደል ማስተማር ላይቀል አይቀርም። በዓለማችን ያሉ በተለያየ ዘመን የተነሱ ኃይማኖቶች ሞክረውት ያልተሳካላቸው ነገር ቢኖር ይህ ጉዳይ ነው። በውስጥ ሊመስሉት ስላልቻሉ የኃይማኖት ካባ ደርበው በውጭ ለመምሰል ጥረዋል።

እግዚአብሔር እንዲሁ በሜዳ አርሱን እንድንመስል አልጠየቀንም። አስቀድሞ እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚያስፈልገውን ሁሉ ሰጥቶናል የሚያስፈልገውም አንድ ነገር ነው። እርሱም የእግዚአብሔር ሕይወት ነው።

«የመለኮቱ ኃይል በገዛ ክብሩና በበጎነቱ የጠራንን በማወቅ ለሕይወትና እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚሆነውን ነገር ሁሉ ስለሰጠን በእግዚአብሔርና በጌታችን በኢየሱስ አውቀት ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ። 2ጴጥ. 1:2-3

እግዚአብሔርን መምሰል እግዚአብሔርን ማስመሰል አይደለም። በመንፈላችን የተካፈልነውን ሕይወት በሥጋ ሰውነታችን በመግለጥ የምንኖረው ኑሮ ነው።

ራሱ የዘላለም ሕይወት የሆነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ያደረገው ይህንኑ ነበር። ሰው ሆኖ ወደ ምድር ከመጣ በኋላ ይህን ሕይወት በሥጋ ሰውነት ገለጠው። እኛም ያመንን ልክ እንደርሱ መምድር አለንና ሕይወትን በመግለጥ አርሱን መምሰል እንችላለን።

ይህ ሕይወት የእግዚአብሔር ሕይወት እንደመሆኑ መጠን በውስጡ የእግዚአብሔር ዘር (ዲ.ኤን.ኤ.) አለበት። እግዚአብሔር የሆነው ሁሉ በዚህ ሕይወት ውስጥ

ተሰውሯል። እንግዲህ ባመንን ጊዜ የተሰጠን ይህ ሕይወት ነው።

> «ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለጠጋ ስለሆነ ከወደደን ከታላቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወትን ሰጠን ...።» ፊሊ. 2:4

ይህን ሕይወት በመካፈላችን ለእውነት በሚሆን ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሣሌ የተፈጠረ አዲስ ሰው በውስጣችን ተፈጥሯል። ሆኖም ይህ ስለሆነ ብቻ እግዚአብሔርን መሰልን ማለት አይደለም። እግዚአብሔርን መምሰል የእግዚአብሔርን ሕይወት ማግኘት ብቻ ሣይሆን ያገኘነውን ሕይወት በኑሮ መግለጥ ነው።

የሕይወት ሕግ

እግዚአብሔርን መምሰል ሕግና ትእዛዛትን የመጠበቅ፣ ሰዎች ያመጣቸውን ደንቦችን እና በዘልማድ የመጡ ወጎችን የማድረግ አለማድረግ ጉዳይ አይደለም። እግዚአብሔርን መምሰል ሕይወትን መግለጥ ነው። ያም ሕይወት በክርስቶስ የተገለጠው የእግዚአብሔር ሕይወት ነው። ይህም ሕይወት የራሱ ሕግ አለው።

ይህን አሳብ ለመረዳት በሕይወት ሕግና በፊደል ሕግ መካከል ያለውን ልዩነት ማየት ይረዳል። እያንዳንዱ ሕያው ፍጥረት የራሱ የሆነ የሕይወት ሕግ አለው። ያን ሕግ የተፈጥሮ ሕግ (ባሕሪ) ብለን ልንጠራው እንችላለን። ማንኛውም ፍጥረት በዚህ ሕግ ውስጥ ሲኖር ሳይነጨነቅ፣ ሳይጠበብ ይፈጽመዋል። የሚከብደው ሕጉን መፈፀም ሳይሆን አለመፈፀም ነው።

ለምሳሌ ንሥር በሰማይ ይበራል፣ ሰው በመሬት ይራመዳል፣ ዓሦች በባሕር ይዋኛሉ። ይህ የሕይወት ሕጋቸው ነው። ንሥር በሰማይ የሚበረው ዓይኑን ከፍቶ ቁልቁል ሲያይ

እየሰቀጠጠው አይደለም፣ ሰውም ሲራመድ መሬቱን የሚረግጠው በመፍራትና በመንቀጥቀጥ አይደለም፣ ዓሦችም በባሕር ሲዋኙ ትንታ እያስቸግራቸውም፣ መታፈን አያስጨንቃቸውም። ለምን? የሚኖሩት በሕይወት (በተፈጥሮ) ሕግ ውስጥ ነዋ።

ነገር ግን ከተፈጥሮአቸው ውጭ የሆነ የጽሑፍ ሕግ ቢወጣና እንዲፈጽሙት ጫና ቢደረግባቸው ያኔ ችግር ይፈጠራል።

ለምሳሌ፦ «ከዛሬ ጀምሮ ንሥሮች በውሃ ውስጥ እንዲዋኙ፣ ሰዎች በአየር እንዲበሩ፣ ዓሦችም በምድር ላይ እንዲንቀሳቀሱ።» የሚል ትእዛዝ ቢወጣ ችግሩ ትእዛዙ ሊፈፀም አለመቻሉ ብቻ ሳይሆን ቢሞከርም ውጤቱ በሞት የሚቋጭ መሆኑ ነው።

ለዚህ ነው ኃጢአት የሕይወቱ (የሥጋ ሕይወት) ሕግ ለሆነው ለሰው በሲና መልካም ሕግ ቢሰጠውም ሊፈጽመውና ሊፀድቅ ያልቻለው። የተሰጠው ሕግ የውስጥ ተፈጥሮው ባሕሪ ሳይሆን በውጭ በድንጋይ ላይ በፊደላት የተቀረፀ ሕግ ስለነበር ሞት አመጣበት እንጂ ወደ ሕይወት ሊመራው አልቻለም።

ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ወደ ምድር የመጣው እንደቀድሞው የተፃፈ ውጪያዊ ሕግ ሊሰጠን ሳይሆን የእግዚአብሔርን ሕይወት ሊያካፍለን ነው።

> «ሕግ በሙሴ ተሰጥቶ ነበርና ጸጋና እውነት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ።»
> ዮሐ. 1:17

ባመንን ጊዜ በጸጋ እውነተኛ ሕይወት ተቀብለናል። የተሰጠንም ሕይወት እንጂ ሕግ አይደለም። ሆኖም በጽሑፍ በዝርዝር የተቀመጡ የፊደል ሕግ የለንምና ሕግ አልባ ነን ስለዚህ እንደልባችን እንኖራለን ማለት አይደለም።

የተሰጠን ሕይወት የራሱ የሆነ የተፈጥሮ ሕግ (ባሕሪ) አለው። ቀደም ሲል ማንኛውም ሕይወት የራሱ የሕይወት ሕግ እንዳለው አንስቻለሁ። ይህም ሕይወት እንዲሁ ነው። የራሱ የሕይወት ሕግ አለው። ይህም ሕግ ከውጭ የመጣ በላያችን ላይ የተጫነ የሚገድል ሕግ ሳይሆን ከውስጥ የሚፈልቅ፣ ያለ ጭንቀት የሚፈፀም፣ የሥጋችንን ጥረት የማይጠይቅ፣ የክርስቶስ ሕይወት ሕግ ነው።

ጳውሎስ ስለዚህ የሕይወት ሕግ በሮም ለነበሩ አማኞች ሲጽፍ፦

> «አንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም። በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛልና።» ሮሜ ፰፡1-2 ብሏል።

አንድንድ ሰዎች የአሪት መጽሐፍት ለብሉይ ኪዳን ሰዎች እንዲፈጽሟቸው የተሰጡ ሕጎች እንደሆኑ ሁሉ የአዲስ ኪዳን መፃሕፍትም ለእኛ እንድንፈጽማቸው የተፃፉልን ሕጎች እንደሆኑ ያስባሉ።

የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ግን አድርግ አታድርግ፣ አትንካ፣ አትቅመስ፣ በሚሉ ሕጎች የተሞሉ መፃሕፍት ሳይሆኑ የእግዚአብሔር ሕይወት የተገለጠባቸው ሰዎች የኖሯቸው፣ የተናገሯቸው እና የፃፏቸው የሕይወት መልእክቶች ናቸው።

መልእክቶቹም በየትኛውም ዘመን የሚኖር ይህ ሕይወት እንዲገለጥበት የሚሻ ሰው ሊለማመዳቸው የሚችልና ምን ያህል ይህ ሕይወት እንደተገለጠበት ራሱን ሊያይ የሚችልባቸው የሕይወት መስተዋቶች እንጂ የሕግ እና የሥርዓት ክምችቶች አይደሉም።

ባሕሪና ክብር

ቀደም ሲል የዘላለም ሕይወት በክርስቶስ የተገለጠ የእግዚአብሔር ሕይወት እንደሆነ ክርስቶስ የሞተውና የተነሳውም እኛ ይህን ሕይወት እንድናገኝና ካገኘንም በኋላ ለፍጥረት ሁሉ በመግለጥ እግዚአብሔር ከዘላለም ዘመናት በፊት የወሰነውን እቅድ እንድንፈጽም መሆኑን ተመልክተናል። አሁን በመቀጠል ሕይወትን መግለጥ ምን ማለት እንደሆነና ይህ መገለጥ እንዴት በዘመን እንደሚከፈል እንመለከታለን።

የእግዚአብሔር ሕይወት አንድ ሕይወት ነው። ነገር ግን ሁለት ገጽታዎች አሉት። በማንኛውም ሣንቲም ወይም ብር ላይ ሁለት ገጽታዎች እንዳሉና የሁለቱም ገጽታዎች መገኘት የገንዘቡን እውነተኛነት እንደሚያረጋግጥልን ሁሉ የእግዚአብሔርም ሕይወት ሁለት ገጽታዎች አሉት። እነዚህን የአንድ ሕይወት ሁለት ገጽታዎች በሌላ የሰው ምሳሌ ለመግለጥ ከመሞከራችን በፊት እግዚአብሔር ራሱ ይህን እውነት ለመግለጥ ለሙሴ የተናገረበትን መንገድ እንመልከት።

ሙሴም እግዚአብሔርን «አባክህ ክብርህን አሳየኝ።» ብሎ ጠየቀ። ጥያቄው ለሰማ ጆሮ ሌላ ጥያቄ የሚጭር ነው። በግብጽ አማልክቶች ላይ አስር መቅሰፍቶች ሲወርዱ፣ የግብጽ አማልክት ሲዋረዱ አይቷል ታድያ ያ የእግዚአብሔር ክብር አልነበረምን? የኤርትራ ባሕር ሲከፈል፣ መራራው ሲጣፍጥ፣ መና ከሰማይ ሲወርድ፣ ከአለት ውሃ ሲፈልቅ አይቷል፣ ያስ የእግዚአብሔር ክብር አልነበረም? ቀን በደመና፣ ሌሊት በእሳት ዐምድ ከፊታቸው ሲሄድ፣ የመገናኛው ድንኳን ተገጣጥሞ ሲያልቅ ደመና ሲሸፍነውና ሕዝቡ ሁሉ ሲሰግድ፣ በሲና ተራራ ላይ እሳት ሲቃጠል የመላእክት መለከት

ሲያስተጋባ፣ የነጎድጓድ ድምጽ ምድርን ሲያናውጥ አይቷል ታዲያ ይህ ሁሉ የእግዚአብሔር ክብር አልነበረም?

ሙሴ ይህን ሁሉ ቢመለከትም የእግዚአብሔር ክብር ለርሱ ከዚህ ሁሉ የላቀ ትርጉም ነበረው። እናም የጠየቀው ተአምራት ማየት ፈልጎ ሳይሆን የእግዚአብሔርን መልክ፣ ክብሩን ለማየት ነው። የእግዚአብሔርም መልስ አንዳች ሚስጥር የሚገልጥ ነውና ቦጥሞና እንመልከተው።

> *«እግዚአብሔርም አንዲህ አለ፦ መልካምነቴን ሁሉ በፊትህ እንዲያልፍ አደርጋለሁ በፊትህም ስሜን እግዚአብሔርን አውጃለሁ ለምምረውም ምህረት አደርጋለሁ ለምራራለትም ርህራሄ አደርጋለሁ። ነገር ግን ማንም እኔን አይቶ መኖር ስለማይችል ፊቴን ማየት አትችልም . . . ከዚያም እግዚአብሔር አንዲህ አለ፦ «ከአጠገቤ ስፍራ አለ አንተም በዓለት ላይ ትቆማለህ ክብሬ በዚያ ሲያልፍ በዓለቱ ስንጥቅ ውስጥ አደርግሃለሁ በዚያን እስክማልፍ ድረስ በእጄ እጋርድሃለሁ ከዚያም እጀን እነሳለሁ ጀርባዬንም ታያለህ ፊቴ ግን መታየት የለበትም።»*
>
> *ዘፀ. 33:18-23*

እግዚአብሔር መንፈስ ነው። መንፈሳዊ መልክ እንዳለው ብናስብም በዚህ ሥፍራ ፊትና ጀርባ የሚለው የሥጋ አካል የሚገለጥበት ዓይነት ፊትና ጀርባ እንዳልሆነ መገመት አያስቸግርም።

በቅድሚያ ልብ ልንለው የሚገባ እውነት እግዚአብሔር «ፊቴ» ያለው ክብሩን ነው። ምክንያቱም ሙሴ «ክብርህን አሳየኝ» አለ እንጂ ፊትህን አሳየኝ አላለም። እግዚአብሔር ግን ግልጽ ሲያደርግለት «ክብሬ ፊቴ ነው ልታየው አትችልም» አለው። በመቀጠልም «መልካምነቴ ሁሉ በፊትህ እንዲያልፍ አደርጋለሁ፣ በፊትህም ስሜን እግዚአብሔርን አውጃለሁ፣ ለምምረውም ምህረት አደርጋለሁ፣ ለምምራለትም ርህራሄ አደርጋለሁ» ካለ በኋላ «ጀርባዬን ታያለህ» ማለቱ «መልካምነቴ፣ የሚታወጅ ስሜ፣ ምህረቴና ርህራሄዬ ሁሉ አሁን ሊታይ የሚችል ጀርባዬ ነው» ማለቱ ይመስላል።

መልካምነቴ፣ ስሙ፣ ምህረቴና ርህራሄው፣ ሊጠቃለል ደግሞ ባሕሪው ተብሎ ሊጠራ ይችላል?

ጌታ ኢየሱስ «ከዓለም ለለጠኸኝ ለዎች ስምህን ገለጥሁላቸው»[23] ሲል በሦስት አመት ተኩል አገልግሎቱ ክብሩን ትቶ በመጣው ስብዕናው ውስጥ የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ባሕሪ ማመልከቱ ነው። ተአምራቶቹና ፈውሶቹ ሁሉ የፍቅር፣ የርህራሄ፣ የደግነት፣ በሰው ስቃይ የመለቃየትና በሰው እረፍት የማረፍ ባሕሪያቱ ነፀብራቅ ነበሩና።

ባጭር ቃል በዚህ ክፍል እንደምናየው የእግዚአብሔር ሕይወት ሁለት ገጽታ አለው፣ ፊትና ጀርባ አለው። ይህም የግዑዙ ፍጥረት ፊትና ጀርባ ዓይነት ሳይሆን ሁለት ገጽታን ለማመልከት የተሰጠ ገላጭ ምሳሌ አድርገን ማሰብ እንችላለን።

እነዚህ ሁለት ገጽታዎችም በዚሁ ክፍል እንዳየነው ክብርና ባሕሪ ናቸው። ለዚህ በቂ ማስረጃ የሚሆነን የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አመጣጥ ነው። ጌታ ሁለቱ አመጣጦች እንዳሉት የታወቀ ነው። አንደኛው በድካም፣ በውርደት፣ ለስቃይና ለሞት የመጣው የመጀመሪያው መገለጡ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በታላቅ ክብርና በአስደናቂ ግርማ ከሰማይ የሚመጣበት ነው። አመጣጦቹን በዝርዝር ከማየታችን በፊት ግን ማንነቱን ለመመልከት ቅድሚያ እንስጥ።

የዕብራውያን መልእክት ፀሐፊ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት ሲጽፍ፦

> *«ሐረሱ የእግዚአብሔር ክብር ነፀብራቅና የባሕርዩ ትክክለኛ ምሳሌ» ነው ይለናል። ዕብ. 1:3*

በዚህ አባባል ውስጥ ሁለት ገጽታዎችን እንመለከታለን።

1. የእግዚአብሔር ክብር፡- ነፀብራቅ
2. የእግዚአብሔር ባሕሪ፡- ምሳሌ

እነዚህ ሁለት ቃሎች ኢየሱስ ክርስቶስ በክብርም ሆነ በባሕሪ በውስጥም ሆነ በውጭ የእግዚአብሔር ፍፁምና ሁለንተናዊ መገለጥ እንደሆነ ይመለክፉልናል። ሆኖም ክብርን በተመለከተ የአሳብ ብዥታን ለማጥራት ቃላትን ወደ መተርጎም ለመሄድ እንገደዳለን። ክብር በሁለት የሚከፈል ቃል ነው።

1. ሰው ለእግዚአብሔር የሚሰጠው፣ ሊሰጠውም የሚገባው ክብር፡- አምልኮ፣ አክብሮት፣ ወዘተ...
2. እግዚአብሔር ለሰው ሊሰጠው ያዘጋጀው ክብር፡- ግርማ ሞገስ፣ ማብራት፣ ማንፀባረቅ፣ ... ወዘተ

ስለዚህ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ክብር ስንል እግዚአብሔር ከእኛም ሆነ በእኛ ምክንያት ከሌሎች የሚቀበለውን ክብር ወይም አክብሮት የሚገባውን ክብደት ያለውን ሕይወት ለማመልከት አለመሆኑን አንባቢ ልብ ሊል ይገባል። እግዚአብሔር «ክብሬን ለማንም አልሰጥም!» ሲል የሚናገረው ስለ አንደኛው እንጂ ስለ ሁለተኛው አይደለምና። የራሱንማ ክብር ላመነ ሁሉ ሊሰጥ ዓለም ሳይፈጠር በፊት ወስኖ የለ?

በዚህም ሥፍራ እየተነጋገርን ያለነው ሰው ለእግዚአብሔር ስለሚሰጠው አክብሮት ሳይሆን የእግዚአብሔር ሕይወት አንዱ ገጽታ ስለሆነውና እግዚአብሔር ለሰው ሊጠሰው ስለወሰነው በመጨረሻው ቀን በሰው አካል ላይ ስለሚገለጠው የሚንፀባረቅ ክብር ነው። ይህም ክብር በሚመጣው ዘመን የሚገለጥ በመሆኑ አሁን ምን እንደሚመስል እንኳ ለመገመት አስቸጋሪ ነው።

ጌታ ኢየሱስ በመጀመሪያው አመጣጡ ከተወለደበት ጊዜ አንስቶ ከሙታን እስከተነሳ ድረስ የኖረው በሰዎች ዓይን የሚታይና ትኩረት የሚስብ ክብር እያንፀባረቀ አልነበረም። ምንም እንኳ በተራራ ላይ ሦስቱ ደቀመዛሙርቱ በተገኙበት ለአፍታ ክብር በሰውነቱ ላይ ቢያንጸባርቅም ያ የአንድ ወቅት ልምምድ የኢየሱስን የምድር ቆይታ ሙሉ በሙሉ ሊወክል እንደማይችል እሙን ነው። ጌታ ኢየሱስ በመጀመሪያው መገለጡ ወደ ዓለም ሲገባ የባሪያን መልክ ይዞ መጣ እንጂ በክብር አልተገለጠም።

ይህን ስንል የእግዚአብሔር ሕይወት ባሕሪ በሚገለጥበት ወቅት የሚኖረው ባሕሪ ብቻ እንጂ ፈጽሞ ክብር የሚባል አይኖርም ማለታችን አይደለም። የእግዚአብሔር ሕይወት ራሱ የክብር ሕይወት ነውና በመከራና በጉስቁልና ውስጥ ሆነን እንኳ ባህረው ሲገለጥብን ለሥጋ ዓይን የሚታይ ባይሆንም ክብር በላያችን ያርፋል በውስጣችን ይፈላል። ለዚህም ማረጋገጫ የሚሆነን ራሱ ጌታ ኢየሱስ ነው። በተሰቀለ ወቅት በዙሪያው የነበሩት ውርደት እንጂ ክብር አላዩበትም እርሱ ግን ሲሰቀሉትም ክብር የክብርም ጌታ ነበር።

> *«ከዚህ ዓለም ገዦች አንዱ እንኳ ይህን ጥበብ አላወቀውም ለውቀውስ ቢሆኑ የክብርን ጌታ ባለሰቀሉትም ነበር . . . » ፩ቆሮ.፪፡፰*

ከዚህ የተነሳ ባሕሪና ክብርን ሰይቶ ለመግለጽ አስቸጋሪ ቢሆንም ክብርን በመጨረሻው ቀን ከሚገለጠው ማንፀባረቅ ጋር ብቻ እንድናስበው እጠይቃለሁ። ይህ ከሆነ አሁን በሚገለጥብን የክብር ባሕሪና በሚመጣው የክብር ማንፀባረቅ መካከል ያለምንም ችግር ሰይተን ማየት እንችላለን።

ክቡር የሆነውን የሕይወት ባሕሪ ከክብር ነጥሎ ማየት ለምን አስፈለገ? የሚል ጥያቄ ይነሳ ይሆናል። ሆኖም በዚህ አገላለጽ ባሕሪን ከክብር እየነጠልን ሳይሆን የአንድ ሕይወት ሁለት ገጽታዎች መሆናቸውን ለማሳየትና መጽሐፍ ቅዱስ ክብርን ወደፊት ከሚመጣ ተስፋ ጋር አያይዞ የሚናገረውን ሃሳብ ለማጉላት[34] እንጂ በባሕሪ ውስጥ የሚገለጠውን ክብር ለማደብዘዝና በዚህ ዘመን በምንም ዓይነት ክብርን እንደማንለማመድ ለመናገር አይደለም።

ጌታ ኢየሱስ የሚመጣውን ክብር ብልጭታ ሊያሳያቸው ሦስቱን የቅርብ ተከታዮችን ይዞ ወደ ደብረታቦር ተራራ ቢወጣና በዚያም በክብር ሲያንፀባርቅ እንዲያዩት ቢያደርግም ለአፍታ የሆነ ቅምሻ እንጂ የሰላሳ ዓመት የምድር ኑሮውን የሚወክል ሊሆን አይችልም። ዘጠምህርቱና በተዓምራቱ የተገለጠውም ክብር ሰዎች አይተውና ሰምተው ለእግዚአብሔር ክብር የሰጡበት እንጂ እግዚአብሔር በክርስቶስ ለሰው ልጅ ያዘጋጀውንና በሚመጣው ዘመን በሙላት የሚገለጠውን ክብር (ነፀብራቅ) አያመለክትም። ከዚህ የተነሳ የኢየሱስ ክርስቶስ የምድር አገልግሎት የእግዚአብሔርን ሕይወት አንድ ገጽታ እርሱም ባሕሪን የመግለጥ እንደሆነ ደፍረን መናገር እንችላለን።

ከደቀመዛሙርቱ አንዱ «አብን አሳየንና ይበቃናል።» ባለው ጊዜ። «እኔን ያየ አብን አይቷል» ያለው ስለ ቃሉና ስለ ሥራው በዚያም ውስጥ ስለተገለጠው የእግዚአብሔር ባሕሪ እንጂ በክብር ስለ ማንፀባረቁ እንዳልሆነ መናገርም አያስፈልግም። አሁን ግን ኢየሱስ ከመሰቀሉ ጀርባ ወደነበረው በሥጋ ትንሳኤ ወደሚገኘው ዘላለማዊ ክብር ውስጥ ገብቷል።

በግርማው ዙፋን ቀኝ ተቀምጧል። ከምድር ይዞት ያረገው ሥጋ ያለልክ ከብሯል።

«ኢየሱስ ስላልከበረ መንፈስ አልወረደም ነበር» በማለት በምድር በነበረበት ጊዜ ገና አለመክበሩን የሚነግረን መጽሐፍ ኢየሱስ ያለልክ ከፍ ከፍ ብሎ በአብ ቀኝ ከከበረ በኋላ በዐሥ ሃምሣ ቀን መንፈስ ቅዱስ ባመኑት ላይ መውረዱን በመንገር የኢየሱስን መክበር አብስሮልናል።

ኢየሱስ በተዋረደና የኃጢአት መሥዋት ምሳሌ በሆነ ሥጋ በመጣበት በመጀመሪያ መገለጡ ያየነው የእግዚአብሔር ሕይወት ገጽታ ባሕሪውን ነው። በሰማያት ከከበረ በኋላ ግን ዓለም አትየው እንጂ እኛ ያመንን በመንፈስ ዓይን በእምነት መነጽር የምናየው ክብር በሰውነቱ ተገልጧል።[35] በእርሱም ፊት ላይ የእግዚአብሔርን የክብሩን እውቀት ብርሃን አግኝተናል። ሆኖም ይህን በመንፈስ ከሩቅ በድንግዝግዝ ያየነውን መልክ በሁለተኛ መገለጡ ፊት ለፊት እናየዋለን።

ይህንን እውነት በሌላም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌ ልናየው እንችላለን። የሙሴ ድንኳን ውስጡ በወርቅ የተሰበጠና በጣፋጭ መዓዛ የታወደ ቢሆንም ውጪው ግን ከአስቆጣ ቁርበትና ከቀይ በግ ቆዳ በመሠራቱ የሚማርክ ገጽታ አልነበረውም። ይህ ድንኳን በምድረ በዳ የተሠራና በበረሃ ሲንከራተት የኖረ ነበር።

የሰለሞንን መቅደስ ስንመለከት ግን ምንም እንኳ የዚያው የሙሴ ድንኳን ቀጣይ ቢሆንም ውስጡም በወርቅ የደመቀ ውጪውም በክቡሩ ድንጋዮች የተንቆጠቆጠ እንደነበረና ያለምንም መንከራተት በተቀደሰችው ከተማ በሞሪያ ተራራ

የተቀመጠ ታላቅ ሕንፃ እንደነበረ እንመለከታለን። የመገናኛው ድንኳን የጌታ ኢየሱስን የምድር ኑሮ የሚያመለክትና እኛም በአሁኑ ዘመን በሚሞተው ደካማ ሥጋችን ውስጥ ባሕሪውን እየገለጥን የምንኖረውን ኑሮ የሚያሣይ ነው።

የሰለሞን መቅደስ ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ከተነሳና በክብር ካረገ በኋላ አሁን በሰማያይቱ ኢየሩሳሌም ያለውን ሁኔታ እንዲሁም እኛ ከሙታን ትንሳኤ በኋላ በበጉ አራትም ሆነ በምድራዊቱ ኢየሩሣሌም የሺህ አመት መንግሥት የምንሰብሰውን በውስጡም በውጭውም የከበረ አካል የሚያመለክት ምሣሌ ነው። ይህንንም እውነት ሐዋርያዊ ጳውሎስ በፍፁም ግልጽነት ሲናገር እንዲህ ብሏል፦

> *«ድንኳን የሚሆነው ምድራዊ መኖሪያችን ቢፈርስ በሰማይ ያለ በእጅ ያልተሠራ የዘላለም ቤት የሚሆን ከእግዚአብሔር የተሰራ ሕንፃ እንዳለን እናውናቀለንና። በዚህ (በድንኳኑ) ውስጥ በእውነት እንቃትታለንና። ከሰማይም የሚሆነውን መኖሪያችንን እንድንለብስ እንናፍቃለን ለብሰን ራቁታችንን አንገኝም። በእውነትም የሚሞተው (ድንኳኑ) በሕይወት ይዋጥ ዘንድ ልንለብስ እንጂ ልንፈፍ የማንወድ ስለሆነ በድንኳኑ ያለን እኛ ከብዶን እንቃትታለን። ነገር ግን ለዚሁ (ለድንኳኑ) የሠራን እግዚአብሔር ነው። እርሱም የመንፈሱን መያዣ ሰጠን።» 2ቆሮ. 5:1-5 (ማብራያው በጸሐፊው የተጨመረ ነው።)*

እንግዲህ ከዚህ ሁሉ በመነሳት ወደ አንድ ድምዳሜ ልንመጣ ይገባናል። ይህ ዘመን በሥራችን፣ በቃላችን፣ በኑሮአችን ሁሉ የእግዚአብሔርን ሕይወት ባሕሪ የምንገልጥበት የባሕሪ ዘመን ነው እንጂ የመንገሥ ወይም የመክበር ዘመን አይደለም። ብንከብርም ያለ ክርስቶስ እንከብራለን። ዘመን ተማቶባቸው አለጊዜው «ከብረናል፣ ነግሠናል፣ በልጽገናል» ላሉት የቆሮንቶስ ሰዎች ጳውሎስ በምፀትና በታላቅ ቃል፦

> *«አሁን ጠግባችኋል፣ አሁኑ ባለጠጎች ሆናችኋል፣ ያለ እኛ ነግሳችኋል፣ እኛ ደግሞ ከእናንተ ጋር እንድንነግሥ ብትነግሡ መልካም ይሆን ነበር።» 1ቆሮ. 4:8*

እንዳለ ይህ ዘመን በምናልፍበት ተግዳሮት ሁሉ የእግዚአብሔርን ሕይወት ባሕሪ እየገለጽን ለሚመጣው ክብር

የምንዘጋጅበት እንጂ የመንገሥና የመከበር ዘመን አይደለም። ማብራት፣ ማንፀባረቅ፣ መንገሥና መግዛት የሞላበት ክብር፣ በዓይን ያላየነው በጉጉት የምንጠብቀው ተስፋ እንጂ ዛሬ የምንወርሰው ርስት አይደለም።[26] በፊታችን የተንጣለለው ውጡና ውረሱት እየተባልን ያለነው ርስት ግን በውስጣችን የታመቀው የሕይወት ባሕሪ ነው። እውነቱ ግን ይህ ነው፦

> *«ሞታችኋልና ሕይወታችሁም በእግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ተሰውሮአልና። ሕይወታችሁ የሆነ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ በዚያን ጊዜ እናንተ ደግሞ ከእርሱ ጋር በክብር ትገለጣላችሁ።» ቆላ. 3:3-4*

ታዲያ በአገልግሎታችንም ሆነ በኑሮአችን የዚህን ሕይወት ባሕሪ ለመግለጥ የሕይወት ራስ ከሆነው ከክርስቶስና የአካሉ ብልቶች ከሆኑ ቅዱሳን ጋር ሕይወትን መካፈል መቻል ይኖርብናል። አለዚያ ግን ያልተካፈልነውን እና በውስጣችን ያልበዛውን ሕይወት ባሕሪ መውረስም ሆነ መግለጥ አንችልም።

ስለመውረስ ሲነሳ ምንም እንኳ ያለን አንድ ተስፋና አንድ ርስት ብቻ እርሱም የእግዚአብሔር ሕይወት እንደሆነ ብናውቅም መጽሐፍ ቅዱስ ግን ይህን አንድ የሕይወት ርስት በሁለት ገጽታ በመክፈል አንዱ በሰማይ እንደሚጠብቀንና በመጨረሻው ቀን እንደሚገለጥ ሌላው ደግሞ በእኛ ዘንድ እንዳለና አሁን በዚህ ዘመን ልንወርሰው እንደሚገባ ይነግረናል። ይህንን ለመረዳት እነዚህን ሁለት ክፍሎች ልብ ብሎ መመልከት በቂ ነው፦

> *«ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን በመነሣቱ ለሕያው ተስፋና ለማይጠፋ እድፈትም ለሌለበት ለማያልፍም ርስት እንደ ምሪቱ ብዛት ሃብተኛ የወለደን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ። ይህም ርስት በመጨረሻው ዘመን ይገለጥ ዘንድ ለተዘጋጀ መዳን በእምነት በእግዚአብሔር ኃይል ለተጠበቃችሁ ለእናንተ በሰማይ ቀርቶላችኋል።» 1ጴጥ. 1:3-5*

ይህ ክፍል ርስት እንዳለን፣ ይህም ርስት በሰማይ እንደሚጠብቀንና በመጨረሻው ዘመን እንደሚገለጥ ይነግረናል። ሌላውስ?

> «የክብር አባት የጌታችን የኢየሱስ አምላክ አርሱን በማወቅ የጥበብንና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ አሰምናስሁ። ይህም የልባችሁ ዓይኖች ሲበሩ የመጥራቱ ተስፋ ምን እንዲሆን በቅዱሳንም ዘንድ ያለው የርስት ክብር ባለጠግነት ምን እንዲሆን ለምናምንም አሁኑ የሚበልጥ የኃይሉ ታላቅነት ምን እንዲሆን ታውቁ ዘንድ ነው።» ኤፌ. 1:17-19

ቡጥቅሶቹ ውስጥ ደማቅና ለየት ብሉ የተባፈውን ክፍል ልብ ብለው ካዩት አንደኛው ርስት በእግዚአብሔር ዘንድ በሰማይ ሌላኛው በቅዱሳን ዘንድ በምድር እንዳለ፣ የሰማዩ የሚገለጠውና የሚወረሰው በመጨረሻው ዘመን ጌታ ዳግመኛ ሲመጣ እንደሆነ፣ በቅዱሳኑ ዘንድ ያለው የምድሩ ግን አሁን የልባችን ዓይኖች ከበሩ ከቅዱሣን ጋር ከሁሉ በሚበልጥ የኃይሉ ታላቅነት ጠላቶቻችንን ድል ነስተን የምንወርሰው እንደሆነ ይነግረናል። ታዲያ እነዚህ ሁለት ርስቶች ምንድናቸው? ፈጽሞ ሁለት አይደሉም። አንድ ርስት እርሱም የእግዚአብሔር ሕይወት ነው። ሁለት ያስመሰሉት ገጽታዎቹ ናቸው። አሁን የምንወርሰው (ጀርባው) የሕይወቱ ባሕሪ ሲሆን ወደፊት የሚገለጠው (ፊቱ) የሕይወቱ ክብር ነው። ይህም እውነት ይህ ዘመን የባሕሪ ዘመን እንደሆነ ያረጋግጥልናል።

አሁንም ባሕሪ ስንል ስለ ሥጋ አመለ ሽጋነት ወይም ግብረገባዊነት እያወራን እንዳልሆነ ልብ ሊባል ይገባል። እየተነጋገርን ያለውን የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ባሕሪ ስለመካፈልና ስለመግለጥ ነው። እንደ እግዚአብሔር ስለመወደድ፣ እንደ እግዚአብሔር ስለመታገሥ፣ እንደ እግዚአብሔር ይቅር ስለማለት፣ እንደ እግዚአብሔር በልግሥና ስለመስጠት፣ እንደ እግዚአብሔር . . . እንደ እግዚአብሔር . .

. እንደ እግዚአብሔር። ማንኛውም አማኝ ጌታ ዳግመኛ በክብር እንደሚገለጥ በዚያም ቅጽበት በክብር እንደሚለወጥና እንደሚነጠቅ ከጌታም ጋር እንደሚኖር ያምናል። ነገር ግን እንደሚከብር እንጂ ምን ያህል የክብር መጠን በላዩ እንደሚገለጥ፣ መጠኑንም የሚወስነውን ጉዳይ ላይገነዘበው ይችላል። ሆኖም በዚያን ጊዜ በሰውነታችን ላይ የሚገለጠው ክብር መጠን አለው። ጳውሎስ ሁላችንም እኩል እንደማንከብር ሲናገር፦

> «የፀሐይ ክብር አንድ ነው የጨረቃም ክብር ሌላ ነው። የከዋክብትም ክብር ሌላ ነው። በክብር አንዱ ኮከብ ከሌላው ኮከብ ይለያልና።» 1ቆሮ. 15:41 ብሏል።

ስለዚህ በክብር መለያየት አለ ማለት ነው። ያም የሚወሰነው በዚያን ቀን ሳይሆን ዛሬ ነው። ዛሬ በምድር ኑሮአችን ባሕሪው በተገለጠበን መጠን ያን ቀን ክብሩም በዚያው መጠን ይገለጥብናል። ዛሬ ባሕሪውን በወረስን ልክ ያን ቀን ለዘላለም ክብሩን እንወርሳለን።

ስለዚህ ዛሬ ትልቅ ቀን፣ ወሳኝ ቀን እንደሆነ ልብ እንበል። ዛሬ ዘላለማችንን የሚወስን ልዩ ቀን ነው። ስለዚህ ከትናንት ፀፀት ከነገ ጭንቀት ወጥተን ዛሬን እንኑር። «ዛሬ ድምፁን ብትሰሙት ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ።» ተብሎ እንደ ተጻፈ ዛሬ ወደ ዕረፍቱ ለመግባት እንትጋ። በሰባተኛው ቀን እግዚአብሔር ከሥራው ሁሉ ያረፈው ሰውን በመልኩና በምሳሌው ፈጥሮ እንደ ሆነ ሁሉ ዛሬም የሚያርፈው እርሱን የሚመስሉ ሲገኙ ነውና እርሱን በመምሠል ያሳረፈንን እናሳርፈው። ይህ እረፍት ምንድን ነው? በክርስቶስ አምነን ሰንድን አርፈን የለ? እረፍት ሁለት ዓይነት ነው። አንደኛው እኛ በእግዚአብሔር ያረፍነው ሲሆን ሁለተኛው እግዚአብሔር በእኛ የሚያርፈው ነው። የእስራኤል ልጆች ከግብፅ ሲወጡ

ከባርነት አርፈዋል። ነገር ግን ያ ብቻውን በቂ አልነበረም አርፈው ለማሳረፍ ወደ ከነዓን መግባት ነበረባቸው። ይህ የጌታ አባባል ይህንን አሳብ ይቋጭልናል፦

> «እናንተ ደክሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ። ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ ከእኔም ተማሩ እኔ የዋህ በልቤም ትሁት ነኝና ለነፍሳችሁም አረፍት ታገኛላችሁ . . . .» ማቴ. 11:28-29

ስለዚህ ክርስቶስን በመምሰል የእግዚአብሔር አረፍት ምክንያት እንሁን።

የተሠማራንበት ሙያ ና የሥራ መስክ የፈለገው ይሁን የሕይወታችን ዓላማ እና የመኖራችን ምክንያት ባሕሪውን መውረስና መግለጥ ይሁን። በዙሪያችን ያሉ ሰዎች በሰማያዊ ስፍራ ያሉ አለቆችና ሥልጣናትም ጭምር ነጋዴውን ሊየሱስ፣ ባለሙያውን ሊየሱስ፣ ባለሥልጣኑን ሊየሱስ፣ ተማሪውን ሊየሱስ፣ የቤት እመቤቱን ሊየሱስ፣ አገልጋዩን ሊየሱስ ወ.ዘ.ተ. እንዲያዮ እንፍቀድላቸው። የአዲስ ኪዳን አገልግሎት በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና በጸጋ ስጦታዎች የታጀበ እንደሆነ ምንም ጥያቄ የለውም። ሆኖም በክርስቶስ ባሕሪ ያልተያዘ የትኛውም ጸጋ ከሚያለማው የሚያጠፋው፣ ከሚገነባው የሚያፈርሰው ይበዛል። ጸጋ ያለ ባሕሪ እደገኛ ነውና። ሰይጣን ከመጣሉ በፊት የተቀባና በሥጦታ የተሞላ መልአክ እንደነበር ነገር ግን ከባሕሪው የተነሳ ተገፎ በውርደት እንደተጣለ መጽሐፍ ያስተምረናልና። የጸጋ ሥጦታ እንደስሙ ጸጋ ሥጦታ ነው። የሚሰጠውም ለማይገባው፣ ለማይመጥነው ሰው ነው። የሚያሳየውም ሰጭውን እንጂ ተቀባዩን አይደለም። የሚሰጠውም ሌሎችን እንድናገለግልበት እንጂ ለራሳችን አይደለም። የክርስቶስን ባሕሪ መልበስ ግን እንደ ዝናብ ከሰማይ የሚወርድ በረከት ብቻ ሣይሆን ከሰማይ የወረደውን

በረከት ተጠቅሞ አርሶ፣ ዘርቶ፣ አርሞና ኮትኩቶ ለፍሬ የመብቃት ጉዳይ ነው።

የአዲስ ኪዳን አገልግሎት የጸጋ አገልግሎት ቢሆንም በዋነኝነት የባሕሪ አገልሎት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ለጢሞቴስም ሆነ ለቲቶ በየቤተክርስቲያናቱ ሽማግሌችን እንዲሾሙ መመሪያ በሰጣቸው ክፍል ውስጥ 98% (ዘጠና ስምንት በመቶ) የጠቀሰው መንፈሳዊ ባሕሪን እንጂ ጸጋ ሥጦታዎችን አልነበረም።[27] በመሠረቱ ጸጋ ሥጦታ የሌለው አማኝ የለም። የጸጋ ስጦታዎችም ዓለማ ያለ ነቀፋና ያለ ነውር ሆነን የጌታን ቀን እንድንጠባበቅ ማስቻል[28] እንጂ አንዳንዶች እንደሚያስቡት የግል ዝናና ጥቅምን ማካበቻ አይደለም። በእርግጥ የጌታን ባሕሪ ለመውረስ መስቀሉን መሸከም፣ ራስን መካድ፣ ከክፉ መንፈሳዊያን ኃይላት ጋር መጋደል፣ ከቅዱሳን ጋር በቅርበት ሕይወትን መካፈል ይጠይቃል። ይህ ሂደት ዛሬ ምንም ያህል ዋጋ ቢያስከፍለንም የሚመጣውን ክብር በማሰብ ወደፊት ልንገሰግስ ይገባል። ይህን አሳብ ከመደምደማችን በፊት ሐዋርያው ጴጥሮስ ስለዚያች ቀንና ያንን ቀን በማሰብ ዛሬ ሊኖረን ስለሚገባው ሕይወት ሲጽፍ ያሉውን እንመልከት፦

> «የጌታው ቀን ግን እንደሌባ ሆኖ ይመጣል፤ በዚያም ቀን ሰማያት በታላቅ ድምፅ ያልፋሉ፤ የሰማይም ፍጥረት በታላቅ ትኩሳት ይቀልጣል፤ ምድርም በእርሷም ላይ የተደረገው ሁሉ ይቃጠላል። ይህ ሁሉ እንዲህ የሚቀልጥ ከሆነ የእግዚአብሔርን ቀን መምጣት እየጠበቃችሁና እያሰቸኮላችሁ በቅዱስ ኑሮ እግዚአብሔርንም በመምሰል እንደምን ልትሆኑ ይገባችኋል?» 2ጴጥ.3:10-11

እንግዲህ ዘመኑ የባሕሪ ዘመን ነውና በኑሯችን፣ በሥራችን፣ በቃላችን ሁሉ እግዚአብሔርን ለመምሰል እንትጋ።

5
ችላ የተባለ ጠላት

በተለያየ አጋጣሚ «የሮም አወዳደቅ» ሲባል ሰምተው ያውቃሉ? ይህ አባባል በዓለም ላይ በስፋት የናኘ ከመሆኑ የተነሳ ለግለሰብ፣ ለቡድን፣ ለማኅበረሰብ ውድቀት እንደ ምሳሌ ይጠቀሳል።

ከክርስቶስ ልደት አስቀድሞ በዓለም ላይ በኃይል የተንሰራፋው የሮም መንግሥት «ፓክሳ ሮማና» (ሮም ለዓለም ያመጣችው ሰላም) በሚል ቅጽል የሚጠራና ከሮም አስቀድሞ ዓለምን ጠቅልሎ ለመግዛት ከተነሱት አገሮች ሁሉ በድል የተመመ በስኬት የደመመ ታላቅ መንግሥት እንደነበር ታሪክ ይመሰክራል። ነቢዩ ዳንኤል እንኳ በራእይ ከሩቅ ተመልክቶ፦

> *«የሚያስፈራና የማያስደነግጥ በጣም ኃይለኛ ተልጦ የበረታ ጥርሶች የነበሩት ያደቅና ይበላ የተረፈውንም ሁሉ በእግሮቹ ይረጋገጥ የነበረ። ከእርሱ በፊት ከነበሩት ለራዊት ሁሉ የተለየ ...»* (ዳን. ፯:፯)

ብሎታል። ታዲያ ይህ የሮም መንግሥት ከክርስቶስ ልደት በኋላ ወደ አራተኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ አይወድቁ አወዳደቅ ወደቀ።

ጊዜው መስከረም 4,476 እ.ኤ.አ. እንደሆነ ይታመናል።[29] ታላቁ የሮም መንግሥት በድንገት መፈራረስ ጀመረ። ይህን የማይደፈር የታፈረና የተፈራ መንግሥት ምን ጣለው? ከጥንት እስከ ዛሬ የተነሱ የታሪክ ምኑራን ለዚህ ጥያቄ ብዙ ምክንያቶችን ቢደረድሩም በሮም አገዛዝ ውስጥ ከላይ አንስቶ እስከ ታች ሥር ሰዶ የነበረው

ግብረገባዊ ዝቅጠት ዋነኛ ምክንያት እንደነበር ብዙዎች ይስማሙበታል።

ይህ ከቄሣሮቹ አንስቶ እስከ ተራ ወታደሮች ድረስ ውስጥ ውስጡን እንደሰደድ እሳት የተቀጣጠለው ሙስና፣ ክልክ ያለፈ ቅምጥልነት፣ በዘፈን የታጀበ ስካርና በልቅነት የተሞላ ሴሰኝነት መንግሥቱን ቦርቡሮ ጨርሶት ጥሮ ከውጭ የመጣውን አናሳ ኃይል መቋቋም ተስኖት ያ ታላቅ መንግሥት እንዳልነበረ ሆኖ ጠፋ። ሰይፍ ሳይመዝ፣ ጦር ሳይሰብቅና ሠራዊት ክተት ሳይል የመጣ ጠላት በሞቀ ልብና በተዘረጋ እቅፍ ተቀባይነት አግኝቶ በጉያ ተሸጉጦ የሮምን መንግሥት ያህል ግዙፍ ነገር እንደነቀዝ በልቶ ጣለው። የሮም ገዥዎች ከነማእረጋቸው በዘቀጠ ግብረገብ ሲቀብጡ፣ በተበላሸ ባሕሪ ሲዋጡ እየተሸነፉ እንደነበር ፈጽሞ አላወቁትም። ከስካራቸው ሲነቁ ግን ሮም በክብሯ አልነበረችም። ችላ የተባለ ጠላት ይሏል ይህ ነው። ድሮም ቢሆን አደገኛ ጠላት ከሩቅ የሚመጣ ሳይሆን በቅርብ የሚገኝ፣ ውጭ ያለ ሳይሆን ውስጥ የሚኖር ነው። በውጭ ካለው ትልቅ ጠላት ይልቅ ለትልቁ ጠላት ሥፍራ የሚሰጥ በውስጥ ያለ ትንሽ መሰል ጠላት ጉዳቱ ያመዘነል። በታሪክ ውስጥ በተደጋጋሚ እንደሚታየው ታላላቅ የጦር ኃይሎች ብዙም ግምት ባልሰጡት አናሳ ኃይል የሚሸነፉት ከጠላት ጋር በሚስጥር ተወዳጅቶ ገበናቸውን የሚገልጠውን ወዳጅ መሰል ጠላት በጉያቸው አቅፈው ሲቀመጡ ነው።

ወደ እኛ ስንመለስ ይህ ቸል የተባለ ጠላት የሁላችንም ዓይን የሚፈጥበት ሰይጣን ሳይሆን ለሰይጣን ብቸኛ መጠቀሚያ የሆነው ሥጋ ነው። ሥጋ ምንድነው?

የሥጋ ሕይወት ምንነት

ስለ ሥጋ አበክረው የሚናገሩትን የአዲስ ኪዳን መፃሕፍት ይልቁንም የጳውሎስን መልእክቶች በሚገባ ለመረዳት ቃሉት መተርጎም አማራጭ የለውም።

የግሪክ ቋንቋ «ሥጋ» የሚለውን ቃል በሁለት አማራጭ ዘይቤ ይጠራዋል። አንደኛው «ሶማ» የሚለው ሲሆን፦ የሚያመለክተው የሥጋን ሰውነት ወይም ግዑዙን አካል ነው። ይህ አካል ደካማና የሰው ውድቀት ተጠቂ ቢሆንም ተቆጣጥሮ የያዘው ሕይወት የሚጠቀምበት ግዑዝ መሣሪያ እንጂ በራሱ ምንም ክፋትም ሆነ ደግነት የለውም። ይህ በእግዚአብሔር እጅ ከምድር አፈር የተበጀ ሥጋ እግዚአብሔር ይመግበዋል፣ ይፈውሰዋል፣ ይጠብቀዋል እንጂ ፈጽሞ ሊያስወግደው አይፈልግም። ኃጢአት አልባ ሆኖ ከድንግል የተወለደው ጌታችን ኢየሱስ እንኳ ይህንን ሥጋ ተካፍሏል። በእግዚአብሔር ዓይን ፊት የሥጋን አስፈላጊነት የምናየው ኢየሱስ በመስቀል ላይ ከሞተ በኋላ በሦስተኛው ቀን ሲነሳ ሥጋን ይዞ መነሳቱ ነው። የእኛም ሥጋ በመጨረሻ እንደሚነሳና ለዘላለም እንደሚኖር መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል።[30]

ሁለተኛው የግሪክ ቃል «ሳርክስ» የሚል ነው። ይህ ቃል በአማርኛ ሥጋ ተብሎ የተተረጎመ ቢሆንም የሚያስተላልፈው ሃሳብ ግን የተለየ ነው። ምንም እንኳን «ሳርክስ» አንዳንድ ቦታ የሥጋን አካል ለመግለጽ በተለዋጭነት ያገለገለ ቢሆንም በዋነኝነት በኃጢአት የተበከለውን የሥጋን አካል በመጠቀም በእግዚአብሔር ላይ የሚያምፀውን የሥጋን ሕይወት የሚያመላክት ነው።

የሥጋ ሕይወት ደም አይደለም። ነገር ግን በደም ውስጥ እንደሚኖር የእግዚአብሔር ቃል ይነግረናል።[31] ይህ ሲፈጠር ንፁህ የነበረ የተፈጠረበትም ዓላማ የሥጋን አካል በሕይወት ለማኖር የሆነ ሕይወት ሙሉ ለሙሉ በኃጢአት ኃይል ቁጥጥር ውስጥ ስለወደቀ ለእግዚአብሔር ሕግ ሊገዛና እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኝ አይችልም። የእግዚአብሔር የማዳን ሥራም ይህንን ሕይወት በማከምና በመፈወስ ላይ ያተኮረ ሳይሆን በማስወገድ ላይ ያነጣጠረ ነው።

ይህ የሥጋ ሕይወት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብዛት የተጠሰቀው ከመንፈስ ጋር ስላለው ተቃርኖ ነው። ከመንፈስ ያልሆነ ሁሉ ከሥጋ ነውና የመንፈስን ምኞት ይቃወማል። እኛም ከአዳም ዘር በሥጋ፣ ከክርስቶስ ዘር በመንፈስ በመወለድ ሁለቱንም የሕይወት ባሕሪ ስለተካፈልን ኃጢአት የሠረፀበት የሥጋ ሕይወትና ጽድቅ የሞላበት የእግዚአብሔር ሕይወት በእኛ በአንድ ድንኳን ውስጥ አድረዋል። ሆኖም በሰላም አይደለም።

> *«ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና እነዚህም እርስ በእርሳቸው ይቃወሙማሉ ...» ገላ. 5:17*

የሥጋ ሕይወት ስንል አሁን በምድር ላይ በሥጋ የምንኖረውን ኑሮ ለማመልከት ሳይሆን በሥጋችን ውስጥ ተሰውሮ በአካላችን ወስጥ አድሮ ሰዓይጣን አሳብ ምሽግ በመስጠት ብልቶቻችንን በመቆጣጠር ለአመጽ ሲያስገዛን የሚቅበዘበዘውን ባሕሪ ነው።

የሥጋ ሕይወት ኃጢአት ሙሉ በሙሉ የተቆጣጠረውን የራሱ ፈቃድ የሌለው የተሸጠ ባሪያ ነው። ለራሱ ባሪያ ሆኖ ብልቶቻችንን ለኃጢአት ባሪያ ለማድረግ ያለመታከት ይሠራል። ይህ ኃጢአተኛ ተፈጥሮ የሚገለጥባቸው ብዙ ባሕሪያት ቢኖሩትም ዋነኛው ምኞት ነው። ሰይጣን በምኞት ይቆጣጠረዋል፣ ይገዛዋል፣ ፈቃዱንም ይፈጽምበታል።

በብሉይ ኪዳን ዘመናት የሥጋ ሕይወት በጥላና በምሳሌ ይገለጽ እንጂ እንዲህ እንደ አሁኑ በእግዚአብሔር ብርሃን ተለይቶ አይታወቅም ነበር። ከምሳሌዎቹም ውስጥ አንዱና ዋነኛው ሸለፈት ነበር። እግዚአብሔር የሥጋን ሕይወት በሸለፈት ስለመሰለው በዚህ ተፈጥሮ ላይ ያለውን ጥላቻ ምሳሌው በተደረገው በሸለፈት ላይ ይገለጽ ነበር።

ባልተገረዙ ላይ ይገለጥ የነበረው የእግዚአብሔር ቁጣ በዚያች ቁራጭ ሥጋ ላይ የተመሠረተ ሳይሆን ቁራጩ ሥጋ ምሳሌ ሆኖ ባገለገለው የሥጋ ሕይወት ላይ ነበር።[32] የመገረዝን ኪዳን ለመቀበል የመጀመሪያ ሰው የሆነው አብርሃም ከእግዚአብሔር ጋር በተለያዩ ጊዜያት የመብትና የግዴታ ውል ሲፈፅም እንመለከታለን። እንደኛው እግዚአብሔር ለአብርሃም ሲፈፅም የገባው ዘርን የመስጠት ተስፋ ሲሆን «ዘርህ» በተባለው በክርስቶስ አማካይነት የእግዚአብሔርን ሕይወት ወደ ሰው ልጆች ለማድረስ ታልሞ የተገባ ኪዳን ነው።[33] ሆኖም አብርሃም ይህን ተስፋ ለመውረስ በእርሱ በኩል ሲፈፅመው የሚገባ ግዴታ ነበር። ያም የአብርሃም ድርሻ የሥጋ ሕይወት ምሳሌ የነበረውን ሸለፈት ማስወገድ ነበር።

ከአዳም ዘር የተወለድን ሁላችን ይህን ተፈጥሮ ተካፍለናል። ልንካፈል የቻልነውም ከሰው ውድቀት አስቀድሞ በመንፈሳዊው ዓለም ውስጥ በሉሲፈር ልብ ተሰውሮ የነበረው የኃጢአት መርዝ የመጀመሪያው ሰው አዳም በከፈተለት በር ተጠቅሞ ወደ ሰው ዘር ውስጥ በጥልቀት በመስረፁ ነው። በአዳም አማካይነት ኃጢአት ወደ ዓለም እስከገባበት ጊዜ ድረስ የምንኖርባት ዓለም ከኃጢአት ነፃ ነበረች።[34] አሁን ግን በእያንዳንዱ ሰው ሥጋ ውስጥ ኃጢአት ያድራል፣ በሥራም ይገለጣል።

እግዚአብሔር ሰውን ይወዳል፣ ኃጢአትን ግን ይጠላል። ኃጢአት ደግሞ በሰው የሥጋ ተፈጥሮ ውስጥ ስለተሸሸገ እግዚአብሔር አጥብቆ የሚወደው ሰውና አምርሮ የሚጠላው ኃጢአት ተጣምረዋል።

እግዚአብሔር ግን በአስደናቂ ጥበቡ ነጥሎ በመምታት የሚወደውን የሰው ልጅ አድኖ የሚጠላውን ኃጢአት የሚበቀልበት ሥራ ሠርቷል። ይህም ታላቅ ጥበብ ለሰው አእምሮ ሞኝነት በሚመስል መንገድ የተገለጠው በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ላይ ነው። በመስቀል ላይ እግዚአብሔር የሚጠላውን የዓለም ሁሉ ኃጢአት በሚወደው ልጁ ላይ አገኘው ለገዛ ልጁ ሳይራራ ኃጢአትን በክርስቶስ ሥጋ ላይ በመኮነን ለኃጢአት የሚገባውን የጽድቅ ፍርድ ሰጠው። ከዚያም በመስቀል ላይ በተሠራው ሥራ አምነን ወደ ዙፋኑ የቀረብነውን የትንሳኤው ተካፋዮች አደረገን።

ስለዚህ በእውነተኛ የወንጌል መሠረት ላይ ለቆሙ አማኞች ሁሉ ኃጢአት ተኮንኖአል። የኃጢአት ባሪያ ፃነበረው ያሥጋ ሕይወት (አሮጌው ሰው) ተወግዷል። ነገር ግን ይህ እውን የሚሆነው በዚህ መሠረት ላይ ቆመው የኃጢአትን ግብዣ አምቢ እያሉ በእግዚአብሔር ጸጋ ለሚኖሩ እንጂ አማኝ ስለተሆነ ብቻ አይደለም። ካልነቃንና ካላስወገድነው ምኞትን ፀንሶ ኃጢአትን የሚወልድ ብሎም ሞትን የማያሳቅፍ የሥጋ ሕይወት በውስጣችን ሊሠራ ይችላል።

የሥጋ ሕይወት ልብንና ኩላሊትን ከሚመረምረው ከእግዚአብሔር ወይም እግዚአብሔር ከገለጠለት ሰው በቀር ማንም የማያውቀው እጅግ ክፉና ተንኮል የተሞላ ዓለም ነው።

«የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ እጅግም ክፉ ነው ማንስ ያውቀዋል?» ኤር. 17:9

ተብሎ እንደተፃፈ የሥጋ ሕይወታችን ኃይማኖታዊ የሆንን በማስመሰል ለነፍሳችን አእምሮአዊና ስሜታዊ እርካታን እየቸረ እያታለለ እና እየታለለ የእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ጥማታችንን ሊገድልና እግዚአብሔርን የመምሰል ጥረታችንን ሊያኮላሽ ይችላል። በተገለጠ ኃጢአት መኖር ባይሆንለት የኃይማኖት ካባ ለብሶ አንገቱን ሰብሮ በውጭው መንፈሳዊ በመምሰል በውስጡ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኖ መኖር ይችልበታል።

ኃይማኖት የሚያዋጣና ትርፍ የሚገኝበት መንገድ መስሎ ከታየው የአምልኮ መልክ መያዝ አያስቸግረውም። ሆኖም የእግዚአብሔር ቃል በውስጣችን ሲበራ ይመረምረዋል፣ ሕይወት ያለው፣ የሚሠራ ስለታም ሰይፍ ስለሆነም የትኛው ከመንፈስ የትኛው ከሥጋ መሆኑን ይለየዋል።

በዘመናችን በየሥፍራው እውነተኛ መንፈሳዊነት እየራባቸው በሥጋ ተንኮል ተታለው መንፈሳዊ የሆኑ እየመሰላቸው በሥጋዊነት አዘቅት ውስጥ ሰምጠው የቀሩ ስንቶች ይሆኑ?

አንግዲህ በሥጋ ሕይወት ከመታለልና ለኃጢአት ከመገዛት ለመዳን መንፈስ ቅዱስ በሚሰጠን የቃሉ ብርሃን የሥጋን ሕይወት (ሳርክስ) ለይተን እንወቅ የየዕለቱ ትኩረታችንም የሥጋን ሥራ በመግደል ላይ ይሁን።

የተዛባ ትኩረት

በክርስትና ሕይወት ዙሪያ በዘመናችን በዋነኛነት የሚንሸራሸሩትን አስተሳሰቦች በጥንቃቄ ስንመረምር እግዚአብሔርን ለመምሰላችን እንቅፋት የሆነው የሥጋ ሕይወት ምን ያህል ችላ እንደተባለ እንመለከታለን።

ሩቅ ሳንሄድ በአገራችን ያለውን እምነትና አስተሳሰብ ስንቃኝ ጎልቶ የምናገኘው ከፍተኛ የሆነ «ሰይጣን ተኮር» አመለካከት ነው። የሥጋ ሕይወት ግን ትኩረት ያልተሰጠው ችላ የተባለ የሕይወት ጠንቅ ሆኖ ይኖራል።

ይህን አሳብ በጉልህ ለመረዳት የሮሜን መልእክት እንደ ምሳሌ እንውሰድ። የሮሜ መልእክት ከግዝፈቱ ባሻገር ከሌሎች የጳውሎስ መልእክቶች ሁሉ ልዩ የሚያደርገው አንድ እውነት አለ። እንደ ተቀሩት መልእክቶቹ ከዚህ ቀደም በሥፍራው ተገኝቶ፣ ጊዜ ወስዶ ለመሠረታት ቤተክርስቲያን የፃፈው የምክርና የማነጽ ቃል ሳይሆን በዐይኑ አይቷት በማያውቅ በሮም ከተማ ለምትገኝ ቤተ ክርስቲያን በአሕዛብ ሁሉ ዘንድ የጣለው የእምነት መሠረት ምን እንደሚመስል ያስተዋወቀበት መጽሐፍ ነው። ጳውሎስ የሮሜን መልእክት ባይጽፍ ኖሮ ዛሬ የአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን መሠረት ምን እንደሚመስል ለማወቅ በተቸገርን ነበር።

ታዲያ በዚህ ታላቅ መልእክት ውስጥ ሐዋርያው «ሥጋ» የሚለውን ቃል በአንድም በሌላም መንገድ 40 ጊዜ ተጠቅሟል። «ሰይጣን» የሚለው ቃል ግን የተጠቀሰው አንድ ጊዜ ብቻ ሲሆን እርሱም በመጨረሻው ምዕራፍ ላይ የጻፈላቸውን ትምህርት የሚቃወሙትንና መለያየትን የሚያመጡትን ሐሰተኛ ወንድሞች በተመለከተ ምን አቋም ሊኖራቸው እንደሚገባ ለማሳሰብ የተፃፈ ነው።

> *«የሰላምም አምላክ ሰይጣንን ለእግራችሁ በታች ፈጥኖ ይቀጠቅጠዋል።» ሮሜ 16:20*

ወደ ዘመናችን የክርስትና ሕይወት ስንመጣ ግን ትኩረታችን የሚያጠነጥረው በሰይጣን ዙሪያ እንደሆነ ለመመልከት

አያዳግትም። ስለዚህም ፀሎታችን፣ ስብከቶቻችን፣ መዝሙሮቻችን፣ ምስክርነቶቻችን በቂ ማስረጃዎች ናቸው።

በቅርቡ በአንድ ስፍራ ስጉባኤው እንዲፀልይ ተጋብዞ ወደ መድረክ የወጣ አንድ ሰው በታላቅ ድምጽ በመጮህና በመደጋገም «በሰማያዊ ሥፍራ የምትገኙ በአየር ላይ የምትበሩ፣ በምድር የምትሽከረከሩ፣ አለቆች፣ ሥልጣናት ወዘተ. . . በኢየሱስ ስም» እያለ ሲገስጽ የሰማው አንድ ሰው ወደ ጆሮው ጠጋ ብሎ «ወንድሜ እነሱ ላይ ትደርሳለህ መጀመሪያ በመካከላችን ያሉትን ጥላቻን፣ ቂም በቀልን፣ ስንፍናን ወዘተ. . . ተቃወምልን» እንዳለ አንድ ወዳጄ አጫውቶኛል።

እንዲህ የምንለው የሰይጣንን ጠላትነት ለማቃለል ሳይሆን ብርቱም ሆነ ደካማ እንዲሆን የሚያደርገውን ምስጥር አውቀን በአግባቡ መዋጋት እና ድል መንሳት እንድንችል ለማንቃት ነው። ሰይጣንን ድል ለመንሳት የግድ ሰይጣን ተኮር መሆን አያስፈልገንምና። ሰይጣን ያለ ሥጋ ሕይወት ከንቱ ነው። መንግሥት የመሠረተውና የዚህ ዓለም ገዥ የሆነው በአዳም መተላለፍ ምክንያት የሥጋን ሕይወት በኃጢአት መርዞ በመግዛቱ ነው። ስለዚህ የሰይጣንና የመንግሥቱ ኃይልና ብርታት የተመሠረተው በኃጢአት በተበከለው የሥጋ ሕይወት ላይ ነው። የዲያቢሎስን ሥራ ለማፍረስ የተገለጠው የእግዚአብሔር ልጅ ሰይጣንንና መንግሥቱን ድል የነሳው ከሰይጣን ጋር ፊት ለፊት ግብ ግብ በመግጠም ሳይሆን ሥጋውን ለሞት አሳልፎ በመስጠት ነበር። ለዚህ ነው የኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀል ሞት ለጨለማው ዓለም ሽንፈት ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል የሆነው።

የጌታ የሱስ የመስቀል ሥራ የሥጋን ሕይወት በማስወገድ ሰይጣንን ሽባ አድርጎታል። ይህንንም ጳውሎስ ለቆላስያስ ሰዎች በፃፈው መልእክቱ እንዲህ በማለት ገልፆታል፦

> «የአለቆችንና የባለሥልጣናትንም ማዕረግ በመግፈፍ በመስቀሉ ድል ነስቶ በአዳባይ አያዘራቸው አንዲታዩ አደረገ።» ቆላ. 2፡15 (አ.መ.ት)

ይህ እውነት የክርስቶስ ተከታዮች በሥጋ ሕይወት ላይ በመሥራት ሰይጣንን ድል መንሳት እንደሚችሉ ያስገነዝባል።

የዲያቢሎስን ሥራ ልናፈርስ የምንችሰው በመንፈስ ቅዱስ ተመርተን የሥጋን ሥራ በማስወገድ በረቂቅ ተንኮሉ ሳንታለል አሳቡን መቃወም ስንችል እንጂ የግድ ከመናፍስት ጋር ጉሮሮ ለጉሮሮ ስለተናነቅን ብቻ አይደለም።

ጠላታችን ዲያቢሎስ ከሁሉ የሚበልጠው የእግዚአብሔርን ኃይል በውስጣችን መኖሩን ስለሚያውቅ ፊት ለፊት ሊገጥመን አይደፍርም። ነገር ግን በሥጋ ነገር በመጠላለፍ በሩቅ ሊያስቀረን ይጥራል። አስቀስድመን ነቅተን የሥጋን ሥራ በመንፈስ ከገደልን ግን የማዕረግ ልብሱንና የጦር እቃውን እንደተገፈፈ ወታደር ፈርጥጦ ከመሸሽ በስተቀር በፊታችን የሚቆምበት ድፍረት አይኖረውም።

ይህን አሳብ ለማጠናከር አንድ ተጨማሪ ምሳሌ ላንሳ፦ የእስራኤል ልጆች ከግብጽ የወጡት ምድረበዳውን አቋርጠው ጠላቶቻቸውን ተዋግተው የተስፋይቱን ምድር እንዲወርሱ ነበር። ነገር ግን ሴቶችና ሕፃናት ሳይቆጠሩ ከስድስት መቶ ሺህ የሚበልጠው ያ ትውልድ በምድረ በዳ ወድቆ የቀረው ከእውነተኛ ጠላቶቹ ጋር ሲዋጋ ሳይሆን ከባርነት ቤት በጽኑ እጅ ካወጣው ከእግዚአብሔር ጋር ሲዋጋ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ተዋጉ እግዚአብሔርም አጠፋቸው።

«እነርሱ ግን ለመቁ ቅዱስ መንፈሱንም ስለመረሩ ስለዚህ ተመልሶ ጠላት ሆናቸው እርሱም ተዋጋቸው።» ኢሳ. 64:10-11

«... ጌታ ስንብዕ አገር ሕዝቡን አድኖ የማያምኑትን በኋላ አጠፋቸው ሳሰስባችሁ አወጸአሁ።» ይሁዳ 5:6

ከእግዚአብሔር ጋር በምን ተዋጉ? የኑሮ ስልታቸው ሥጋዊ ስለነበር አንዱ የሚበላ ሥጋ በመመኘት ሲፈታተኑት፣ ሌላ ጊዜ የወርቅ ጥጃ በማምለክ ሲሳለቁበት፣ አንዱ ከሞዓብ ቆነጃጅት ጋር በመሴሰን ሲያስቆጡት፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ውሃ ጠፋ ብለው በማጉረምረም በመረረ አንደበት ሲያጉረመርሙና ሲያጉተመትሙ፣ በመጨረሻም በፊታቸው የተንጣለለውን ርስት ውጡና ውረሱ ሲላቸው የምድሪቱ ሰዎች ከእኛ ይልቅ ይበረታሉና አንችላቸውም በማለት አብሯቸው የነበረውን ከንድ ሲንቁ በየምዕራፉ ረግፈው አለቁ። መንፈስ የሆነው እግዚአብሔር የሥጋ ጠረናቸውን ሊታገሰው አልቻለም። ስለዚህ ጠላቶቻቸው በየአገሩ ዳርቻ ላይ ሥራ ፈተው ተቀምጠው እነርሱ ከአጻኖቸው ጋር ሲዋጉ በምድረ በዳ ወደቁ። የሥጋን ምኞት በመካድ እግዚአብሔርን የተከተሉት እያሱና ካሌብ ግን አዲስ ትውልድ እየመሩ ጠላቶቻቸውም እንደ እንጀራ እየሆኑላቸው የተሰጠውን ተስፋ ወረሱ ብሉም አወረሱ።

እኛም ተስፋችንን ለመውረስ እንችል ዘንድ ትኩረታችንን እንደገና እንቃኝ። «ሰይጣን ተኮር» ከሆነ አመለካከት እንላቀቅ፣ ክርስቶስን ማዕከል አድርጎ የሥጋን ባሕሪ በማስወገድ ላይ ያተኮረ ሕይወት እንምራ።

የሥጋ ሕይወት እንቅፋትነት

ከውስጥ የሰበሰነው ልብስ ከውጭ በምንለብሰው እንደሚሸፈን ሁሉ የውስጥ ሕይወት በውጭ በሚንፀባረቅ ሕይወት መሸፈኑ አይቀርም።

አማኞች የድል ሕይወት ከመምራት ይልቅ ተራና የዘቀጠ ሥጋዊ ኑሮ የምንኖር ከሆነ ይህ የሆነው በውስጣችን የላቀና የከበረ መንፈሳዊ ሕይወት ስለሌለ ሳይሆን ያ ክቡር ሕይወት በሥጋ ሕይወት ስለተሸፈነ ነው። ነገር ግን ሥጋዊነታችን በመንፈስ እንጂ መንፈሳችን በሥጋችን ውስጥ ባለው የኃጢያት ተፈጥሮ ሊሸፈን አይገባውም። የብሉይ ኪዳን ታላቁ ሊቀ ካህን አሮንና ልጆቹ ወደ እግዚአብሔር ፊት ከመቅረባቸው በፊት በብልሃተኛ ጥበብ የተሠራውን ልብስ ተክህኖ እንዲጎናፀፉ የተፈለገው ሥጋቸው በእግዚአብሔር ፊት እንዳይታይ ነበር።[35]

እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት እንኖር ዘንድ ከጥልቅ የሚወጣ ከሰማይ የሚወርድ መፍትሄ አያስፈልገንም። መልሱ በውስጣችን ነው። እግዚአብሔር ያልሰጠን ምንም ነገር የለምና። የሚሰጠንንም ሁሉ በልጁ ሕይወት ውስጥ ጠቅልሎ ሰጥቶናል። ቻይናዊው የእግዚአብሔር ሰው ዋች ማኒ እንደሚለው ሰማይ በመንፈሳዊ ነገሮች የተሞላ አይደለም። በሰማይ ያለው ስብዕና ነው። እርሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱም የመንፈሳዊ ነገሮች ሁሉ ድምርና ሙላት ነው።[36] ስለዚህ የክርስቶስ ሕይወት ካለን የመንፈሳዊ ነገሮች ሁሉ ንጥረ ነገር አለን። ሆኖም ይህ ሕይወት እንዳይገለጥ እንቅፋቱ የሥጋ ሕይወት መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል።

በመንፈሳችን ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር ሕይወት እና በደማችን ውስጥ ያለው የኃጢያት ተፈጥሮ ፈጽመው የተለያዩ እና እርስ በእርስ የሚቀዋወሙ ናቸው። የሚዋጉትም አንዱ ሌላውን በማስገዛት የማንነትን ሠገነት ለመቆጣጠርና ራስን ለውጭው ዓለም ለመገለጥ ነው።

ሥጋም የሥጋን ሥራ መንፈስም የመንፈስን ፍሬ ለመግለጥ ይፋለማሉ። ፍልሚያውም አንድን ሥፍራ ለመያዝ ነው። ያም ሥፍራ አዕምሮ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ በተለይ በአዲስ ኪዳን ነፍስ ወይም ልብ በማለት የሚጠራው ሐሳባችንን፣ ስሜታችንን እና ፈቃዳችንን ነው። እነዚህ ነገሮች አንዳንዱ አእምሮ በሚለው ቃል ይጠቀለላሉ። እኛም ለአገላለጽ እንዲያመቸን ከዚህ በመቀጠል «አእምሮ» በማለት እንጠራዋለን።

አእምሮ የማንነታችን ሠገነት፣ የፍልሚያችን ገዢ መሬት እና የሕይወት መንፀባረቂያ መድረክ ነው። ሕይወት የመንፈስም ይሁን የሥጋ የሚተላለፈውና ለውጪው አለም ራሱን የሚገልፀው በአእምሮ አማካይነት ነው። አእምሮን የተቆጣጠረ የትኛውም ሕይወት ያለምንም ችግር ባሕሪውንና ማንነቱን መግለጽ ይችላል። ይህን ወሳኝ ክፍል ያልተቆጣጠረ ሕይወት ግን ይኖራል እንጂ ምን ይምሰል ምን ለውጭው አለም መታየት አይችልም። እኛ የያዝነው ጉዞ ደግሞ እግዚአብሔርን የመምሰል ጉዞ ነው። እግዚአብሔርን መምሰል በመንፈሳችን የተካፈልነውን የእግዚአብሔር ሕይወት በምድር ኑሮአችን መግለጥ እንደሆነ አስቀድመን ገልፀናል። እንግዲህ ይህ ከዙርና ዘላለማዊ ዓላማ አውን ይሆን ዘንድ ይህ ተግባር በሕይወታችን መከናወኑ የግድ ነው።

እዚህ ጋ እንዳንታለል መጠንቀቅ አስፈላጊ ነው። እየተነጋገርን ያለነው መልካምና ጥሩ ሰው፣ አመለ ሸጋ ወይም ግብረገባዊ ሰው ስለመሆን አይደለም። ይህ በራሱ ምንም ክፋት ባይኖረውም ከእግዚአብሔር ሕይወት ያልፈለቀ ከሆነ ከሰማዳ እንሰሳነት ብዙም የተለየ አይሆንም። አሁን እያየን ያለነው ግን የእግዚአብሔርን ሕይወት በመለማመድ እግዚአብሔርን ስለመምሰል ነው።

በኑሮዎ በቀላሉ የሚገለጠው የእግዚአብሔር ሕይወት ነው? ወይስ የሥጋ ሕይወት? ወደ አእምሮዎ ፈጥኖ ከሚመጡት አሳቦች ያለ አንዳች አክል የሚከናወነው የመንፈስ አሳብ ነው? ወይስ የሥጋ አሳብ? መልሶ የሥጋ አሳብ ከሆነ ምን ያህል አእምሮዎ በሥጋ ሕይወት ቁጥጥር ሥር እንዳለ ያሳያል። የመንፈስ አሳብ ካሉ ደግሞ ተቃራኒውን። ሆኖም የእምሮአችን በመንፈስ ሕይወት ቁጥጥር ሥር መዋል ረጅም ሂደት እንጂ በአንድ ጀምበር የሚፈፀም ክስተት አለመሆኑን ልብ ማለቱ ተገቢ ነው።

በመጀመሪያ የተወለድነው በሥጋ እንጂ በመንፈስ አይደለምና አስቀድሞ ሥፍራ የያዘው ለኃጢያት የሚገዛው የሥጋ ሕይወት ።

> *«ነገር ግን አስቀድሞ ፍጥረታዊ ቀጥሎም መንፈሳዊው ነው እንጂ መንፈሳዊው መጀመሪያው አይደለም።» 1ቆሮ. 15:46*

በክርስቶስ አምነን ስንድን እና መንፈሳችን በእግዚአብሔር ሕይወት አዲስ ሕፃን ሆኖ ሲወለድ የሥጋ ሕይወታችን አእምሮአችንን በመቆጣጠርና ራሱን ለመግለጽ የብዙ ዓመታት ልምድ ነበረው። የክርስቶስ ሕይወት በበዛልን ቁጥር መንፈሳችን እያደገና እየጠነከረ ሲሄድ ግን ራሱን ለመግለጽ ይፈልጋል። ይሄኔ ነው ፍልሚያው የሚጀምረው። አእምሮን

ከሥጋ ሕይወት ቁጥጥር ነፃ አውጥቶ በመንፈስ ሕይወት ቁጥጥር ሥር እንዲውል ማድረግ የአጭር ጊዜ ጉዳይ ሳይሆን ጊዜ የሚፈጅ ሂደት ነው። ሂደቱንም የአእምሮ መታደስ (የነፍስ መዳን) ብለን እንጠራዋለን።[37]

አእምሮአችን ይህን መለኮታዊ ዕውቀት በማግኘት ከታደሰ አሮጌውን ሰው ከነሥራው በመግፈፍ በእውነተኛ ጽድቅና ቅድስና የፈጠረውን እንዲመስል ማድረግ አስቸጋሪ አይሆንም።

የሥጋ ሕይወት እንዴት ሊወገድ ይችላል?

መጀመሪያ ሊወገድ ይችላል ወይ? የሚለውን ጥያቄ ማንሳት መልካም ነው። አምን ሊወገድ ይችላል። ነገር ግን ሙሉ በሙሉ አይደለም። በደም ውስጥ ያለው የኃጢያት ተፈጥሮ ከሰውነታችን ውስጥ ሙሉ በሙሉ የሚወገደው ስንሞት አልያም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በክብር ሊወስደን ሲመጣ ብቻ ነው። እስከዚያው ድረስ ከሁለንተናችን ባይወገድም በአእምሮአችን (በአሳባችን፣ በስሜታችን እና በፈቃዳችን ላይ) ያለው የበላይነት ሊወገድ ይችላል። በምድር በዚህ ድንኳን እያለን ልንጎናፀፈው የምንችለው ትልቅ ድል ቢኖር ይህ ነው።

ይህ የሥጋን ሕይወት (የኃጢአትን ተፈጥሮ) የማስወገዱ ሂደት መንፈስ ቅዱስ የእኛን ፈቃድ በመጠቀም የሚያከናውነው ሥራ ሲሆን ሥራውን ለመፈፀም ሦስት ወሳኝ መሣሪያዎችን ይጠቀማል። እነርሱም፦

1. የእግዚብሔርን ቃል
2. የመስቀሉ መንገድ እና

3. የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ናቸው።

የእግዚአብሔር ቃል

ሥጋ ማለትም በሥጋችን ውስጥ የተሰወረ የኃጢአት ባርያ የሆነ ተፈጥሮ የግድ መወገድ አለበት። እግዚአብሔር ለዚህ አሮጌ ተፈጥሮ ከሞት የተሻለ ምንም መፍትሔ የለውም። እንዲኖር ከተተወ ለኃጢአት ሕልውና በመስጠት ብልቶቻችንን ተጠቅሞ ኃጢአትን በየዓይነቱ ስለሚፈለፍል ሞቱ እንደ ፅድቅ ይቆጠራል። ቅዱስ ቃሉ የሞተስ ከኃጢአቱ ፀድቋል እንደሚል።[38] ይህን ተፈጥሮ ሕግን በማስጠበቅ ማሰልጠንና ሰው ማድረግ ፈጽሞ አይቻልም። በአርግጥ ሕግ አስቀድሞ ተሰጥቶት ነበር ነገር ግን ሕግ በሥጋ ውስጥ ለሚያድረው ኃጢአት ኃይልን በመስጠት ሥጋ ኃጢአቶችን የማፈለፈል ፍጥነቱን ከመጨመር በቀር የሚፈይድለት ነገር የለም። ሰይጣንም ይህን አጋጣሚ በመጠቀም በክስና በሹነኔ ሕሊናን እየደወለ መንፈስን ያደቃል፣ ከእግዚአብሔር ጋር ጎብረት የማድረግ አቅምን ያቀጭጫል።

ስለዚህ ይህ የሕይወት ባሕሪ ቀስ በቀስም ቢሆን የግድ መሞት አለበት። ካልሞተ መጋረጃው አይቀደድም፣ የመንፈስ ሕይወት አይገለጥም፣ እግዚአብሔርን መምሰል አይታይም።

እግዚአብሔር በዚህ ሕይወት ላይ ያለምንም ርህራሄ ሞት ፈርዶበታል። በመስቀል ላይም ጠርቆ ከመንገድ አስወግዶታል። ይህ በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ላይ እዚያና ያኔ የተሠራ እውነት ዛሬ በእኛ ኑሮ ውስጥ እዚህና አሁን እንዲገለጥ የእግዚአብሔር ፍፁም ፈቃድ ነው። ያኔ በክርስቶስ ሥጋ ውስጥ ሊገድለው ያልራራ እግዚአብሔር አሁን በእኔና በእናንተ ሥጋ ሊያደቀው፣ ሊገድለውና ቀስ በቀስ

ከመንገድ ሊያስወግደው ፈጽሞ አይራራም። ነገር ግን የእግዚአብሔር እጅ በሕይወታችን ይህን ትሠራ ዘንድ የእኛ ፈቃድ እጅግ ወሳኝ ነው። «ፈቃደኛ አይደለሁምን?» ብሰን እንጠይቅ ይሆናል። ነገር ግን ፈቃድ በጊዜያዊ ስሜት ላይ የተመረኮዘ ሳይሆን በጠለቀ እውቀት ላይ የሚመሠረት ውሳኔ በመሆኑ የሥጋ ሕይወት ከምኞቱና ከክፉ መሻቱ ጋር ለማስወገድ ወደ ዘላቂ ውሳኔ የሚያደርስ በመገለጥ የሆነ እውቀት ያስፈልጋል።

ከሁለት ሺህ ዓመታታ በፊት እግዚአብሔር አንዱ ለሁላችንም በመስቀል ላይ የገደሰውን ሕይወት አሁን በእኛ ውስጥ የማስወገድን ሥራ ይሠራ ዘንድ ፈቃደኝነታችንን ለእግዚአብሔር ማሳወቅ ይኖርብናል። ወደዚህ ወደቆረጠና ወደጨከነ ውሳኔ እንድንመጣ ደግሞ አስቀድመን እንዳልነው እውቀት የግድ ነው።

ይህ እውቀት የኃጢአት ባሪያ የሆነው የሥጋን ሕይወት ውስጠ ሚስጥር በብርሃን እንድንመለከትና ከእግዚአብሔር እንዲያው ከተሰጠን አዲስ ሕይወት ጋር በማስተያየት አንዱን ለመውረስ በእርሱም ለመውረስ ሌላውን ደግሞ ምንም ያህል ውድ ቢሆን የሚከፈለውን ዋጋ ከፍሎ ለማስወገድ የማያዳግም ውሳኔ ላይ ለመድረስ ይረዳናል። ወደዚህ ውሳኔ ለመድረስ የሚያስችለው እውቀት የሚገኘው በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ብቻ ነው።

ስለዚህ አንዱን ሕይወት የማስወገዱና ሌላውን የመግለጡ ሂደት ከእግዚአብሔር ቃል ይጀምራል ለማለት እንደፍራለን።

የእግዚአብሔር ቃል በውስጣችን ሲበራ የተሰጠንን የእግዚአብሔር ሕይወት እየገለጠ በደስታ በማስፈንደቅ ብቻ አይወሰንም። ከአዳም ዘር የወረስነውን፣ እግዚአብሔር የሚጠላውን፣ ለኃጢአት የማጊዛውን የሥጋን ሕይወት ምንነት

አየገለጠ ያሳየናል። ይህ ልምምድ ምንም እንኳ ለጊዜው ደስ የማያሰኝና ሥራው የሚካሄድበትን ሰው ልብ የሚሰብር ቢሆንም ለታገሰው ውጤቱ የማይለካ ነው። እናም ስንወስን፣ ፈቃደኝነታችንንም ስንገልጽ የሥራው ባለቤት የሆነው መንፈስ ቅዱስ የቃሉን ብርሃን በመጠቀም ተግባሩን ማከናወን ይጀምራል።

የእግዚአብሔር ቃል የመንፈስ ሰይፍ ነው። ሰይፍነቱም በሁለት ይከፈላል። አንዱ ከጌታ አፍ የሚወጣ በእኛ እጅ ያለ ጠላትን ለመቁረጥ የሚያገለግል መንፈሳዊ የጦር ዕቃ ሲሆን ሌላው ከሊቀ ካህኑ እጅ የማይጠፋ፣ በሁለት ወገን የተሳለ፣ ለመስዋትነት የቀረቡትን የአንስሳት ሥጋ ቅልጥምና ጅማት እየለየ በመውጋት ለእግዚአብሔር የተወደዱ መስዋዕት አድርጎ ለማቅረብ የሚጠቀምበት መሣሪያ ነው።

> *«የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና የሚሠራውም ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፣ ነፍስንና መንፈስንም ጅማትንና ቅልጥምንም አስከሊይ ድረስ ይወጋል፣ የልብንም ስሜትና አሳብ ይመረምራል» ዕብ. 4:12*
>
> *«አሀዛብ በመንፈስ ቅዱስ ተቀድሰው የተወደደ መስዋዕት ሲሆኑ ለእግዚአብሔር ወንጌል አንደ ካህን እያገለገልሁ . . . » ሮሜ 15:15*

ካህኑ በያዘው ስለታም ሰይፍ ለመስዋዕት የቀረበለትን እንስሳ አንደ ሥርዓቱ ይበልት እንደነበረ ሁሉ ዛሬም ታላቁ ሊቀካህናችን ኢየሱስ ሰውነታቸውን የተወደደ መስዋዕት አድርገው የሚያቀርቡትን በቃሉ የመለየትና የመግለጥ ሥራ ይሠራል። ታዲያ ስንቶቻችን ነን የእግዚአብሔር ቃል በውስጣችን ገብቶ ከሥጋ የሆነውን ሁሉ አጥርቶ ለይቶ እውነተኛ ተፈጥሮውን እናውቅ ዘንድ እርቃኑን እንዲያሳየን የምንፈቅድ?

ከፈቀድንለት የቃሉ ብርሃን የሥጋዊነታችንን ጥልቅ ተፈጥሮና የጎደፈ ማንነት ገላልጦ ለራሳችን ያሳየንና በመወገዱ ወደ

መስማማት ያመጣናል። ይህም የእግዚአብሔር ቃል በማንበብ፣ በማጥናት በፀሎት መንፈስ በማሰላሰል የሚከናወን ሥራ ነው።

ታዲያ እውነቱ ይህ ከሆነ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ምን ያህል የጠበቀ ዝምድና አለን? መጽሐፍ ቅዱስን ምን ያህል እናነበዋለን? አብረውን ጽድቅን ከሚከተሉ ቅዱሳንስ ጋር ምን ያህል እንካፈለዋለን? መልሳችን በውስጣችን ከሚከናወነው ሥራ መፍጠንና መዘግየት ጋር የተቆራኘ ነውና እናስብበት ብሎት ርምጃ እንውሰድ።

<u>መስቀል</u>

መንፈቅ ቅዱስ የቃሉን ብርሃን በመጠቀም መንፈስንና ሥጋን ለይቶ የሥጋን እውነተኛ ተፈጥሮ በማሳየትና በውስጣችን ካለው የእግዚአብሔር ሕይወት ጋር ያለውን ተቃርኖ በማስረዳት በመወገዱ እንድንስማማ ካደረገን በኋላ ይህን የኃጢአት ሥጋ የማስወገዱ ሂደት ወዲያው በውስጣችን መከናወን ይጀምራል። የሚከናወነውም በመስቀል አማካይነት ነው።

ይህ ሥራ በመስቀል አማካይነት እንዴት እንደሚከናወን ዝርዝር ወደ ሆነ ነገር ከመግባታችን በፊት ራሱ መስቀል ምን እንደሆነ ገልፆ ማየቱ ጠቃሚ ይሆናል። ይህንንም የምናደርገው በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ በአማኞች ዘንድ በርካታ የተዛቡ አመለካከቶች ስለሚስተናገዱና መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነውን ካልሆነው በመለየት ሚዛናዊ አመለካከት ላይ እንድንቆም ለማገዝ ነው።

ስለ መስቀል ሁለት ጽንፈኛ አመለካከቶች አሉ። እንደኛው መስቀልን የመከራና የጉስቁልና ሕይወት ብቻ በማድረግ ከየትኛውም አቅጣጫ የሚመጣን መከራ እየተቀበሉ በስቃይ መኖር

የሚል ጨለምተኛ አመለካከት ሲሆን ሌላኛውና በዘመናችን በስፋት የሚንሸራሸረው አሳብ «ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ እዳችንን ስለከፈለልን መከራ፣ ስደት፣ ችግር የሚባል ነገር ሊያልፍም አይነካንም» የሚል ጽንፍ ነው።

ከረዥም አመታት በፊት «መስቀል» የሚለውን ቃል ለመተርጎም በተዓፈ አንቡተኛ ጽሑፍ ላይ መ= መከራ፣ ስ= ስቃይ፣ ቀ= ቀራንዮ፣ ል= ልመና፣ የሚል ነገር ማንበቤን አስታውሳለሁ። ይህ ዓይነቱ አመለካከት የመጀመሪያውን ጽንፍ የሚወክል ሲሆን ሌላኛው ደግሞ መስቀል አልባ ክርስትና ሕይወትን የማያቀነቅን አስተሳሰብ ነው።

ታዲያ መስቀል ምንድነው? መስቀል መንገድ ነው። የሥጋን ሕይወት ቀስ በቀስ እየገፈፈ በውስጣችን ያለው የእግዚአብሔር ሕይወት እንዲገለጥ ለማድረግ እግዚአብሔር በኪነ ጥበቡ የሚቀይሰውና እንድንሄድበት የሚጋብዘን ጎዳና ነው።

በዚህ መንገድ ላይ መከራ ሊኖር ይችላል። ነገር ግን መከራነቱ ለሥጋችን እንጂ ለመንፈሳችን አይደለም። መከራውም በቀጥታ ሰይጣን የሚያመጣብን ጉስቁልና ሳይሆን በእግዚአብሔር ፈቃድ የምናልፍበት የክብር መንገድ ነው። ዳዊት ከተቀባ በኋላ በብዙ መከራ ውስጥ አልፏል። ነገር ግን የአመፃ ልጅ መከራን እንደማይጨምርበት የተነገረው አስቀድሞ ነበር።

> *«. . . ባሪያዬን ዳዊትን እገኝሁት ቅዱስ ዘይትም ቀባሁት። እጄም ትረዳዋለች ክንዴም ታበርትዋለች። ጠላት በእርሱ ላይ አይጠቀምም የአመፃ ልጅም መከራን አይጨምርብም።» መዝ. 89:20-22*

ጌታ ኢየሱስም ከፊቱ የነበረውን የመስቀል መከራ የገለፀው ሰይጣንና ክፉ ሰዎች የሚያደርሱበት ስቃይ አድርጎ ሳይሆን የዚህ ዓለም ገዥ አንዳች ጥቅም የማይገኝበት አብ በበጎ ፈቃዱ የሰጠው ጽዋ እንደነበረ ነው።

«ከዚህ በኋላ ስለናንተ ጋር ብዙ አልናገርም የዚህ ዓለም ገዥ ይመጣልና በእኔ ላይም አንዳች የለውም ነገር ግን አብን እንድወድ ዓለም ሊያውቅ አብም እንዳዘዘኝ አንዲሁ አደርጋለሁ።» ዮሐ. 14:30-31

«ኢየሱስም ጴጥሮስን፦ ሰይፍህን ወደ ሰገባው ክተተው አብ የሰጠኝን ጽዋ አልጠጣትምን? አለው።» ዮሐ. 18:11

ከዚህ የምንረዳው መስቀል ምንጩ ያልተጣራ መከራን ሁሉ በትእግሥት የምናግበሰብስበት ከንቱ የመከረኛነት ሕይወት አለመሆኑን ነው። በመሠረቱ መስቀል ከሰው አንፃር ሲታይ ሽንፈት ቢመስልም ከእግዚአብሔር አንፃር ላየው ግን ድል የሞላበት የሕይወት ጉዞ ነው። መስቀል ሥራው አንድና ግልጽ ነው። እርሱም የሥጋን ሕይወት በመግደል የመንፈስ ሕይወት በሥጋ አካል ውስጥ እንዲገለጽ መንገድ መጥረግ ነው።

አንዳንድ አማኞች ያለምንም ምርጫ በግድ የመጣባቸውን መከራ ሁሉ «መስቀል» ብለው መጥራት ይቀናቸዋል። መስቀል ግን ያለ ፈቃዳችን በግድ የሚመጣብን ጣጣ ሳይሆን ፈቅደንና ተስማምተን የምንክፈለው፣ እግዚአብሔርም አቅማችንን መጥኖ የሚለቀው፣ ከጀርባው ክብር የሞላበት የጽድቅ ጎዳና ነው።[39] እግዚአብሔር መንፈሳችንን እንደ ቀንዲል ተጠቅሞ[40] በቃሉ ብርሃን ውስጣችንን ገልፆ ቢያሳየን ይህ ስለ እርሱ የምናወራው የሥጋ ሕይወት በእርግጥ መሞት እንዳለበት፣ በተቻለ ፍጥነት መወገድ እንዳለበት የምንወስነው እኛው ራሳችን እንሆን ነበር። ያን ጊዜ መስቀል ውርደት ሳይሆን ክብር፣ ሽንፈት ሳይሆን ድል፣ ውድቀት ሳይሆን ትንሳኤ፣ መጥፋት ሳይሆን መብዛት፣ መሆኑን እንገነዘባለን።

አለዚያ ግን ነገሮች ሁሉ ተቃራኒ ይሆናሉ። በሥጋ ክብር ያልነው ውርደት፣ ነፃነት ያልነው ባርነት፣ ማግኘት ያልነው ማጣት፣ ይሆንብናል። በአካሄዳችንም ለሥጋ አየሳሳን

መንፈስን የምናጠፋ፣ ለክርስቶስ ኢየሱስ መስቀል ጠላቶች ሆነን የምንመላለስ እንሆናለን።

መስቀሉን እንሸሸም ስንል እኛው ራሳችን መከራን ጎትተን እናምጣ ማለታችን አይደለም። ያለ እኛ አስተዋጽኦ ከመጣ ግን እንደ ክርስቶስ ኢየሱስ በጎ ወታደር እንቀበለው እንጂ ከመከራ አንሸሽ ማለታችን ነው። ለነገሩማ በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰልን የምንኖር ከሆነ መከራና ስደት በአድራሻችን ፈልገውን ይመጡ የለ።

ሆኖም የዘመናችንን ክርስትና በጥንቃቄ ስንመረምር ከመከራ የፀዳ፣ መስቀል አልባ አዲስ ኃይማኖት የመሠረትን ይመስላል። አሁን ይህን ክፍል ስጽፍ የምገኘው በእስራኤል አገር ውስጥ ነው። በየቀኑ ስለ አይሁድ ሕዝብ ስለ ምድሪቱና ስለ አይሁድ ኃይማኖት ስጠይቅና ስማር አንድ የሚገርም ነገር ሰማሁ። «አይሁዳውያን በየሰንበቱ በምኩራቦቻቸው የነቢያትን መጽሐፍት ያነባሉ። ታዲያ ምንጊዜም የኢሳይያስ መጽሐፍ ሲነበብ ማንኛውም ተራ የደረሰው አንባቢ እንደ አጋጣሚ ምዕራፍ 53 ላይ ከደረሰ ያለምንም ጥያቄ ዘሎት ያልፋል እንጂ የትኛውም ተራ ሰው ሆነ መምህር አያነበውም አሉ። ለምን? ስለ መስቀል ስለሚናገር። ሲጠየቁም መልሳቸው «እኛ መሲሁ እንደሚነግሥና እንደሚገዛ እንጂ እንደሚዋረድና መከራ እንደሚቀበል መስማት አንፈልግም» ይላሉ። ለዚህም ነው የናዝሬቱ ኢየሱስን መሲህ አድርገው መቀበል የተሳናቸው።

እስልምናም ቢሆን ኢየሱስ ከመወለዱ በፊት መኖሩን፣ ከድንግል መወለዱን፣ ማስተማሩንና ተዓምራቶችን መሥራቱን እቀበላለሁ ቢልም በመስቀል ላይ ሞተ መባሉን መስማት አልፈልግም፤ እርሱን የመሰለ መልእክተኛ እንዴት መከራን ይቀበላል? በማለት በመስቀል መሞትን የውርደትና የሽንፈት

ሜዳ አድርጎ ይናገራል። ይህ ሁሉ በእግዚአብሔር እርዳታ ካልሆነ በቀር የመስቀሉን ሥራ መረዳት አስቸጋሪ መሆኑን ይጠቁመናል።

እንግዲህ እግዚአብሔርን በመምሰል ማደግ የምንፈልግ ከሆነ በመስቀሉ ጎዳና ከመንዝ ሌላ ምንም አማራጭ የለንም። የሥጋ ሥራ ሲገፈፍ የእግዚአብሔር ሕይወት በሚሞተው ሥጋችን ሲገለጥ የሚችልበት ብቸኛ የእግዚአብሔር ጥበብ መስቀል ነውና። «ልጄ ሆይ ልብህን ስጠኝ ዐይኖችህም መንገዴን ይውደዱ» ተብሎ እንደተፃፈ የመስቀሉን መንገድ እንወቀው፣ እንውደደው፣ እንሂድበት።

<u>የመንፈስ ቅዱስ ኃይል</u>

በቃሉ ብርሃን የሥጋና የመንፈስን ሕይወት ለይተን አየን፣ በመስቀሉ መንገድ የሥጋ ሕይወት የሚሻርበትንና የሚወገድበትን ጉዞ ጀመርን ከዚህ በኋላ የሚቀረውና ቀጣዩ ክንውን የመንፈሳችን በኃይል መጠንከር ነው። እነዚህ ሦስቱ በአግባቡ ከተከናወኑ የእግዚአብሔር ሕይወት በሥጋ አካል በምድር ኑሮአችን ውስጥ ይገለጣል ያንንም እግዚአብሔርን መምሰል ብለን እንጠራዋለን። መንፈሳችን ምንም እንኳ የእግዚአብሔርን ሕይወት ቢካፈልም ሕፃን ሆኖ በመወለድ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የገባ አዲስ ፍጥረት እንጂ ሙሉ ሰው ሆኖ አልተፈጠረም[41]። ሕፃኑ መንፈሳችን አሳብን ስሜትንና ፈቃድን በመቆጣጠር ሥጋን አስገዝቶ ማንነቱን ለመግለጽ በሚያደርገው ፈታኝና እልህ አስጨራሽ ጉዞ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይሄ ነው የማይባል ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል።

የውስጥ ሰውነታችን ሲያደክሙትና ሲያደቁት በተከማቹ ኃይላት የተከበበ ነው። እነዚህም ኃይላት እርስ በርሳቸው

ይደጋገፋሉ። ሞት ኃጢአትን እንደጦር ሰብቆ ሥጋን እንደፈረስ እየጋለበ መንፈሳችንን ሊወጋ ዘወትር ይዘምታል። በዙሪያችን ያሉ የክፋት መንፈሳዊያን ሠራዊት የሞትን ድል መንሣት እየቋመጡ የመንፈሳችንን ተወግቶ መውደቅ ለማየት በመናፈቅ በሰልፉ ሜዳ ውስጥ በአመጽ ያቅራራሉ። ታዲያ ለዚህ የኃይል ወረራ መፍትሔው ከኃይል ውጭ ሌላ ምንም ሊሆን አይችልም። ኃይል በኃይል ይመከታልና። እግዚአብሔርን በመምሰል ሂደት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ያስፈለገንም በየጊዜው ለሚገጥመን የኃይል ተግዳሮት መንፈሳችንን ለማጠንከር ነው። ይህን በተመለከተ የጠራ አመለካከት እንዲኖረን ሐዋርያው ጳውሎስ የሚለውን እንይ፦

> *«... በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታችሁ በኃይል እንድትጠነክሩ ክርስቶስም በልባችሁ በእምነት እንዲኖር እንደክብሩ ባለጥግነት መጠን ይስጣችሁ ...»* ኤፌ. 3:16

መንፈሳችን ሥጋንም ሆነ ሥጋን በመጠቀም የሚዋጉንን የክፋት ኃይላት ለመቃወም እና ክርስቶስን መስሎ ለመኖር ጥንካሬ ያስፈልገዋል። ያም ጥንካሬ የሚገኘው መንፈስ ቅዱስ በሚሰጠው ኃይል ውስጥ ብቻ ነው።

ይህ ኃይል ካመንበት ጊዜ አንስቶ ዘወትር በእኛ ዘንድ አለ። ለመሥራትና ለመንቀሳቀስ ግን የሚጠቀው የእኛን ፈቃድ ነው። ዝለንና ደክመን በወደቅንበት ወይም በጠላት ፍላፃ ቆስለን ተስፋ በቆረጥንበት ሰዓት እንኳ ይህ ኃይል ከእኛ ጋር ነበር። ሆኖም የሚሠራው በእኛ እምነት ውስጥ አልፎ ስለሆነ የእምነት በር እስከንከፍት ይጠብቃል። ይህ ኃይል መንፈሳችንን በማጠንከር ርስታችን የሆነውን የእግዚአብሔር ሕይወት ከቅዱሳን ጋር እንድንካፈል ያበረታናል። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን የሕይወት ርስት ያውቁ ዘንድ የልባቸው ዐይኖች እንዲበሩ ለሚፀልይላቸው ቅዱሳን የጥበብና የመገለጥ መንፈስ እንዲሰጣችሁ የምጸልየው

«... ለምናምንም ከሁሉ የሚበልጥ የኃይሉ ታላቅነት ምን እንዲሆን ታውቁ ዘንድ . . . ነው።» ኤፌ. 1:19

በማለት ይነግራቸዋል። ይህ ኃይል በእምነት የሚሠራና የእግዚአብሔር ክብር ከሰማይ እስከሚገለጥበት ቀን ድረስ የሚጠብቀን ስለመሆኑ ሐዋርያው ጴጥሮስ እንዲህ በማለት ይጽፋል፦

«ይህም ርስት በመጨረሻው ዘመን ይገለጥ ዘንድ ለተዘጋጀ መዳን በእምነት በእግዚአብሔር ለተጠበቃችሁ ለእናንተ በሰማይ ቀርቶላችኋል።» 1ጴጥ. 1:5

ታዲያ ይህን ኃይል እንዴት ነው የምንለማመደው? ይህን ኃይል ለመለማመድ ፀሎት ትልቅ ድርሻ አለው። ፀሎት ራሱን የቻለ ሰፊ ዓለም ነው። አምልኮ፣ ምሥጋና፣ ዝማሬ፣ ምልጃ፣ መጋደል፣ ልመና ወ.ዘ.ተ. በፀሎት ውስጥ የሚካሄዱ አብይ ተግባራት ናቸው። እናም በእያንዳንዱ ዘርፍ ውስጥ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ስለምንገናኝ ኃይል ከእርሱ እየወጣ ያበረታናል። ምንም እንኳ ፀሎት በከብደት እንጂ በርቀት የማይለካ ቢሆንም በመንፈስ ነቅተን በጌታ ፊት የምናሳልፈው ቆይታ በውስጥ ሰውነታችን ኃይሉን ለመካፈልና ብርታት ለመሰነቅ እጅግ ጠቃሚ ነው። ሥጋችንን ገዝተን አእምሮአችን ቃሉን እያሰላሰለ በጌታ ፊት በቆይታ በምንቆይባቸው ጊዜያት የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በውስጣችን ሲንቀሳቀስ ሊታወቀን ይችላል። ዶሮ እንቁላልዋን እንደምትታቀፍ በምትሰጠውም የመቀት ኃይል የእንቁላሉ ውስጠኛ አካል እየጠነከረ ነፍስ እንደሚዘራ በኋላም የውጭውን ቅርፊት ሰብሮ ሕያው ሆኖ እንደሚገለጥ ሁሉ መንፈስ ቅዱስም ከላያችን በመስፈፍ የውስጥ ሰውነታችንን በኃይል አጠንክሮ ክርስቶስ በኑሮአችን እንዲገለጥ ያደርጋል። ይህ ድንቅ ሥራ በሕይወታችን ይከናወን ዘንድ በፀሎት ከመትጋት ሌላ ምንም አማራጭ የለውም።

6
የምሳሌ ያለህ

አንድ ቀን ከባለቤቴ ጋር ወደ አንድ ቦታ ወጣ ብለን መምጣት አሰብንና መዘጋጀት ጀመርን። ለባብሰን ከጨረስን በኋላ ዘወትር እናታ ከቤት ስጥወጣ የምትከፋውን ትንሿን ልጃችንን «ፍቅርን» ለማግባባት ፅጣው እኔ ላይ ወደቀና በርከክ ብዬ በልጅ አነጋገር፦ «ፍቅር ምን ገዝቼልሽ እንድመጣ ትፈልጊያለሽ?» አልኳት እኔ እያወራኋት ሳለ እናታ በጓሮ በር እንድትወጣ በማሰብ።

የሁለት ዓመት የልደት ሻማዋን በቅርቡ ያጠፋችው ፍቅር ግን ዐይኖቿን ከእኔ ላይ ነቅላ የጓሮውን በር በመልከት «ሞኝህን ፈልግ!» አለችኝ። ተነቅቶብሃል በሚል ስሜት። ለጥቂት ሰኮንዶች መብረቅ እንደመታው ሰው ደርቄ ቀረሁ። በምንም ተአምር ከሁለት ዓመት ሕፃን ይሄን መልስ አልጠበቅሁም። ከእኔ አብራክ መውጣቷን እስክጠራጠር ድረስ አነጋገርዋ አስደነቀኝ። ሆኖም ይህን አባባል ፍቅር ከሆድ ተምራው አልወጣችም ከእኛው ሰምታው እንጂ። ከትንሿ ፍቅር አንደበት ስለማው ቢያስደንቀኝም እኛ አዋቂዎቹ እንደቀልድ የምንናገረው ቃል ነበር።

እግዚአብሔር አዳምን በመልኩና በምሳሌው እንደፈጠረ የሚነግረን መጽሐፍ ቅዱስ ከጥቂት ምዕራፎች በኋላ አዳምም ልጅን በመልኩና በምሳሌው እንዳወለደ ይነግረናል።

እኛ ዛሬ ልጆችን በመልካችን እና በምሳሌያችን እንወልዳለን ብሎም እናሳድጋለን እንጂ አዲስ ነገር ልንፈጥር አንችልም።

ልጆች በዙሪያቸው ያለነውን ሊመስሉ መርጠው አይደለም። ክፉውንም ደጉንም ይቀስማሉ። እንኪን ነፍስ ማወቅ የጀመሩ አዳጊዎች ስለ መኖራቸው ልብ የማንላቸው እግራችን ስር ውር ውር የሚሉ ጨቅላዎች ያያሉ፣ ይሰማሉ ጊዜ ጠብቀው ያንኑ ይደግማሉ።

ይህ የመምሰል ጉዳይ በሕፃናት ብቻ ሳይሆን በአዋቂዎችም ዘንድ ይስተዋላል። በእርግጥ ሰው ያየውን ሁሉ አይመስልም። የሚያከብረውን፣ የሚማርከውን፣ የሚስበውን ይመስላል። አንዳንዴ አውቆ ብዙ ጊዜ ግን ሳያውቅ ይመስላል። መምሰሉንም ያስተዋሉት ይነግሩታል እንጂ እርሱ ራሱ ላይገነዘበው ይችላል።

መሪነት የሥልጣን ወንበር ሳይሆን በሰዎች ሕይወት ውስጥ ተጽእኖ ማምጣት እንደሆነ ይታመናል።

ተጽእኖ በሁለት ተከፍሎ የሚታይ ነው። በጎ ተጽእኖ፣ ክፉ ተጽእኖ። እናም ማንም ከእነዚህ ሁለት ተጽእኖ ውጭ መሆን አይችልም። እነዚህ ተጽእኖ አምጪዎች ከእኛ ብዙም የራቁ ላይሆኑ ይችላሉ። ቤተሰብ ውስጥ አባት፣ እናት፣ ታላላቅ ወንድምና እህት፣ ቤተክርስቲያን ውስጥ አገልጋዮች፣ መሪዎች፣ መሥሪያ ቤት አለቆች፣ በትምህርት ቤት መምህራን፣ በማኅበራዊ ኑሮ ስፖርተኞች፣ አርቲስቶች፣ ወይም የፖለቲካ መሪዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ለዚህ ነው ግለሰቦች ቤተሰብን፣ ቤተሰብ ማኅበረሰብን፣ ማኅበረሰብ ሕዝብን፣ ሕዝብም አገርን የሚቀርጸውና ብሔራዊ ማንነት የሚፈጠረው። የዚህ ሁሉ ጥንቅር አንድ ኅብረተሰብ የራሱ የሆነ መገለጫ፣ መታወቂያና መለያ እንዲኖረው ያደርጋል።

የሁሉ ባለቤት የሆነው እግዚአብሔር በሰው ውስጥ ያስቀመጠውን የመምሰል አቅም በዋዛ አይመለከተውም። የሚመጣው ትውልድ ገጽታ እንዳይበላሽ አባቶችን ይጠራል። ልጆችን ከመስጠቱ በፊት ጊዜ ወስዶ ይቀርፃል ከዚያም ይባርካል ያበዛል።

አብርሃም ፡- የእምነት ምሳሌ

ለዚህም ቀደምት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌያችን አብርሃም ነው። ከስሙ እንደምንረዳው እግዚአብሔር ይህን ሰው የጠራው ለብዙ ሕዝቦች አባት ሊያደርገው ነው። ያውም የእምነት አባት። ለዚህ ነው እምነትን ሊማር፣ በእምነት ሊፈተንና በሞሪያ ተራራ በእምነት ሊመረቅ ያስፈለገው። ይህ ስልጠና የዋዛ አልነበረም። 25 ዓመታት የፈጀ ረዥም ጉዞ ነበር። እግዚአብሔር ይህን ሁሉ ዘመን ከአብርሃም ጋር የደከመው አንድ ሰው ብቻ በማሰብ ሳይሆን እንደ ባሕር ዳር አሸዋ፣ እንደ ሰማይ ክዋክብት የማይቆጠር ሕዝብ በውስጡ አያየ ነበር። ዋና ዓላማውም ከእርሱ በኋላ ለሚመጣው ለዘሩ ሁሉ ምሳሌ እንዲሆን ነበር።

> *«እግዚአብሔርም አለ፦ እኔ የማደርገውን ከአብርሃም አሰውራለሁን? አብርሃም በእውነት ታላቅና ብርቱ ሕዝብ ይሆናልና የምድር አሕዛብም ሁሉ በእርሱ ይባረካሉና። ጽድቅንና ፍርድን በማድረግ የእግዚአብሔርን መንገድ ይጠብቁ ዘንድ ልጆቹንና ከእርሱ በኋላ ቤቱን እንዲያዝ አውቃለሁና። ይህም እግዚአብሔር በአብርሃም ላይ የተናገረውን ነገር ሁሉ ያመጣ ዘንድ ነው።»* ዘፍ. 18:17-19

በዚህ ክፍል ውስጥ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ የእግዚአብሔር ንግግር «ጽድቅንና ፍርድን በማድረግ የእግዚአብሔርን መንገድ ይጠብቁ ዘንድ ልጆቹንና ከእርሱ በኋላ ቤቱን እንዲያዝ አውቃለሁና።» የሚለው ነው። ይህ አባባል የአብርሃም ሕይወት ምሳሌነት በኖረበት ዘመን ብቻ የተገለደ ላይሆን እስከ ዓለም መጨረሻ የሚዘልቅ መሆኑን ያመልክተናል።

የአብርሃም ምሳሌነት በሥጋ ልጆቹ ለነበሩት ለእስራኤላውያን ብቻ ሳይሆን በእምነት ፈለጉን ከተከተሉ ስፍር ቁጥር ለሌላቸው አሕዛብ ጭምር ሆኖአል።

የአብርሃም ምሳሌነት ከባድ የማያደርገው ምሳሌነቱን ይከተል ዘንድ ከእርሱ በፊት እርሱ የተጓዘውን መንገድ የሄደበት ሰው በቅርብም ሆነ በቅርብ ሩቅ አለመኖሩ ነው። ከእርሱ በኋላ የመጡት ልጆቹ እርሱን ተመልክተው የሆኑትን ቢሆኑም እርሱ ግን ከፊቱ የሚመለከተው አንዳች ሰው አልነበረውም። ከዚህ በመነሣት በዘመኑ በዓለም ላይ የነበረ አንድ ብቸኛ የእግዚአብሔር ተከታይ እርሱ ነበር ማለት ይቻላል። ይኖርበት በነበረው አገር ከእርሱ በፊት አባቶቹ በዙሪያው የነበሩ አሕዮቹ ጣኦታትን ሲያመልኩ እርሱ ግን ወዴት እንደሚሄድ እንኳን ሳያውቅ በተስፋ ወደተሰጠው ምድር ለመውጣት በእምነት ታዘዘ።

አብርሃም ለዘሩ የተስፋ ምሳሌ ነበር፣ የኪዳን ምሳሌ ነበር፣ እግዚአብሔርን የመስማትና የመታዘዝ ምሳሌ ነበር፣ በደረሰበት ሁሉ መሰዊያ በመሥራትና መሥዋዕት በማቅረብ የእውነተኛ አምልኮ ምሳሌ ነበር፣ ራሱን፣ ልጆቹንና በቤቱ የሚኖሩትን ወንዶች ሁሉ በመገረዝ የሥጋን ሽለፈት የማስወገድ ምሳሌ ነበር፣ አብረውት ከልጆቹ ጋር በድንኳን በመቀመጥ የእንግድነትና የመፃተኝነት ኑሮ በመኖር ሰማያዊቱን አገር የመጠበቅ ምሳሌ ነበር፣ ከሁሉ በላይ ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ተስፋ በእምነት በመውረስ የእምነት ምሳሌ የእምነት አባት ሆኖአል።

የእምነት ምሳሌ መሆን ቀላል ነገር አይደለም። ምክንያቱም እምነት የእለት ተእለት ኑሮ እንጂ የአንድ ቀን ጀብዱ አይደለምና። ነገር ሁሉ በተመቻቸበት የሰላም ቀን የእምነት

ሰው መስሉ መታየት ይቻል ይሆናል። እምነት የሚመዘንበት ሚዛን፣ የሚነጥርበት እሣት ሲመጣ ግን በፈተና ቀን ፀንቶ በመቆም ለሌሎች ምሳሌ መሆን በእግዚአብሔር እጅ መሠራትንና በእምነት ማደግን ይጠይቃል። ለዚህ ነው የዕብራውያን መልዕክት ጸሐፊ ምናልባት አሁን በሥጋ ሕይወት የሌሉትን የቀድሞ መሪዎቻቸውን በማስታወስ መከራ በሆነበት በትልቅ ተጋድሎ የኖሩበትን እምነትና ያም እምነት ያፈራውን ፍሬ በመጥቀስ እንዲመስሏቸው የሚመክረው።

> *«የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩላችሁን ዎናቻችሁን ለሰዙ የኑሮአቸውንም ፍሬ አየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሉአቸው።» ዕብ. 13:7*

ታዲያ በእምነት ለሌሎች ምሳሌ ለመሆን የግድ ዋና መሆን በእድሜ መግፋት ወይም በሞት ማለፍ አያስፈልግም። ለዚህም ሐዋርያው ጳውሎስ ለወጣቱ ጢሞቴዎስ

> *«... በቃልና በኑሮ በፍቅርም በእምነትም በንጽህናም ለሚያምኑቱ ምሳሌ ሁን እንጂ ማንም ታናሽነትህን አይናቀው።» 1ጢሞ. 4:12*

ብሎ መፃፉን ማስታወስ በቂ ነው።

ወደተነሳንበት ወደ አብርሃም ስንመለስ የአብርሃም እምነትና ከእምነት የሚነሳ መታዘዝ ለዘመናትና ለትውልዳችን የማይሽር ምሳሌ መሆኑን እንመለከታለን። ከዓለም የወጣነው እንደ አብርሃም ነው። የተጠራነው እንደ አብርሃም ነው። ከአባቶቻችን ቤት ከዘመዶቻችንና ከሕዝባችን የኑሮ ስልት የተለየነው እንደ አብርሃም ነው። እምነታችን ጽድቅ ሆኖ የተቆጠረልን እንደ አብርሃም ነው። የሥጋን ባሕሪ ለማስወገድ የመስቀሉ ስለት በሥጋችን እንዲያልፍ በመፍቀድ የልብን ግርዛት የምንቀበለው እንደ አብርሃም ነው። ከእግዚአብሔር የተቀበልነውን ተስፋ ለመውረስ የምንጓዘው እንደ አብርሃም ነው። ይህም እውነት እግዚአብሔርን በመምሰል ሂደት ውስጥ የምሳሌዎች ድርሻ ከፍተኛ መሆኑን ያሳየናል።

ምንም እንኳ ይህን በጥቅሱ ብልም የእግዚአብሔርን አባታዊ ባሕሪ የተላበሱ ጸጋ በበዛላቸው መጠን ለብዙዎች ምሳሌ የሚሆኑ ግለሰቦች መኖራቸው በፍፁም መካድ አይቻልም። በየዘመናቱ እግዚአብሔር ራሱን ያለ ምስክር አይተውምና የሱም ብንል የእግዚአብሔርን ሥራ መካድ ይሆንብናል። ሙሴ ያዕቆብ ስለገመው ስሮቤል እና ለነገዱ

> «ሮቤል በሕይወት ይኑር አይመትም ሰዎቹም በቁጥር ብዙ ይሁኑ።» ዘዳ 33:6

በማለት እንደማለደ አባቶች በሕይወት ይኑሩልን ቁጥራቸውም ይብዛ እንጂ አይነስ እያልን ነው።

አንዳንድ ጊዜ ወጣቶች በሥርዓት ላለመሄዳቸው ምክንያቱ ምሳሌ የሚሆኑ መንፈሳዊ አባቶች አለመኖራቸው እንደሆነ ሲናገሩ ይደመጣል። ሆኖም እንዲህ ዓይነቱ ማመካኘት በእግዚአብሔርም ሆነ በሰው ዘንድ ተቀባይነት ሊኖረው አይቻልም መንፈሳዊ አባቶች በዙሪያችን ባይኖሩና ያሉትም መጥፎ ምሳሌነትን የሚያሣዩ ቢሆኑም የሁሉ አባት የሆነ እግዚአብሔር በሰማይ መኖሩን መዘንጋት አይገባም። የአባቶች ሁሉ ምሳሌነት ቢደበዝዝም እርሱ በዙፋኑ ላይ ለዘላለም እንደደመቀ ይኖራል። ያም አባትነት ከእኛ የራቀ አይደለም። መንፈስ ቅዱስ ቃሉን እያበራ በየዕለቱ ልምምዳችን አባትነቱን በቃልም በተግባርም ያሳየናልና። በመሠረቱ የእግዚአብሔርን አባትነት ያልተረዳና ያልተለማመደ ሰው የሰዎችን አባትነት እንዴት ሊመዝን ይችላል?

ስለዚህ የአባቶች አለመኖር በሥርዓት ላለመሄዳችን አስተዋጽኦ ቢኖረውም እንኳ እንደ ዋና ምክንያት ተወስዶ ለሥነ አርነት ሊሰጥ አይገባም። ምሳሌ የሚሆኑ አባቶች በሌለበት መንፈሳዊ ልጅ ብሎም መንፈሳዊ አባት መሆን እንደማይችል የሚያስተምረንን የሳሙኤልን ታሪክ እንመልከት።

ጡት ከጣለበት ጊዜ አንስቶ ወላጆቹ በእግዚአብሔር ፊት እንዲያድግ በሴሎ በነበረው የእግዚአብሔር ማደሪያ ትተውት የሄዱት ሳሙኤል እያየ ያደገው ጥሩ ምሳሌ የሚሆን መንፈሳዊ አባት አልነበረም። ይልቅ ካህናት ተብዬ ልጆቹ በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ከሚያገለግሉ ደናግል ሴቶች ጋር ሲያመነዝሩ የዝሆን ጆሮ ስጠኝ ብሉ ሰምቶ እንዳልሰማ ዝም የሚል፣ ለእግዚአብሔር መስዋዕት ለማቅረብ ከድፍን እስራኤል ከሚመጡት አምላኪዎች ጋር ሰቡን ካልሰጣችሁት የተቀቀለውን አንበላም በማለት በመሠዊያው አጠገብ ሥጋ ሲጎተቱ አይቶ እንዳላየ ዝም የሚል፣ ፍርድ እየመጣበት እንደሆነ የሚያስጠነቅቅ ነቢይ ተልኮ ሲነግረው «እርሱ እግዚአብሔር ነው የወደደውን ያድርግ» በማለት በቸልተኝነት የሚመልስ ከነቤተሰቡ መንፈሳዊነት የጠፋበት ዐይኑ የፈዘዘ ጉልበቱ የደነዘ ሰው ነበር። ሳሙኤል ግን እግዚአብሔርን በመፍራት እንዲያድግና በሥርዓት እንዳይሄድ ይሄ ሁሉ ምክንያት ቢኖረውም ፈጽሞ አላስተናገደውም ነበር። ይልቅ ከዚህ ሁሉ ግርዶሽ ባሻገር የእግዚአብሔር የአባትነት ድምጽ አሳደገው። የእግዚአብሔር ቃል ቀረፀው። ከዚያ ከተበላሸ ክበብ ውስጥ ኪዳን እስከቤርሳቤህ ለእስራኤል ሁሉ አባት የሚሆን ነቢይ ወጣ። ይህ ሕያው ታሪክ ለእኛ ለዛሬዎቹ የሚያበራ ደማቅ ምሳሌ ነው።

የጳውሎስ የምሳሌነት አስተምህሮና ልምምድ

ወደ ዛሬው የእኛ ሁኔታ ከመምጣታችን በፊት አስቀድመን የዚህን እውነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሩይዳ እንመልከት።

ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለምላሉነት ትምህርትና ተግባር እንደ አብነት የምንወስደው በአንደኛው ክፍለ ዘመን የኖረውን የተርሴሱን ጳውሎስ ነው። ጳውሎስ በግል ሕይወቱ ክርስቶስን ለመምሰል ስለነበረው ትጋትም ሆነ የሚያገለግላቸው አማኞች ወደዚህ ግብ እንዲደርሱ ስለነበረው ቅናት ብዙ ጽፎልናል። ከእነዚህም መካከል ጥቂቱን እንመለከታለን። ታዲያ እነዚህን ክፍሎች ስንመለከት አሳቦቹን ከአውዱ ነጥለን ለመተርጎም እንዳንፈተንና ትክክለኛ መልእክታቸውን እንዳንስት በየክፍላቸው ውስጥ ተወስነን ለማየት እንሞክር።

ምሳሌነት በአንደኛ ቆሮንቶስ

> *«ይህን የምጽፍላችሁ እንደተወደዳችሁ ልጆቼ አድርጌ ልመክራችሁ እንጂ ላሳፍራችሁ ብዬ አይደለም። ምንም አንኳ በአሥር ሺህ የሚቆጠሩ ሞግዚቶች በክርስቶስ ቢኖሩአችሁም ብዙ አባቶች ግን የሉአችሁም በወንጌል አማካይነት በክርስቶስ ኢየሱስ ወልጃችኋለሁና። ስለዚህ እኔን እንድትመስሉ አሰምናችኃለሁ። እንግዲህ በጌታ የተወደደውንና የታመነውን ልጄን ጢሞቴዎስን የላክሁላችሁ በዚህ ምክንያት ነው። እርሱም በየስፍራው በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ከማስተምረው ትምህርት ጋር የሚስማማውን በክርስቶስ ኢየሱስ ያለውን የሕይወት አካሄዴን ያሳስባችኋል።»1ቆሮ. 4:14-17 (ንባቡም ከመቀጠሉ በፊት ምዕራፉን በሙሉ ቢያነቡት ይመረጣል)*

በመሠረቱ ይህንን ክፍል ለመተርጎም መሞከር አያስፈልግም በራሱ የተተረጎመና ግልጽ ነውና። ነገር ግን «እኔን እንድትመስሉ አሰምናችኃለሁ።» ሲል በምን እንዲመስሉት ማለቱ እንደሆነ ግልጽ እንዲሆን ብቻ ጥቂት እንበል።

ጳውሎስ ለቆሮንቶስ አማኞች ከብዙ ሞግዚቶች መካከል እንደ አንዱ ሳይሆን በክርስቶስ ወንጌል በብዙ መከራ አምጦ የወለደ አባት እንደሆነ በድፍረት ያሳስባቸዋል። አባት ከሆነ ደግሞ ሊመስሉት እንደሚገባ በመግለጽ ይማፀናል። ለመምሰል ማየት ወሳኝ ነውና በጊዜው እርሱ መምጣት ባይቻልም «ልጄ»

የሚለውን ጢሞቴዎስን ሊልክላቸው እናያለን። ጢሞቴዎስን የመረጠበትን ምክንያት ሲገልጽ «በየሥፍራው በሚገኙ አብያተክርስቲያናት ሁሉ ከማስተምረው ትምህርት ጋር የሚስማማውን በክርስቶስ ኢየሱስ ያለውን የሕይወት አካሄድን ያሳስባችኋል።» ይላል። የቆሮንቶስ ሰዎች በጢሞቴዎስ በኩል ጳውሎስን እንዲመስሉ ሲጋብዙ ስናይ ጳውሎስም በክርስቶስ በኩል እግዚአብሔርን ለመምሠል ያለውን ትጋት ስንመለከት «የመምሠል ሰንሰለት» ወይም «የመምሠል ቅብብሎሽ» በጉልህ ይታየናል።

እንግዲህ ጥሪው «እኛን ምሰሉ» የሚል ነው። ለምን? የቆሮንቶስ ሰዎች የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ያገኙት፣ ሃብታም የሆኑት፣ የነገሡት (የምፀት ንግግር ቢሆንም) በሥጋ ነው። በመንፈስ ግን የሚያስፈልጋቸውን አጥተዋል፣ ደህይተዋል፣ ተዋርደዋል። እነ ጳውሎስ ሞት እንደተፈረደባቸው ሰዎች ከሁሉ መጨረሻ የተሰለፉት፣ ለመላእክት ለሰዎችም ትርዒት የሆኑት በሥጋ እንጂ በመንፈስ አይደለም። ይልቅ በመንፈስ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ አግኝተዋል፣ በልጽገዋል፣ በእውነተኛ መንገሥ በሕይወት ነግሠዋል። የቆሮንቶስ ሰዎች መንፈሳዊውን ከሥጋዊው የሚመጣውን ዘመን ከእሁኑ አጣርሰውታል። መንፈሳዊ ነገር ቢያውጁም እንዲፈፀም የሚፈልጉት በሥጋ ነው። የክርስቶስን ነገር ለሥጋ ትርፍ ለማዋል ፈልገዋል። የጳውሎስ የሕይወት መርህ ግን በሥጋው ድካም የክርስቶስ ኃይል መገለጡ ነው። ስለዚህ በዚህ አቅጣጫ እኔን ምሰሉ ይላቸዋል። የሚላቸውም በቃል ብቻ ሣይሆን በተግባር ስለመሆኑ።

> *«የእግዚአብሔር መንግሥት የወረ ንዳይ ሳይሆን የኃይል ንዳይ ነው።» 1ቆሮ. 4:20*
>
> *«እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ።» 2ቆሮ.11:1 በማለት ያረጋግጥላቸዋል።*

በቀደመው ክፍል ያላቸው «እኔን ምሰሉ ብቻ ነበር።» አሁን ግን «እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ።» በማለት የእርሱንም ክርስቶስን መምሰል አክሎበታል። ሌሎች እኛን እንዲመስሉ ልናስከትል የምንችለው እኛ ክርስቶስን በመሰልጠት አቅጣጫና መጠን ብቻ ነውና።

ይህ የመምሰል ጥሪ በ1ቆሮ11፡1 ላይ ቢነሳም እንኳ አሳቡ የሚጀምረው ግን ምዕራፍ 8 ላይ ነው። በቆሮንቶስ አማኞች መከከል ለጣዖት የተሰዋን ሥጋ ስለ መብላትና አለመብላት የተነሳውን ጥያቄ በመመለስ ይነሳና የራስን መብት በመተው የሌላውን ጥቅም ስለማስቀደም ይጽፋል። ከመልሱ እንደምንረዳው አንዳንዶች እውቀት ነፃ ካወጣኝ በመብቴ ማንም ሰው አያገባውም የሚል ፍልስፍና ለማራመድ ታጥቀው የተነሱ ይመስላል።

ሐዋርያው ወንድሜን የሚያሰናክለው ከሆነ ለዘላለም ከቶ ሥጋ አልበላም በማለት ተነስቶ በቆሮንቶስ በቆየባቸው አሥራ ስምንት ወራት ከቆሮንቶስ አማኞች የተንዘብ ጥቅም የማግኘት መብት እየነበረው እነርሱን ላለማሳናከል ሲል መብቱንና ጥቅሙን ወደ ጎን ማድረጉን በማስታወስ ይቀጥላል።[42] ይህንንም ለማድረግ ያነሳሳው ሩጫውን ከፈፀመ በኋላ የሚያገኘው አክሊል እንደሆነ ይናገርና በመቀጠል ሩጫ ጀምረው ያልጨረሱትን የእስራኤላዊያንን የምድረ በዳ ጉዞ ለአብነት ያነሳል።[43]

ሲደመድምም «እያንዳንዱ ሰው የባልንጀራውን ጥቅም እንጂ የራሱን ብቻ አይፈልግ ... እንግዲህ ስትበሉም ሆነ ስትጠጡ ወይም ማንኛውም ነገር ስታደርጉ ሁሉንም ነገር ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት። ለአይሁድም ሆነ ለግሪኮች

ወይም ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን መሰናክያ አትሁኑ። እኔ ሰውን ሁሉ በማንኛውም ረገድ ለማስደሰት እንደምጥር እናንተም እንዲሁ አድርጉ። ብዙዎችም ይድኑ ዘንድ ለራሴ የሚጠቅመውን ሳይሆን ለአነርሱ የሚጠቅመውን እሻለሁና።» 1ቆሮ. 10:23-32 ይላል።

በሌላ ክፍል «እያንዳንዳችን ባልንጀራችንን ለማነጽ እርሱንም ለመጥቀም ደስ የሚያሰኘውን ነገር ማድረግ ይገባናል። ክርስቶስ ራሱን ደስ አላሰኘምና . . .።» ሮሜ 15:2-3 በማለት የራስን መብት ትቶ ለሌላው የሚጠቅመውን ማሰብ የክርስቶስ ሕይወት መርህ እንደሆነ ይጽፋል። ይህንንም በማመልከት «እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ።» በማለት ይደመድማል።

<u>ምሣሌነት በፊሊጲስዮስ መልዕክት ውስጥ</u>

«ወንድሞች ሆይ እኔን የምትመስሉ ሁኑ እኛም እንደምሳሌ እንደምንሆንላችሁ እንዲሁ የሚመላለሱትን ተመልከቱ።» ፊሊ. 3:17

ሐዋርያው አሁንም የመምሰልን ሰንሰለት ወይም ቅብብሎሽ በድጋሜ ያነሣል። እንዲመስሉት ከባፈላቸው በኋላ እርሱ በደብዳቤ እንጂ በአካል በመካከላቸው ስለሌለ በመካከላቸው ያሉትን የእርሱን ምሣሌነት የሚከተሉትን እንዲመለከቱ ይጋብዛል።

ሐዋርያው የመምሰልን ጥሪ የሚያቀርብባቸውን ክፍሎች በጥንቃቄ ስንመለከት በአፋቸው የክርስቶስን ስም እየጠሩ በተግባራቸው ግን ዓለምን ‹‹ሚመስሉ ምስሉኝ ባዬች በተነሱበትና አማኞችም በውጪያዊ ማንነታቸው በመማረክ እነርሱን ለመምሰል ሽር ጉድ በሚሉበት ሁኔታ ውስጥ ነው።

በዚህው በውጪያዊ ገጽታቸው ይመኩ ዘንድ እንዲገረዙ የሚወተውቷቸው አገልጋይ ተብዬዎች ነበሩ (3:2)። በእርግጥ የፊሊጲሲዮስ ሰዎች በሥጋ አሕዛብ እንደመሆናቸው መጠን የሰውነታቸውን ሸለፈት በሰው እጅ አልተገረዙም ነገር ግን በሥጋ ባለመመካት፤ በኢየሱስ ክርስቶስ በመታመን እና በመንፈስ እግዚአብሔርን በማምለክ እንጂ በሥጋ መቆራረጥ የማይገኘውን እውነተኛው መገረዝ መካፈላቸውን ይጽፍላቸውና ወደ ራሱ ምስክርነት ያልፋል። በምስክርነቱም ትምክህት ካስፈለገ በሥጋ የሚመካበት ብዙ ነገር እንዳለው ከዘረዘረ በኋላ ሌሎች የሚንገበገቡለትንና የሚመኩበትን ነገር እንደ ጉድፍ እንደሚቆጥረው ይነግራቸዋል። ይልቅ የነፍሱ ምኞት፣ የልቡ ናፍቆት የዘወትር ጥማቱ ክርስቶስን ማግኘት፣ በክርስቶስ መገኘት፣ የትንሳኤውን ኃይል ማወቅና፣ በመከራው መካፈል መሆኑን ይገልፃል። በመቀጠልም ይህን ክርስቶስን የመምሰል ጥማቱን ገና ሙሉ በሙሉ እንዳላገኘው በማተት እስከፍፃሜ ለመድረስ ወደፊት በመዘርጋት እንደሚሮጥ ይገልፅና በዚህ አቅጣጫ እርሱን እንዲመስሉት ይጋብዛቸዋል።

ምሳሌነት በአንደኛ ተሰሎንቄ መልዕክት ውስጥ

«ደግሞ እናንተ ቃሉን በብዙ መከራ ከመንፈስ ቅዱስ ደስታ ጋር ተቀብላችሁ እኛንና ጌታን የምትመስሉ ሆናችሁ ስለዚህም በመቄዶንያና በአካይያ ላሉት ምእመናን ሁሉ ምሳሌ ሆናችሁላቸው። . . . እናንተ ወንድሞች ሆይ በይሁዳ የሚኖሩትን በክርስቶስ ኢየሱስ ያሉትን የእግዚአብሔርን ማኅበሮች የምትመስሉ ሆናችኋል፤ እነርሱ ከአይሁድ መከራ እንደ ተቀበሉ እናንተ ደግሞ ያንን መከራ ከአገራችሁ ሰዎች ተቀብላችኋልና።»

፩ተሰ. 1:6-7፤ 2:14

ሐዋርያው ጳውሎስ ደብዳቤ ለፃፈላቸው አብያተክርስቲያናት ወይም በወንጌል አብረውት የሚሠሩ አገልጋዮች መንገዱ ይሊያይ እንጂ የመምሰል ጥሪ ያላቀረበበት ቦታ የለም። «እኔን ምሰሉ» በማለት ሲጣራ የሚያስተጋባው የገደል ማሚቱ «ክርስቶስን ምሰሉ» የሚል ድምጽ ስመሆኑ ጥርጥር የለውም።

ሰተሰሎንቄ ሰዎች የፃፈውን ከሌሎች ትንሽ ለየት የሚያደርገው እንዲመስሉ ጥሪ ያቀረበበት ሳይሆን ምን ያህል እንደመሰሉ በመንገር ያበረታታበት መሆኑ ነው።

በመግቢያው «እኛንና ጌታን የምትመስሉ ሆናችሁ» ያላቸው በሁሉ ነገር ሳይሆን በአንድ አቅጣጫ ነው። ያም አቅጣጫ የተሰሎንቄ ሰዎች ወንጌልን በተቀበሉ ጊዜ ከገዛ ሕዝባቸው ከፍተኛ ተቃውሞና ስደት ደርሶባቸው ነበር። የመከራው ዓይነት ተስፋ አስቆራጭና ወደ ኋላ እንዲመለሱ የሚያስገድድ ነበር። እነርሱ ግን በመከራ ውስጥ ይሄ ነው የማይባል የመንፈስ ቅዱስ ደስታ ይፈስባቸው ነበር። የእግዚአብሔርንም ቃል ያለምንም ጥርጥር በእምነት ተቀበሉ እንጂ በመከራው ተናውጠው ወደ ኋላ አላሉም። በዚህም የአባቱን ፈቃድ ለመፈፀም ከኃጢአተኞች በደረሰበት መከራ የፀናውን ጌታን መሰሉ። ለአሕዛብ የወንጌልን የምሥራች ለማድረስ ከአሕዛብም ሆነ ከወገኖቹ ከአይሁዳዊያን የደረሰበት ጽኑ መከራ ሳይበግረው በደስታ ፀንቶ ከፊቱ ያለውን ክብር እያየ የሚያገለግለውን ጳውሎስን መሰሉ። ይህ መምሰል በእነርሱ ብቻ ተወሰኖ አልቀረም። የእነርሱን ወሬ በሰሙት ከአካይያ (ቆሮንቶስ) እና በመቄዶንያ (ፊሊጵሲዮስ) ላሉት ምእመናን ሁሉ የጽናት ምሳሌ ሆነላቸው።

ምሳሌነት በሁለተኛ ተሰሎንቄ መልዕክት ውስጥ

«እኛን ልትመስሉ እንዴት እንደሚገባችሁ ራሳችሁ ታውቃላችሁና በእናንተ ዘንድ ያለ ሥርዓት አልሄድንምና ከእናንተ ዘንድ በአንዱ ሰንኳ እንዳንክብድበት ሌሊትና ቀን በድካምና በጥረት እየሠራን እንኖር ነበር እንጂ ስማንም እንደራን አንጨያው አልበላን። ይህም እኛን ልትመሰሉ ራሳችንን እንደ ምሳሌ እንሰጣችሁ ዘንድ ነበር እንጂ ያለ ሥልጣን ስለሆንን አይደለም።» 2ተሰ. 3:7-8

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በቅርቡ ይመጣል በሚል አጉል መገለጥ ተደናግጠው የእለት ተእለት የኑሮ እንቅስቃሴያቸውን

ችላ ባሉት የተሰሎንቄ ሰዎች መካከል «ነገ ጌታ ሊመጣና ወደ ሰማይ ሊወስደን ዛሬ ሥራ ምን ያደርጋል» የሚሉ ዳተኞች ተስፋፍተው እንደነበር ከመልእክቱ መረዳት ይቻላል። ይህን ወቅታዊ ችግር ለመፍታት ሐዋርያው ጳውሎስ አዲስ ነገር መፍጠር ወይም አዲስ መገለጥ ማምጣት አላስፈለገውም። ለአፍታ ወደኋላ በመመለስ እና ትዝታቸውን በመቀስቀስ መጀመሪያ በእነርሱ ዘንድ በነበረበት ጊዜ ያሣያቸውን ባሕሪ ያስታውሳቸዋል። የተሰሎንቄ ሰዎች በጳውሎስ ሕይወት ውስጥ አስደናቂ የሥራ ባሕል እና የአካሄድ ሥርዓት ለመመልከት ታድሰው ነበር። የሚገርመው በመካከላቸው ባለሥልጣን ሆኖ ሳለ ሥልጣኑም በቃል ብቻ ሣይሆን በብዙ ተዓምራትና ምልክቶች ታጅቦ ሳለ እንደ ባለሥልጣን አልተከፈሰም፣ «ንገሥ በሉኝ» አላለም። በዓይናቸው ፊት እንደባሪያ እየሠራ እንጀራውን በገዛ ገንዘቡ ይብላ ነበር። ይህንን ያደርግ የነበረው እንደ እንግዳ የሚያስተናግደው፣ እንደ አገልጋይ የሚያቆላምጠው አጥቶ ሳይሆን ሆን ብሎ ነበር።

> «ይህም እኛን ልትመስሉ ራሳችንን እንደ ምሳሌ እንሰጣችሁ ዘንድ ነበር።» ስለዚህ ዛሬ ችግር ሲፈጠር መፍትሔ ፍለጋ ውጣ ውረድ አላበዛም በእነርሱ ሕሊና ውስጥ አስቀድሞ ያስቀመጠው መፍትሔ ነበርና ያንን መንካት ብቻውን በቂ ነበር። ስለዚህም «እኛን ልትመስሉ እንዴት እንደሚገባችሁ ራሳችሁ ታወቃላችሁ።»

በማለት በድፍረት ሊፅፍላቸው እናያለን።

እንግዲህ ስለ ጳውሎስ የአባትነትና የምሳሌነት ሕይወት ይህን ያህል ብለናል። ለመሆኑ ዘመናችን ምን ይመስላል? ስለ ዛሬው ገጽታ ምንም ሣንል ብናቆም ከታሪክ ተወቃሽነት ባሻገር የአርምጃ ሰዎች ለመሆን አንችልም። እንደ እውነቱ ከሆነ ዘመን አፍ ቢኖረው ኖሮ «የምሳሌ ያለህ! የአባቶች ያለህ!» ብሎ በጮኸ ነበር። ለነገሩማ አስካሁንስ ሳይጮህ ቀርቶ ነው? ሰሚ አጥቶ እንጂ። አምን በትውልዱ ውስጥ ይጮሃል፣ በአንባና በደም ይጮሃል፣ በሲቃ ይጣራል።

የአባቶች ያለህ

ለመሆኑ የዘመናችን አባቶች የት አሉ? እንከተላቸውስ ዘንድ ምሳሌነታቸው የታል? ከአመታት በፊት በአንድ አጋጣሚ ወጣት አገልጋዮች ተሰባስበን በችግሮቻችን እና በመፍትሄዎቻቸው ላይ መወያየት ጀመርን። ከመካከላችን አንዱ ተነሳና የእኛ ችግር የአባቶች አለመኖር ነው። አባቶች የሉንም አለ። የተቀሩትም እየተቀባበሉ «አዎን አባቶች የሉንም» በማለት አጀቡት። ይህ ሃሳብ በጥቅስ እየተደገፈ ሲንሸራሸር ሳለ አንድ ወንድም እጁን አወጣና «አባቴ ሰካራም ነበር፣ አባቴ ሌባ ነበር፣ አባት ተደባዳቢ ነበር ወዘተ ... ማለት ይቻላል። አባት የለኝም ማለት ግን አይቻልም። አባት የለኝም ማለት እኔም የለሁም እንደማለት ነውና።» በማለት ተናገረና የውይይታችንን አቅጣጫ ገራው።

አዎን አባቶች አሉን። ነገር ግን ምን ይመስላሉ? ምንስ እንድንመስል እየጋበዙን ነው? ብሎ መጠየቁ አግባብ ነው። በዘመናችን አባቶች ብለን ከምንጠራቸውና ቀና ብለን ከምናያቸው አንጋፋዎች መሃል ብዙዎቹ እርስ በእርስ ሲጣሉ እንጂ ሲፋቀሩ አናይም። ሲካሰሱ እንጂ ይቅር ሲባባሉ አናይም፣ ለወንበር እና ለሥልጣን ሲራኮቱ እንጂ የጠፋውን እና የባዘነውን ፍለጋ ሲደክሙ አናይም። በለስ ከቀናቸው ጋር ሲዝናኑና ኑሮአቸውን ለማመቻቸት ሲሯሯጡ እንጂ ወንጌልን በየገጠሩ ለማድረስ ሲጋደሉ አናይም። ስለ ደሞዝ ሲካሰሱ እንጂ በእጃቸው ሲሠሩ አናይም። መከራን ሲሸሹ እንጂ በጽናት ሲጋፈጡ አናይም። በሥጋ ለመመካት ሲጣጣሩ እንጂ የሥጋን ትምክህት ንቀው በነገር ሁሉ ጌታን ለመምሰል ሲዘረጉ አናይም። ከሁሉ በላይ ከሥራቸው የሚነሱትን አገልጋዮች ሲገፉና ሲያወግዙ እንጂ ሲያሳድጉና ሲተኩ አናይም። ታዲያ

ከዚህ በላይ የምሳሌ ያለህ! የአባቶች ያለህ! ብሎ የሚያስጮህ ምን ጉድ ሊመጣ ይችላል? ችግሩን የባሰ የከፋ የሚያደርገው እነዚህን አባቶች በትኩረት የሚመለከተው አዲስ ትውልድ «በዚህ ነገር ክርስቶስን አልመሰላችሁምና እኔም አልመሰላችሁም» ማለት አለመቻሉ ነው። ክፋታቸውንም ቢሆን ከመምሠል አይመለስም። መምሠል ተፈጥሮአዊም መንፈሳዊም ሕግ ነውና።

አምላክ በኪነጥበቡ መላ ካላለው በቀር የትውልዱ ፍጻሜ እጅግ አሣሣቢ ነው። ምሳሌ የሚሆኑ፣ መልካም ባሕሪን የሚያወርሱ እውነተኛ አባቶች የሌሉበት ቤት፣ ቤተክርስቲያን ሆነ አገር መሠረት እንደሌለው ሕንፃ ነው። መሠረት የሌለው ሕንፃ የፈለገውን ያህል ውጪው ቢያምር ውሎ አድሮ መውደቁ እንደማይቀር ሁሉ ትውልድም ምሣሌ የሚሆኑ አባቶች ሲያጣ በትምህርት ነፋስ ይፍገመገማል በዓለም ርኩሰት፤በገንዘብ ፍቅር ይነደፋል ፍጻሜውም መፍረስ ነው። የአባቶች እና የልጆች ልብ መለያየት ፍርድን ያመለክታል። ልጆች የሚመስሏቸው አባቶች፣ አባቶችም የሚተኳቸው ልጆች ያጣሉ። በውጤቱም እግዚአብሔርን መምሰል ይጠፋል ምድርም በእርግማን ትመታለች። ለዚህ ነው ነቢዩ፡ -

> *«እነሆ ታላቁና የሚያስፈራው የእግዚአብሔር ቀን ከመምጣቱ በፊት ነቢዩ ኤልያስን እልክላችኋለሁ። መጥቼ ምድርን በርግማን እንዳልጠፋ እርሱ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች የልጆችንም ልብ ወደ አባቶች ይመልሳል።» ሚል. ፬:፭ ያለው።*

አባቶች ከሰማይ አይወርዱም በመካከላችን ይወለዳሉ፣ ያድጋሉ፣ እነርሱም ይወልዱና በተራቸው አባት ይሆናሉ። ብዙን ጊዜ ችግራችን ስለ አባትነት ሲነሳ የሚታዩን ሌሎች መሆናቸውና ጣታችንን እነርሱ ላይ እየቀሰርን ኃላፊነትን ማስተላለፋችን ተጠያቂነትን ወርድ ከራስ ማለታችን ነው።

ጥቂትም ቢሆን ቀና ብለው የሚያዩን እርዳታን ከእኛ የሚሹ ሰዎች በዙሪያችን ካሉ ቢያንስ ለእነርሱ አባት ሆነናል። ታዲያ ታሪክን እንደግማለን? ወይስ ከታሪክ ተምረን ታሪክ እንሰራለን? እኔ በዚህ መከራ አልፈያለሁና እነርሱም ይለፋበት እንላለን? ወይስ «ከእኔ ተማሩ» «በእኔ ይብቃ» እንላለን? በተሰይ በእንድም በሌላም መንገድ መድረክ ላይ የምንወጣ ከሆነ እልፍ ጥንድ ዓይኖች በአትኩሮት እንደሚያዩን አንርሳ። እኛ አንወቃቸው እንጂ እነዚያ ዓይኖች በየመንገዱ አሉ፣ በየገበያው አሉ፣ በየታክሲው ውስጥ አሉ፣ በየካፌው አሉ። ስለዚህ መጥፎ ምሳሌ እንዳንሆን እንዳናስናክላቸውም ልንጠነቀቅ ይገባል። አንዳንዶች እንደሚሉት «እኔን አትመልከቱ ጌታን እዩ» እንበል። በእኛ ላይ ካልሆነ ጌታን የት ይዩት?» ሰማይ ላይ? ወይስ የጣሊያን ሠዓሊዎች በሠሩት ስዕል ላይ? ዘወትር የሚያላስበን በየሰንበቱ መድረክ ላይ የምንናገረው የእግዚአብሔር ቃል ብቻ አይሁን። ይልቅ የኑሮአችንን ፍሬ እያዩ በእምነታችን ይመስሉን ዘንድ ለሌሎች የምሣሌነት ኑሮ ለመኖር እንትጋ።

መምሰል የራስን ማንነት ክዶ ሌላውን ሰመሆን መሞከር አይደለም። በእኛ ሁኔታ እግዚአብሔር ልጁን እንዲገልጥ መፍቀድ ነው። እግዚአብሔር በምንም ዓይነት ማንነታችንን አይለውጥም። እያንዳንዳችን በዘላለም ውስጥ አንድ ብቻ ነንና። ነግር ግን በፈቀድንለት መጠን በእኛ ሁኔታ ልጁን ይገልጣል።

በዘመናችን ሁሉ የምንመስላቸው አባቶች የሚመስሉን ልጆች አያሳጣን!

7
እግዚአብሔርን የመምሰል ልምምድ

ገና በጠዋቱ የክረምቱ ደመና በአዲስ አበባ ሰማይ ላይ ከብዷል። ዕለቱ የሥራ ቀን እንደመሆኑ መጠን ሠራተኛው ወደ ሥራው፣ ነጋዴው ወደ ንግዱ፣ ተማሪውም ወደ ትምህርት ቤት በሰዓቱ ለመድረስ ይጣደፋል። የመኪናው ጭንቅንቅ የሰው ግፊያ ለከተማዋ ልዩ መልክ ሰጥቷታል።

በቦሌ አለም አቀፍ አየር ማረፊያ አካባቢ ከወትሮ ለየት ያለ እንቅስቃሴ ይስተዋላል። የኤርፖርቱ ግርግር እንደተለመደው የሚሄድን ወዳጅ ለመሸኘት የሚመጣን አንግዳ ለመቀበል አልነበረም ሌላ ምክንያት ነበረው። በሥፍራው ወጣ ገባ የሚሉት የአየር ማረፊያው ሠራተኞች ብቻ ሳይሆኑ የከተማው ባለሥልጣናትና የስፖርት ኮሚሽን ኃላፊዎች ነበሩ። ሽርጉዱ በውድድር ሜዳ ድል ነስቶ በአለም አደባባዮች የአገሩን ባንዲራ በክብር በማውለበለብና የሕዝቡን መዝሙር ማስተመም ልማዱ የሆነው ኃይሌ ገብረ ሥላሴ በድል አሸብርቆ ከውጭ ስለሚመጣ ነበር። ኃይሌንና ሌሎች አትሌቶችን የያዘው አውሮኘላን ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ እንደሚያርፍ ዜናው ከናኘ በኋላ ድምቀቱ ጨመረ። ባካባቢው ባሉ ኢትዮጵያዊያን ፊት ላይ ከኩራትና ከእልህ የመነጨ የደስታ ስሜት ይነበባል።

አይሮኘላኑ አርፎ ጀግናውን አትሌት ለመቀበል ወደ ተሰበሰቡት ባለሥልጣናትና የአየር መንገዱ ሠራተኞች ሲጠጋ በክንፎቹ (የአብራሪዎቹ ክፍል) መስኮት ተከፍቶ የኢትዮጵያ ባንዲራ ሲውለበለብ ላየው ልዩ የደስታ ስሜት የሚፈጥር ነበር።

በአየር ማረፊያው ለኃይሌ የተደረገለት አቀባበል ብቻውን በቂ አልነበረም። በተገኘው ድል በደስታ የናኘው የአዲስ አበባ ሕዝብ ለአትሌቱ አክብሮቱን ለመግለጽ በአዲስ አበባ ስታዲየም ተሰብስቦ ነበርና ኃይሌ በክብር ታጅቦ ወደ ሥፍራው አመራ።

ዝማሬው፣ ጭብጨባው፣ አልልታው፣ ቱጨቱና ጨኸቱ ይህ ነው የሚባል አልነበረም። ወቅቱ አትሌቱ ለአራት ተከታታይ አመታት የአለም ሻምፒዮን የሆነበትና የበርካታ ሪኮርድ ባለቤት በመሆን በድል ያንፀባረቀበት በመሆኑ የሕዝቡ ስሜት ከፍተኛ ነበር። መቼስ የማያልቅ የለምና የስታድየሙ ዝማጅት አልቆ ኃይሌ ከቤተሰቡ ጋር ወደ መኖሪያ ቤቱ አቀና። በዚያም የጠበቀው ፀጥና ረጭ ያለ ጓዳ አልነበረም። ወዳጅ ዘመድ የቅርብም የሩቅ ጓደኛ ቤቱን አጨናንቆታል ሁሉም የሚጠባበቁት ኃይሌ መጥቶ አብሯቸው ተቀምጦ ስለድሉ እንዲያወጉ ነበር።

የሆነው ግን ከዚያ ፈጽሞ የተለየ ነበር ኃይሌ ገብቶ ሰሁሉም በፈገግታና በመፍለቅለቅ የታጀበ ሰላምታ ካቀረበ በኋላ ተቀመጠ ገበታ ቀረበ ተበላ ተጠጣ። ከጥቂት ቆይታ በኋላ ኃይሌ ሰዓቱን ተመለከተ። አዎን የልምምድ ሰዓቱ ደርሷል። ዙሪያውን ሲመለከት ሁሉ ተመቻችቶ ተቀምጧል እንጂ ለመሄድ ያሰበ አልነበረም። ቀስ ብሎ ወደ ጓዳ ገባና ልብሱን ከቀየረ በኋላ ለባለቤቱ «ስለደከመው ተኝቷል በይልኝ» በማለት መልእክት አስተላለፈና ወደ ጓሮ ዘለቆ የልምምድ ጫማውን ያጠባብቅ ጀመር። ዙሪያውን ሲመለከትም እንግዶቹ ሳያዩት የሚወጣበት በር አልነበረውምና አንድ ያልተለመደ እርምጃ ለመውሰድ ተገደደ። በአጥር ዘሎ ወጣና የሩጫ ልምምዱን ተያያዘው።[44]

ይህ እውነተኛ ታሪክ ለሰሚ ቢያስገርምም ለታሪኩ ባለቤት ግን ከብዙ ገጠመኞቹ መሃል አንዱ ነውና አምብዛም አይገርመውም። በዓለም አደባባዮች የተጎናፀፈው ድል ከብዙዎች የተቸረው ክብር መሠረቱ ምን እንደሆነ ታውቋል። «ልምምድ!»

የተለያዩ ታላላቅ ስፖርተኞች በአደባባይ ድል ሲቀዳጁ በአድናቆት ከሚያያቸው ተመልካች መሃል ስንቱ ከድሉ ጀርባ ያለውን ፈታኝና እልህ አስጨራሽ ልምምድ ማየት እንደሚችል አይታወቅም።

በቀደሙት ምዕራፎች የሥጋን ሕይወት በመግፈፍና የእግዚአብሔርን ሕይወት በሥጋ ሰውነት በመግለጥ ክርስቶስን መምሰል እንደሚቻል ለመግለጽ ተሞክሯል። በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ወደዚያ የሚደረሰው አልጋ በአልጋ ሣይሆን ትጋት በታከለበት ብርቱ ልምምድ እንደሆነ ለማሳየት በጀግናው አትሌት ኃይሌ ገብረሥላሴ ታሪክ አሃዱ ብለናል ::

የአዲስ ኪዳን መጻሕፍትን አንድ ሦስተኛ በብዕሩ የቀለመው ሐዋርያው ጳውሎስ መንፈሳዊ ሕይወትን እርሱ በኖረበት ዘመን ገናና በነበረው የሩጫ ውድድር መስሎ ማቅረብ ያዘወትር እንደነበር ከመልዕክቶቹ መረዳት ይቻላል።[1]

ለዚህ ነው ለጢሞቴዎስ እግዚአብሔርን ለመመሠል ራስን ስለማስለመድ ሲፅፍለት የአካል ብቃት ልምምድን እንደ ምሳሌ የሚጠቀመው፡ -

> *«እግዚአብሔርን ለመምሰል ግን ራስህን አስለምድ ሰውነትን ሰሥጋዊ ነገር ማስለመድ ለጥቂት ይጠቅማልና እግዚአብሔርን መምሰል ግን የአሁንና የሚመጣው ሕይወት ተስፋ ስላለው ለነገር ሁሉ ይጠቅማል።» ፩ጢሞ. ፬፡፯*

የቀድሞው መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም «አስለምድ» የሚለውን አዲሱ «አሰልጥን»፣ የቀድሞው «ሰውነትን ለሥጋዊ ነገር ማስለመድ» የሚለውን አዲሱ «ለአክል ብቃት እንትክቃሴ ማሰልጠን» በማለት የበለጠ ግልፅ ያደርገዋል።

ልምምድ የሌለንን አይሰጠንም ነገር ግን ኖሮን የተደበቀውን ክህሎት ገሃድ ያወጣዋል። ለምሣሌ ሮጦ የማያውቅ አንድ ሆዱ የገፋ ሰው የከተማ አውቶብስ ላይ ለመድረስ አንድ ምእራፍ ቢሮጥ ትንፋሹ ሊቆራረጥ፣ ላቡ ሊንቆረቆር ይችላል። ታዲያ ይህን ሰው እንዴት ማራቶን እናስሮጠዋለን? ሆኖም ሰውየው በምንም ዓይነት ሊሮጥ አይችልም አላልንም። አበላልን ገርቶ ሰውነቱን ገዝቶ ልምምድ ቢጀምር ትንሽ በትንሽ እያለ ሊሻሻል አድጎም ሰውድድር ሊበቃ ይችላል። የሚያስፈልገው አንድ ነገር ብቻ ነው የማያቋርጥ «ልምምድ»።

አንድ ሰሞን እኔም ነሸጥ አረገኝና ጠዋት ተነስቼ መሮጥ ጀመርኩ። አነሳሴ ጥሩ ነበር። ግና ጥቂት እንደሮጥኩ የእጄ ሰዓት ከበደኝ። አውልቄ ኪሴ አደረኩት፣ ትንሽ ሳይቆይ አተነፋፈሴ ተሰወጠ ቀጥሎ የእግሬ ጡንቻዎች እንደመቆጣት ይላቸው ጀመር። የተወሰነ ርቀት ከተጓዝኩ በኋላ አንገቴ ራሴን፣ እግሬም ከወገብ በላይ ያለውን ሰውነቴን መሸከም አቃተው። ከዚያማ የሰውነቴ ጅማትና ቅልጥሞች አፍ አውጥተው የሚናገሩ እስኪመሰለኝ ድረስ «በቃህ አቁም!» የሚል ስሜት ያስተጋቡ ጀምር። ድምፃቸው እየናረና እየከረረ መጣ። አካባቢዬን ስመለከት እንደ እኔ ለጤና የሚሮጡ ሰዎች አየሁ። በጆሮአቸው ላይ የሙዚቃ ማዳመጫ ሰክተዋል። ምናልባት እኔን ያስቸገረኝ ዓይነት የሰውነታቸውን የእንቢታ ጩኸት ላለመስማት ይሆን? አልኩ በቀልድ ስሜት። ሆኖም

ብዙ አልገፋሁም የሰውነቴ የተቃውሞ ድምጽ አየለና መንገድ ዳር የነበረ አንድ ድንጋይ ላይ አረፍ አልኩ።

እግዚአብሔርን መምሰል እንዲሁ ነው አንድ ቀን በስሜት ተነሣስተን ልንፈጽመው አንችልም። ቀስ በቀስ አንድ ባንድ ራሳችንን ካስለመድን ግን በእርግጥ እንደርስበታለን። በልምምድ የሌለንን አናመጣም ኖሮን በውስጣችን የተሰወረውን ግን እንገልጣለን።

የማይደረስበት የሚመስል ቅርብ

እግዚአብሔርን ስለመምሰል ወይም ስለ እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ስናስብ ከመነሻው ተስፋ የሚያስቆርጡን በርካታ ነገሮች መኖራቸው የማይታበል ሐቅ ነው።

ኢየሱስ አገልግሎቱን በጀመረበት ሰሞን ለማስተማር ወደ ተራራ ሲወጣ ተማሪዎቹ ሲሆኑ የወሰኑት ተከትለውት ከአፉ የሚወጣው ለመስማት በዙሪያው ተቀመጡ። በአባቶች ወግ የተሰጠጠው የሙሴ ሕግ ትከሻቸውን አጉብጦት መፍትሔ ለሚፈልጉት ለነዚያ በዙሪያው ለተሰበሰቡት አይሁዳዊያን

> *«እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍፁም እንደሆነ አናንተም ፍፁማን ሁኑ።»* ማቴ. 5:48

ሲሳቸው ምን ስሜት ተፈጥሮባቸው ይሆን? «አይ እንዲህ ያለው ባያውቀን ነው። እኛ እንኳን እንደ ሰማዩ አባት እንደ ሙሉም ፍፁም አልሆን።» ብለው ይሆን? ወይስ «የዚህ ሰው ትምህርት ሊደረስበት የማይችልና ከቶ የማይፈፀም ሕልም ነው።» ብለው?

> *«አኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝና አናንተ ቅዱሳን ሁኑ።»* ዘሌ.19:2

የተባሉት የጥንት አስራኤላዊያንስ?

> *«አኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ ስለ ተፃፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደሆነ አናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ»* 1ጴጥ. 1:15-16

የተባሉት የአዲስ ኪዳን መጻተኞችስ ምን ተሰምቷቸው ይሆን? እንደ እግዚአብሔር ቅዱስ መሆን የማይታሰብ ይመስላልና።

ሆኖም ይህ የማይደረስበት የሚመስል እግዚአብሔር የመምሰል ጉዞ ክርስቶስ ከሠራው ሥራ የተነሳ ማንም ሊደርስበት የሚችል ቅርብ የመሆኑ የምሥራች ታውጇል። አዎን እግዚአብሔርን መምሰል በእርግጥ ይቻላል! እንዴት የሚለውን ተራ በተራ እንመልከተው።

1. የጽንሰ ሐሳቡ ነዳፊ፣ የጅማሬው መሠረት ጣይ፣ የሥራው ሂደት መሪ፣ የፍፃሜውም ወራሽ ራሱ ጌታ ኢየሱስ ስለሆነ።

> *«አናንተንም ነውርና ነቀፋ የሌለባችሁና ቅዱሳን አድርጎ በአርሱ ፊት ያቀረባችሁ ዘንድ በፊት የተሰደቻችሁትን ክፉ ሥራችሁን በማድረግ በአሳባችሁ ጠላቶች የነበራችሁባትን አሁን በሥጋው ለውነት በሞቱ በኩል አስታረቃችሁ። ይህም ተመሥርታችሁና ተደላድላችሁ ከሰማችሁትም ከወንጌል ተስፋ ሳትናወጡ በኃይማኖት ጸንታችሁ ብትኖሩ ይሆናል ...።»* ቆላ. 1:21-23

በዚህ ክፍል ውስጥ እንደምንመለከተው የጌታ ራእይ እኛን ነውርና ነቀፋ የሌለብን ቅዱሳን አድርጎ በአባቱ ፊት ማቅረብ ነው። ነገር ግን እንዲህ ይሆኑለት ዘንድ የሰማይ መላእክትን የምድር ፍጡራንን ፍለጋ አልሄደም። የመረጠው ከክፉ ባሕሪያችን የተነሳ ከእግዚአብሔር ተሰይተን በአሳባችን ጠላቶች የነበርነውን እኛኑ ነው።

ሥራውንም የጀመረው በሥጋው ሰውነት በሞቱ በኩል ከእብ ጋር በማስታረቅ ነው። የሥራውም ፍፃሜ እስቀድመን እንደጠቀስነው የእግዚአብሔር ባሕሪ የተገለጠባቸው እርሱን የሚመስሉ ሰዎች ማፍራት ነው።

በዚህ ውስጥ የእኛ ድርሻ ቢኖርም ዋናውና ግዙፉ ሥራ በክርስቶስ ተፈፅሟል። የእኛ ድርሻ በእምነት መመሥረትና እና ተደላድሎ መቆም፣ ከሰማነውም የወንጌል ተስፋ ሳንናወጥ በእምነት ፀንቶ መኖር ብቻ ነው።

የሰው ንድፍና አቅድ ሊወድቅ ይችላል። የጌታ ንድፍ ግን ይሰምራል እንጂ አይወድቅም። የእኛን ድርሻ እስከተወጣን ድረስ ወደ ፍፃሜ መድረስ ይቻላል። ስለዚህ እኛም ከሐዋርያው ጋር በታላቅ ድምጽ «. . . ይሆናል! » ልንል ይገባል።

2. የእግዚአብሔር ሕይወትና እግዚአብሔርን ለመመሰል የሚያስፈልገው ሁሉ ተሰጥቶናል

> *«የመለኮቱ ኃይል በገዛ ክብሩና በበጎነቱ የጠራንን በማወቅ ለሕይወትና እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚሆነውን ነገር ሁሉ ስለሰጠን በእግዚአብሔርና በጌታችን በኢየሱስ እውቀት ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ።» 2ጴጥ. 1:2-3*

በአሁኑ ዘመን በባሕሪ እግዚአብሔርን እንድንመስል የተጠየቅነው እንዲሁ በሜዳ አይደለም። የመለኮቱ ኃይል ከመለኮታዊው ባሕሪ ተካፋዮች እንሆን ዘንድ የእግዚአብሔርን ሕይወት እና በቀጣይነትም እግዚአብሔርን ለመምሰል ወይም ለእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት የሚያስፈልገንን ሁሉ ራሱ አስቀድሞ ሰጥቶናል።

ለቤት ግንባታ የማያስፈልገው ቁሳቁስ ዓይነት በዓይነት የቀረበለት የግንባታ ባለሙያ ቤት መገንባት ሊሳነው እንማይችል ሁሉ እኛም እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚያስፈልገው ሁሉ ስለተሰጠን የማይደረስበትና የማይቻል አድርገን ልንቆጥር አይገባም። ይልቅ በዚህ እምነታችን ላይ ትጋትን ሁሉ እያሳየን በጎነትን፣ እውቀትን፣ ራስን መግዛት፣

መጽናትን፣ እውነተኛ መንፈሳዊነትን፣ የወንድማማች መዋደድን እና ፍቅርን ላይ በላይ እየጨመርን እግዚአብሔርን በመምሰል ልናደርግ ይገባናል።

3. የተጠየቅነው ያልሆንነውን እንድንሆን ሳይሆን በውስጥ የሆነውን በውጭ እንድንገልጥ ነው።

> *«. . . እውነተኛ በሆነው ጽድቅ እንዲሁም ቅድስና እግዚአብሔር እንዲመስል የተፈጠረው አዲሱን ሰው እንድትላበሱ ነው።» ኤፌ. 4:24 (አ.መ.ት)*

አንድ ሰው ያማረ የልብስ ሥጦታ ቢሰጠንና ያን ልብስ ቁምሳጥናችን ውስጥ ብናስቀምጠው ከእኛ በስተቀር እኛን የሚያዩ ሰዎች አዲሱን ልብስ የማየት አድል አይኖራቸውም። ብንለብሰው ግን በደረስንበት ሁሉ የሚያዩን ሰዎች እኛን አይተው ልብሳችንን ሳያዩ ማለፍ አይችሉም። ያደረግነው አንድ ነገር ነው ልብሱን ከተደበቀበት ቁምሳጥን አውጥተን በመልበስ ለሁሉ ገለጥነው። መልበስ መግለጥ ነው። ዛሬ በውጭ የሚታይብም በሚያታልል ምኞት ያደፈ አሮጌ ሰው ነው? ወይስ በእውነተኛ ፅድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረው አዲስ ሰው? መልሶ የመጀመሪያው ቢሆንም እንኳ በክርስቶስ አምነው እስከዳኑ ድረስ በውስጥም እውነተኛ በሆኑ ጽድቅና ቅድስና እግዚአብሔርን እንዲመስል የተፈጠረ አዲስ ሰው አለ። ይህን ሰው ለመፍጠር እግዚአብሔር እንጂ እርስም የሰሩት ሥራ የለም። እግዚአብሔር በታላቅ ምጎረቱ በክርስቶስ የፈፀመው ሥራ ነው። የእርስዎ ድርሻ አንድና ግልጽ ነው በውስጥዎ ያለውን አዲሱን ሰው «መልበስ»። ከለበሱት ገልጠውታል፣ ከገለጡት ደግሞ በሚያይዎት ሁሉ ፊት እግዚአብሔርን መስለዋል። ይህን እወቁ እግዚአብሔር ልብስ ይሰጣል እንጂ አያስብስም። ስለዚህ እግዚአብሔር አስኪያስብሶት አይጠብቁ። ወይም አልብሰኝ ብለው አይፀልዩ

ይልቅ ይነሱና ይልበሱ። መልበስ ማለት መግለጥ ነውና በውስጥም የተሰወረውን የክርስቶስ ባሕሪ በውጭ ይግለጡት።

ይህ እውነተኛ በሆነው ጽድቅና ቅዱስና እግዚአብሔርን እንዲመስል የተፈጠረው አዲሱ ሰው የፈጠረውን ይመስል ዘንድ እለት እለት እንዲታደስ የማያስፈልገው አንድ ነገር ነው። «እውቀት!» በመንፈስ ቅዱስ ቅባት በቃሉ አብርሆት የሚሆን እውቀት ሲያገኝ ይታደሳልና።

እኔ እኔን የምመስለው በቁርበት ውስጥ የእኔ ሕይወት ስላለ ነው። የውስጥ ሕይወት የሰውነት ክፍሎቼን በመቆጣጠር አሳቡን ስሜቱንና ፈቃዱን በውጭ ስለሚገልፅ እኔ እኔን መምሰል ችያለሁ። አሁን ግን የእኔ ሕይወት ተወግዶ የእግዚአብሔር ሕይወት ከተተካ ይህም ሕይወት በውስጤ ነግሦ ሃሳብ ስሜትን ከገዛ በውጭ ለሚያየኝ ሰው እኔ እኔን ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርን እመስላለሁ።

የእውነት ዓምድና መሠረት

ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ መቄዶንያ ሲሄድ የኤፌሶንን ቤተክርስቲያን እንዳለች መተው አላስቻለውም። በቤተክርቲያኒቱ ላይ ይመጣ ዘንድ ያለውን መንፈስ ቅዱስ ገልጦለት ነበርና በእምነት ልጁ የሆነውን የሚወደውን ጢሞቴዎስን በዚያ እንዲቀይ ሊሰምነው ተገደደ።

አሁን ከሄደ ጊዜያት ተቆጥረዋል ስለዚህም ፈጥኖ መመለስ ያስባል። ነገር ግን የመንገድ ነገር አስተማማኝ ስላልሆነ ምናልባት ቢያዘገየው የማይዘገይ መልእክት በውስጡ

ታምቂልና በብራና ጽፎ ቀድመውት በሚመጡ ሰዎች እጅ ወደ ጢሞቴዎስ ሊሰድደው ወደደ።

ክፍሉን በጥሞና ስንመለከት የመልእክቱ ቁልፍ ቃል «ታውቅ ዘንድ» የሚለው መሆኑን ለመረዳት እያስቸግርም። «ሰዎች በእግዚአብሔር ቤት እንዴት መኖር እንዳለባቸው እንዲያውቅ»። ስለ እግዚአብሔር ቤት ምንነት ሲያብራራም «ቤቱም የእውነት አምድና መሠረት እርሱም የሕያው እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ነው» ይለዋል። ይህ ቤት በድንጋይና በሲሚንቶ ላይሆን በቅዱሳን አንድነት የተገነባ እውነትን አቅፎና ደግፎ፣ ከፍ አድርጎና አጉልቶ የሚያሳይ መንፈሳዊ ቤት መሆኑን ይነግረዋል።

ጳውሎስ ወደዚህ የአሳብ ድምዳሜ ከመምጣቱ በፊት ከምዕራፍ ሁለት አንስቶ በዚህ የእግዚአብሔር ማደሪያ ቤት ውስጥ ሰዎች እንዴት መኖር እንዳለባቸው አንድ ባንድ ጽፎአል። የማኅበር አምልኮና ፀሎት፣ ወንዶችን፣ ሴቶችን፣ የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎችን፣ ዲያቆናትን በተመለከተ መመሪያ ሰጥቷል። ሲደመድመውም በዚህ እግዚአብሔር በሚያድርበት መንፈሳዊ ቤት ውስጥ ለመኖር፣ ለማደግ፣ ለመበልፀግ፣ ለመከናወን ሚስጥሩ አንድ እንደሆነ ይጽፋል። ይህንንም የሚጽፈው ጢሞቴዎስ በግል ሕይወቱም ሆነ ለቅዱሳን ባለው አገልግሎት በዚህ ታላቅ የኃይማኖት ሚስጥር ላይ እንዲያተኩር ለመጠቆም ነው።

ሚስጥሩም ለዘላለም ተሰውሮ የኖረ አሁን ግን በክርስቶስ በሥጋ መምጣት፣ በመስቀል ላይ መሞትና ከሙታን መነሳት የወጣ የክርስትና እምነት ብቸኛ መሠረት መሆኑን ያበስራል። በመቀጠልም ምናልባት በዘመኑ በነበረች ቤተክርስቲያን

የተለመደ መዝሙር ሳይሆን የማይቀረውን ስንኝ በመጥቀስ ሃሳቡን ይደመድማል።[3]

ከዚህ ክፍል የምንማረው ቁምነገር የቅዱሳን ጎብረት (የቤተክርስቲያን) ዋና መሠረት ውጪያዊ ሕግና ደንብ፣ ሥርዓትና መመሪያ ሳይሆን እያንዳንዱ አማኝ እግዚአብሔርን ለመምሰል ወይም በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ለመኖር የሚያደርገው ጥረት መሆኑን ነው። ይህ ነገር የውጭ ገጽታ ብቻ ሣይሆን የልብ ሁኔታ፣ የነፍስ አዝማሚያ፣ የአሳብ ዝንባሌ ነው።

መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድስ እንኳ የለም። እግዚአብሔርን ካሳየነው ደግሞ እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል ስለማናውቅ ልንመስለውም አንችልም አሁን ግን እግዚአብሔር በሥጋ እንደመጣ፣ ሰው ሆኖ በምድር እንደኖረ፣ ከመወለዱ አንስቶ፣ በእድገቱ፣ በምድረ በዳ ፈተናው፣ በአገልግሎቱ እንዲሁም በሞት መከራው መላእክት እንዳዩትና እንዳገለገሉት፣ በሥጋ የመገለጡ ዜና በተወለደበት፣ ባደገበት፣ ባገለገለበትና ሞቱ በተነሳበት በእስራኤል አገር በአይሁድ ሕዝብ መካከል እንደታወቀ የቅርብ ተከታዮቹ ፊት ለፊት እያዩት በክብር እንዳረገ የምስራቹም በኢየሩሳሌም ሳይወሰን ለአሕዛብ (ለምድር ሕዝቦች) በኃይልና በሥልጣን እንደታወጀ አዋጁም በአለም ባሉት በብዙዎች ዘንድ እንደታመነ ይገልፃል።

በኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት የእግዚአብሔር ሕይወት በሥጋ ተገልጦ በሰዎች መካከል ከታየ እኛ በሥጋ ያለን የእግዚአብሔርንም ሕይወት የተካፈልን እርሱ እንደነበረ ዛሬ በምድር የምንኖር ልንመሰለው እንደምንችል እርግጠኝነት በውስጣችን ሊሰፍን ይገባል።

እንግዲህ የአዲስ ኪዳን ትምህርት የሐዋርያት መልእክት በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የሚያስተጋባ የነቢያት ድምጽ ይዜ ነው።

በውሃ ላይ መሄድ ለዚያውም በማዕበል በሚናወጥ ባህር ላይ መራመድ የማይቻል ብቻ ሣይሆን የማይታሰብ ጉዳይ ነው። ኢየሱስ ግን በዚያች ሌሊት በገሊላ ባሕር ላይ ተራመደ። ይህን ያደረገው ችሎታውን በማሳየት ደቀመዛሙርቱን ለማስደነቅ አልነበረም። እነርሱም በእምነት ይህን ማድረግ እንደሚችሉ ለማሳወቅና ለማደፋፈር እንጂ። ለዚህ ነበር ጴጥሮስ እመጣ ዘንድ ጥራኝ ባለው ጊዜ እንደርሱ በውሃ ላይ እንዲሄድ «ና» ብሎ የጠራው። ልክ እንዲሁ ክርስቶስ በሥጋ መጥቶ እግዚአብሔርን መምሰልን ያሳየው በእርሱ አንድንደነት ብቻ ሳይሆን በሥጋ ዓይን ሲታይ በውሃ ላይ ከመሄድ የሚከብደውን ይህን ልምምድ ደፍረን እንድንገባበት ምሳሌ ሊሆነን ነው። አሁንም ጌታ ብዙዎችን በሚያስጥመው ማዕበል ላይ ቆሞ ከኃጢአት በላይ እንድንራመድ ይጠራናል። እንግዲህ ማነው በእምነት ከታንኳው የሚወጣ? ማነው እኔን ጥራኝ! የሚል? አምን በውስጣችን እርሱን ትኩር ብለን ካየን ይቻላል። ብንደክምና ብንሰጥም እንኳን እጃችንን ይዞ የሚያወጣ ጌታ በአጠገባችን አለና የሚያስፈራ ነገር የለም።

እንግዲህ ስለልምምድ አስፈላጊነት ይህንን ያህል ካልን ከዚህ በመቀጠል የምናየው የልምምዳችንን ተግባራዊ አቅጣጫ ይሆናል። ይህም ተግባራዊ አቅጣጫ በክርስቶስ የተገለጡትን የእግዚአብሔርን ባሕሪያት ተራ በተራ በማየት እንድናውቃቸውና እንድንለማመዳቸው የሚረዳን ነው። ልንለማመዳቸው የሚገቡንን የክርስቶስ ባሕሪያት በአንድ

ምእራፍ ውስጥ ብቻ ዘርዝረን መፈፀም እንደማንችል መታወቅ አለበት ሆኖም የአንድ ሺህ ኪሎ ሜትር ጉዞ በአንድ እርምጃ ይጀመራልና እንጀምረው።

ማንን እንመስላለን?

በሥጋችን ላይ ጨክነን ራሳችንን ካስለመድን እግአብሔርን መምሰል እንደሚቻል ብዙ ብለናል ነገር ግን እግዚአብሔርን ለመምሰል ልምምድ ከመጀመራችን በፊት አሁን ማንን እንደምንመስል፤ ወደፊትም ይህን እውነት ቸል ካልን ማንን ልንመስል እንደምንችል ከቃሉ እንመልከት።

ልጅ ሁሉ አባቱን ይመስላል። የተፈጥሮ አጋጣሚ ሆኖ በመልክ ባይመስለው እንኳ በባሕሪ መምሰሉ አይቀርም። በተግባሩ የማይመስለው ከሆነ ግን እውነተኛ ልጅነቱ አጠራጣሪ ይሆናል። በአገራችን ባሕል አንድ ልጅ መልካምም ሆነ ክፉ ሲሠራ «የማን ልጅ ነው?» ተብሎ መጠየቅ የተለመደ ነው። እንዲህ የሚደረገው ባሕሪውንና ተግባሩ ከወላጆቹ ማንነት ጋር የተሳሰረ ነው ተብሎ ስለሚታመን ነው።

ማንኛውም የሰው ተግባር የግለሰቡን አሳብ፣ ስሜትና ፈቃድ ሳያሳትፍ አይፈፀምም (በጣም የተለየ አጋጣሚ ካልሆነ በቀር) አሳቡ፣ ስሜቱና ፈቃዱ ደግሞ በተቆጣጠራቸው ሕይወትና መንፈስ እጅ የተያዙ ናቸው።

ምንም እንኳ እያንዳንዱን የሰውን አንቅስቃሴ ከመንፈስ ጋር ማዛመድ ተገቢ ባይሆንም አልፎ አልፎ የሰዎችን ባሕሪ ትኩረት ስናስተውል ከተግባራቸው ጀርባ የሚንፀባረቀውን መንፈሳዊ ተጽእኖ አለማየት አስቸጋሪ ነው። የዚህን አባባል እውነተኛነት ለማረጋገጥ ሐዋርያው ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች

በጻፈው መልእክቱ ውስጥ የገለጠውን እውነት ለአብነት እንመልከት፦

> *«እናንተ በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ምክንያት ሙታን ነበራችሁ፤ በዚህም የዓለምን ክፉ መንገድ ተከተላችሁ በአየር ላይ ላሉት መንፈሳውያን ኃይላት ገዥ ለሆነውና አሁንም ለእግዚአብሔር በማይታዘዙት ሰዎች ላይ ለሚሠራው መንፈስ እየታዘዛችሁ ትኖሩ ነበር።»* ኤፌ. 2:1-2 (አ.መ.ት)

ከመዳናችን በፊት እያንዳንዳችን በዕለት ተዕለት ተግባራችን የዓለምን ክፉ መንገድ በመከተል በአየር ላሉት መንፈሳዊያን ኃይላት ገዥ ለሆነው መንፈስ እንታዘዝና ፈቃዱን በመፈፀም እንኖር እንደነበር ስንቶቻችን ያኔ እናውቅ ይሆን? አሁንም እንኳ ወደ ኋላ ሄደን በተግባሮቻችን ውስጥ የመንፈስ ተጽእኖ እንደነበር ለመቀበል ያስቸግረን ይሆናል። ሆኖም የእግዚአብሔር ቃል ግልጽ እንደሚያደርግልን ያኔ እኛ ዛሬ ደግሞ ለእግዚአብሔር የማይታዘዙ ሰዎች ሁሉ በዚህ አለቃ መንፈስ ፈቃድ እንደሚመላለሱ ይነግረናል። ስለዚህ ባሕሪ የባዮሎጂ፣ የሳይኮሎጂና የኬሚስትሪ ውጤት ብቻ ሣይሆን በአንድም በሌላም መንገድ ከመንፈሳዊው ዓለም ጋር የተቆራኘ እንደሆነ እንመለከታለን።

ሐዋርያው ዮሐንስ ኃጢአትን የሚያደርጉና ጽድቅን የሚያደርጉ ሰዎችን ለይቶ የሚያስቀምጠው ጥሩና መጥፎ፣ መልካምና ክፉ፣ ጨዋና አመለኛ፣ ግብረገባዊና ሥርዓት አልባ በማለት ሳይሆን ግልጽ ባለና በማያሻማ ቃል የዲያቢሎስ ልጆች እና የእግዚአብሔር ልጆች በማለት ነው። (ይህንን የሚለው ለአማኞች በተጻፈ መልእክት ውስጥ መሆኑን ልብ ይሏል።)

> *«የእግዚአብሔር ልጆችና የዲያቢሎስ ልጆች በዚህ የተገለጡ ናቸው። ጽድቅን የማያደርግና ወንድሙን የማይወድ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም።»* 1ዮሐ. 3:10

ማንኛውም ሰው ሥጋዊ አባት እንዳለው ሁሉ ወደደም ጠላ መንፈሳዊ አባት አለው። አንድ ሰው በተለያየ ምክንያት

አባቱን «አላውቀውም አባቴ አይደለም» ብሎ ስለካደ አባቱ አባቱ ከመሆን አይፋቅም። ወደዚህ ዓለም ለመምጣቱ ምክንያት ሆኖታልና። ልክ እንዲሁ ሰው አወቀም አላወቀ መንፈሳዊ አባት አለው። በተግባሩም አባቱን ይመስላል።

መጽሐፍ ቅዱስ ሁለት አባት (አባትነት) እንዳለ ይነግረናል። አንደኛው እግዚአብሔር ሌላኛው ዲያቢሎስ። አሰቀድመን በዮሐንስ መልእክት ውስጥ እንዳነበብነው የእግዚአብሔር ልጆችና የዲያቢሎስ ልጆች የሚለዩት በውጪያዊ መልክ ሳይሆን ከውስጣቸው በሚገለጠው ባሕሪና ተግባር ነው። የእግዚአብሔር ልጆች እግዚአብሔርን ይመስላሉ፣ የዲያቢሎስ ልጆች ደግሞ ዲያቢሎስን ይመስላሉ። በዚህ ንዑስ ርዕስ የተነሳንበት ጥያቄ ይህ ነው፡- «እኔ ማንን እመስላለሁ?»

ሌሎች ማንን እንደሚመስሉና የማን ልጆች እንደሆኑ ማወቅ መልካም ቢሆንም አስቀድሞ ስለ ራስ ማወቅ ትልቅ ሚስተዋል ነው። በእርግጥ ማንም የፈለገውን ያህል የዲያቢሎስ ልጅ ቢሆን «እኔ ኮ የዲያቢሎስ ልጅ ነኝ።» ብሎ እንዲተዋወቀን አንጠብቅም። በአፉ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ እያለ በተግባሩ የዲያቢሎስ ልጅ ሆኖ ይቀጥላል እንጂ መንፈሳዊውን እውነታ ገልያ መናገር አዳጋች ነው።

በእርግጥ ብዙዎች የማይናገሩት ለመደበቅ ስለሚፈልጉ ብቻ ሣይሆን ስለማያውቁትና መንፈሳዊ አባታቸው በሆነው በዲያቢሎስ ስለተታለሉ ነው።

የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ወይስ የዲያቢሎስ ልጅ? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ መጀመሪያ እግዚአብሔርም ሆነ ዲያቢሎስን አጥርቶ ማወቅ ይጠይቃል። እግዚአብሔርም ሆነ ዲያቢሎስ በሚገባ የማያውቁ ሰዎች የዲያቢሎስ ልጅ «እኔ የእግዚአብሔር

ልጅ ነኝ» በማለት በውጪው የኃይማኖት ካባ ደርበው ቢመጣ አሜን ብለው ከማንገስ፣ የእግዚአብሔር ልጆች ደግሞ የዲያቢሎስ ልጆች ተብለው በሐሰት ሲከሰሱ በድንጋይ ከመውገር አይመለሱም።

እናውቃለን የሚሉት እንኳ አንዳንድ ጊዜ የሚታለሉት ዲያቢሎስ እንደፈለገ መልኩን ስለሚቀያይር ነው። ታዲያ ይህን መልክ የመቀያየር ችሎታ ለራሱ ብቻ ሳይሆን ለልጆቹም ይችራል።

> *«እንደዚህ ያሉ ሰዎች የክርስቶስን ሐዋርያት ለመምሰል ራሳቸውን የሚለዋወጡ ሐሰተኞች ሐዋርያትና አታላዮች ሠራተኞች ናቸው። ይህም የሚያስደንቅ ነገር አይደለም። ምክንያቱም ሰይጣን ራሱ የብርሃን መልአክ ለመምሰል ራሱን ይለዋወጣል። እንግዲህ የእርሱ አገልጋዮች የጽድቅ አገልጋዮች ለመምሰል ራሳቸውን ቢለውጡ የሚያስገርም አይደለም። ፍፃሜያቸውም እንደ ሥራቸው ይሆናል።» 2ቆሮ. 11:13-15 (አ.መ.ት)*

ችግሩ «የዲያቢሎስ ልጆች» የሚለው አሳብ ሲነሳ አእምሮአችን ፈጥኖ የሚሄደው በዓለም ወዳሉ ጠንቋዮች፣ ደጋሚዎች፣ አመንዝራዎችና ስካራሞች፣ ሌቦችና ነፍሰ ገዳዮች ወዘተ... ብቻ መሆኑ ነው። የሚያስገርመው ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ዲያቢሎስ ልጆች የተነገሩት ቃላት በአለም ስላለው ሣይሆን በቤተክርስቲያን፣ በሴኩዩላር ዓለም ስላለው ሳይሆን በኃይማኖት ዙሪያ የሚያጠነጥኑ መሆናቸው ነው።

ዲያቢሎስ ግዛቱ ስለሆነ በዓለም ብዙም የረቀቀ የሚታለል ስልት መጠቀም አያስፈልገውም። በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ግን ባለ በሉላ ተንኮሉ ካልተጠበቀ በቀር ዕድሜው አጭር ስለሚሆን ፈጥኖ የሽንገላ መረቡን በስውር ይዘረጋል።

ስለዚህ ራሳችንን ከዲያቢሎስ ባሕሪ ለመጠበቅ የዲያቢሎስንም ልጆች ለይቶ ለማወቅ መጽሐፍ ቅዱስ በሚገልጥልን ልክ ዲያቢሎስን በትክክለኛ መልኩ ማወቅ ይጠቅማል።

ስለ ዲያቢሎስ ልጆች በኃይማኖት ሰፈር ከተወሳ የዲያቢሎስ ልጅነትን አርቆና አሽቀንጥሮ ማሰብ አይጠቅምም። ይልቅ ደፈር ብሎ መለኪያውን ለማንሳትና በአግባቡ ለመመርመር መዘጋጀት ያዋጣል።

ይህ በቤተክርስቲያን ውስጥ «አይነኬ» የሆነ ርዕሰ ጉዳይ የበለጠ በጉልህ ለማሳየት አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን እንቃኝ።

ታሪኩ የሚገኘው በዮሐንስ ወንጌል ስምንተኛ ምዕራፍ ላይ ነው። ኢየሱስ ስለ አብና ስለ ራሱ አንድነት ሲናገር የሰሙት አይሁዳውያን «በቃ አመንብህ» ብለው ወደ እርሱ መጡ። ጌታም አመንን ማለታቸው ከልባቸው አንዳልነበር ስለሚያውቅ

> «አናንተ በቃሌ ብትኖሩ በእውነት ደቀመዛሙርቴ ናችሁ እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል አላቸው።» ዮሐ. 8:31

«የእኔ ተከታይ መሆናችሁ በወሬ የማይገለጽ ሣይሆን እውነትን ኣውቃችሁ በእውነትም አርነት ወጥታችሁ በቃሌ በመኖራችሁ የሚታይ ጉዳይ ነው።» ማለቱ ነው።

ሆኖም የእነዚህ አመንን ባዮች እውነተኛ ማንነት በገሃድ ለመጋለጥ ጊዜ አልፈጀበትም። «አርነት ትወጣላችሁ» የሚለው የጌታ ቃል ስለከነከናቸው፦

> «የአብርሃም ዘር ነን ለአንድም ሰንኳ ኣቶ ባሪያዎች አልሆንም አንተ፦ አርነት ትወጣላችሁ እንዴት ትላለህ? አሉት» ዮሐ. 8:33

በእርግጥ ጌታ አርነት ትወጣላችሁ ያለው ከኃጢአት ባርነት ነፃ ስለመውጣት ነው። ስለ ሥጋዊ ባርነት ሲሆንም እንኳ በዘመናት ውስጥ ተራ ደርሶት አይሁዳውያንን ያልገዛ ሕዝብና መንግሥት በጣት የሚቆጠር ነውና «እንዴት አርነት ትወጣላችሁ ትላለህ?» የሚያሰኝ ጉዳይ አልነበረም።

ጌታ ኢየሱስ ግን መንፈሳዊ እውነታ ላይ በማተኮር በእርሱና የአብርሃም ልጆች ነን የማንም ባሪያ አልነበርንም ማንም ነፃ

አያወጣንም በሚሉት አይሁዳውያን መካከል ያለውን ልዩነት ማሳየቱን ቀጠለ።

> «እኔ በአባቴ ዘንድ ያየሁትን እናገራለሁ አናንተም ደግሞ በአባታችሁ ዘንድ ያያችሁትን ታደርጋላችሁ።» ዮሐ. 8:38

የእነርሱ ትምህርት የአብርሐም ዘር ነን የሚል ነው። ጌታ በሥጋ የአብርሃም ዘር መሆናቸውን ቢቀበልም የአብርሃም ልጆች ነን የሚለውን ፉከራቸውን አሳስተናገደም። ለምን? መልሱ «አብርሃምን አትመስሉም» የሚል ነው። ልጅ አባቱን መምሰል አለበትና። አብርሃም የሥጋ አባት ብቻ አይደለም። የእምነት ፈለጉን ለሚከተሉ ሁሉ መንፈሳዊ አባትም ነው። ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ የአብርሃም ልጅነታቸውን በሥጋ እንጂ በመንፈስ ፈጽሞ አልተቀበለውም። ያቀረበው ምክንያት፦

> «የአብርሃም ልጆች ብትሆኑ የአብርሃምን ሥራ ባደረጋችሁ ነበር። ነገር ግን አሁን ከእግዚአብሔር የሰማሁትን እውነት የነገርኋችሁን ሰው ልትገድሉኝ ተፈልጋላችሁ። አብርሃም እንዲህ አላደረገም።» ዮሐ. 8:39-40

አለን የሚሉትና የሚመኩበትን የአብርሃም ልጅነት የተነፈጉት አይሁዳውያን ወዲያው ከአብርሃም ወደ ሙሴ በመዝለል

> «እኛስ ከዝሙት አልተወለድንም አንድ አባት አለን እርሱም እግዚአብሔር ነው አሉት።» ዮሐ. 8:41

ጌታ ኢየሱስም እንዲህ በማለት መለሰላቸው፦

> «እግዚአብሔር አባታችሁ ቢሆን በወደዳችሁኝ ነበር። እኔ ከእግዚአብሔር ወጥቼ መጥቻለሁና ... ።» ዮሐ. 8:42

ባጭር ቃል እግዚአብሔር አባታችሁ አይደለም ማለቱ ነው።

የአብርሃም ልጆች ነን ሲሉ አይ አይደላችሁም ምክንያቱም ሥራችሁ አብርሃምን አይመስልም። የእግዚአብሔር ልጆች ነን ሲሉ አይ አይደላችሁም ምክንያቱም ባሕሪያችሁ እግዚአብሔርን አይመስልም። የተባሉት አየሁዳውያን እና ታዲያ የማን ልጆች ነን? በሚል ስሜት ሊጠይቁ የተሰጣቸው መልስ ፈጽሞ ያልጠበቁት ነበር።

«እናንተ ከአባታችሁ ከዲያቢሉስ ናችሁ ...::» ዮሐ. 8:42

ኦ! እነዚያን የኃይማኖት ሰዎች የዲያቢሉስ ልጆች ብሎ ማለት እጅግ አስቸጋሪ ነው:: ጌታ ኢየሱስ ግን እንዲህ ያላቸው በላያቸው ላይ አባብ እንደተጠመጠመ በራእይ አይቶ ሳይሆን ማንም ሊያየውና ሊረዳው በሚችለው ሥራቸውና እርሱን በተመለከተ በሚገልጡት ባሕሪ ነበር:: ይህንንም

«እናንተ ከአባታችሁ ከዲያቢሉስ ናችሁ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ::» ዮሐ. 8:44

በማለት ገልፆታል::

ጌታ ኢየሱስ አብርሃምን አትመስሉም እግዚአብሔርን አትመስሉም ያላቸውን ሰዎች «ቁርጥ ዲያቢሉስን ትመስሳላችሁ» ያላቸው ዲያቢሉስን ከጥንት ጀምሮ ጠንቅቆ ስለሚያውቀው ነው:: ለዚህም ነው:-

«እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበር እውነትም በእርሱ ስለሌለ . . . ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና::» ዮሐ. 8:44

በክፍሉ መጀመሪያ «በስምህ አምነናል» ብለው ወደ ኢየሱስ የመጡት እነዚህ አይሁዳውያን እውነትን በነገራቸው ጊዜ ብዙም ሳይቆዩ «ሳምራዊ ነህ፣ ጋኔን አለብህ» ለማለትና በድንጋይ ለመውገር አልተመለሱም:: ዮሐ. 8:48-59 ያ የነገራቸው የአባታቸው የዲያቢሉስ የነፍሰ ገዳይነት ባሕሪ የተናገረው ሳይደርቅ በተግባር ተገለጠ::

መጥምቁ ዮሐንስም «እናንተ የእፉኝት ልጆች» ብሎ የጠራቸው ኃጢአተኛነታቸውን አምነው ለንስሐ ሊጠመቁ ወደ እርሱ የመጡትን ቀራጮችና ጋለሞቶች ላይሆን ጽድቅ ከእኛ በላይ ላሳር በማለት ውጪያቸውን በኃይማኖት ካባ አሽቆጥቁጠው ሕዝብ የሚመሩ ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ነበሩ:: እንዲህ ያላቸው ውጪያቸው የፈለገውን ቢመስልም በውስጣቸው ግን

መርዛም እፉኝት የፈሰፈሳቸው ሰመንደፍና ለመግደል ድክ ድክ የሚሉ የእፉኝት ግልገሎች ስለነበሩ ነው::

እዚህ ጋ አንባቢ «እና ታዲያ ምን ልትለን ነው?» በማለት ይጠይቅ ይሆናል:: ቤተክርስቲያን ውስጥ የዲያቢሉስ ልጆች የእፉኝት ግልገሎች የሉም ብሎ ማሰብ ምኝነት ነው:: በፊትም ነበሩ አሁንም ይኖራሉ:: እነዚህ ሰዎች አንዳንዴ ሕዝብ ሆ የሚልባቸው አገልጋይ፣ የክብር ወንበር የሚሰጣቸው መሪዎች ሊሆኑ ይችላሉ::

መፍትሔው ግን መመርመር እንጂ መጠርጠር አይደለም:: የምናውቃቸውም በራእይና በመገለጥ ሳይሆን በሥራቸውና አዘወትሮ በሚገለጥባቸው ባሕሪ ነው:: ሥራቸው ዲያቢሉስን ከመሰለ መጠሪያ ስማቸው የአገልግሎት ቢሮአቸው የፈሰገው ይሁን የዲያቢሉስ ልጆች ናቸው::

እንግዲህ ከዚህ አደጋ ለመትረፍ መፍትሔው አንድ ብቻ ነው «ማንን እመስለለሁ?» ብሎ በመጠየቅ ራስን መመርመርና በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን ለመምሰል መትጋት ነው::

8
የክርስቶስ ባሕሪያት

በዓለማችን ጠንካራ ከሚባሉት ማዕድናት አንዱና ዋነኛው አልማዝ ነው። ከመሬት የወጣን ጥሬ አልማዝ መስበርና ለጌጥ እንዲሆን መቅረፅ እጅግ አድካሚና በውስን ባለሙያዎች የሚከናወን የጥበብ ሥራ ነው።

ታዲያ ይህ ጠንካራ ክቡር ድንጋይ ሲሰበር በተለያዩ አቅጣጫዎች የተለያዩ ሕብረ ቀለማትን ማንፀባረቅ ይጀምራል። ልክ እንዲሁ የእግዚአብሔር ሕይወት በሰው ውስጥ እንዳይገለጥ የሚከለለው ከላይ የሚሸፍነው የሰው ውጭያዊ ሕይወት ሲሰበር የእግዚአብሔር ባህሪያት በተለያየ አቅጣጫ ማንፀባረቅ ይጀምራሉ። ምንም እንኳ ሥራው አድካሚ ቢሆንም ግለሰቡ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር እየተስማማ በመስቀሉ መንገድ ከሄደ ቀስ በቀስ የተዋረደው ተወግዶ የከበረው መገለጡ አይቀርም።

የእግዚአብሔር ሕይወት በሰው ኑሮ ውስጥ ሲገለጥ ልክ እንደ አልማዙ የእግዚአብሔር ባሕሪያት በተለያየ አቅጣጫ ማንፀባረቅ ይጀምራሉ። እነዚህ ባህሪያትም ብዙ ከመሆናቸው የተነሳ አንድ ባንድ እንዘርዝራቸው ብንል ወረቀትና ቀለም አይበቃንም። ሆኖም ዋና ዋናዎቹን ማናነሳ ብናልፍ ጉዟችንን ያደናቀፋልና አውራ የምንላቸው ሰባት ባህሪያት ላይ ብቻ አተኩረን አንድ ባአንድ እንመለከታለን።

አነዚህንም ባህሪያት የምናወሳው በጥቂቱ ነው። በጥልቀት እንመልከት ካልን ለእያንዳንዱ አንድ አንድ መጽሐፍ መፃፍ ሊኖርበት ይችላል። ሆኖም አንባቢያንን ለበለጠ ፍለጋ ለማነሳሳት በጥቂቱም ቢሆን ማቅመሱ መልካም ነውና ባሕሪያቱን በጥቂቱ እንመልከት።

እነዚህ ባህሪያት ከራሳችን፣ ከእግዚአብሔር እና ከሰዎች ጋር በሚኖረን የዕለት ተዕለት ግንኙነት ውሳኔ ሚና ይጫወታሉ። እንግዲህ በጥሞና ተመልከቶ ከራስ ጋር ለማዋሃድ ብሎም ለመለማመድ መትጋቱ ምትክ አይገኝለትም።

ፍቅር

> *«እንግዲህ እንደተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን ምሰሉ ክርስቶስ እንደወደደን ራሱንም ስለ እኛ መልካም መዓዛ ያለው መባና መሰዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር እንደሰጠ እናንተም በፍቅር ተመላለሱ።»*
>
> *ኤፌ. 5:1-2*

እግዚአብሔርን በመምሰል ልምምድ ውስጥ ፍቅርን ተራ ቁጥር አንድ ላይ ያመጣነው ያለምክንያት አይደለም። ምንም እንኳን ሌሎች ብዙ የባሕሪ መገለጫዎች ቢኖሩም እንደ ፍቅር ለእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ማንጠሪያ እሳት መለኪያ ጣት ስለሌለ ነው። እግዚአብሔር ሁለንተናው ፍቅር ነውና በፍቅር የማይኖር ከእግዚአብሔር አይደለም እግዚአብሔርንም ሊመስል አይችልም።

ፍቅር ብዙዎች እንደሚያስቡት ስሜት በስሜት ይገለፃል እንጂ ራሱ ስሜት አይደለም። ፍቅር ውሣኔ ነው። ራስን የመስጠት ውሣኔ። መስዋዕትነት የሌለበት ፍቅር እውነተኛ ፍቅር ሊሆን አይችልምና። በመስዕትነት ራስን መስጠት በጎ

ቃልን መስጠት፣ ስጦታን (ገንዘብን) መስጠት፣ ጊዜን መስጠት፣ ደስታን መስጠት፣ ወዘተ ... ሊሆን ይችላል። ይህን ዓይነቱን ፍቅር የመስዋዕትነት ፍቅር የሚያሰኘው ደስ ሳይለን ደስታን መስጠት፣ ሳይተርፈን ገንዘብ መስጠት፣ ተጣበን ጊዜን መስጠት፣ ሳይሰማን በጎና መልካም ቃል ለመስጠት ስንችል ነው። ታዲያ መስጠት ሁሉ ከፍቅር ጋር ሊዛመድ አይገባም። ዓሣ ለለመነ እባብ መስጠትም አለና።

ከላይ የጠቀስነው ክፍል «እንግዲህ እንደ ተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን ምሰሉ . . .።» ሲል በምሳሌ የሚያሳየን በአንድ ትልቅ ቤት ውስጥ የሚኖሩ የአንድ አባት ልጆችን ነው። በአንድ ቤት ውስጥ ብዙ ልጆች ቢኖሩም ሁሉ እኩል አይወደዱም፣ ልጅ በመሆናቸው እኩል ቢሆኑም እንኳን በምግባራቸው የበለጠ የሚወደዱ ልጆች ይኖራሉ። ጳውሎስም እያለ ያለው «እናንተም ልጆች ብቻ ሣይሆን «የተወደዱ ልጆች» ሁኑ» ነው። የተወደዱ ልጆች እነማን እንደሆኑ ሲነግረን ወላጃቸውን የሚመስሉት እንደሆኑ በማመልከት «እንደተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን ምሰሉ ይለናል።» እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል ለማሳየትም በቀጥታ የሚጠቅሰው በክርስቶስ የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ፍቅር ነው። እግዚአብሔር በሥጋ የተገለጠው በክርስቶስ ነውና። ስለዚህ «ክርስቶስ እንደወደዳችሁ ... እናንተም በፍቅር ተመላለሱ።» ይለናል። የመወደዳችን ልክ ግልጽ ሆኖ ተቀምጦልናል። «ክርስቶስ እንደወደደን»። ክርስቶስ የወደደን በላይ በዙፋኑ ላይ ተቀምጦልናል። ጌታ ኢየሱስ ፍቅሩን የገለፀልን በስማይ ዙፋኑ ተቀምጦ «እወዳችኋለሁ!» በማለት ሳይሆን «ስለ እኛ መልካም መዓዛ ያለው መባና መስዋእት

አድርጎ በመስቀል ላይ ራሱን ለእግዚአብሔር በመስጠት ነበር።»

መባና መሥዋዕት መዓዛ የሚኖረው ሲቃጠል ነው። የሚቃጠል መሥዋዕት እንዴት እንደሚቀርብ በዘሌዋውያን ምዕራፍ አንድ አስከ ምእራፍ አራቸ በሚገባ ተጽፎልናልና ልናየው እንችላለን።

ስለሚቃጠል መስዋዕት በቅድሚያ መታወቅ ያለበት የእንስሳው ሥጋ የሚቃጠለው ስለሌላው ሰው ኃጢአት እንጂ ስለ ራሱ አለመሆኑ ነው። የሚቀርበውም ለእግዚአብሔር እንጂ ለለው አይደለምና መከራውን የሚያይለት እግዚአብሔር ብቻ ነው። ስለ ፍቅር ለሌላው በመቃጠሉ የሚወጣው ሽታ ሰሌሎች ደስ የማያሰኝ ቢመስልም እግዚአብሔር ግን በውስጡ ፍቅርን ስለሚያሸት የተወደደና ጣፋጭ መዓዛ ያለው ሽታ ይሆንለታል።

ለዚህ ነው ሐዋርያው ዮሐንስ ስለፍቅር ሲጽፍ ፦

«እግዚአብሔር ፍቅር ነው በፍቅር የሚኖር በእግዚአብሔር ይኖራል እግዚአብሔርም በእርሱ ይኖራል። በዚህ ዓለም እርሱን እንመስላለንና።» ፩ዮሐ. 16፣17 ያለው። (አ.መ.ት)

ይህንኑ ክፍል ሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም እንዲህ ይለዋል፦

«. . . ፍቅር በዚህ ከእኛ ጋር ተፈጽሞለል አርሱ እንዳለ እኛ ደግሞ እንዲሁ በዚህ ዓለም ነንና።» (የ1962 ትርጉም)

እንግዲህ እርስ በርሳችን ልንዋደድበት የሚገባን የእግዚአብሔር ፍቅር ማለት ይህ ነው።

ጌታ • ኢየሱስ በተራራው ትምህርት በዙሪያው ለተሰበሰቡ አይሁዳውያን ተከታዮቹ በፀጋና በእውነት የተሞላውን የሕይወቱን ሕግ ከቀደመው የጽሕፈት ሕግ ጋር እያነፃፀረ ሲሰጥ

> *«ለቀደሙት ‘አትግደል እንደተባለ ሰምታችኋል የገደለም ሁሉ ፍርድ ይገባዋል።’ እኔ ግን እላችኋለሁ በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል . . .።» ማቴ. 5:21-22*
>
> *ብሏል። «የሚቆጣ» የሚለው አንዳች ስህተት አይቶ የሚቆጣ ሰማለት ሳይሆን የጥላቻ ቁጣ በውስጡ የሚነድ ማለቱ ነው። በሌላ ሥፍራ «ወንድሙን የሚጠላ ሁሉ ነፍስ ገዳይ ነው። . . .።» ተብሎ እንደተገፈ።*

የቀደመው (አትግደል) የውጭ ድርጊትን የሚያመለክት ሲሆን የአሁኑ (አትቆጣ/አትጥላ) የውስጥ ዝንባሌን ያሳያል። የቀደሙት ሕጉን ለመጠበቅ የሚጥሩት ባለመግደል ሲሆን የአሁኖቹ ግን ባለመጥላት ነው። እንግዲህ እግዚአብሔርን ለመምሰል ራስን ማስለመድ ማለት ወንድምን ወይም እህትን ወይም ሌላውን ሰው ላለመጥላት ልብን ማስለመድ ማለት ነው።

ከምንግዜውም ይልቅ በዘመናችን ብዙ የአካል ብቃት ማሰልጠኛ ተቋሞች እየተከፈቱ ነው። ይህም የሚያመለክተው ሰዎች ለጤናቸውና ለሰውነታቸው ቅርጽ ምን ያህል ግድ እያላቸው እንደመጣ ነው። ይህ ልምምድ በእርግጥ ይጠቅማል ሆኖም ጥቅሙ በምድር የተወሰነ ነዉና ለጥቂት ይጠቅማል። ነገር ግን ለአሁኑም ለሚመጣውም ሕይወት ተስፋ ስላለው ለነገር ሁሉ የሚጠቅመው እግዚአብሔርን ለመምሰል ራስን ማስለመድ ነው።

ልብን ለጽድቅ ለማሰልጠን፣ መንፈሳዊ ጤንነትን ለመጠበቅና ክርስቶስን ለመምሰል መንፈስ ቅዱስ ከዘመናት በፊት የከፈተው ጂም አለ። ያም ጂም ቤተክርስቲያን ናት።

የቅዱሳን መሰብሰብ ዓላማ የስብከትና የዝማሬ ትርጒት ለማየት ሳይሆን የዕብራውያን መልዕክት ፀሐፊ እንደሚለው፡ -

> *«. . . ለፍቅርና ለመልካም ሥራ እንድንነቃቃ እርስ በርሳችን እንተያይ በአንዳንዶች ዘንድ ልማድ እንደሆነው መሰባሰባችንን እንተው . . ።» ዕብ.11:24-25*

ስለዚህ የመተያየታችን ዓላማ አስቀድሞ ለፍቅር ከዚያም ከፍቅር ለሚመነጭ መልካም ሥራ ለመነቃቃት እንጂ ፕሮግራም ለመከፈል ብቻ መሆን የለበትም። የእግዚአብሔርን ሕይወት ተካፍለናልና እንደ እግዚአብሔር በመስዋዕትነት ማፍቀር እንችላለን። ወደዚህ ለመድረስ የሚያስፈልገን አንድ ነገር ብቻ ነው ያለመታከት የሥጋን ባሕሪ እየገፈፍን የእግዚአብሔርን ሕይወት ባሕሪ ለመግለጥ ራስን ማስለመድ።

ይቅርታ

> *«እግዚአብሔርም ደግሞ በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ ይቅር ተባባሉ።» ኤፌ. 4:32*

የይቅርታ ጥያቄ ከምንጊዜውም ይልቅ የዘመናችን፣ ከውጭ ሥቹ ይልቅ (የሌሎቹን ጓዳ ስለማናውቅ) የአገራችን፣ ከፖለቲካው ይልቅ የቤተክርስቲያናችን ጥያቄ ከሆነ ውሎ አድሯል።

ይህ መጽሐፍ በሚዘጋጅበት ጊዜ እንኳ በአገርም ውስጥ ሆነ ከአገር ውጭ ተበትነው ያሉ ብዙ ኢትዮጵያን ቅዱሳን ተጣልተዋል፣ ተከፋፍለዋል፣ ተካሰዋል፣ እርቅ አሻፈረኝ ብለው፣ ለያዥ ለገራዥ አስቸግረዋል።

ሆኖም የእግዚአብሔርን ቃል እውነተኝነት የሚወስነው በእኛ ብርታትና ድካም አይደለምና እኛ ብንስትም እውነቱ

አይለወጥምና የእውነትን ባንዲራ ከፍ አድርገን ማውለብለባችንን አንተውም።

ደግሞስ እግዚአብሔር እውነተኛ የንሥሐ መንፈስ ሰጥቶን በእሺታም መንፈስ ደግፎን ወደልባችን ተመልሰን አንታረቅና ዳግም የመንፈስ አንድነት ይኖረን እንደሁ ማን ያውቃል?

ታዲያ ይህ ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር እኛን በክርስቶስ ይቅር እንዳለን እኛም እርስ በእርሳችን ይቅር እንድንባባል ያስፈልጋል። ይቅርታ ስንል የሽንገላ፣ የይሉኝታ፣ የግብር ይውጣ፣ በኘሮግራም የሚመጣ ካንገት በላይ መሳሳምና የአዞ እባ የማፍሰስ ጉዳይ ሣይሆን ከልብ የመነጨ ፣ያለፈውን ወደኋላ ጥሎ የወደፊቱን ተግዳሮት ቢጋራ ለመፍታት የሚያስችል እውነተኛ ይቅርታ ማለታችን ነው።

እግዚአብሔርን መምሰል በአሁኑ ዘመን በረከት በሚመጣው ደግሞ ሽልማት እንዳለው ሁሉ እግዚአብሔርን አለመምሰል በተቃራኒው ዓለምን መምሰልና የሥጋን ባሕሪ መግለጥ ርግማንና ፍርድን እንደሚያመጣ ልንዘነጋው አይገባም።

የጌታ ደቀመዝሙር የዮና ልጅ ስምኦን ባልንጀራውን ምን ያህል ጊዜ ይቅር ማለት እንዳለበት ለጠየቀው ጥያቄ ጌታ በሰባ በማባዛት ከመለሰለት በኋላ ለደቀመዛሙርቱ የነገራቸው ምሳሌ ትልቅ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነው።

ንጉሱ የመንግሥቱን ሂሳብ በሚቆጣጠርበት ጊዜ ዕዳ የነበረበትን ባሪያ ይዘውለት መጡ። የነበረበት ዕዳ አልፍ መክሊት ሲሆን በአሁኑ ዘመን በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ብር ጋር ይስተካከላል።[45] ዕዳውን ባይተውለት ኖሮ የነበረው

አማራጭ መክፈል ስለማይችል በዘመኑ ሥርዓት እርሱ፣ ሚስቱ፣ ልጆቹ እና ያለው ሁሉ ተሸጦ ዕዳው መከፈል ነበረበት። ነገር ግን ባለዕዳው ወድቆ በለመነው ጊዜ ንጉሱ ምኅረት አደረገለት፣ ዕዳውንም ተወለት።

ምሳሌው በመቀጠል ይህ ብዙ ዕዳ የተተወለት ባሪያ ከንጉሡ ፊት ከወጣ በኋላ መቶ ዲናር የእርሱ ዕዳ የነበረበትን ሌላ ባሪያ እንዳገኘ ይነግረናል። መቶ ዲናር በዘመናችን ሲሰላ ጥቂት ብር እንደሆነ ይገመታል።[46] ይህ ከንጉሡ ምህረት ያገኘ ሰው የራሱን ባለዕዳ ገንዘቤን ክፈለኝ ብሎ ያዘና አነቀው። ይህ ባለዕዳም ወድቆ እንዲታገሰው ለመነው ልክ እርሱ በንጉሡ ፊት እንዳደረገው። ይህኛው ግን አልራራለትም፣ ሊምረውም አልወደደም። ይልቅ ዕዳውን እስኪከፍል ድረስ እስር ቤት አኖረው። ይህን ያዩ የንጉሡ ባሪያዎች የሆነውን ነገር ለንጉሡ አወሩለት። ንጉሡም ያን ዕዳ የነበረበትን ነገር ግን በምህረትም የተተወለትን ሰው አስጠራና «አንተ ክፉ ባሪያ፡- ስለ ለመንኸኝ ያን ዕዳ ሁሉ ተውሁልህ እኔ እንደማርሁህ ባልንጀራህ የሆነውን ያን ባሪያ ልትምረው አንተስ አይገባህምን? አለው። ጌታውም ተቆጣና ዕዳውን እስኪከፍል ድረስ ለሚያሰቃዩት አሳልፎ ሰጠው።»

ጌታ ኢየሱስ ይህን ምሳሌ ካቀረበ በኋላ እንዲህ በማለት በአንድ ዓረፍተ ነገር ሲቋጨው እናያለን።

> *«ስለዚህ አያንዳንዱ ወንድሙን ከልቡ ይቅር ካለ አንዲሁ ደግሞ የሰማዩ አባቴ ያደርግባችኋል።» ማቴ. 18:35*

ይህ ምሳሌያዊ ትምህርት አስደንጋጭ መልእክት አለው። ዛሬ የትኛውም ሰው እኛን ለመበደል ሙሉ ጊዜውን ቢሰጥ እንኳ እኛ በዘመናችን ሁሉ እግዚአብሔርን የበደልነው ያህል ሊበድለን አይችልም። እግዚአብሔር ይቅር ያለን የአልፍ

መክሲቱን ያህል ሲሆን እኛ ደግሞ ባልንጀራችንን ይቅር አንድንል የተጠየቅነው የዲናሩን ያህል ነው። ይህን ማድረግ ከተሳነን ግን በቃሉ እንደተፃፈው እግዚአብሔርም የእኛን የበደል ዕዳ እንደገና መቁጠር ይጀምራል። በእግዚአብሔር መንግሥት ሥርዓት ውስጥ ሰውን የሚያሳስረው ባለዕዳ መሆን አይደለም። ባለ ዕዳ ይቅርታ በመጠየቅ ብቻ ምሕረትና የዕዳ ስረዛ ያገኛልና። የማያሳስረው ግን የእኛ ዕዳ ኖሮበት ይቅርታ የጠየቀንን ምሕረት ለመስጠት ፈቃደኛ ባለመሆን ማሰር ነው። ሥርዓቱ ይሄ ነው። ሌላውን ይቅር ማለት ተስኖት ያሰረ ይታሰራል አስሩም ይበረታል። መታሰር ማለት መኖር ማቆም ማለት ሣይሆን ነፃነት ማጣት፣ የፈለጉትን አለመሆን፣ ወደ ወደዱት አለመሄድ፣ ባጭር ቃል መገደብ ማለት ነው። በቅርቡ አሁን በአስር ላይ የሚገኙ አንድ የቀድሞ ትልቅ ባለስልጣን ልጠይቅ ወደ ወህኒ ቤት አመራሁ። እኘህ ሰው አዚያው እስር ቤት ውስጥ ወደ ጌታ መጥተው እግዚአብሔርን ያመልክሉ። ከብዙ ፍተሻና ጥበቃ በኋላ ገባሁና ጠባቂ ፖሊስ መሃከላችን ቆሞ ከአጣና በተሠራ የአንድ ሜትር ርቀት ባለው አጥር ተንጠራርተን ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ስለ ጌታ ነገር የጦፈ ጫወታ ጀመርን። ለተወሰኑ ደቂቃዎች ከተነጋገርን በኃላ ጫወታችንን ሳንጨርስ በመካከላችን የነበረው ፖሊስ ሰዓቱ እንደደረሰና ማቆም እንዳለብን ነገረን ያን ጊዜ እኛ የቀድሞ ትልቅ ባለስልጣን በለሆሳስ «አባክህ አምስት ደቂቃ» ብለው ቢለምኑትም ፈቃደኛ አልነበረምና የጀመርነውን ሳንጨርስ አሳቸውም ወደ ክፍላቸው እኔም ወደ ቤቴ በየፊናችን ለመለያየት ተገደድን። እኘህ ሰው በመታሰራቸው መኖር አላቆሙም ነገር ግን የወደዱትን ማድረግ እንዳይችሉ ተገደቡ። ይህንን ሁኔታ ላለፉት ብዙ አመታት ኖረውበታል ከዚህ በኃላም ምን ያህል ጊዜ እንደሚኖሩበት አላውቅም ነገር ግን ወደ

በነፃነት ዓለም ወደ ቤቴ እየቀናሁ የመታሰርን መራርነት ለመጀመሪያ ጊዜ ማጤን ቻልኩኝ። ዛሬ በእግዚአብሔር መንግሥት (በቤተክርስቲያን) ውስጥ ስንቶች ስንቶችን ይቅር ባለማለት አስረን ስላሰርንም ታስረን ይሆን?

በሰማያዊው መንግስት ሥርዓት ለመፈታት መፍትሔው አንድ ነው። መፍታት፣ ሥልጣኑ ለለሌለን ሰዎችን በአካል አናስር ይሆናል። በደሉን ለምንላቸው ሰዎች ከልብ ይቅርታን ለመስጠት የማንወድ ከሆነ ግን ሰላማቸውን፣ ጤናቸውን፣ በረከታቸውን፣ ስኬታቸውን . . . ወዘተ እናስራለን ስላሰርን ደግሞ እኛም እንታሰራለን።

ይቅርታ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የገባንበት በውስጡም የምንኖርበት የህልውናችን መሠረት ነውና ይህን መሠረት ማፍረስ የቆምንበትን እንደ መናድ ነውና ልንጠነቀቅ ይገባል።

በሌሎች በደል ሲደርስብን የሚፈጥረው ስሜት ቀላል አይደለም። በግንኙነት መሃል አንድ በደል ሲፈፀም ሁለት እጥፍ ተጠቂ የሚሆነው ተበዳዩ ሰው ነው። አንድም በተፈፀመው ነገር ይጎዳል ሌላም ስሜቱ በመጉዳቱ ለጥላቻ፣ ለቂምና ለበቀል ይጋለጣል። የተበደለን ሰው በዋነኝነት የሚጉዳው ሌላው ግለሰብ ያደረሰበት ነገር ሳይሆን በዚያ ምክንያት ከሚከቡት የጥላቻ፣ የቂምና የበቀል አሳቦችና ስሜቶች ጋር የሚገጥመው ግብ ግብ ነው።

እነዚህን አሳቦችና ስሜቶች ለጊዜው ያባረርን ሊመስለን ይችል ይሆናል ውሎ ካደረና የተፈፀመውን ነገር በይቅርታ ሳንቋጭ ፀሐይ ደጋግማ ጠልቃ ከወጣች ግን እነጥላቻ በላያችን

ከመብረር አልፈው በውስጣችን ጉጆ መቀለስ ይጀምራሉ። በጉጆአቸውም የሚያድረውና የሚስተናገደው የዲያቢሎስ አሳብና ፈቃድ ይሆናል። ስለዚህ የተበደለ ሰው ለውጪያዊም ለውስጣዊም፣ ለአካላዊም ለመንፈሳዊም ጥቃት ተጋላጭ ነውና በእርግጥ ሊታዘንለት ይገባል።

ሆኖም መፍትሄው ያለው በራሱ እጅ ነው። አስቀድሞ ራሱን ከዚያም የበደለውን ሰው የሚታደገው ስሜቱን አሽንፎ ፣ ሃሳቡን ገዝቶ ከልብ ይቅርታ ሲያደርግ ብቻ ነው።

አንድ ጊዜ አንዲት ውብ፣ የተማረችና ብሩህ አእምሮ የነበራት ወጣት ከአንድ ወንድ ጋር አጭኝነት ትጀምርና ለጥቂት አመታት አብረው ይጓዛሉ። ይህች ወጣት በፍቅር ታስራለችና ሁሉንተናዋን በእርሱ ላይ ጥላ የወደፊት ኑሮአቸውን ታልማለች።

ሆኖም ይህ ያፈቀረችው ሰው ታማኝ ሆኖ አልተገኘም። ገንዘቧን፣ ንብረቷን ዘርፎ ይሔድና ሌላ ሴት ጋር ኑሮ ይጀምራል።

ይህች ወጣት በሁኔታው ትሰበራለች፣ ቤተሰቦቿ ወዳጆቿ በነገሩ ይበግናሉ። ያ ሕይወቷን ያበላሸ ሰው ግን ኮጥቂት ጊዜ በኋላ ገንዘቡን ሁሉ ጨርሶ በበሽታ ተለክፎ መማቀቅ ይጀምራል። መቼም ወሬ አይደበቅምና ሰውየው ታሞ በሞት አፋፍ ላይ እንዳለ ይህች ወጣት ትሰማለች። ወዲያውኑ ያለበትን አጠያይቃ ትሄድና ከልብ ይቅርታ እንዳደረገችለት ትነግረዋለች።

በደረሰባት ነገር እጅግ ካዘኑት ወዳጆቿ መሃል አንዱ ያደረገችውን ሲሰማ ይናደድና እንዴት እንዲህ ታደርጊያለሽ? በማለት በቁጣ ይጠይቃታል። እሷ ግን በእርጋታ "ይኸውልህ ወዳጄ እውነትህን ነው። ይህ ሰው ካደረሰብኝ ጉዳት የተነሳ ይቅርታ እንዳደርግለት አይገባው ይሆናል። ይቅርታ ያደረኩለት ግን እርሱ ስለሚገባው ብቻ ሳይሆን እኔ ስለሚገባኝ ነው።

ላለፉት ረዥም ወራት እኔ በጥላቻ በቂምና በበቀል ስሜት ስሰቃይ ከርሜያለሁ ሄጀ ይቅርታ ከሰጠሁት በኋላ ግን ልነግርህ "የማልችለው ሰላምና ደስታ እረፍትና ነፃነት በውስጤ አለ። ታዲያ ይህ ለእኔ አይገባኝምን?" በማለት መለሰችለት።

ሰዎችን ይቅር የምንለው እነርሱ ስለሚገባቸው ብቻ ሣይሆን እኛ በይቅርታ የሚገኘው እረፍትና ነፃነት ስለሚገባን ነው።

ብዙን ጊዜ ተበድለን ወደ ደቅርታ የማንሄደው በሽንገላ ምክንያት ነው። ተጉድተንና አዝነን፣ በጥላቻና በበቀል ስሜት ተሞልተን እያለ "አይ እኔ ደህና ነኝ አልተጐዳሁም፣ ጥላቻም የለብኝም ..... ይብላኝ ለሱ ወይም ይብላኝ ለሷ" በማለት ራሳችንን እናታልላለን። ውስጣችን በነገር ተመርዞ እንደበታችን ሰላም እንደሆንን ቢናገርም የውስጡ ጥላቻ በውጭ በተግባር መገለጡ አይቀርም።

ለዚህ መፍትሄው እውነትን ተቀብሎ ፊት ለፊት መጋፈጥ ነው። ከተበደልን ተጉድተናልና በእግዚአብሔርም በሰው ፊት እውነተኛ ሆነን መፍትሄ መሻት ይኖርብናል። የመፍትሄውም ሀ ... ሁ... ይቅርታ ነው።

መቼም ቢሆን በግንኙነት መሐል ግጭቶች መፈጠራቸው አይቀርም። ስለዚህ የግጭት መከሰት ሊያስደንቀን አይገባም። ሊያስደንቀን የሚገባው ግጭቱ የተፈታበት መንገድ ነው። ግጭቶችን ለመፍታት የእግዚአብሔርን መንገድ ወይም የዲያቢሉስን መንገድ፣ የመንፈስን ወይም የሥጋን መንገድ፣ ንጽህት የሆነችውን የሳይኖይቱን ጥበብ ወይም ከምድር ከሥጋና ከአጋንንት የሆነውን የታችኛውን ጥበብ ልንከተል እንችላለን። አሁንም ምርጫው የእኛ ነው።

የእግዚአብሔርን መንገድ ከመረጥን ጉዳያችን የሚጀመረውም ሆነ የሚጨረሰው በይቅርታና በምህረት ነው። በእርግጥ ይህን መንገድ ስንመርጥ በሰዎች ዓይን እንደሞኝና እንደ ደካማ ልንቆጠር እንችል ይሆናል። የሕይወት እሴታችን፣ የኑሮ ስሌታችን እግዚአብሔርን መምሰል ከሆነ ግን ግድ የሚሰን በእግዚአብሔር ፊት የሚኖረን ማንነት ነውና በሰዎች ፊት የመዋረድን ነውር መናቅ አይከብደንም።

በዘመናችን በቤተክርስቲያን አካባቢ ለዚያውም በመሪ አገልጋዩች ዙሪያ የሚከሰቱ ግጭቶችን በይቅርታ መፍታት በምህረት መቋጨት የማይታሰብ ጉዳይ እየሆነ መጥቷል። በአደባባይ ይቅርታን የሚያውጁ «ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ» ብለው ሕዝብን የሚማፀኑ ሰዎች እርስ በርሳቸው መታረቅ አቅታቸው በየአደባባዩ ሲራኮቱ ማየት የተለመደ ተግባር ከሆነ ሰንብቷል።

ለምን? አንድ የተታለልንበት ረቂቅ የዲያቢሉስ ስልት አለ። «አንተ አኮ ከአገሉ ጋር የግል ጥል የለህም ይህ የአሠራርና የድርጅት ህልውና ጉዳይ ነው።» የሚል የዲያቢሉስ ሽንገላ። ሆኖም እነዚህ ሰዎች በአሰራር እና በድርጅት ስም ይሁን እንጂ

ከሚሟገቷቸው ሰዎች ጋር የግል ጥላቻ እንዳላቸው ተግባራቸው ይመሰክራል።

ለመሆኑ በድርጅት ህልውና ስም ይቅርታን መንፈግና ጥላቻን ማንገስ የተፈቀደው የቱ ጋ ነው? እግዚአብሔርስ በግል መጣላትንና በቡድን መጣላትን ለይቶ ያየዋልን? በግል ሆነ በቡድን ጥል ጥል ነውና። ታዲያ በቡድን ሲሆን የሚፀድቀው በየትኛው ሥሌት ነው?

በአገር ውስጥ ሆነ በውጭ ያሉ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያናት ግጭቶች ቢጠኑ ሊለዩ በሚገቡ አስተምህሮዎችና የቅድስና ጉዳዮች ላይ የተመሠረተ ችግር እምብዛም አይታይም። አብዛኛው ምናልባትም ሁሉም ከወንበርና ከጥቅም ጋር የተሳሰሩ እንዳይሆኑ ያስፈራል።

ደግሞስ በአስተምህሮና በቅድስና ጉዳይስ ቢሆን እንደቃሉ በፍቅርና በማቅናት መንፈስ እርምጃ ይወሰዳል እንጂ በጥልና በክርክር የሚገኝ ምን ፋይዳ አለ?

ይቅርታ የእግዚአብሔር ባህሪ ነው። እግዚአብሔርን ለመምሰልና የእርሱን ባህሪ ለመግለጥ የምንወድ ከሆነ ግጭቶቻችንን በእውነተኛ ይቅርታ ከመፍታት ሌላ ምንም አማራጭ የለንም። በእርግጥ ደረሰብን ከምንለው በደል የተነሳ በይቅርታ የማለፍ ጥያቄ ሲነሳ ሥጋችን አካኪ ዘራፍ ማለቱ የማይቀር ነው። ነገር ግን በፀሎትና በቃሉ በታገዘ ልምምድ መንፈሳችን ጠንክሮ ሥጋችንን መግዛት ከቻለ ልፍስፋውን ፀጥ ማሰኘትና በዙሪያችን ላሉ ሁሉ የመንፈስን ፍሬ ጣዕም ማቅመስ ይችላል።

ከእርሱ ጋር ላለን ግንኙነት ስስ ልብ፣ ከሰዎች ጋር ላለን ግንኙነት ደግሞ ጠንካራ ቆዳ እግዚአብሔር ይስጠን።

ትህትና እና የዋኅነት

እግዚአብሔርን በግርማውና በሞገሱ በገናናው ዙፋኑ ላይ ስናስበው «ትሑት» ነው ብሎ ለመገመት ያስቸግራል። ክብሩ ታላቅነቱን እንጂ ትህትናውን አያሳየንምና። የብሉይ ኪዳን መጻሕትም ቢሆኑ እግዚአብሔር ትሑት ስለመሆኑ እምብዛም አልነፉልንም።

ይህ እንግዲህ እኛ ስለ እግዚአብሔር ያለን ግምት ነው። አሁን ግን እግዚአብሔር በልጁ ተገልጧል። እግዚአብሔርን ያየው አንድም ሰው ባይኖርም እንኳ በእቅፉ ያለው አንድ ልጅ አርሱ ተርኮልናል። ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ቆይታው የማይታይ አምላክ ምሳሌ እንደመሆኑ መጠን አያንዳንዱ እንቅስቃሴው የማይታየዉን ባሕሪ በገሃድ የሚገልጽ ነበር።

በእርግጥ ኢየሱስ የዋህና ትሁት ነበር። በናዝሬት ከተማ አነስተኛ ገቢ ባለው ቤተሰብ ውስጥ ሲያድግ፣ በቤተመቅደስ መምህራን እግር ሥር ተቀምጦ ሲሰማና ሲጠይቅ፣ ወደ ቤተሰቦቹ ተመልሶ ሲታዘዝ፣ በዮሐንስ እጅ ሲጠመቅ፣ ያልተማሩ ዓሣ አጥማጆችን እና ጎብረተሰቡ ያገለላቸውን ቀራጮች ተከታዮቹ ሲያደርግ፣ ከኃጢአተኞች ጋር ሲበላና ሲጠጣ፣ ድሆችን ሲያስተምር፣ ለምፃሞችን ከነቁስላቸው በእጁ እየዳሰሰ ሲፈውስ፣ በቢታንያ በማርታና በማርያም ቤት ሲስተናገድ፣ ወደ ኢየሩሣሌም በአህያና በውርንጭላ ተጭኖ ሲገባ፣ የደቀመዛሙርቱን እግር ሲያጥብ፣ በሚገርፉት፣ በሚፈርዱባትና፣ በሚያንላቱት ፊት ዝም ሲል፣ በመስቀል ላይ የመጨረሻ የውርደት ሞት ለመሞት ፈቃደኛ ሲሆን በዚህ ሁሉ ውስጥ ትህትናው እና የዋህነቱ እጅግ ደምቆ ይታያል።

ትሑት ነው ማለት አቅም የለውም ኃይል የለውም ማለት አይደለም። ኢየሱስ በጠላት ፊት፣ በትዕቢት ፊት ብርቱና ኃያል እንጂ የዋህና ትሁት ሆኖ አያውቅም። ትህትናን የት ኃይልን ደግሞ የት እንደሚገልጥ ያውቃል። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን ዮሐንስ በፍጥሞ ደሴት ያየውና በራእይ መጽሐፍ ውስጥ የጻፈው ትዕይንት ነው። በሰማይም ሆነ በምድር ላይ ከምድርም በታች ቢሆን የሰውን ልጆች ዘላለማዊ ጉዳይ ይዞ የተዘጋውን መጽሐፉን ሊዘረጋ ወይም ሊመለከተው ማንም እንዳልቻለ ሰምቶ እጅግ ባለቀሰ ጊዜ ከሽማግሌዎቹ አንዱ መጥቶ «አታልቅስ እነሆ ከይሁዳ ነገድ የሆነው አንበሳ አርሱም የዳዊት ሥር መጽሐፉን ይዘርጋ ዘንድ ሰባቱንም ማህተም ይፈታ ዘንድ ድል ነስቶአል» አለው። ዮሐ. ራዕይ 5:1-6

ዮሐንስ ጠላቶቹን ሁሉ ድል ስለነሳ አንበሳ ሲሰማ ለማየት ቸኩሎ ለማየት ዞር ሲል ያየው የጠበቀውን ሳይሆን የተሰየ ነገር ነበር።

«ለዙፋኑና በአራቱ አንስሶች መካከልም በሽማግሌዎች መካከል እንደታረደ በግ ቆሞ አየሁ . . .::»

ድል ስለነሳ አንበሳ ተነግሮት ዞር ሲል ያየው ግን የታረደ በግ ነበር። አዎን ኢየሱስ በጠላቶቹ ፊት የሚያደቅና የሚሰባበር አንበሳ፤በአባቱ ዙፋን ፊት ግን የታረደ በግ ነው።

በግ የትህትና፣ የየዋህነት ምሳሌ ነው። ኢየሱስም እንወርሰውና እንመስለው ዘንድ የእግዚአብሔርን የትህትና ባሕሪ ገልያልናል።

«.. ከእኔም ተማሩ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና ...» ማቴ 11:29

በማለት።

ጌታ ኢየሱስ በዮርዳኖስ ወንዝ በውሃ ተጠምቆ ሲወጣ መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ላይ ያረፈበት መንገድና በበዓለ ሃምሳ በደቀመዛሙርቱ ላይ የወረደበት መንገድ መለያየቱም አንድ ነገር ይጠቁመናል። በኢየሱስ ላይ መንፈስ ቅዱስ የየዋህነትና የንጽህና ምሳሌ በሆነችው እርግብ ተመስሎ አረፈበት በደቀመዛሙርት ላይ ግን ያው መንፈስ በሚያነዛና በሚያጠራ እሳት ተመስሎ ወረደባቸው።[47] ይህም የኢየሱስን የልብ ሁኔታ የሚያረጋግጥልን ሌላ ማስረጃ ነው።

እስራኤላውያን ከሮም አገዛዝ ነፃ የሚያወጣቸው መናገሻውን ኢየሩሳሌም አድርጎ ዓለምን እንደሚገዛ ተስፋ የሚያደርጉት መሢህ ሲመጣ ሠራዊቱን አስከትሎ በነጭ ፈረስ በምሥራቁ በር ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚገባ የነቢያትን መጽሐፍት መሠረት አድርገው በታላቅ ጉጉት ይጠብቁ ነበር።

ምንም እንኳ ለብዙ ዘመናት አስራኤልን ድል ነስተው ሲገዟት የመጡት ነገሥታትና የነገሥታት ልዑካን በፈረስ ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ ሲገቡ በቁጭት ሲመለከቱ ኖረዋል። ኢየሱስ አገልግሎቱን ከጀመረ በኋላ ግን መሢህ እንደሆነ ገምተው የተከተሉት አይሁዳዊያን አንድ ቀን በድል ሠራዊቱን አስከትሎ ወደ ከተማይቱ እንደሚገባና ንግሥናው እንደሚታወጅ እያሰቡ ያንን ቀን በናፍቆት ይጠብቁ ነበር። ታዲያ ይህ ይሆናል ብለው በገመቱበት በፋሲካ ወቅት በብዙ አጀብ ወደ ከተማይቱ እየመጣ እንደሆነ ሰምተው ዘንባባ ይዘውና ጨርቅ አንጥፈው ሲጠብቁት የመጣው በፈረስ ሳይሆን በአህያ ተቀምጦ ነበር። ለምን? በነቢዩ በዘካርያስ፦

> «ለጽዮን ልጅ፦ እነሆ ንጉሥሽ የዋህ ሆኖ በአህያ ላይና በአይሀያይቱ ግልገል በወርንጫይቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል በሉአት ተብሎ በነቢዩ የተነገረው ይፈፀም ዘንድ . . .።» ማቴ 21:4-5

አምን ጌታ ኢየሱስ ወደፊት ለመንገሥ ዳግመኛ ሲመጣ በታላቅ ኃይል ወደ አየሩሳሌም ይገባል። አሁን ግን ለመንገሥ ሣይሆን ለማዳን ራሱንም ስለ ኃጢአት መስዋዕት ለማድረግ በኃጠአተኞች እጅ መከራን ለመቀበል ስለመጣ ሰለ ሰው ልጆች በውርደት ውስጥ ለማለፍ ፈቃደኛ የሆነ ትሁት፣ የዋህ ልብ እንዳለው ለማሳየት በአህያ እና በውርንጭላይቱ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ ገብቷል። በዚያን ዘመን ነገሥታት ከቦታ ቦታ የሚዘዋወሩት በፈረሶች በሚጎተት ሠረገላ ሲሆን የተቀለቡ ፈረሶቻቸውና የተሸለሙ ሠረገሎቻቸው ከመንጎራዝነታቸው ባሻገር የነገሥታቱን የልብ ትዕቢትና የሥጋ ትምክህት ስለሚያሳዩ ጌታ ደግሞ በተቃራኒው ታላቅና ዘላለማዊ ንጉሥ ቢሆንም የልቡን ትህትናውን ለማሣየት በአህያ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም እንደገባ እናያለን።

ትህትና የልብ ሁኔታ፣ የውስጥ ጠባይ፣ የነፍስ ዝንባሌ፣ የአእምሮ አስተያየት ወይም አመለካከት እንጂ ውጪያው መሽቆጥቆጥ አይደለም። ጌታ ኢየሱስ በአህያ ተቀምጦ ኢየሩሳሌም ሲገባ ብቻ ሳይሆን ከደረሰም በኋላ ወደ መቅደስ ገብቶ የሚሸጡትንና የሚለውጡትን ሲያወጣ፣ የገንዘብ ለዋጮችን ገበታዎች፣ የርግብ ሻጮችን ወንበሮች ሲገለብጥም ፍፁም ትሁትና የዋህ ነበረ።

ትህትና ለእግዚአብሔር፣ ለራሳችንና ለሰዎች የሚኖረን ትክክለኛ እሣቤ እና ተግባር እንጂ ውጪያዊ መቅለስለስ ስላልሆነ በልብ ሁናቴ እንጂ በመልክ ሊጻኝ አይችልም።

ሰው ያጣ የነጣ ድሃ ሆኖ፣ የበታች ሆኖ፣ በሰው እጅ ወድቆ ትሁት ቢመስል አያስደንቅም። በውጭ የሚታየው ትህትና መሰል እንቅስቃሴ ልባዊ መሆኑን የሚፈተነው ያጣው

ባለጠጋ፣ የበታቹ የበላይ፣ መጎይሙ ባለብዙ ዲግሪ ሆኖ ሲታይ ነው። ሰው ከፍ ሲል በዝቅታ የነበረው ትህትናም አብሮት ከፍ ካለ እውነተኛ የልብ ትህትና እንደሆነ መረዳት አያስቸግርም። ትናንት በዝቅተኛ ሥፍራ ሆነው ሲሸቆጠቆጡ ትሁት ይመስሉን የነበሩ ሰዎች ዛሬ አጋጣሚ ተፈጥሮ ከፍ ሲሉ ውጪያዊ ትህትናቸውን እንደቱታ አወልቀው ትዕቢትን የሚጎናፀፉ ስንቶች ይሆኑ?

ጌታ ኢየሱስ ግን በበረት ሲወለድ፣ በናዝሬት ሲያድግ፣ በኢየሩሣሌም ሲያገለግል፣ በቀራንዮ ሲሰቀል የነበረው ትህትና ወደ ሰማያት ከፍ ከፍ ብሎ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ሲቀመጥ አብሮት አረገ እንጂ በምድር አልቀረም። ትህትና የልብ ሁኔታ ቢሆንም እንኳ በውጭ የሚንፀባረቅባቸው መንገዶች አሉት። ከእነዚያም ውስጥ ዋናዎቹን በሁለት ከፍለን ልናያቸው እንችላለን።

አነርሱም ለእግዚአብሔር እና ለሰዎች የምንሰጣው ምላሾች ናቸው። ትህትናችን ወደ እግዚአብሔር አቅጣጫ የሚገለጥበት መንገድ ለእግዚአብሔር ቃል በምንሰጠው ምላሽ ነው። እግዚአብሔር በነቢዩ አፍ፡ -

> *«እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ሰማይ ዙፋኔ ነው ምድርም የእግሬ መረገጫ ናት የምትሰሩልኝ ቤት ምን ዓይነት ነው? የማርፍበትስ ሥፍራ ምንድነው? እነዚህን ሁሉ እጄ ሰርታለችና እነዚህ ሁሉ የእኔ ናቸው ይላል እግዚአብሔር፤ ነገር ግን ወደዚህ ወደ ትሁት መንፈሱም ወደ ተሰብረ በቃሌም ወደሚንቀጠቀጥ ሰው አመለከታለሁ።» ኢሣ. 66:1-2*

ሲል ወደ እግዚአብሔር አቅጣጫ የሚገለጥ እውነተኛ ትህትና ለእግዚአብሔር ቃል ባለን አክብሮት እንደሚፈተን ያስረዳናል።

ለዚህ እውነት ሌላ ምሳሌ የሚሆነን የይሁዳ ንጉሥ እዮስያስ ነው። እዮስያስ ወደ መንግሥት በመጣ ጊዜ ከእርሱ በፊት

የነበሩት አባቶቹ ምናሴና አሞጽ በሠሩት ክፋት ተዘግቶ የነበረውን የእግዚአብሔርን ቤት እንዲከፈት ትዕዛዝ ሰጠ። በተከፈተም ጊዜ ካህኑ ኪልቅያስ ለረጅም ዘመን ከሕዝቡ ተሰውሮ የኖረውን የሕጉን መጽሐፍ አገኘና በንጉሱ ፀሐፊ አጅ ወደ እዮስያስ ላከለት። እዮስያስም በመንግሥቱ ዙፋኑ ተቀምጦ ሕጉ ሲነበብለት ያኔ ለእግዚአብሔር ያለው የልቡ ትህትና ተገለጠ።

> *«ፀሐፊውም ሳይን ለንጉሡ ካህኑ ኬልቅያስ መጽሐፍ ሰጥቶናል ብሎ ነገረው። ሳይንም በንጉሡ ፊት አነበበው። ንጉሡም የሕጉን መጽሐፍ ቃል በሰማ ጊዜ ልብሱን ቀደደ . . .»*

ንጉሡ ለእግዚአብሔር ቃል ልቡ በትሕትና ሲዋረድ እግዚአብሔር ዝም ብሎ አላየም ነብይ ላከና እንዲህ አለው ፦

> *«እግዚአብሔርን ለመጠየቅ ለላካችሁ ለይሁዳ ንጉሥ ግን እንዲህ በሉት፦ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ስለሰማኸው ቃል ልብህ ገር ሆኖልና እነርሱም ለድንቅና ለመገረም እንዲሆኑ በዚህ ስፍራና በሚኖሩበት ላይ የተናገርኩትን ሰምተህ በእግዚአብሔር ፊት ተዋርደሃልና ልብስህን ቀደህልና በፊቴም አልቅሰሃልና እኔ ደግሞ ሰምቼሃለሁ ይላል እግዚአብሔር . . .»* *2ነገ. 22:11-13-18=19*

ለእግዚአብሔርና ለቃሉ ያለን የልብ ሁኔታ አብረናቸው ከምንኖራቸው ሰዎች ጋር በሚኖረን ግንኙነትም ይገለጣል።

ልጆች ለወላጆቻቸው፣ ሚስት ለባሏ፣ ምዕመናን ለቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች፣ ሕዝብ ለመንግሥት ለመገዛት ከሁሉ በላይ ትህትናን ይጠይቃል። ለሥልጣን የሚገዛ ሰው የሚገዛው ለባለሥልጣኑ ሳይሆን የሥልጣን ሁሉ ምንጭና ባለቤት ለሆነው ለእግዚአብሔር ነው። ሊቃወምም የሚቃወመው ግለሰቦቹን ሳይሆን እግዚአብሔርን ነው። ለዚህ ነው ሐዋርያው ጴጥሮስ ሽማግሌዎች ለመንጋው ምሳሌ እንዲሁኑ እንጂ በኃይል እንዳይገዙ፣ ጎልማሶች ደግሞ ለሽማግሌዎች እንዲገዙ በፃፈበት ክፍል፡ -

«ሁላችሁም እርስ በርሳችሁ እየተዋረዳችሁ ትህትናን እንደ ልብስ ታጠቁ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማልና ለትሁታን ግን ፀጋን ይሰጣል።» ያለው።

እንግዲህ እግዚአብሔር በሥጋ ተገልጦ በክርስቶስ ኢየሱስ ፊት ላይ ስናየው ትሁት መሆኑን፣ እኔነት አልባ መሆኑን፣ የተዋረዱትን የማይንቅ መሆኑን፣ እስከመጨረሻ ዝቅ ለማለት ፈቃደኛ መሆኑን ተመልክተናል። እንግዲህ እኛም ይህን ሕይወት ተካፍለናል የምንል ሁሉ በትዕቢት የተሞላውን የሥጋ ባሕሪ ገፈን እየጣልን በውስጣችን ያለውን የትህትና ባሕሪ ለመግለጥ መንፈስ ቅዱስ በሚመራንና በሚያሳልፈን መንገድ በትህትና ራሳችንን እናሰልጥን።

ቸርነት ልግሥና

«... የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ቸር ስጦታ አውቃችኋልና ሀብታም ሲሆን እናንተ በእርሱ ድህነት ባለጠጎች ትሆኑ ዘንድ ስለ እናንተ ድሃ ሆነ።» 2ቆሮ. 8:9

መስጠት የእግዚአብሔር ሕይወት ሕግና ባሕሪ ነው። እግዚአብሔር በመስጠት ደስ ይለዋል። የሰውን ልጆች ከዘላለማዊ ጥፋት ለማዳን ጽድቁ የጠየቀው ዋጋ ሊታሰብ የማይቻል ውድ መሥዋዕት ነበር። ዓለማትን የፈጠረበትን ሁሉን ወራሽ ያደረገውን አንድ ልጁን አሣልፎ መሥጠት። እግዚአብሔር ግን አልሰሰተም፣ ለገዛ ልጁም አልራራም በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ አለምን እንዲሁ ወደደ። የጌታ ኢየሱስ የምድር ኑሮ ያረጋገጠው ይህንኑ ነበር። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሰው ልጆች መዳን ዙፋኑን እና ክብሩን መተው ብቻ ሣይሆን ውርደት በሞላበት በመስቀል ሞት ነፍሱን ለመሥጠት ፈቃደኛ ሆነ። በዚህም መስጠት የእግዚአብሔር ሕይወት ባሕሪ መሆኑን አረጋግጧልናል።

በመግቢያችን ላይ ያነበብነውን ጥቅስ በትኩረት ብንመለከት ራሳችንን ልናስለምድ የሚገባንን የክርስቶስን የቸርነትና የልግሥና ባሕሪ በጉልህ ማየት እንችላለን። ይህ ጥቅስ ጥቂት የማይባሉ የብልጽግና ሰባኪዎች ለራሳቸው በሚመች ሁኔታ ከአውዱ ነጥለው ስለተረጎሙት የትርጉም ለሰባ ከሆኑት የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አንዱ ሆኖአል።

ሰባኪዎቹ «ክርስቶስ ስለ እናንተ ድሃ ሆኖአልና ሃብታም ሁኑ።» ለማለት ቢጠቀሙበትም ሐዋርያው ግን ሲል የወደደው «በኢየሩሣሌም ቅዱሳን መካከል በርካታ ድሆች አሉ። ይህም ድህነት በሥራ ፈትነትና በሥንፍና የመጣ ሣይሆን በጊዜው በተከሰተው ድርቅና በሥፍራው ካለው መልከዓ ምዳራዊ ገጽታ እንዲሁም በወቅቱ ከነበረው ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ የተነሳ ነው። የእናንተ ሁኔታ ደግሞ ከእነርሱ የተሻለ ነው። ስለዚህ ካላችሁ በማካፈል ጥቂት ዝቅ ለማለት ፈቃደኞች ሆኑ ወይም በኢየሩሣሌም ስላሉት አይሁዳዊያን ወንድሞቻችሁ ስትሉ አንዳራዊ ድሆች ለመሆን ፍቀዱ። አንዳንድ ትርፍ ነገሮቻችሁን መሥዋዕት አድርጉና ወንኖቻችሁን እርዱ።» እያለ ነው። ለዚህም የጠቀሰላቸው ምሳሌ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ነው። «እርሱ ሃብታም ሲሆን እናንተ በእርሱ ድህነት ባለጠጎች ትሆኑ ዘንድ ስለ እናንተ ድሃ ሆኖአልና» እናንተም እርሱን በመምሠል በኢየሩሳሌም ስላሉት ያሙ የነጡ ቅዱሳን አንዳራዊ ድሃ ለመሆን ፍቀዱ» እያላቸው ነው።

እውነተኛ መስጠት ስለመስጠት ሲሰበክ በስሜት ተነስተን የምንሰጠው ወይም በመስጠት ስለምናገኘው እጥፍ ድርብ ሃብት በምኞት ተወጥረን የምናደረግው ሳይሆን መስጠት የእግዚአብሔር ሕይወት ባሕሪ መሆኑን ተረድተን እኛም

ይህንን የሕይወት ዘይቤአችን በማድረግ ክርስቶስን ለመምሰል ካለን ልባዊ መሻት በመነሳት የምናደርገው ሲሆን ነው።

ሰዎች የዚህ ዓለም ገንዘብ እያላቸው ለሌላቸው ለማካፈል የሚችገሩት ለምን እንደሆነ ያውቃሉ? «ያለኝ ይበቃኛል» ማለት ስለማይችሉ ነው። ያለኝ ይበቃኛል ማለት በሂሳብ ስሌት የሚገኝ ቀመር ሳይሆን እግዚአብሔርን የመምሰል ውጤት ነውና።

ከራሳቸው አልፎ ለትውልድ የሚበቃ ሃብት አምቀው ዛሬም በላይ በላይ ለመጨመር የሚንሰፈሰፉና ላሰሯቸው ሠራተኞች እንኳ የሚገባቸውን ለመክፈል የሚንቆጠቆጡ ሰዎች ምንም ያህል ሃብት ቢጨመርላቸው የተጠናወታቸው የስስት አባዜ እስካለቀቃቸው ድረስ «ኑሮዬ ይበቃኛል» ሊሉ አይችሉም።

> *«ኑሮዬ ይበቃኛል ለሚለው ግን አግዚአብሔርን መምሰል እጅግ ማትረፊያ ነው።»*

አንዳንዶች እንደሚያስቡት ኑሮዬ ይበቃኛል ማለት ትርፋማነትን ከስመከላከልና ገቢን ከመገደብ ጋር አንዳች ግንኙነት የለውም። የስንፍና መደበቂያ ዋሻም አይደለም። ነገር ግን የምንሠራውና የምናገኘው ራሳችንን ባለጠጋ ለማድረግ ብቻ ሳይሆን ለእኛ የሚያስፈልገንን ካገኘን በኋላ የሚያስፈልጋቸው ለሌላቸው ለመትረፍ እንድንችል መሆን አለበትና በዚህ መንፈስ አስከተንቀሳቀስን ድረስ የፈለግውን ያህል ብናገኝ አንዳች ችግር የለውም። ቃሉም «ኑሮዬ ይበቃኛል» እንጂ «ኑሮአችው ይበቃቸዋል» አይልም።

በአንድ ሰው ውስጥ የሚገለጠው የሥጋ ባሕሪ ይሁን የእግዚአብሔር ባሕሪ ለመለየት ቀላሉ መንገድ የቸርነትና

የልግሥና ልምምዱን ባጠቃላይ ስለ ገንዘብ ያለውን አመለካከት መቃኘት በቂ ነው።

> *«ነገር ግን የዚህ አለም ገንዘብ ያለው ወንድሙም የሚያስፈልገውን ሲያጣ አይቶ ያልራራለት ማንም ቢሆን የእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ እንዴት ይኖራል?» 1ዮሐ. 3:17*
>
> *«ወንድም ወይም እህት ራቁታቸውን ቢሆኑ የእለት ምግብንም ቢያጡ ከእናንተ አንዱም፦ በደህና ሂዱ እሣት ሙቁ ጥገቡም ቢላቸው ለሰውነት ግን የሚያስፈልጉትን ባትሰጡአቸው ምን ይጠቅማቸዋል? እንደዚሁም ሥራ የሌለው እምነት ቢኖር በራሱ የሞተ ነው።» ያዕ. 2:16*

ምንም እንኳን ይህን ቸርነትና ልግሥና ለሰው ሁሉ ማድረግ ቢኖርብንም በተለይ አንዱን መንፈስ አብረናቸው ለጠጣን የእምነት ቤተሰቦች ይህን አለማድረግ ምን ያህል ክርስቶስ እንዳልተገለጠልንና እንዳላወቅነው የሚያሳይ የሕይወት መስታወት ነው።

ክርስቶስን ማወቅ ማለት ስለ አወላለዱ፣ አስተዳደጉ፣ አሟሟቱና ትንሣኤው ታሪካዊና ሥነ-መለኮታዊ ትንታኔ መስጠት ብቻ ሳይሆን ክርስቶስን በአካሉ በቤተክርስቲያን ውስጥ የአካሉ ብልቶች በሆኑት በእያንዳንዱ አማኞች ውስጥ ማወቅና የሚገባውን ማድረግ መቻል ነው። እምን ለዘላለም ተሰውሮ የነበረውና አሁን የተገለጠው ሚስጥር የክብር ተስፋ ያለው ክርስቶስ በቅዱሳኑ ውስጥ መሆኑ ነው።[48] ስለዚህ ለክርስቶስ ያለንን ተግባራዊ ፍቅር የምንገልጠው አየር ላይ ሳይሆን በአማኞች ላይ መሆኑን አንርሳ። ለአንድ አማኝ ያደረግነው ለክርስቶስ እንዳደረግነው ይቆጠራል። ለዚህ ነው ጌታ በመጨረሻው ቀን «ተርቤ አብልታችሁኛልና፣ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና . . . ታርዤ አልብሳችሁኛልና ...።» ወይም «ተርቤ አላበላችሁኝምና ተጠምቼ አላጠጣችሁኝምና ... ታርዤ አላለበሳችሁምና . . . » የሚለን። ምክንያቱንም ሲያስረዳ «እውነት እላችኋለሁ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞች

ለአንዱ ስንኳ ስላደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት::» ወይም «እውነት እላችኋለሁ ከሁሉ ከሚያንሱት ከእነዚህ ለአንዱ ስላላደረጋችሁት ለእኔም ደግሞ አላደረጋችሁትም» ብሎአል ማቴ. 31-46::

ለዚህም መፍትሔው አንድ ነው:: በውስጣችን ያለውን የእግዚአብሔር ሕይወት መሠረት በማድረግ በቸርነት እና በልግሥና ክርስቶስን ለመምሰል ራሳችንን ማስለመድ ነው:: ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ስለ ባለጠጎች የፃፈለት ምክር አዘል ትዕዛዝ አሳባችንን ደህና አድርጎ ይቋጭልናል::

«ለውነተኛውን ሕይወት ይይዙ ዘንድ ለሚመጣው ዘመን ለራሳቸው መልካም መሠረት የሚሆንላቸውን መዝገብ እየሰበሰቡ መልካምን እንዲያደርጉ በበጎ ሥራ ባለጠጎች እንዲሆኑ ሊረዱና ሊያካፍሉም የተዘጋጁ እንዲሆኑ ምከራቸው::» 1ጢሞ. 6:18-19

ትዕግሥት

ትዕግሥት እግዚአብሔር በሰዎች ውስጥ ተገልጠው ሊያያቸው ከሚፈልጋቸው ባሕሪያት መካከል አንዱ ነው:: ይህ ባሕሪ በእለት ተእለት ኑሮአችን ሰዎችን መታገስ ብቻ ሣይሆን ስለ ጽድቅ መከራን መታገስ እንዲሁም እግዚአብሔር ክርስቶስን እንድንመስል ሲሠራን እጁን መታገስን ያጠቃልላል::

እግዚአብሔርን መምሰል በዚህ ምድር ሹመትና ሽልማት አያስገኝም:: ይልቅ የመከራና የስደት መስህብ ነው::

ሐዋርያው ለእምነት ልጁ አብሮትም ሠራተኛ ለሆነው ለጢሞቴዎስ ሲጽፍለት:

«ለእውነት በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ::» 2ጢሞ. 3:12

አለው እንጂ ስሙጥር እና ዝነኛ ይሆናሉ አላለውም:: ዓለምና ገዥዋ መቼም ቢሆን መስማት የማይፈልጉት ስም፣ ማየት የማይፈልጉት መልክና ማሽተት የማይፈልጉት መዓዛ ቢኖር ክርስቶስ ኢየሱስ ብቻ ነው:: ስለዚህ ይህን መልክ የሚመስል፣ ይህን መዓዛ የሚያውድና ይህ ባሕሪ የሚገለጥበት ሰው የዚህ ዓለም ገዥ ከሚገዛቸው ሰዎች ጋር ይነሳበታል ፣ይቃወመዋል ፣ያሳድደዋል:: የክርስቶስ መዓዛ ለሚድኑት የሕይወት ሽታ ቢሆንም ለሚጠፉት የሞት ሽታ ነው:: በሞት ሽታ የሚደሰት ማንም የለምና ይህን መዓዛ ተሸክመው በሚሄሩ ላይ ስደቱ ይፀናል መከራውም ይበረታል:: እንጂ በፍፁም አልጋ በአልጋ አይሆንም::

ይህ ደግሞ እግዚአብሔርን በመምሰል ሂደት ውስጥ ትእግሥትን እጅግ ውድና ተፈላጊ ባሕሪ ያደርገዋል::

«ወንድሞቼ ሆይ ልዩ ልዩ መከራ ሲደረስባቸው እንዳ ሙሉ ደስታ ቁጠሩት ምክንያቱም የእምነታቸው መፈተን ትዕግሥትን እንደሚያስገኝ ታውቃላችሁ:: ምንም የማይጎድላችሁ ፍፁማንና ምሉዓን እንድትሆኑ ትዕግሥት ሥራውን ይፈፅም::» ያዕ. 1:2-4 (ኢ.መ.ት)

ትዕግሥት እግዚአብሔርን የመምሰል ባሕሪ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርን ወደ መምሰል የሚያደርስ መንገድ ነው:: ክርስቶስን እንመስል ዘንድ እግዚአብሔር በሕይወታችን የጀመረው መልካም ሥራ ሊጠናቀቅ የሚችለው ትዕግሥት ሲኖረን ብቻ ነው:: ይህም ትዕግሥት በሕይወታችን የምትሠራውን የእግዚአብሔርን እጅ ሥራዋን አስከትጨርስ ድረስ የምንታገሥበት ባሕሪ ነው::

ታዲያ ይህ ባሕሪ እንዲሁ ከሰማይ የሚወርድ ሳይሆን በምናልፍባቸው ትግስት ፈታኝ አልህ አስጨራሽ ጎዳናዎች የምንሸምተው ስንቅ ነው:: ይህንንም መንገድ

ከተለማመድነውና ትኩረታችን ሂደቱ ላይ ሳይሆን ውጤት ላይ ካተኮረ ደስታችን ሙሉ ይሆናል። ይህንኑ አሳብ ጳውሎስ በሮሜ መልዕክቱ ላይ ሲያንፀባርቅ እንዲህ ብሏል፦

> «. . . የእግዚአብሔርንም ክብር ተስፋ በማድረግ ሐሴት እናደርጋለን። በዚህ ብቻ ሳይሆን በመከራችንም ሐሴት እናደርጋለን ምክንያቱም መከራ ትዕግሥትን እንደሚያስገኝ እናውቃለን ትዕግሥትም ጽናትን ጽናት የተፈተነ ባሕሪይን የተፈተነ ባሕሪ ተስፋን ይህን ተስፋ ለእፍረት አይዳርገንም ...» ሮሜ 5:2-5 (አ.መ.ት)

ማንም ሰው መከራን አይወድም። መከራን መሸሽም የሥጋችን እውቅ ባሕሪ ነው። ሥጋችን ስጊዜው የሚፈለገውን ካገኘና ደስ ከተሰኘ ስለ ዘላለማዊ ደስታና ክብር ቁብ የለውም። ወትሮም ዘላለማዊነት በውስጡ ስለሌለና በሞት የሚያከትም ምድራዊ ሕይወት ስለሆነ ስለዘላለም ቅንጣት አይገደውም። በሥጋ ሕይወት ቁጥጥር ሥር ያሉ ክርስቲያኖችም ከዚህ የተነሳ መከራን ይሸሻሉ። ከመከራ ነፃ ለመውጣት የማይፈነቅሉት ድንጋይ አይኖርም። እንዲያውም ስለ መከራና ፈተና ፣ስለ መታገስ የተፃፉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ወጥተው ምድርን ገነት ማድረግ የሚችሉበትን ጥቅሶች ቢተኩ ደስታውን አይችሉትም።

በሥጋዊ ሕይወት ቁጥጥር ሥር ያለን አማኝ በቀላሉ የምንለየው በመከራ ውስጥ ሲያልፍ እንደበቱ ይሾላል፣ ቃሉቹ መራራ ይሆናሉ፣ በመናገር ብዛት መከራው የሚቀልለት ይመስል የባጥ የቆጡን ይናገራል። የሚያልፍበትን መከራ ከሕይወቱ መሠራትና ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር ከማገናኘት ይልቅ ለመከራው ምክንያት ናቸው ብሎ በሚያስባቸው ሰዎችና ሁኔታ ጋር በመዛመድ በቁጣ ይነሳል። የትዕግሥት ምሳሌያችን የሆነው ጌታ ኢየሱስ ግን በዚያ ጽኑ መከራ ውስጥ ሲያልፍ

የነበረውን ሁኔታ የአይን ምስክሩ ጴጥሮስ ለተምሕርታችን ይሆን ዘንድ እንዲህ ዘግቦታል፦

> «የተጠራችሁትም ለዚሁ ነው ምክንያቱም ክርስቶስ ስለ እናንተ መከራን የተቀበለው የእርሱን ፈለግ እንድትከተሉ ምሳሌን ሊተውላችሁ ነው። እርሱ ኃጢአት አላደረገም። በአፉም ተንኮል አልተገኘበትም። ሲሰደብ መልሶ አልተሳደበም መከራ ሲደርስበት አልዛተም ነገር ግን በጽድቅ ሰሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ።» 1ጴጥ. 2:21-23 (አ.መ.ት)

ጥፋተኛና በደለኛ ሰው መከራ ቢቀበል አግባብ እንደሆነ ማንም ሰው ይስማማል ነገር ግን ያለምንም ኃጢአትና በደል መከራን መቀበል ለብዙዎች ሊዋጥ የማይችል ጉዳይ ነው። ጌታ ኢየሱስ ግን ያስተማረን ክፉ ሠርተን ቅጣትን መታገስ ሳይሆን መልካም ሥራ ሠርተን መከራ መቀበልን እና መታገሥን ነው። ምክንያቱም ይህ ዓይነቱ ትዕግሥት በእግዚአብሔር ዘንድ ምሥጋና ያስገኝልናል።

የኢዮብ አጽናኞች የሳቱበት ፍልስፍና የዚህ እውነት ተቃራኒ ነው። «ሰው በደል ሳይፈጽም መከራን ይታገሥ ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም። ስለዚህ ይህ መከራ እንዲሁ አልመጣብህም የሰወርከው ኃጢአት አለና ተናዘዝ።» እያሉ ሲነዘንዙትና ሲያታክቱት እንደነበረ እናነባለን። ይህ ንዘንዛቸው ኢዮብን ሳይወድ ጽድቁን እንዲቆጥር ስለ ጽድቁም ከእግዚአብሔር ጋር እንዲሟገት አድርጎታል። በእርግጥ በፍፃሜው ኢዮብም ጽድቁን ስለመቁጠሩ ንስሐ ሲገባ፣ጓደኞቹም ስለ ተናገሩት ስንፍና ሲገሰፁና በኢዮብ ምልጃ ምሕረትን ሲያገኙ እንመለከታለን።[ሙ]

በውስጣችን ያለው የክርስቶስ ሕይወት ከሆነ የክርስቶስ ትዕግሥት በውስጣችን ታምቋል ማለት ነው። ስለዚህ እንግለጠው። የሥጋን ሕይወት ባሕሪ እያስወገድን

እግዚአብሔርን ለመምሰል ራሳችንን እናስለምድ። ሆኖም ይህ ጉዳይ በቅጽበት እንዲከናወን ውጤቱም ወዲያው እንዲከሰት አንጠብቅ። መንገዱ ጊዜ የሚፈጅ ፣ዋጋ የሚያስከፍልና ጽናትን የሚጠይቅ ነውና ዋጋችንን ተምነን እንጓዝ።

ስለ ልምምድ ሲነሳ አንድ ገጠመኝ ትዝ አለኝ። ከጥቂት አመታት በፊት እኔና ባለቤቴ «ጎልደን ጂም» በሚባል ትልቅ የአካል ብቃት ማዕከል ውስጥ ኤሮቢክስ (የአካል እንቅስቃሴ ስፖርት) እንሠራ ነበር። አሠሪያችን አካሏ በጡንቻ የዳበረና የማይደክማት እንደልቧ ጎንበስ ቀና የምትል ወጣት ነበረች። አንድ ቀን አንድ ያለልክ ወፍራም የሆኑ በሃምሳዎቹ መጨረሻ አካባቢ የሚገኙ ሰው እንቅስቃሴውን ለመሥራት ወደ ማዕከሉ መጡና በማለዳ ከእኛ ጋር ተቀላቀሉ። ገና ሳያቸው ከውፍረታቸው ማስፈራት የተነሣ በሃኪም ማስጠንቀቂያና በወዳጅ ዘመድ ምክር ወደ ስፖርት ዓለም እንደመጡ ገመትኩ። ሰውየው ውፍረታቸው ቢያግዳቸውም እንደምንም የአሠሪዋን መመሪያ በመከተል ሲሰሩ ቆዩ። ከ45 ደቂቃ በኋላ ኘሮግራሙ አልቆ ተበተንን። ዕለቱ የሥራ ቀን ማለዳ ስለነበር ሰው ሁሉ ለመተጣጠብና ሥራ ለመግባት ወደ የመታጠቢያ ክፍሉ ሲያመራ እኚህ ሰው ግን ከሰው የተለየ አቅጣጫ ይዘው ሄዱ። ድርጊታቸው ቀልቤን ስለሳበው ቆሜ መመልከት ጀመርኩ። ሰውየው ያመሩት ወደ ክብደት መለኪያ ሚዛን ነበር። ሚዛኑ ላይ ከቆሙ በኋላ የመለኪያውን ዘንግ በትኩረት ይመለከቱ ጀመር። እግዚአብሔር ያሳያቸሁ የመጡት ገና ዛሬ ነው፤ የተንቀሳቀሱት ለ45 ደቂቃ ነው ፣ታዲያ እንዴት ነው ለ30 እና ለ40 ዓመታት የተገነባ ስብ በ45 ደቂቃ ፈርሶ ክብደት የሚቀንሰው? የሚያሳዝነው እኚህ ሰው ከዚያ ቀን በኋላ ወደ ማዕከሉ አልተመለሱም። ከዚህ በኋላ ሰው የአካል እንቅስቃሴ

ለጤናቸው መፍትሔ እንደሆነ ቢነግራቸውም «አይ እሱንማ ምክሬዋለሁ አይሰራም!» ሊሉ እንደሚችሉ መገመት አያስቸግርም።

ከዚህ ምሣሌ የምንረዳው የእግዚአብሔርን ባሕሪ ለመላበስና ክርስቶስን ለመምሰል ስናልም በትዕግሥት እስከፍፃሜ መጓዝ ይኖርብናል እንጂ በአጭሩ ተስፋ ማድረግ፣ በቀላሉም ተስፋ መቁረጥ አይኖርብንም።

ንጽህና

«ወዳጆች ሆይ እኛ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን ወደፊት ምን እንደምንሆን ገና አልተገለጠም። እርሱ በሚገለጥበት ጊዜ እናየዋለንና እርሱን እንደምንመስል እናውቃለን። በእርሱ ይህን ተስፋ የሚያደርግ ሁሉ እርሱ ንፁህ እንደሆነ ራሱን ያንፃል።» *፲ዮሐ. 3:2-3*

ዘመናችን ከየትኛውም ዘመን ይልቅ አይንን በሚያጓድፍ ልብን በሚያሳድፍ ትዕይንቶች የተሞላ ነው። በተለይ ሥልጣኔው ባየለበት በምዕራቡ ዓለም «እንዴት በልብ ንጽህና መኖር ይቻላል?» የሚል ጥያቄ እስኪያስነሳ ድረስ ራቁትነቱ፣ ሴሰኝነቱ፣ ስሜታዊነቱ፣ ከመጠን በላይ ገኗል።

ሴሰኝነትና ሰርኩሰት የሚያዘጋጅ አስትምህሮ በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ሰርፆ ከመዋዕለ ህፃናት እንስቶ እስከ ትላልቅ ዩኒቨርሲቲዎች ድረስ አስቀድሞ ረቂቅ በሆነ ስልት እያደርም በገሃድ ይሰጣል።

ዘመናዊነት (ሞደርኒዝም) የሥልጣኔ ጉዳይ ከመሆን አልፎ የምዕራባዊያን ሃይማኖት ከሆነ ውሎ አድሯል። ይህ በርካታ ሰይጣናዊ አመለካከቶችን በውስጡ ያዘለ መርዘኛ ሃይማኖት የቅድስናን ምሰሶዎች በመናድና የንጽህናን አውታሮች ከሰው

ሕይወት በመበጣጠስና እግዚአብሔር የመሠረተውን የቤተሰብን ሕይወት በማቃለል ልቅነትን እያራገበ ይገኛል ፍሬውም የአደባባይ ሚስጥር ሆኖአል።

«ከለማበት የተጋባበት» እንዲሉ በአሜሪካና በአውሮፓ የነፈሰው ሁሉ ሳይውል ሳያድር እኛም አገር መድረሱ አይቀርምና ያለ እውቀት ሲባባስና ትውልድን ሲመርዝ ማየት የተለመደ ሆኖአል። ሰለጠኑ በተባሉት አገራት ለሥራ ወይም ለጉብኝት ሄደው ያረፉበትን ሆቴል ወይም የተቀበሉትን ሰው ቤት ቴሌቪዥን ከመክፈቶ በፊት ደጋግሞ ማሰብ ይጠይቃል። ገና ፀሐይ ስትጠልቅ ሕፃናት ወደ መኝታ ሳይሄዱ በቴሌቪዥን የሚተላለፈው ሴሰኝነትና አመንዝራነት ልክ የለውም። ሰዓቱ እያሸቀለቀለ ሄዶ ከምሽቱ አራት ሰዓት ካለፈ በኋላ ግን ጨርሶ አለመክፈቱ ይመረጣል የርኩሰቱ ወላፈን ክፉኛ ይፋጃልና።

ምግብ በአፍ ወደሆድ እንደሚገባ ሁሉ ነገርም በዓይን በወደነፍስ ይወርዳል። ታዲያ እንዲህ ያለውን ርኩሰት ለጥቂት ደቂቃዎች እንኳ ታግሰው ከተመለከቱ ትናንት ምሽት በአይና የገባው ምስል በነጋታው በአይኖ ሲወጣ እስኪገረሙ ድረስ ራስዎን በርኩሰት ተመርዘው ያገኙታል። ይህ ደግሞ «ማነህ?» «ማነሽ?» ብሎ ሰው የሚመርጥ ሳይሆን ራሱን ሳይገዛ በትዕግሥት የተመለከተውን ልብ ሁሉ በርኩሰት የሚነድፍ የእባብ መርዝ ነው። ለዚህ ነው ብዙ የእግዚአብሔር ሰዎች ሳይቀሩ የወጥመዱ ሰለባ የሆኑት።

በቅርቡ «ሊደርሽኝ ሜጋዚን» የተባለ በአሜሪካ የሚታተም ክርስቲያናዊ መጽሔት አንድ ሺህ ፓስተሮች ላይ ጥናት አካሂዶ ነበር።

ከሺዎቹ ውስጥ መቶ ሃያዎቹ (12 እጁ) በአገልግሎት ላይ ሆነው ዝሙት መፈፀማቸውን ተናግረዋል።

በዚያው አገር የሚታተም «ክርስቲያኒቲ ቱዴይ» የተሰኘ ሌላ ታዋቂ መጽሔት ደግሞ የመጽሔቱ ደንበኞች በሆኑ አንድ ሺህ አማኞች ላይ ተመሳሳይ ጥናት አካሄዶ ሁለት መቶ ሠላሳ (23 እጁ) ከትዳር ጓደኞቻቸው ውጪ ዝሙት መፈፀማቸውን ሲገልፁ አራት መቶ ሃምሣዎቹ (45 እጁ) አግባብ የሌለው ወሲባዊ ዝንባሌና ልምምድ እንደነበራቸው አምነዋል። ይህ ሲጠቃለል የሚያሳየው ከአራት ክርስቲያኖች አንዱ ለትዳሩ ታማኝ አለመሆኑን እና በዝሙት ኃጢአት መውደቁን ነው። የሚገርመው ሁለተኛው ጥናት የተካሄደባቸው የዚህ መጽሔት ደንበኞች በብዛት ከኦሌጆች የተመረቁ መሪዎች እና የበላይ ተመልካቾች እንዲሁም የቤተክርቲያን አስተማሪዎች መሆናቸው ነው።

ይህ እንግዲህ የአሜሪካው ነው። የእኛ አገሩ ግን የነጮቹ ግልጽነት ሰለማይነካካው እግዜር ይወቀው ፣ቤት ይቁጠረው ብሎ ከማለፍ ውጪ የጽሑፍ ማስረጃ ለማቅረብ አይቻልም። አንድ ነገር ግን ከግምት ባሻገር እርግጠኛ መሆን ይቻላል። የውጭውን ትተን በቤተክርስቲያን ውስጥ የሴሰኝነት ፍም ውስጥ ለውስጥ እየጋመ ነው።

በተለይ በብዙ ወጣቶች ዘንድ ጥንቃቄዎችን መውሰድ እንደ አላዋቂነትና የቀድሞ ክርስቲያኖች ኋላ ቀር ልምምድ ተደርጎ ስለሚወሰድ ብዙዎች ለአደጋ እየተጋጡ ነው። ለዚህ ውድቀት ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርጉት ደግሞ ልቅነት የሞላባቸው ፊልሞችና በኢንተርኔት የሚተላለፉ ፕሮግራሞች ናቸው።

አንድ ታዋቂ ክርስቲያን ወይም አገልጋይ ፊልም ቤት ለመግባት በር ላይ ሰልፍ ይዞ ቢታይ (በእኛ አገር ሁኔታ) ብዙዎች እንደሚሰናከሉበት አያጠያይቅም። ነገር ግን ዛሬ ከእነዚያ የባሱ ፊልሞች በቪዲዮና በዲቪዲ ተዘጋጅተው ቤት ድረስ መጥተዋልና እግዚአብሔርን ካልፈራ በስተቀር ማንም የፈለገውን ቢያይ የሚታዘበው ሰው አይኖርም።

በምድር እስካለን ድረስ በውስጣችን የኃጢአት ባሪያ የሆነ የሥጋ ሕይወት አለ። ምንም እንኳ አሮጌው ሰጋችን ከክርስቶስ ጋር እንደሞተ ብናውጅም በሥጋችን ውስጥ የሚያድረው የኃጢአት ኃይል አልሞተምና እድል ካገኘ የማያንሰራራበትና ነፍስ የማይዘራበት ምንም ምክንያት አይኖርም። ሰዎች እንኳ እባብ ገድለው የትም አይጥሉትም። አፈር ልሶ ይነሳል ተብሎ ስለሚታመን ከአፈር አርቀው ከፍ አድርገው ይሰቅሉታል። እኛም እግዚአብሔርን በመምሰል ልምምድና በደቀመዝሙራዊ ራስን መግዛት ሥጋችንን በውስጣችን ከሚያድረው ኃጢአት ካልነጠልነው በስተቀር ኃጢአት ያይላል። እንደ ክፉ አውሬም ሊውጠን ይነሳል። ይህን አውሬ የሚቀሰቅሰው ምግብ ነው። በአይን የሚገባ የአምሮትና የምኞት ምግብ። ሳናስልስ ከመገብነው በኃይል ይበረታል። ከትናንቱ ዛሬ በርትቶአልና ትናንት የሰጠነው የምግብ መጠን አይበቃውም። ጨምሩ ይላል። እኛም የዚህን አውሬ አፒታይት (የምግብ ፍላጎት) ለመሙላት በፊልምም ሆነ በኢንተርኔት ርኩሰትን ማግበስበስ እንጀምራለን።የርኩሰትን ምኞት መመገብ እንጂ ማጥገብ ወይም ማርካት አይቻልምና በመገብነው መጠን አፒታይቱ ክፉኛ እየተከፈተ ይሄዳል። ይህ የጓዳ ቅሰባ በጓዳ ተሰውሮ አይቀርም በመንገድ ባለፍን ባገደምን ቁጥር የምናያቸውን ተቃራኒ ፆታዎች በርኩሰት ዓይን

መመልከት ይጀመራል፣ ቀስ እያለም በአጠገባችን የሚያልፉትን ሴቶች ቀሚስ በአይን መግለብ ይቀጥላል። ከዚያማ ምን ቅጡ። ውጪያችን በልብስ ተሸፍነን ሰው መስለን እንታይ እንጂ ውስጣችን በሃጢአት የተበከለ የጉድፍ ማጠራቀሚያ ይሆናል። ይህ ክፉ አውሬ የምንሰጠው አልበቃ ሲለው እኛኑ ለመዋጥ ይነሣል። በመጨረሻም ሕይወታችንን፣ ክብራችንን፣ ጤናችንን፣ ብሎም ዘላለማችንን ይውጣል።

ይህን አውሬ በሥጋ ምኞት አለመቀስቀስ መልካም ነው። አንዴ ከተቀሳቀሰ ግን ለመግደል ያለው መፍትሔው አንድ ብቻ ነው። ማስራብ! በአይን የማያግበሰብሰውን የርኩሰት ቀሰብ መንፈግ። (በርኩሰት ውጥመድ ተይዘው ብዙ ለገፉ ከዚህ ጣጣ መላቀቁ ቀላል ስለማይሆን የበሰለ ሰው ምክርና የፀሎት ድጋፍ ሊያስፈልጋቸዋል ይችል ይሆናል።) ሆኖም በየትኛውም ደረጃ ይህን አውሬ ለመግደል ከማስራብ ውጪ ሌላ አማራጭ የለም። ርኩሰትን ተርቦ በዚያ አስቀያሚ አፉ እያዛጋ ሆዱ በጠኔ ሲጮሀና ሲያስፈራራ መፍትሔው ጨክኖ «አምቢ!» ማለት ነው።

ዝሙት ወይም አመንዝራነት ከሴት ጋር መተኛት ብቻ እንደሆነ አድርጎ በማሰብ በዐይንና በሃሳብ ለርኩሰት ስፍራ መስጠት ትልቅ መታለል ነው። አይቶ መመኘት አብሮ ከመተኛት በምንም እንደማይተናነስ ጌታ ኢየሱስ ግልጽ አድርጎ አስቀምጦታልና።

> *«አታመንዝር እንደተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ አመንዝራል» ማቴ. 27:28*

ጌታም ለችግሩ ብቸኛ መፍትሔው በሥጋ ላይ መጨከን መሆኑን ሲያስረዳ ያለው ይህን ነበር ፡ -

«አይንህ ብታሰናክልህ አውጣት ሁለት አይን ኖሮህ ተሳቸው ወደማይሞት አሳቱም ወደማይጠፋበት ወደ ገሃነም እግት ከመጣል አንዲት አይን ኖራህ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት ይሻልሃል።» ማር. 9:47-48

ሰው በዚህ ኃጢአት ሲጠመድና ሲወድቅ ከራሱ ባሻገር የበደሉን ገፈት የሚጋቱት ሰዎች ቁጥር ጥቂት የሚባል አይደለም የትዳር ጓደኞችን፣ የሌላው የትዳር ጓደኛ፣ ልጆቻችን፣ ወላጆቻችን አብረውን የሚያመልኩ ቅዱሳን በየደረጃው የበደላችን ሰለባ ይሆናሉ ከሁሉ በላይ ደግሞ እግዚአብሔር ያዝናል። ታዲያ በነዚህ ሁሉ ላይ ከምንጨክን በጊዜ በሥጋ ሥሜታችን ላይ መጨከን አማራጭ እንደሌለው ይህ የጌታ አባባል ያስገነዝበናል።

የጥንቱ ኢዮብ እንኴን፡ - «ወደ ኮረዳይቱ ላለመመልከት ከአይኔ ጋር ቃል ኪዳን ገብቻለሁ» ኢዮብ 31:1 ብሎ የለ። እንዲህ ያለው ወደሌት በሴሰኝነት አይን መመልከት የሚያመጣውን ፍርድ ስለተገነዘበ ነበር። ይህንንም እንዲህ በማለት ገልፃታል : -

«ይህ አሳፋሪ ፍርድም የሚሻው ኃጢአት ነውና። ይህ የሚያቃጥልና የሚያጠፋ እግት ነው።» 11:12

እንግዲህ በዚህ ሴሰኝነት በነገሠበት ርኩሰት እንደ ውሃ በሚጠጣበት ዘመን እግዚአብሔርን ለመምሰል ራስን በልብ ንፅህና መኖርን ከማስለመድ ውጪ ምን አማራጭ አለ?

ጌታ ኢየሱስ በእርግጥ ይመለሳል፣ በክብርም ይገለጣል እኛም እናየዋለን። እርሱንም እንመስላለን። ነገር ግን በክብር እርሱን መምሰል እንዲሁ በዋዛ የሚገኝ ጉዳይ አይደለም። ነገ ሲገለጥ በክብር እርሱን ለመምሰል ዛሬ በባሕሪ እርሱን መምሰል የግድ ነው። ነገ ክብሩ በሰውነታችን የሚገለጥበት መጠን ዛሬ ባሕሪው በኑሮአችን በተገለጠበት ልክ ነውና።

እርሱን ከምንመስልባቸው ባሕሪያት አንዱ ደግሞ ንጽህና ነው። የልብ ንጽህና፣ የውስጥ ንጽህና። ልንጨነቅ የሚገባን በሰው ፊት ለሚኖረን ማንነት ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔር ፊት ላለን የልብ ሁኔታ መሆን ይኖርበታል። የልብ ንጽህና እጅ በመጫን የሚሰጥ ነፃ ሥጦታ ሳይሆን ባመንን ጊዜ በተሰጠን ሕይወት ላይ ቆመን በክርስቶስ ሞትን ትንሣኤ ላይ ተመስርተን ዕለት ዕለት ያለመታከት እግዚአብሔርን ለመምሰል በምናደርገው ስልጠና የሚገኝ ድል ነው። ነገ የምንካፈለውን ክብር ተስፋ እያደረግን ስጋችንን እያስገዛን እግዚአብሔርን ለመምሰል እየደከምን ቅዱስ ላብ እያላበን እንደርሱ ንፁህ ለመሆን እንትጋ። ለዚህ ነው፡ -

«በእርሱ ይህን ተስፋ የሚያደርግ ሁሉ እርሱ ንፁህ እንደሆነ ራሱን ያነፃል።» 1ዮሐ. 3:3

የተባለው።

እግዚአብሔርን መፍራት

«ከእሴይ ግንድ በትር ይወጣል ከሥሩም ቁጥቋጥ ያፈራል። . . . እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ ያርፍበታል። እግዚአብሔርን በመፍራት ደስታውን ያያል።» ኢሳ. 11:1-3

«አርሱም በሥጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን አቀረበ። እግዚአብሔርንም ስለመፍራቱ ተሰማለት ...።» ዕብ. 5:7

እግዚአብሔርን መፍራት እግዚአብሔርን የመምሰል ዋነኛ ባሕሪ ነው። የቀድሞው (የአማርኛ) መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በብዙ ሥፍራዎች «እግዚአብሔርን መምሰል» በማለት ሲተረጉመው የቆየውን «ዮሰቢያ» የተሰኘውን የግሪክ ቃል በአንድ ሥፍራ «እግዚአብሔርን መፍራት» በማለት መተካቱ በሁለቱ ጽንሰ ሃሳቦች መካከል ጽኑ ትስስር መኖሩን ያመላክታል።

በመግቢያችን ላይ የጠቀስናቸውን ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በጥሞና ካነበብን «ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ እግዚአብሔር ሆኖ እንዴት እግዚአብሔርን ሊፈራ ይችላል?» የሚል ጥያቄ ውስጣችን መጫሩ አይቀርም።

እግዚአብሔር ዓለም ሳይፈጠር በፊት ለሰው ልጆች ሕይወቱን (የዘላለም ሕይወት) ለማካፈል የተስፋ ቃል የሰጠበት ምክንያት የገዛ ሕይወቱን በሰው ልጆች ውስጥ ተገልጦ ማየት ስለፈለገ ነው።

የእግዚአብሔር ሕይወት በሰዎች ውስጥ ሲገለጥ የሕይወቱ ባለቤት የሆነውን ራሱን እግዚአብሔርን የሚያስደንቅና የሚያስገርም፣ የሚማርክና የሚመስጥ ልዩ ውበት ይዞ ይገለጣል። እግዚአብሔር ከሁሉ አስቀድሞ ይህ እንዲሆን የወሰነው ውበቱን በሰው ልጆች ላይ ለማየት ፈልጎ ነው። ስለዚህ ለእግዚአብሔር የገዛ ሕይወቱን በሰው ውስጥ ተገልጦ ከማየት የበለጠ የሚያስደስተው ነገር የለም።

የእግዚአብሔር ልጅ ፍፁም ሰው ሆኖ በምድር ላይ በተመማላለሰበት በሥጋው ወራት ጎልተው ከታዩት የሕይወት ባሕሪያት መካከል እግዚአብሔርን መፍራት አንዱ ነበር። እግዚአብሔርን መፍራት የሚለውን ሐሳብ ለመረዳት በቅድሚያ የቃሉን ፍቺ ማወቅ ይጠቅማል።

መቼም «መፍራት» የሚለው ቃል በቀጥታ የሚያስተላልፈው መልእክት «መስጋት» «መራድ» ወይም «መንቀጥቀጥ»ን ነው። ይህም የቃሉ አንድ ወገንና ጨለምተኛ ትርጓሜው ነው። ነገር ግን መፍራትን ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋለው «ዮሳቢያ» የተሰኘው የግሪክ ቃል ምንም እንኳ ከላይ የጠቀስነውን ዓይነት

ትርጉም ቢኖረውም በሉላ መልኩ «አክብሮታዊ ፍርሃትን» (Awe) ከእውነተኛ ኃይማኖት የመነጨ የተቀደሰ ፍርሃትን (Piety) እንዲሁም አክባሪነትን (Reverent) የሚገልጽ ትርጉም እንደሚያትት የቋንቋው ሊቃውንት ያስረዳሉ።[1]

እንዲያውም ውስትኩት የተሰኙት ሊቅ «ዮሳቢያ» የሚያመለክተው አንድ ሰው በሚያልፍበት ሁኔታ ውስጥ እያንዳንዱን ገጠመኞቹን ጥንቃቄና ማስተዋል ባሞላበት መንገድ በአክብሮት መመልከት መቻሉን የሚያሳይ መሆኑን ገልፀዋል።

ይህን አተረጓጎም «ኮይኔ» የተሰኘው የአዲስ ኪዳን ግሪክ ብቻ ሣይሆን በሰባዎቹ ሊቃውንት አማካይነት የብሉይ ኪዳን መፃሕፍት ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክ የተመለሱበት (ሴፕቱጀንት) ክላሲክ ግሪክም ይጋራዋል። ለዚህም በምሣሌ 28:14 ላይ

«ሁልጊዜ የሚፈራ ሰው ምስጉን ነው ልቡን የሚያዘና ግን በክፉ ላይ ይወድቃል።»

በሚለው ጥቅስ ውስጥ ያለውን «የሚፈራ» የሚለውን ቃል ኃይማኖታዊና አክብሮታዊ ፍርሃት» በማለት መተርጎሙ በቂ ማስረጃ ነው። በሥጋ ሕይወት ውስጥ እግዚአብሔርን መፍራት የሚባል ነገር ጨርሶ የለም።

ሐዋርያው ጳውሎስ ከሥጋ ማንነት የተነሳ አይሁዳውያን ጨምሮ ዐለም ሁሉ ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች ብይን የሚጠባበቅ ተከሳሽ መሆኑን በገለጠበት ክፍል

«በዓይኖቻቸው ፊት እግዚአብሔርን መፍራት የለም።» ሮሜ 3:18

በማለት ከመዝሙረ ዳዊት ጠቅሶ ያረጋግጥልናል።

እግዚአብሔርን መፍራት የእግዚአብሔር ሕይወት ባሕሪ ነው። ይህ ባሕሪ በመላት የሚታየው የእግዚአብሔር ሕይወት በሰው ውስጥ ሲገለጥ ብቻ ነው። ለዚህ ነው ኢየሱስ በፍፁም አምላክነቱ ብቻ በነበረበት በዘላለም ዘመን ውስጥ እግዚአብሔርን ስለመፍራቱ የተፃፈ አንዳች ነገር ሳይኖር ሰው ሆኖ በመጣበት በሥጋው ወራት ይልቁንም በጌቴሰማኔ የሞት ጣሩ ወቅት እግዚአብሔርን መፍራቱ በድምቀት መገለጡ እግዚአብሔርን መፍራት የእግዚአብሔር ሕይወት በሰው ማንነት ውስጥ ሲገለጥ የሚታይ አንድ ገጽታ መሆኑን ያሳየናል።

ሌላው እግዚአብሔርን መፍራት ከእግዚአብሔር መንፈስ የሚገኝ አንጂ በሥጋ ሕይወት ውስጥ የሌለ ንጥረ ነገር መሆኑን የሚያረጋግጥልን ነቢዩ ኢሳያስ ስለመሢሁ መምጣት በተነበየበት በአሥራ አንደኛው ምዕራፍ ላይ እግዚአብሔርን ስለመፍራቱ የተናገረው አስቀድሞ የእግዚአብሔር መንፈስ እንደሚያርፍበት ከመገለፁ በኋላ መሆኑ ነው።

ብዙን ጊዜ እግዚአብሔርን መፍራትን የምናስበው እግዚአብሔር ምን ያመጣብኝ ይሆን ብሎ ከመስጋት እና ፈቃዱ ያልሆነውን ብናደርግ ወይም ፈቃዱ የሆነውን ባናደርግ ከሚያመጣብን ፍርድና ቁጣ ጋር በማዛመድ ነው።

ሆኖም ይህ አስተሳሰብ እግዚአብሔርን ካለማወቅ ባሕሪውን ካለመረዳት የመነጨ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም።

ምንም እንኳ እግዚአብሔር ኃጢአትን በጽድቅ የሚፈርድና ኃጢአተኞችን የሚቀጣ አምላክ ቢሆንም ይህን የሚያደርገው በብዙ ትዕግሥትና ምህረት እንደሆነ ቃሉ ይነግረናል።

«አንተ ቸርና ይቅር ባይ ታጋሽም ምህረትህም የበዛ ክሰፉው ነህርም የተነሳ የምትፀፀት አምላክ እንደሆንህ አውቄ ነበርና።» ዮናስ 4:2 (አ.መ.ት)

«. . . አምላካችሁም እግዚአብሔር ቸርና መሀሪ ቁጣው የዘገየ ምህረቱም የበዛ ለክፉትም የተፀፀተ ነውና ወደ እርሱ ተመለሱ።» ኢዮ. 2:13 (አ.መ.ት)

ዛሬ በዓለማችን በክህደት፣ በርኩሰትና እግዚአብሔርን በመሣደብ ክፋትን የሚፈፀሙ የአመጽ ተዋንያን ምንም እንኳ ንስሐ ካልገቡ በቀር በመንገዳቸው ፍፃሜ ዘላለማዊ ፍርድ እንደሚጠብቃቸው ብናውቅም ዛሬን ተንሰራፍተው ዐሕይን እንደልባቸው እየሞቁ፣ንጹሕ አየር እየተነፈሱ መኖራቸውን ስናይ እውነትም እግዚአብሔር ቁጣው የዘገየ ምህረቱም የበዛ መሆኑን እንድናስብ ያደርገናል።

ስለዚህ እግዚአብሔርን መፍራት ማለት እግዚአብሔርን ከመውደድ የሚመነጭ እርሱን ላለማሳዘን የሚደረግ ጥንቃቄና ፈቃዱን አውቆ በማድረግ እርሱን ደስ ለማሰኘት የሚሆን ቅንዐት። ይህንን ነው እግዚአብሔርን መፍራት ወይም እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ብለን የምንጠራው።

በዚህ ባሕሪ ውስጥ ሊመላለስ የሚችል ሰው የእግዚአብሔር ታላቅነት የገለጠለትና ፍቅሩ የበራለት ብቻ ነው።

በዋነኛነት እግዚአብሔርን እንድንፈራው የሚያደርገን ኃይሉ ሳይሆን ፍቅሩ፣ ቁጣው ሳይሆን ርህራሄው፣ ፍርዱ ሳይሆን ምህረቱ ነው።

ይህ ዓይነቱ አምላክና አባት እንዲደሰት እንጂ እንደያዝን ስለማንፈልግ መንገዳችንን በጥንቃቄ እናቀናለን። ፈቃዱን አውቀን ለማድረግ እንተጋለን፣ ከሚያሳዝነው፣ ስሜቱንም ከሚጎዳ ከማናቸውም ነገር ለመራቅ እንጨክናለን፣ብንስት እንኳ

ፈጥነን ንስሓ በመግባትና በኢየሱስ ደም በመረጨት ሕብረታችንን ለማደስ እንጥራለን። እንግዲህ እግዚአብሔርን መፍራት ማለት ይሄ ነው።

እግዚአብሔር ምን ያመጣብኝ ይሆን? ብሎ መፍራት በሥጋ ባሕሪ ውስጥ የሚገለጥ የሰይጣን ማታለል እንጂ እግዚአብሔርን ከመምሰል ጋር አንዳች ግንኙነት የለውም። ይህ ዓይነቱ ፍርሃት መንፈሣዊነት ያለው ቢመስልም የሚፈረጀው ግን የተሰጠችውን አንዲት መክሊት ቀብሮ ጌታው መጥቶ በጠየቀው ጊዜ «ስለ ፈራሁህ ቀበርኩት» እንዳለው ሃኬተኛ ባሪያ ጎራ ነው። ይህ ዓይነቱ ፍርሃት እውነተኛ መንፈሳዊነት ቢኖረው ኖሮ ያ ሰው በተሸለመ ነበር። የጌታው ፍርድ ግን ልቅሶና ጥርስ ማፏጨት ባለበት በውጭ ባለው ጨለማ ውስጥ እንዲጣል ሆነ። አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔርን ባሕሪ ካለማወቅና በሰይጣን ከመታለል የሚመጣ እውነተኛ ያልሆነ እግዚአብሔርን መፍራት የኃይማኖት ካባ ደርቦ እንደመልካም ነገር ሊወደስ ይችል ይሆናል። ሆኖም መጨረሻው ቅጣት ነው።

«ፍርሃት ቅጣት ስላለው የሚፈራ ሰው ፍቅሩ ፍጹም አይደለም።» 1ዮሐ. 4:18

እግዚአብሔርን መፍራት ግን ጥበብ፣ የጥበብም መጀመሪያ ነው። እግዚአብሔርን መፍራት ማንኛውንም ነገር መልካም ብሎ ለመያዝ ከመጣደፍ ወይም ክፉ ነው ብሎ ለማምለጥ ከመሮጥ በፊት ቆም ብሎ የእግዚአብሔርን ሃሳብ ለማወቅ መጣርና፣ ፍቃዱን ለመረዳት መትጋት ነው። ከዚያም ፈቃዱ ሊገለጥልን ምንም እንኳ ዋጋ የሚያስከፍልና ለሥጋ የማይመች ቢሆንም ጊዜያዊውን ደስታ ትተን ዘላለማዊውን ትኩር ብለን በማየት መታዘዘ እውነተኛ እግዚአብሔርን የመፍራት ባህሪና የጥበብ ቁንጮ ነው። ይህችን ጥበበ ነው

ኢዮብ፡ -

«በምዝምግ ወርቅ አትገኝም
ብርም ስለ ዋጋዋ አይመዘንም
በኦፊር ወርቅ በከበረም መረግድና ሰንፔር አትገመትም።
ወርቅና ብርጭቆ አይወዳደሩትም
በጥሩ ወርቅም ዕቃ አትለወጥም።
ስለዛንልና ስለ አልማዝ አይነገርም።
የጥበብ ዋጋ ከቀይ አንቁ ይልቅ ይበልጣል።
የኢትዮጵያ ቶጳዝዮን አይተካከሉትም
በጥሩ ወርቅ አትገመትም።» ኢዮብ 28:15-19

የሚለት። እግዚአብሔርም፡ -

«. . . በዚያን ጊዜ አያት ገለጣትም አዘጋጃትም ደግሞም መረመራት። ለሰውም፦ እነሆ እግዚአብሔርን መፍራት ጥበብ ነው ክፉንም መራቅ ማስተዋል ነው ለሰው።» ኢዮብ 28

እንግዲህ የእግዚአብሔር ሕይወት በውስጣችን ካለ ይህ ከፍቅር የሚመነጭ እግዚአብሔርን የመፍራት ባሕሪ በውስጣችን ተሰውሯል ማለት ነው። ተሰውሮም እንዳይቀር ልምምድ ሊገልጠው ይገባል። ሳንታክት በየዕለቱ በመንገዳችን በሚገጥሙን ሁኔታዎች ውስጥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንመርምር። ለሥጋችን ጊዜያዊ ደስታ፣ ክብር፣ ወይም ማንኛውም ዓይነት ጥቅም የሚሰጠንን መንገድ ትተን ለጊዜው ባይመቸንም ዘላለማዊ ፋይዳ ያለውን ጎዳና በመምረጥ እግዚአብሔርን ለመፍራት ራሳችንን እናስለምድ። እግዚአብሔርን መምሰል ማለት ይህ ነውና።

ማጠቃለያ

በኑሮአችንና በአገልግሎታችን ሊገለጥ የሚገባው የእግዚአብሔር ሕይወት ባሕሪ እንደ አባይ ወንዝ ነው። እኔም በዚህች አነስተኛ ጽሑፌ በጭልፋ መጥለቁን እንኳ እርግጠኛ አይደለሁም።

ሆኖም «ሮም በአንድ ቀን አልተገነባችም» እንደሚለው ብሂል እግዚዘብሔርን ስለመምሰል ጽፎ መጨረስ ባይቻልም አንድ ፅኑ መሠረት ከተጣለ እንኳ ትልቅ ሥራ እንደተከናወነ ማሰብ ይቻላል።

ስለ ዓላማ በማውሣት የጀመርነውን ጉዞ ከመደምደማችን በፊት ግን እስከአሁን ድረስ በየምዕራፎቹ ያስተዋልነውን ቁም ነገሮች የምናሰላስልበትንና ውሣኔዎቻችንን የምናፀናበት ዳርቻ ላይ ደርሰናል። በመጀመሪያዎቹ ምእራፎች እግዚአብሔርን በመምሰል አስተምህሮ ላይ በማተኮር መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን ስለመምሰል የሚያስተምረውን ለመመልከት ሞክረናል። በመጨረሻዎቹ ምእራፎች ደግሞ ትኩረታችንን እግዚአብሔርን በመምሰል ልምምድ ላይ በማድረግ በቃል የተማርነውን እንዴት በተግባር እንደምንተረጉም ተመልክተናል። ከዚህ በኋላ የሚቀረው አንድ ነገር ብቻ ነው። ያነበብነው ቃል ሥጋ የሚሆንበት ከሕይወታችንም ጋር ተዋህዶ በተግባር የሚገለጥበት የመጨረሻ ምእራፍ።

ይህ ምዕራፍ ግን በቀለም ሳይሆን በእግዚአብሔር መንፈስ፣ በወረቀት ላይ ሳይሆን በልቦ ጽላት ላይ ተጽፎ ለሰው ሁሉ የሚነበብ የእርሶ ሕይወት ነው። በዚህ ቀጣይ ምዕራፍ ውስጥ ዋና ተዋንያን እርሶ ነምትና ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ የሚካፈሉትን ክብር በናፍቆት እየጠበቁ በእያንዳንዱን አሰት እግዚአብሔርን በመምሰል ይኑሩ። የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ፀጋ ከመንፈስዎ ጋር ይሁን ።

ማስታወሻ

1. ዮሐንስ 1:18፣ቈላ.1:15፣ሮሜ1:20
2. ዘኁልቁ 12:8
3. ዘፀዓት 33:20
4. ዘፀዓት 19:16-19
5. 2ቆሮንቶስ 4:4
6. ሮሜ 1:23
7. «ምንአልባት ቃላቱ በግጥም መልክ መፃፋቸው የዮንቷ ቤተ-ክርስቲያን ሃይማኖቷን ለመግለጽ ከምትጠቀምበት መዝሙር የተወሰደ ሊሆን ይችላል።» ከአዲሱ መደበኛ ትርጉም የጢሞ. 3:16 ማብራሪያ ጽሁፍ የተወሰደ።
8. ዕብራውያን 10:5
9. ኤፌሶን 3:10-11
10. ማቴ. 16:18
11. Briges, Jarry : The practice of godliness
12. Strong's, James, New Strong's exhaustive concordance of the Bible.
13. ቲቶ 2:12፣ ኤፌሶን 2:6-7
14. ዘፍጥረት 1:2
15. ኤፌሶን 2:15፣ 4:24፣ ቆላስያስ 3:10
16. የሐዋርያት ሥራ 19:9, 23፣ 22:4፣ 24:14, 22
17. ማቴዎስ 10:24-25
18. Srong's Exhaustive Concordence and Vine's Expository Dictionary of Old and New Testament.
19. የዮሐንስ ራዕይ 20:10
20. ሉቃስ 24:20፣ ዮሐንስ 16:2-3
21. ማርቆስ 11:12-14፣ 20-23
22. ማቴዎስ 16:16
23. ዮሐንስ 17:6

24. የሐንስ 4:9
25. ቆላስያስ 2:9፤ 2ጢሞቲዎስ 6:15-16
26. ሮሜ 8:23-25
27. 1ጢሞቲዎስ 3:1-7፤ ቲቶ 1:5-9
28. 1ቆሮንቶስ 1:7-8
29. Wikipedia, Encyclopidea (The fall of Rome)
30. 1ቆሮንቶስ 6:14፤ 15:20-23
31. ዘሌዋውያን 17:11
32. ዘፍጥረት 17:14፤ ዘፀዓት 4:24-26
33. ገላትያ 3:14-16
34. ሮሜ 5:12
35. ዘፀዓት 28:42-43
36. Nee, Watchman; Christ the Sum of all Spiritual Things
37. ፊሊጲስዮስ 2:12-13፤ 1ጴጥሮስ 1:8-9
38. ሮሜ 6:6
39. 1ቆሮንቶስ 10:13፤ ዕብራዊያን 12:2፤ 1ጴጥሮስ 4:12-14
40. ምሣሌ 20:27
41. 1ቆሮንቶስ 3:1-8
42. 1ቆሮንቶስ 8:13 — 9:18
43. 1ቆሮንቶስ 10:1-13
44. በጀግናው አትሌት በሻለቃ ኃይሉ ገ/ሥላሴ ፈቃደኝነት የተጻፈ. የግል ገጠመኝ ነው።
45. የአዲሱ መደበኛ ትርጉም የማቴዎስ 18:24 የግርጌ ማስታወሻ
46. የአዲሱ መደበኛ ትርጉም የማቴዎስ 18:28 የግርጌ ማስታወሻ
47. ማቴዎስ 3:16፤ የሐዋርያት ሥራ 2:3
48. ቆላስያስ 1:27
49. ኢዮብ 42:1-9